# የወንጌል ስርጭት ቁልፍ ዕቅድ

## በሮበርት ኮልመን

የጥናት መምሪያ በሮይ ጄ. ፊሽ
መቅድም በቢሊ ግራሃም



# የወንጌል ስርጭት ቁልፍ ዕቅድ

## (The Master Plan of Evangelism)

### በሮበርት ኮልመን

ትርጉም

ዓለማየሁ ጎሹ

እርማት

ኃይሉ ልመንህ፣ ሚናስ ብሩክ እና

ዘነበ ገብረሐና

1997 ዓ.ም

1998 ዓ.ም

የአሳታሚው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው።

Copyright
© 2005 by SIM International, Canada.
Copyright © 1963, 1964, 1993 by Robert E.Coleman
Originally published in English under the title
The Master Plan of Evangelism by Fleming H. Revell,
a division of Baker Publishing Group,
Grand Rapids, Michigan, 49516, U.S.A.
All rights reserved.

አሳታሚ፦ የኤስ አይ ኤም ሥነ ጽሑፍ
የፖ.ሣ. ቁጥር 127፤ አዲስ አበባ
ስልክ - 011 - 349 - 3252
ኢ-ሜይል፡ SIMmedia@ethionet.et
የኮምፒውተር ጽሑፍ፦ ጥሩወርቅ በቀለ
እና
ዓለምፀሐይ እውነቱ
የሽፋን ሥዕል፦ ከርት ሚክለር

BIBLE BASED BOOKS
SIM PUBLISHING

# ማውጫ

ገጽ

1. መቅድም— በዶክተር ቢሊ ግርሃም ....4
2. መግቢያ——በፖል ኤስ. ሬስ....6
3. መንደርደሪያ—መምህሩና ዕቅዱ ....8
   1. ምርጫ ....17
   2. መተባበር ....30
   3. ለአገልግሎት መቀደስ....46
   4. ክህሎትን ማካፈል ....59
   5. በተግባር ማሳየት....70
   6. ውክልና....79
   7. ቁጥጥር ....92
   8. መባዛት ....101
4. ዝክረ ታሪክ ፡ መምህሩና የአንተ ዕቅድ....113
5. የጥናት መመሪያ....126
   መግቢያ ....126
   ትምህርት 1 መምህሩና ዕቅዱ ....129
   ትምህርት 2 ምርጫ....133
   ትምህርት 3 መተባበር ....138
   ትምህርት 4 ለአገልግሎት መቀደስ....141
   ትምህርት 5 ክህሎትን ማካፈል....147
   ትምህርት 6 በተግባር ማሳየት....151
   ትምህርት 7 ውክልና ....155
   ትምህርት 8 ቁጥጥር ....159
   ትምህርት 9 መባዛት....163
   ትምህርት 10 መምህሩና የአንተ ዕቅድ - 1ኛ ደረጃ....168
   ትምህርት 11 መምህሩና የአንተ ዕቅድ - 2ኛ ደረጃ....172
   ትምህርት 12 መምህሩና የአንተ ዕቅድ - 3ኛ ደረጃ....176
   ትምህርት 13 መምህሩና የአንተ ዕቅድ - 4ኛ ደረጃ....180
   የመማር ሂደት መልሶች ....183

# መቅድም

ዛሬ በእኛ ትውልድ ሮበርት ኮልመን እንደ ጻፉት «የወንጌል ስርጭት ቁልፍ ዕቅድ»ን የመሰሉ ዓለምን በወንጌል ለመድረስ በሚደረገው ጥረት ታላቅ ተጽዕኖ ያሳደሩ ጥቂት መጻሕፍት አሉ። ባለፉት ሠላሳ ዓመታት ይህ ዘመን የማይሽረው መጽሐፍ ዓለምን በወንጌል ለመድረስ በሚደረገው ጥረት ውስጥ ቁጥራቸው ይህ ነው የማይባሉ ሰዎችን ዓለምን ለክርስቶስ ለመማረክ ልባቸውን አነሣስቶታል። በመሆኑም፣ በ30ኛው የኅትመቱ ልዩ በዓል ይህ መጽሐፍ እንደገና በመታተሙ የተሰማኝ ደስታ ታላቅ ነው።

የዚህን መጽሐፍ ተጽዕኖ ምሥጢር ለመረዳት ከባድ አይደለም። የወንጌል ስርጭትን በተመለከተ በወቅቱ በገነኑ ፈሊጦችና አዳዲስ ዘዴዎች ላይ ከማተኮር ይልቅ፣ ዶ/ር ኮልመን ወደ መጽሐፍ ቅዱሳቸው መለስ በማለት አንድ ወሳኝ ጥያቄ ይጠይቃሉ። ጥያቄውም፣ «የክርስቶስ የወንጌል ስርጭት ስልት ምን ነበረ?» የሚል ነው። ይህን በማድረጋቸውም ማንኛውም ሁነኛ የወንጌል ስርጭት አገልግሎት ሊታጠቃቸው የሚገባቸውን የማይለወጡና ቀለል ያሉ (ሆኖም ጥልቀት ያላቸው) መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርሖዎችን አመልክተዋል።

በመሆኑም፣ ይህ መጽሐፍ ጊዜ የማይሽረው ጥራት በውስጡ የያዘ ነው። ለሦስት አሥርት ዓመታት ለሴቶችና ለወንዶች የእግዚአብሔር ሰዎች እንደ ተናገረ ሁሉ ዛሬም ወንጌል ስርጭትን በተመለከተ የጌታን የልብ ምት የአዲሱ ክርስቲያን ትውልድ በተረዱ የመጽሐፉ ምንነት በአዲስ መንፈስ ግንዛቤ ሊያገኝ ይገባል።

ዛሬም ይህን መጽሐፍ እግዚአብሔር ከነገር ሁሉ ቅድሚያ ሊሰጠው ይገባል ወደሚለው ወንጌል ስርጭት ሁላችንንም የሚጠራበት መሣሪያ አድርጐ የሚጠቀምበት እንዲሆን ምኞቴ ነው። ከነገሮች ሁሉ ቅድሚያ ልንሰጠው የሚገባን ተልዕኳችንም የሚያስኘው ለዚህ ግራ ለተጋባና ወደ ሞት በመገስገስ ላይ ላለው ዓለም ስለ እግዚአብሔር ምሕረትና በክርስቶስ ኢየሱስ ስለሚገኘው ሰላምና ተስፋ የሚያበስረውን መልካም ዜና በፍቅር ማብሰር ነው።

ቢሊ ግርሃም



ሮበርት ኢ. ኮልመን በደቡብ ሐሚልተን፣ ማሳቹሴትስ በሚገኘው የጐርደን ኮንዌል ሥነ መለኮት ሴሚናሪ በጣም የተከበሩ የወንጌል ስርጭትና የደቀ መዝሙርነት ፕሮፌሰር ናቸው። ወደ ጐርደን ኮንዌል ከመምጣታቸወ ቀደም ብለው ዶ/ር ኮልመን በትሪኒቲ ኤቫንጄሊካል ዲቪኒቲ ትምህርት ቤት የሚገኘውን ስኩል ኦፍ ወርልድ ሚሽንስ ኤንድ ኢቫንጄሊዝም በዳይሬክተርነት መርተዋል። ከዚህም ባሻገር የቢሊ ግራሃም ዓለም አቀፍ የወንጌል ስርጭት ትምህርት ቤትን በዲንነት ያገለገሉ ሲሆን፣ በዊተን ኮሌጅ ለነበረውም ለቢሊ ግራሃም ማዕከል የወንጌል ስርጭት ተቋም ዳይሬክተር በመሆን ሠርተዋል።

ዶ/ር ኮልማን የሎዛን ዓለም አቀፍ የወንጌል ስርጭት ኮሚቴ መሥራች አባልና በዚያም ኮሚቴ ውስጥ ለሰሜን አሜሪካው ዘርፍ ሰብሳቢ በመሆን ለብዙ ዓመታት አገልግለዋል። ተልዕኮ አሜሪካ በተባለው አገልግሎት የአስተባባሪው ኮሚቴ አባል ሆነው እያገለገሉ የሚገኙ ሲሆን፣ በበርካታ ዓለም አቀፍ የወንጌል ተልዕኮ ቦርዶችም አስተዋጽዖ በማድረግ ላይ ናቸው። ቀደም ሲልም የወንጌል ተልዕኮና የሥነ መለኮት ትምህርት አካዳሚ ፕሬዚዳንት በመሆን አገልግሎታቸውን አበርክተዋል። «የወንጌል ስርጭት ቁልፍ መርሕ»፣ «ሊመጣ ያለው ዓለም አቀፍ መነቃቃት» እንዲሁም «ከመላእክት ጋር መዘመር» ከተባሉት መጻሕፍት ባሻገር፣ ዶ/ር ኮልማን በመቶዎች የሚቆጠሩ መጣጥፎችንና ሃያ ሦስት የሚሆኑ መጻሕፍትን ጽፈዋል። ከጻፏቸው መጻሕፍት አንዱ ወይም ከዚያም በላይ የሚሆኑት ከመቶ በላይ ወደሚሆኑ ቋንቋዎች የተተረጐሙ ሲሆን፣ በእንግሊዝኛ የተጻፉት መጻሕፍት ብቻ ከሰባት ሚሊዮን የሚበልጡት ኅትመታቸው ተጠናቅቆ ለንባብ ቀርበዋል።

# መግቢያ

በአንድ ወቅት ካርል ማርክስ፣ «ፈላስፎች ለዚህ ዓለም የተለያየ ትርጊሜን ብቻ ሰጥተዋል፣ ዋነኛው ቁም ነገር ግን ዓለምን መለወጥ መቻሉ ላይ ነው» ብሎ ጽፎ ነበር።

ምንም እንኳን በመሠረታዊው አቋማቸው አንድ ባይሆኑም፣ ክርስትና እና ኮሚኒዝም እዚህ ነጥብ ላይ ይስማማሉ። ሆኖም ስምምነቱ ከዚህም ጥቂት እልፍ ይላል። ከዚህ ለየት ባለ ሁኔታ ቤተ ክርስቲያን የተለወጠ ዓለም የተለወጡ ሰዎች ውጤት ነው ብላ ታውጃለች። አሳቦችን የሚያሰላስል ሰው አዲስ የሆነን ፍልስፍና ያመነጭ ይሆናል፤ በእርግጥ አዲስ ለሆነ ኅብረተሰብ ፍንጭ ይዞ የሚቀርበው ዳግም የተወለደው ሰው ብቻ ነው።

የወንጌል ስርጭትን ከተራ ጽንሰ- አሳብነት ወይም መፈክርነት ፈጽሞ ልዩ የሚያደርገው ነገር ቢኖር፣ «እግዚአብሔር በክርስቶስ ሆኖ ዓለምን ከራሱ ጋር ያስታርቅ ነበር» በሚለው በምስራቹ ቃል ላይ የተመሠረተ አቋም መሆኑ ነው። ይህም የወንጌል ስርጭትን በጣም አስፈላጊ ትኩረት እንዲያገኝ ያደርገዋል።

ታዲያ እዚህ ላይ አንድ ጥያቄ ይነሣል፣ ይሄውም፡- ክርስቶስ ኢየሱስን እንደ ግል አዳኛቸው አድርገው በእምነት በመቀበል የተለወጡ አማኞችን የሚያቅፈው አካል እየሰፋ በሚሄድበት፣ ቀጣይ፣ እንደ ሰደድ እሳት የሚሰፋና ችላ የማይባል በሆነ መልኩ የወንጌል ስርጭትን ልናካሂድ የምንችለው እንዴት ነው?

ሮበርት ኢ. ኮልመን በጥንቃቄ እንደሚገባ ከተጠኑ የወንጌል ስርጭትን አመለካከት ከተሳሳቱ አቅጣጫዎች ሊጋርዱ የሚችሉ የተወሰኑ መርሖዎችንና የአፈጻጸም ዕቅዶችን አቅርበዋል። በዚህም ጥረታቸው ወንጌል ስርጭትን «ልዩ» እና «ወቅታዊ» ከሚባሉት የአመለካከት አንጻሮች በማላቀቅ መሠረታዊና ቀጣይ በሆነው የምእመናኑ ምስክርነት ላይ የተመሠረተ እንዲሆን አድርገዋል።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በተለየ ሁኔታ የወንጌል ስርጭትን ሲያካሂዱ በነበሩት እንደ በእነ ሙዲ፣ በሰንደይ ወይም ግርሃም



በመሳሰሉት ተጠቅሞ የእግዚአብሔር መንፈስ ያከናወናቸውን ብርቱ፣ የተቀናጀና ወቅታዊ የሆኑ ሥራዎችን የሚያጣጥል አንዳች አሳብ የለውም። ከትናንሽ ቡድኖች እየጀመረ ወደ ምእመናን የምስክርነት አገልግሎት ለሚያድገው ደቀ መዝሙርትን የማፍራት ተግባር እንድንሻገር ጥሪ የሚያደርጉ ብዙ ነገሮችን ከእነዚህ ሊቃውንት አግኝተናል። በአጠቃላይ መልኩ፣ እነዚህ ሁሉ ጥረቶች ለምንሰብከው ወንጌልና ይህን ወንጌል እንድንኖር በሚያስችለን ሕይወት መካከል ያለውን ግንኙነት ለማሳየት ታቅደው የተደረጉ ናቸው።

በጌታችንንና በደቀ መዛሙርቱ አካሄድ ላይ ያተኮረው የደራሲው ሥራ በመጽሐፍ ቅዱሳዊ ይዘት የረሰረሰ ነው። ዘዴውን በተለየ መልኩ ለማስማመርና ለማጊያጌጥ ደራሲው ያደረጉት ጥረት የለም። በጠቅላላው የመጽሐፉ ይዘት ግልጽና ቀጥተኛ ነው። በተመሰጡበት መሪ አሳብ ላይም ለረጅም ጊዜ በጥልቀት እንዳሰቡባቸው መጽሐፉ ያለመቆጠብ ያንጸባረቀ ሲሆን፣ ደራሲው የነበራቸውንም ጉልህ ቅንነት በቀላሉ ለማየት ይቻላል።

ዛሬ ጠዋት አንድ ሰው በሬዲዮ እንዲህ በማለት ያስተዋለውን ነገር ሲገልጽ ሰማሁ፡- «ብዙ ጊዜ ከሁለቱ በአንዱ መንገድ እንንዛለን። ከቃላት ወደ ተግባር፣ ወይም ከተግባር ወደ ቃላት።» ይህም ማለት በጽንሰ አሳብ ደረጃ ያሉ ነገሮችና ወይም አቋሞች ተጨባጭ ወደ ሆኑ ተግባሮች ልናሻግራቸው ካልቻልን ተጨባጮቹ ተግባሮች በቃላት ጋጋታ ውስጥ ተውጠው ይቀራሉ ማለት ነው።

ይህ ቅን የሆነ መጽሐፍ ቀደም ሲል የጠቀስኩት ዓይነት ጥፋት እንዳይደርስብን ሊረዳን ይችላል ባይ ነኝ። ስለዚህ ታነቡትና ትጠቀሙበት ዘንድ ሳሳስባችሁ በደስታ ነው።

ፖል ኤስ. ሪስ

እኔ መንገድ ነኝ
ዮሐ. 14:6

## መንደርደሪያ
## መምህሩና ዕቅዱ

### በወንጌል ስርጭት ዘዴዎች ውስጥ ያለው ችግር

ዓላማና አግባብነት የተሰኙት ለሥራችን በጣም ቁልፍ የሆኑ አሳቦች ናቸው:: አንዱ ከሌላው ጋር የተሳሰረ ከመሆናቸውም በላይ፣ አንዱን ከአንዱ ምን ያህል እንደሚጣጣሙ ለማወቅ የምናስቀምጠው መለኪያ በአብዛኛው ተግባራችን የሚኖረው ዋጋ የሚወሰን ነው:: ምናልባትም ወዲያና ወዲህ ስለ ተጠዳደፍን ወይም ችሎታው ስላለንና አንዳንድ ነገሮችን ስላደረግን አንዳች ነገር አከናውነናል ማለት አንችልም:: ሁልጊዜ መጠየቅ ያለበት ጥያቄ፣ «የሠራነው ሥራ መሠራት የሚገባው ነውን? የታለመለትን ዓላማ መቷልን?» የሚለው ነው::

ቤተ ክርስቲያን ዛሬ ከምታደርገው የወንጌል ስርጭት ጋርም ተያይዞ ሁልጊዜ ሊነሣ የሚገባው ጥያቄ ይህ ነው:: አገልግሎታችን ወደፊት እንዲጓዝ በምናደርገው ጥረታችን ክርስቶስ የሰጠንን ታላቁን ተልዕኮ እያሳካን ነውን? ከእኛስ አገልገሎት የተነሣ ከዕለት ወደ ዕለት ቁጥራቸው እያደገ የሚሄድ በመስጠት ወንጌልን ለዓለም በማድረስ ላይ ያሉ ሰዎችን አፍርተናልን? አዎ፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በየጊዜው የወንጌል ስርጭት ዕቅዶችን በማውጣት ሥራ መወጠራችን በእርግጥ የማይካድ ነው:: ጥያቄው ግን ዓላማችንን ከግብ እያደረስን ነው ወይ? የሚለው ነው::

### ቅርጽ ወይም አቀራረብ ተግባርን ይከተላል

በዚህ ነገር ላይ ስናተኩርና ከረጅም ጊዜ ግብ አንጻር ማዕከል



ያደረገና የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴው በጥንቃቄ የታሰበበትን የእንቅስቃሴ ዘዴ በመቀየስ አስፈላጊነት ላይ ወዲያው እንድናተኩር ያደርገናል::

ከተፈጠርንለት ዓላማ አንጻር የታቀደለትን ግብ እያሰበች ነፍሳችን ሐሴት ታደርግ ዘንድ እግዚአብሔር ለሕይወታችን ካቀደው ዘላለማዊ ዕቅድ ጋር እያንዳንዱ ሥራችን እንዴት እንደሚስማማ ልናውቅ ይገባል:: ይህ ደግሞ በማንኛውም ዓይነት ወንጌልን ለማሰራጨት በምንጠቀምባቸው ዘዴዎች ሁሉ ላይ የሚሠራ ነው:: ይህ ማለት ደግሞ አንድ ቤት ሲገነባ ከግንባታው በኋላ ሊውል ለታሰበበት አገልግሎት ተብሎ በተዘጋጀው ንድፍ መሠረት እንደሚገነባ ሁሉ፣ እኛም የምናደርገው ነገር ሁሉ ዓላማ ሊኖረው ይገባል:: አለበለዚያ ግን ሥራችን ሁሉ ከዓላማቢስነትና ከግራ መጋባት የተነሣ ዋጋ አልባ ይሆናል::

### በመርሖዎች ላይ የተደረገ ጥናት

ይህን ጥናት ለማካሄድ ጥረት የተደረገው በርእሱ በተገለጸው ምክንያት ነው:: ጌታ ያደርገው ከነበረው እንቅስቃሴ በስተጀርባ ድርጊቱን ይቆጣጠሩ ደግሞም ወሳኝ ሚና የነበራቸው መርሖዎች ምን እንደ ነበሩ ለማየት ይህ ጥናት አድርጓል:: ይህም የተደረገው እኛም አቋሙን ብንረዳ አገልግሎታችንን በዚያው መልክ ለመቅረጽ ያስችለናል በሚል ተስፋ ነው:: ከዚህም የተነሣ ይህ መጽሐፍ ጌታ ኢየሱስ ሰውን በግል በመቅረብ ወይም በጉባዔ በመስበክ የተጠቀመባቸውን የወንጌል ስርጭት ዘዴዎች እየዘረዘረ የማብራራት ጥረት አያደርግም:: ከዚህ ይልቅ ይህ ጥናት የጌታ አገልግሎት በስተጀርባ የነበሩትንና በወንጌል ስርጭት ዘዴዎቹ ላይ ወሳኝ ሚና የነበራቸውን የሚመለከት ነው:: ጌታ ኢየሱስ በምድር ላይ በተመላለሰበት ጊዜ ሕይወቱን በመስጠት ባገለገለበት የወንጌል

ስርጭት ዘዴ ላይ የተደረገ ጥናት ሊባልም ይችላል፡፡

## ብዙ የምርምር ጥናት ሊካሄድ ይገባል

በወንጌል ስርጭት ዘዴዎች ዙሪያ የተጻፉ በርካታ መጻሕፍት እግረ መንገዳቸውን ጠቀስ አድርገውት ይለፉ እንጂ በዚህ ጉዳይ ላይ በዚህ መልኩ ለጎትመት የቀረቡ ጽሑፎች በአስገራሚ ሁኔታ በጣም ጥቂት ናቸው፡፡ የጌታ ኢየሱስ የማስተማር ዘዴንም ሆነ ጠቅላላ አገልግሎቱንና ሕይወቱን በተመለከተ ያለውም ነገር ከዚህ ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡

ምናልባትም በጣም በጥንቃቄ የተጠናውና በጌታ ሰፊ የወንጌል ስርጭት ዕቅድን ትኩረቱ ካደረጉት የደቀ መዛሙርትን ሥልጠና አስመልክቶ በኤ. ቢ. ብሩስ የተጻፈው "<The Trainging of the Twelve> የ(አሥራ ሁለቱ ሥልጠና)" የሚለው መጽሐፍ በጣም ጥሩ መጽሐፍ ነው፡፡ በመጀመሪያ እ.ኤ.አ በ1871 ከዚያም በ1899 ተከልሶ የታተመው ይህ መጽሐፍ ደቀ መዛሙርት ከጌታ ጋር በነበሩበት ጊዜ የነበራቸውን እድገት በመተረክ ከሌሎች አሁን አሉ ከሚባሉት መጻሕፍት በጉዳዩ ላይ ሊስተዋሉ የሚገባቸውን እውነቶች በማመልከት በኩል ተወዳዳሪ የለውም፡፡ ሌላው ደግሞ በሄኔሪ ላዝም የተጻፈውና "(Pastor Pastorum) የመጋቢው እረኝነት" የተሰኘውና እ.ኤአ. በ1890 ዓ.ም ለኅትመት የበቃው እጅግም ሁሉን አቀፍ ባይሆንም፣ ጌታ ኢየሱስ በሚያሠለጥንበት ጉዳይ ላይ ያተኮረ መጽሐፍ ነው፡፡ ከዚያን ዘመን ጀምሮ ይህንን ርእሰ ጉዳይ በመከታተል በኩል የሚረዱ አነስተኛ ጥራዝ ያላቸው ሌሎች በርካታ መጻሕፍት ወጥተዋል፡፡ በእርግጥም ሁሉም አንድ ዓይነት የሆነ ወንጌላዊ የሆነ ሥነ መለኮታዊ እይታ የላቸውም፡፡ ሁሉም ግን ጌታ ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ያከናወነውን ሥራ ማዕከላዊ ትኩረት በምንገመግምበት ጊዜ መነሻ ያደረጉት ተመሳሳይ ሁኔታ



መሆኑ የሚያስገርም ነገር ነው፡፡

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የቤተ ክርስቲያንን ሕይወትና አገልግሎት በሚመለከት በተለያዩ ዘርፎች የቀረቡ አያሌ ተጨባጭ ሥራዎችን በተመለከተ ለተከናወኑ ኅትመቶች ይህ እውነት ነው፡፡ በተለይም በማደግ ላይ ያሉትን ትንንሽ ቡድኖች እና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በምእመናን አማካይነት እየተደረገ ያለውን የምስክርነት እንቅስቃሴ በሚመለከት ለሚዘጋጁ በርካታ ጽሑፎች ይሄው እውነት በጉልህ የሚታይ ነው፡፡ እነዚህ ጸሐፊዎች የወንጌል ስርጭት ዘዴን መሠረት አድርገው እንዳልጻፉ የምናውቅ ቢሆንም፣ በጌታ አገልግሎትና ተልዕኮ ውስጥ ላሉት መሠረታዊ መርሖዎች ትልቅ ስፍራ በመስጠታቸው ባለውለታነታችንን ልንገልጽላቸው ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ፣ የጌታ ኢየሱስ መሠረታዊ ዘዴ የሚለው ጉዳይ ግን ሊሰጠው የሚገባ ትኩረት አልተሰጠውም፡፡ ይህን ጉዳይ ከግንዛቤ ያስገቡ ሰዎችንና ሥራን ሳናደንቅ የምናልፈው፣ የደረሱበትንም ግኝት ችላ የማንለው ቢሆንም፣ ተጨማሪ ማብራሪያዎችንና ምርምሮችን የማድረጉ አስፈላጊነት ግን ምን ጊዜም በውስጣችን የነበረ ጉዳይ ነው፡፡ ይህም ተጨማሪ ምርምሮችንና ማብራሪያዎችን የማድረግ አስፈላጊነት በተለይ መሠረታዊ ምንጮችንም በማጥናት በኩል በሚደረገው ጥረት እውነት ነው፡፡

## የጥናታችን ዕቅድ

የጌታ ኢየሱስን ዕቅድ በሚገባ ለመረዳት የፈለገ ሰው ወደ አዲስ ኪዳን በተለይም ወደ ወንጌላት መሄድ ይኖርበታል፡፡ በዚህ ላይ ጌታ በአገልግሎት ላይ በነበረበት ጊዜ ያከናወነውን ሁሉ የዘገቡ ብቸኛ

የዓይን ምስክሮቻችን ወንጌላት ናቸው (ሉቃስ 1:2፣ 3፤ ዮሐንስ 20:30፤ 21:24፤ 1ኛ ዮሐንስ 1:1):: አንድ ነገር እርግጥ ነው ይሄውም ወንጌላት በመሠረቱ የተጻፉት የእግዚአብሔርን ልጅ ክርስቶስን ሊያሳዩንና በስሙ በማመን ሕይወትን ማግኘት እንድንችል ነው (ዮሐንስ 20:31):: ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ ሳናስተውል የምንቀረው ነገር ቢኖር የተገለጸው ያ የክርስቶስ ሕይወት የእርሱን አኗኗርና እኛም የእርሱን ኑሮ በመሰለ ኑሮ እንኖር ዘንድ ያስተማረበትን መንገድም አብረው መግለጻቸውን ነው:: ልንረሳው የማይገባን ነገር ወንጌላትን የጻፉ ሰዎች እውነቱን የተመለከቱ ብቻ እንዳልነበሩና፣ በዚያ እውነት የእነርሱም ሕይወት ተለውጦ እንደ ነበር ነው:: ከዚህ የተነሣ እነዚህ ጸሐፊዎች ይህን ታሪክ በሚያቀርቡ ጊዜ የእነርሱንና የሌሎችንም ሕይወት የለወጠውንና ሁሉን ትተው እንዲከተሉት ያደረጓቸውንም ነገሮች ጽፈውልናል:: በእርግጥ ሁሉም ነገር አልተዘገበም:: እንደ ማንኛ ውም ታሪክ ዘጋቢ እነዚህ ወንጌል ጸሐፊዎች ዓይነተኛ በሆኑ ሰዎችና ክስተቶች ላይ በማተኮር አጠቃላይ ገጽታው ምን እንደሚመስል ያመለክታሉ:: ነገር ግን እነዚህ በመንፈስ ቅዱስ አነሣሽነት በፍጹም ቅንነት ከተመረጡትና የተዘገቡት ክስተቶች ጌታ የተጓዘባቸውን መንገዶች እንከተል ዘንድ ታስበው የተጻፉ ለመሆናቸው እርግጠኞች ልንሆን እንችላለን:: ስለዚህም ነው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ ክርስቶስ የሚተርኩት ክፍሎች ለወንጌል ስርጭት መሪ መጽሐፍችን እጅግ ምርጥና ስሕተት አልባ መሠረት ሆነው የተገኙት::

ስለሆነም የዚህ ጥናት ዕቅድ ያለምንም ተጨማሪ ረዳት መጻሕፍት በወንጌላት ላይ እንደተገለጸው ኢየሱስ የተጓዘባቸውን ዱካዎች ማግኘት መቻል ነው:: በዚህም ጥረት የኢየሱስን ሕይወትና አገልግሎት በተደጋጋሚና ከተለያየ አቅጣጫ በተደጋጋሚ በማየትና በማጥናት አገልግሎቱን ለመፈጸም ያነሣሱትን ምክንያቶች ለመረዳት ሙከራ ተደርጓል:: ከሰዎች ጋር ያደርጓቸው በነበሩ ግንኙነቶች ይጠቀምባቸው የነበሩትን ዘዴዎች ጥልቅ ምሥጢር ሊገልጹ ይችላሉ በሚል ከአገልግሎቱ አኳያ የተጠቀመባቸው ስልቶች ሰፋ ባለ መልኩ በጥንቃቄ ተጠንተዋል:: እውነቱን ለመናገር ይህን ማድረግ ቀላል አልነበረም፣ የምንማረው ገና ብዙ ነገር እንዳለ ለመግለጽ ደግሞ የመጀመሪያው ሰው እሆናለሁ:: ውሱን ያልሆነው የክብር ጌታ ታላቅነት ፍጹምነቱን በሚገልጹ ምንም ዓይነት ሰብዓዊ አተረጓጎም ሊወሰን አይችልም:: በመሆኑም አንድ ሰው ጌታን አትኩሮ ሲመለከተውና ይህንንም እውነት ይበልጥ ሲያጤነው የሚረዳው ይህንኑ ነው::

## ክርስቶስ፣ እንከን - የለሽ ምሳሌ

ይህንን እውነት ስንረዳ ከዚህ ጥናት የሚበልጥ ብድራት ያለው እንደሌለም እንረዳለን:: እንድናስተውል የሚያስችሉን ብልቶች ውሱን እንደ መሆናቸው መጠን፣ እንደ ጌታ ያለ እንከን አልባ አስተማሪ አናገኝም:: እርሱ በፍጹም ተሳስቶ አያወቅም:: የእኛን ሕይወት ተካፍሎ እንደ እኛ በነገር ሁሉ ቢፈተንም፣ ስለ እኛ ሲል በተቀበለው ለሥጋው ውሱንነት ምክንያት ግን አልተሸነፈም:: መለኮታዊ የሆነውን ሁሉን አዋቂነቱን መጠቀም በማይመርጥባቸው ጊዜያት እንኳ አስተሳሰቡ ጥርት ያለ ነበረ:: ምን ጊዜም ትክክለኛ የሆነውን ነገር ምን እንደሆነ ያውቃል፣ ፍጹም ሰው እንደ መሆኑም መጠን፣ እግዚአብሔር በሰዎች መካከል የሚኖረውን ዓይነት ኑሮ ነበር የኖረው::

## ዓላማው ግልጽ ነበር

በሥጋው ያሳለፋቸው ወራት ከጥንት ዘመን ጀምሮ የነበረው

የእግዚአብሔር ዘለዓለማዊ ዕቅድ ነበር። ሁልጊዜ በአሳቡ ውስጥ የነበረውም ይሄው ነበር። ዕቅዱም ሰዎችን ከዓለም ለራሱ አድኖ በማውጣት የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ የሆነችውን የማትጠፋዋን ቤተ ክርስቲያን መመሥረት ነበር። ናፍቆቱ ሁሉ በክብርና በኃይል መንግሥቱ ለምትመጣበት ለዚያች ቀን ነበር። እርሱ ስለ ፈጠራት ይህች ዓለም የራሱ ነበረች። ይሁን እንጂ፣ እስከ መጨረሻው መኖሪያው ሊያደርጋት ምርጫው አልነበረም። መኖሪያው በሰማያት ነው። በሰማያት ዘለዓለማዊ መሠረት ያለውን ስፍራ ለሕዝቡ ሊያዘጋጅ ወደዚያው ተመልሶ ሄደ።

ከዚህ ውድ ከሆነው ዓላማው ውጭ ማንም ሰው አልተገለለም። ፍቅሩ መላውን ዓለም ያካተተ ነበር። ይህንን በፍጹም አትሳቱ። ለዚህም ምንም ጥርጥር የለውም። ምክንያቱም ፍቅሩ ዓለማቀፋዊ ነበር «የዓለም አዳኝ» ነበር (ዮሐ. 4:42)። የሰው ልጆች ሁሉ እውነቱን በእምነት እንዲቀበሉና እንዲድኑ የእግዚአብሔር መሻት ነው። ከዚህም ዓላማ አንጻር ጌታ ኢየሱስ ለሰው ልጆች ሁሉ ከኃጢአት ሁሉ የሚያነጻ ደኅንነት ይሰጥ ዘንድ ራሱን አቀረበ። በዚህም ለአንድ ሰው የሞተውን ያህል፣ እንዲሁም ለሰው ልጆች ሁሉ ሞተ። ጥልቀት እንደሌለው እንደ እኛ አስተሳሰብ ሳይሆን፣ በእርሱ ዘንድ የአገር ውስጥና ከአገር ውጪ ተልዕኮ የሚል የአመለካከት ልዩነት በፍጹም አልነበረም። ለኢየሱስ ሁሉም ዓለምን በወንጌል የመድረስ ጉዳይ ነበር።

## ዕቅዱ ለማሸነፍ ነበር

በሕይወቱ ያደርገው የነበረውን እንቅስቃሴ የሚመራው የሚከተለው ዓላማ ነበር። ያደረገውና የተናገረው ነገር ሁሉ የሚከተለው አጠቃላይ ሂደት አንዱ ክፍል ነበር። ዓለምን ሁሉ ይህንን ማድረጉ ለእግዚአብሔር ለመዋጀት ላለው ለሕይወቱ



ዘለቄታ ዓላማ አስተዋጽኦ የሚያደርግ ስለነበረ አስፈላጊ ነበር። ባህሪውን ይቆጣጠር የነበረውም ይሄው ራእይ ነበር። እያንዳንዱ እርምጃው ከዚህ ጋር የተጣጣመ ነበር። በሚገባ ካስተዋልን ጌታ ኢየሱስ ከዚህ ግቡ ላይ ላፍታ እንኳን ዓይኑን አንሥቶ አያውቅም።

ለዚህም ነው ጌታ ኢየሱስ ግቡን ለመምታተ የተጊዘበትን አካሄድ መመልከት እጅግ አስፈላጊ የሚሆነው። ዓለምን ለራሱ ለመማረክ እግዚአብሔር የተለመውን ስልት መምህሩ ፈጸመው፡ በተቀየሰውም ስልት መሠረት በወቅቱ በሚገባ ስለ ኖረ በቀጣይ ሊመጣ ስላለው ነገር በጣም እርግጠኛ ነበር። ጌታ ኢየሱስ በምድር ሳለ በአጋጣሚ ያደረገው አንዳች ነገር አልነበረም- በከንቱ ያባከነው ኃይል ወይም ያለአንዳች ጥቅም ከአንደበቱ የወጣ ንግግር አልነበረም። የእግዚአብሔርን ሥራ በመሥራት ላይ የተጠመደ ነበር (ሉቃ. 2:49)። ቀድሞ በታቀደው መሠረት ኖረ፣ ሞተ፣ ከሞት ተነሣ። የጦርነቱን ስልት እንደሚቀይስ የጦር መሪ የእግዚአብሔር ልጅ ወደ ድል የሚያመራውን ስልት ይቀይስ ነበር። ዕድልና አጋጣሚ ይዘው የሚመጡትን ቆሞ መጠበቅ አልመረጠም። እያንዳንዱን አማራጭና በሰው ልጆች ልምምድ ውስጥ የሚያጋጥሙ ተለዋዋጭ ክስተቶችን ከመዘነ በኋላ ፈጽሞ ሊሰናከል የማይችል ስልት ቀየሰ።

## በጥንቃቄ ሊታይ የሚገባው

ይህንን ሁኔታ ማጥናት በእጅጉ ማስተዋልን የሚገልጥ ነው። የክርስቶስ ተማሪ እዚህ ነጥብ ላይ በቁም ነገር የሚያሰላስል ከሆነ፣ በጣም መሠረታዊ ወደ ሆነና ምናልባትም የእስከ ዛሬውን አቋሙን ወደሚያናጋ ድምዳሜ ላይ ይደርሳል። ሆኖም፣ ይህ ድምዳሜ እውን የሚሆነው በጣም ዝግ ባለና በአታካች መንገድ ሊሆን ይችላል። በእርግጥ እንዲያውም መጀመሪያ ስናየው ኢየሱስ ዕቅድ ያለው አይመስልም። ከሌላ አቅጣጫ ሲታይ፣ አንድ የሆነ ስልት

ብቻ እንደነበረው ያመለክት ይሆናል፣ ነገር ግን ለዚያ ስልት መሠረት የሆነው ጉዳይ ሊዘነጋ ይችላል:: አስደናቂ ከሆኑት የክርስቶስ ስልት ገጽታዎች አንዱም ይሄ ነው:: በበርካታ ትኩረት የሚሰጠው የማይመስልና ውካታ የሌለበት በመሆኑ በሥራዎች በተጠመዱ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ዘንድ ይህ ግንዛቤም አያገኝም:: በስተመጨረሻ ሁሉን የሚቆጣጠረው የዚህ ስልት ግንዛቤ በደቀ መዛሙርቱ የተከፈተ ልብ ውስጥ ሲበራ ስልቱ ምን ያህል ቀላል እንደ ነበረና እስከ ዛሬም ሊያስተውለውና ሊጠቀምበት ባለመቻሉ ይገረማል:: የሆነው ሆኖ፣ ዕቅዱን ስናሰላስለው መሠረታዊ የሆነው መሪ አሳብ አሁን ካለችው ዘመናዊት ቤተ ክርስቲያን እጅግ ለየት ያለ በመሆኑ ተግባራዊ ግንዛቤው ሥር ነቀል ነው::

የዚህ መጽሐፍ ቀጣይ ክፍል የጌታ ኢየሱስን ስምንት መሠረታዊ መመሪያዎች ለማብራራት ጥረት ያደርጋል:: ይሁንና፣ እያንዳንዱ እርምጃ የግድ የተጸፈውን ሥርዓት ተከትሎ አንዳችም ሳይዛነፍ ይከናወናል ብሎ ማሰብ ተገቢ አይደለም:: እንደዚህ ብሎ ማሰብ የመጀመሪያዎቹን ልንተገብር እስካልቻልን ድረስ የመጨረሻዎቹን ልንፈጽማቸው አንችልም ማለት ነው:: በእርግጥ ሁሉም ደረጃዎች በእያንዳንዱ ደረጃ ሊካተቱ ይችላሉ፣ በተወሰነ መጠን ደግሞ የሁሉም ጅማሬ የመጀመሪያው ነው:: የመጽሐፉ አስተዋጽኦ ዓላማ ለስልቶቹ ወጥ የሆነ አወቃቀር ማስያዝ በጥቅሉ የዕቅዶቹን አካሄድና ተያያዥነት ማሳየት ነው:: የክርስቶስ ኢየሱስ አገልግሎት እያደገ በሄደ ቁጥር፣ እያንዳንዱ ደረጃ ይበልጥ እየታየና አንዱ ከሌላው ጋር ያለው ተከታታይነት ይበልጥ ግልጽ እየሆነ ይመጣል::



ከእነርሱም አሥራ ሁለት መረጠ
ሉቃስ 6 :13

# 1
# ምርጫ

## ስልቶቹ ሰዎች ነበሩ

ሁሉም ነገር የጀመረው ኢየሱስ ይከተሉት ዘንድ ጥቂት ሰዎችን በመጥራቱ ነበር:: ይህ ደግሞ የኢየሱስ የወንጌል ስርጭት ዘዴ ምን ዓይነት አካሄድ እንደሚኖረው ወዲያውኑ የሚያመለክት ነው:: የእርሱ ትኩረት ሕዝቦችን በወንጌል የሚደርስበትን የወንጌል ስርጭት ዕቅድ መቀየስ ላይ ሳይሆን፣ ብዙዎች የሚከተሉአቸውን ሰዎች ማፍራት ላይ ነበር:: የሚገርመው ምንም ዓይነት የወንጌል ስርጭት ዘመቻ ከማዘጋጀትና ምንም ዓይነት ስብከት በጉባኤ ፊት ከመስበኩ በፊት ያደረገው ነገር ቢኖር እነዚህን ሰዎች መምረጥና መሰብሰብ ነበር:: ምክንያቱም ዓለምን ወደ እግዚአብሔር ለመማረክ የተጠቀመበት መሣሪያ «ሰዎች» ነበሩ::

የኢየሱስ ዕቅድ ተቀዳሚ ዓላማ በምድር ስለ ሕይወቱ ምስክሮች የሚሆኑትንና ወደ አባቱም ከተመለሰ በኋላ እርሱ የጀመረውን ሥራ የሚቀጥሉትን ሰዎች መመልመል ነበረ:: ኢየሱስ መጥምቁ ዮሐንስ ታላቁን መነቃቃት ያካሂድ ከነበረበት ከዮርዳኖስ ማዶ ካለችው ከቢታንያ ሲመለስ በመጀመሪያ የጋበዛቸው ዮሐንስንና እንድርያስን ነበር (ዮሐ. 1:35-40):: እንድርያስ ደግሞ በበኩሉ ወንድሙን ጴጥሮስን ይዞ መጣ (ዮሐ. 1:41-42):: በቀጣዩ ቀን ኢየሱስ ወደ ገሊላ በመሄድ ላይ የነበረውን ፊልጶስን አገኘው፣ ፊልጶስ ደግሞ ናትናኤልን አገኘው (ዮሐ. 1:43-51):: እነዚህን ደቀ መዛሙርት በመረጠበት ጊዜ ለቆራጥነቱ እንጂ ለችኩልነቱ መረጃ

የሚሆነን ነገር እናገኛም:: ከብዙ ወራት በኋላ አራቱ ዓሣ አጥማጆች ከገሊላ ባሕር አጠገብ እስከተጠሩበት ጊዜ ድረስ የዮሐንስ ወንድም የነበረው ያዕቆብ የዚያ ቡድን አባል ተደርጎ ሲጠቀስ አናይም (ማር. 1:19፤ ማቴ. 4:21):: ብዙም ሳይቆይ ኢየሱስ በቅፍርናሆም በኩል ሲያልፍ ማቴዎስን (ሌዊን) ይከተለው ዘንድ ጠራው (ማር. 2:13-14፤ ማቴ. 9:9፤ ሉቃስ 5:27-28):: የተቀሩትን ደቀ መዛሙርት አጠራር በተመለከተ በወንጌላት ላይ የተጻፈ ነገር አናገኝም፣ ቢሆንም የመምረጡ ሥራ ጌታ አገልግሎቱን በጀመረበት በመጀመሪያው ዓመት እንደ ተከናወነ ይታመናል::

በምድር ላይ በነበረባቸው ጊዜያት እነዚህ ነፍሳትን ለመማረክ ጌታ ያደረጋቸው ጥረቶች በዘመኑ በነበረው ሃይማኖታዊ ሕይወት ላይ የነበራቸው ድርሻ ጥቂት እንዲያውም ምንም ቅጽበታዊ ተጽዕኖ አላደረጉም ሊባል ይችላል:: ወደ ኋላ ላይ እንደምንመለከተው፣ ቀደም ሲል በጌታ አማካይነት የተለወጡት እነዚህ ጥቂቶች ነበሩ ወንጌልን እስከ ዓለም ዳርቻ ይዛ ለምትሰፋው የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች እንዲሆኑ የታጩት:: ከእርሱም የዘለቄታ ዓላማ አንጻር የሕይወታቸው ቁም ነገር ለዘላለም ሲታወስ የሚኖር ነው::

## ለመማር ፈቃደኛ የሆኑ ሰዎች

በጣም የሚያስገርመው ነገር እነዚህ የተመረጡት ሰዎች መጀመሪያ ስናያቸው ያን ያህል አስፈላጊ ናቸው ብለን እንኳ ቦታ የምንሰጣቸው ሰዎች አልነበሩም:: ከእነርሱ ማንኛቸውም በምኩራብ ውስጥ የክብር ቦታ አልነበራቸውም፣ ወይም የቤተ መቅደስ ካህናትም አልነበሩም:: እንዲያውም አብዛኞቹ ለነበራቸው ሙያ ድጋፍ ከሚሆን መሠረታዊ እውቀት በቀር ምንም ዓይነት የሙያ ሥልጠና ያልነበራቸው ተራ ለፍቶ አዳሪዎች ነበሩ:: ምናልባትም



መጠነኛ ገቢ ካለው ቤተሰብ እንደ መጡት እንደ ዘብዴዎስ ልጅ ካሉት ጥቂቶች በስተቀር፣ ማንኛቸውም ባለጸጋ የሚባሉ አልነበሩም:: በወቅቱ በነበሩት የፍልስፍና ወይም የሥነ ጥበብ ሙያዎች ዲግሪ አልነበራቸውም:: እንደ መሪያቸው የእነርሱም የትምህርት ደረጃ በምኩራብ ይሰጥ ከነበረው ትምህርት የዘለለ አልነበረም:: አብዛኞቹ ያደጉት በገሊላ አካባቢ በሚገኝ የደሀው ኅብረተሰብ ክፍል ውስጥ ነው:: ከአሥራ ሁለቱ ውስጥ ምርጥ ከነበረው የይሁዳ ክልል የመጣው የአስቆሮቱ ይሁዳ ብቻ ነው:: ያኔም ሆነ አሁን እጅግ የተለያየና የመጠቀ ባህል ባላቸው ሕዝቦች ባህል አንጻር ብንመለከት ገራገር የሆኑ ሰዎች የተሰባሰቡበት ነበር:: ኢየሱስ እንዴት ሊጠቀምባቸው ቻለ ብሎ አንድ ሰው ሊገረም ይችላል:: ችኩሎች፣ ስሜታዊነት የሚታይባቸው፣ በቀላሉ ስሜታቸው የሚጎዳና አካባቢያቸው የነበረውን የአመለካከት ተጽዕኖ ይዘው ያደጉ ነበሩ:: በአጠቃላይ የጌታ ረዳቶች ይሆኑ ዘንድ በእርሱ የተመረጡት እነዚህ ሰዎች በዘመናቸው የነበረውን አማካይ የኅብረተሰብ ክፍል የሚወክሉ ነበሩ:: ዓለምን ለክርስቶስ ይማርካል ተብሎ የሚመረጠው ቡድን የዚህ ዓይነት ይሆናል ብሎ ማንም አይጠብቅም::

ኢየሱስ ግን በእነዚህ ተራ ሰዎች ውስጥ ለመንግሥቱ የሚሆነውን የማስተዳደር ብቃት አይቶ ነበር:: በእርግጥም በዚህ ዓለም መስፈርት እነዚህ ሰዎች ያልተማሩና መሐይሞች ይሁኑ እንጂ (የሐዋ. ሥራ 4:13)፣ የሚማር ልብ ግን ነበራቸው:: አንዳንድ ጊዜ የተሳሳቱ ውሳኔዎችን የሚወስኑና መንፈሳዊውን ነገር ለመረዳትም ዝግ ያሉ ቢሆኑም፣ ችግራቸውን በግልጽነት የሚያስታውቁ ሰዎች ነበሩ:: ጠባያቸው አስቸጋሪ፣ ችሎታቸውም ውሱን ቢሆንም፣ ከዚያ ከከዳተኛው በቀር ሁሉም ትልቅ ልብ ነበራቸው:: ምናልባትም በሕይወታቸው ውስጥ ይታይ የነበረው

ትልቁ ነገር ለእግዚአብሔርና ከእርሱ ለሚገኘው የሕይወት እውነታ የነበራቸው ጉጉት ነበር:: ጥልቀት ያልነበረው የአካባቢያቸው ሃይማኖታዊ ገጽታ ስለ መሢሑ የነበራቸውን ተስፋ አላበላሸባቸውም ነበር (ዮሐ. 1:41፣ 45፣49፤ 6:69):: በጊዜው አገሪቱን ያስተዳድር በነበረው መንግሥት ግብዝነት ተሰላችተዋል:: እንዲያውም አንዳንዶቹ በመጥምቁ ዮሐንስ የመነቃቂያ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ተካፋዮች ነበሩ (ዮሐ. 1:35):: እነዚህ ሰዎች የደኅንነትን መንገድ የሚመራቸው ሰው በመፈለግ ላይ ነበሩ፡ በጌታ እጆች ውስጥ ሊተጣጠፉ የሚችሉት እነዚህን መሳይ ሰዎች በአዲስ መልክ ሊቀረጹ ይችላሉ:: ኢየሱስ እንዲጠቀምበት ፈቃደኛ የሆነውን ማንኛውንም ሰው ሊጠቀምበት ይችላል::

## በጥቂቶች ላይ ያተኮረ

ይሁን እንጂ፣ ይህንን ሁኔታ ልብ ስንል፣ ኢየሱስ በምን ዓይነት ተግባራዊ እውነታ እንደ ተገበረው ሳናውቅ መቅረት አንፈልግም:: እንግዲህ የእርሱ ስልት ጥበብ እነሆ እዚህ ላይ ነው፣ ይህንንም በሚገባ በመመልከት እርሱ ይጠቀምባቸው ዘንድ ወዳተኰረባቸው ወደዚያ መሠረታዊ መርሖ እንመለሳለን:: በዓለም ውስጥ ያሉት ሰዎች በግለሰብ ደረጃ እስካልተለወጡ ድረስ ማንም ዓለምን ሊለውጥ አይችልም:: በጌታ እጆች ካልተቀረጹ በስተቀር ግለሰቦችም ቢሆኑ ሊለወጡ አይችሉም:: ጥቂት ረዳቶችን መምረጥ ብቻ ሳይሆን ውጤታማ የሆነ ሥራ መሥራት ይቻል ዘንድ የቡድኑን አባላት ቁጥር መወሰን አስፈላጊ መሆኑ ግልጽ ይሆናል::

በኢየሱስ ዙሪያ ያሉት ተከታዮች እየጨመሩ በሄዱ ቁጥር በሁለተኛው የአገልግሎት ዓመት አጋማሽ ላይ ከእነዚህ ከተመረጡትም ውስጥ ይበልጥ ለአሠራር ምቹ እንዲሆን ቁጥራቸውን መቀነስ አስፈላጊ ሆነ:: ስለሆነም ኢየሱስ፣ «ደቀ



መዛሙርቱን ጠራ፣ ከእነርሱም አሥራ ሁለት መረጠ ደግሞም ሐዋርያት ብሎ ሰየማቸው» (ሉቃ. 6፡13-17ን ከማር. 3:13-19 ጋር አነጻጽሩ):: ቁጥራቸው አሥራ ሁለት በመሆኑ አንዳዶች ሊሰጡት ከሚወዱት ተምሳሌታዊ ትርጉም ሌላ እነዚህ ሰዎች በመንግሥቱ ሥራ ላይ ልዩ መብትና ኃላፊነት እንዲኖራቸው ኢየሱስ እንደፀቀደ ግልጽ ነው::

ይህ ማለት ግን ኢየሱስ አሥራ ሁለቱን ሐዋርያት ለመምረጥ መወሰኑ ሌሎች እንዳይከተሉት አድርጓቸዋል ማለት አይደለም:: እንደምናውቀውም፣ ብዙዎች የሥራ አጋሮቹ ሆነው አብረው ተቆጥረዋል፣ እንዲያውም ከእነዚህ አንዳንዶቹ በቤተ ክርስቲያን ሥራ ውስጥ ውጤታማ አገልጋዮች ሆነዋል:: ሰባዎቹ (ሉቃስ 10:1)፤ ወንጌልን የጻፈው ማርቆስና የእርሱም ወንድም ያዕቆብ (1ኛ ቆሮ. 15:7፣ ገላ 2:9፣12ን ከዮሐ. 3:12፣ 7፤2-10 ጋር ያነጻጽሩ) ለዚህ ተጠቃሽ ምሳሌዎች ናቸው:: ይህም ሆኖ ግን ከአሥራ ሁለቱ ውጪ ላሉት በፍጥነት የመነመነ ትኩረት ይሰጥ እንደ ነበረ ማስተዋል ይገባናል::

ይሄው ደንብ በተገላቢጦሽ ሊታይም ይችላል፣ ከእነዚህ ከተመረጡት ጴጥሮስ፣ ያዕቆብ፣ ዮሐንስ ከቀሩት ከዘጠኙ ይልቅ ከመምህሩ ጋር ለየት ያለ ኅብረትና መቀራረብ ነበራቸው:: ልጁ ወደ ታመመችበት ወደ ምኩራብ አለቃው ቤት ሲገባ አብረውት እንዲገቡ የተጋበዙት እነዚህ የታደሉት ጥቂት ደቀ መዛሙርት ብቻ ነበሩ (ማር. 5:37፣ ሉቃ. 8: 51):: ከመምህሩ ጋር በሚሄድ በመለወጥ ተራራ ላይ የሆነውን የእግዚአብሔርን ክብር ለማየት የታደሉት እነዚሁ ብቻ ነበሩ (ማር. 9:2፤ ማቴ. 17፣1፤ ሉቃ. 9፣28):: በወይራ ዛፎቹ መካከል ለፋሲካ በወጣው ደማቅ የጨረቃ ብርሀን ሥጋት የሰፈነበት ጥላ ፈጥረው ለምሽቱ ልዩ ውበትን ፈጠሩበት:: ጌታቸው በሚጸልይበት ሰዓት በጌቴሴማኒ የአትክልት

ስፍራ ይህ ታናሽ ቡድን በአቅራቢያው ሆነው ይጠብቁ ነበር:: (ማርቆስ 14:33፤ ማቴ. 26:37):: ለእነዚህ ለሦስቱ የተሰጠው ልዩ አመለካከት በጉልህ ይታይ ነበረና በክርስቶስ ማንነት ራስን መካድ በጉልህ በመገለጹ ነበር እንጂ በተቀሩት ሐዋርያት ዘንድ የቅሬታ ስሜት ባስከተለም ነበር:: በሌሎች ጉዳዮች ሲያጉረመርሙ ቢታዩም፣ እነዚህን ሦስቱን ወደ ራሱ በማስጠጋቱ ግን የተቀሩት ሐዋርያት አጉረመረሙ የሚል ነገር ተዘግቦ አለመገኘቱ፣ ይህ ደግሞ በቀና መንፈስና ለትክክለኛ ዓላማ የሚደረግ ልዩ አመለካከት ተቃውሞን እንደማያስከትል መረጃ ይሆናል::

## መርሑ ሲስተዋል

በአጠቃላይ ጌታ ኢየሱስ ሲያሠለጥናቸው ለመረጣቸው ሕይወቱን ለማጋራት የተጠቀመበትን ሆን ብሎ ያደረገውን ስንመለከት በእርግጥ የሚያስገርም ሆኖ እናገኘዋለን:: ከዚህ በተጨማሪ መሠረታዊ የሆነ የማስተማር ስልትን በግልጽ ለማየት ያስችለናል:: የሚደረጉት ሌሎቹ ነገሮች እኩል ሆነው የምናሠለጥነው ቡድን ቁጥር ውሱን መሆኑ በራሱ የመማር ማስተማር ሂደቱን ይበልጥ ውጤታማ የማድረግ አስተዋጽኦ እንዳለው ያሳየናል::

ኢየሱስ በምድር ላይ የነበረው ቀሪውን የሕይወት ዘመኑን ለእነዚህ ጥቂት ለሆኑት ሐዋርያቱ በሙላት ሰጥቶ ነበር:: እንዲያውም በግልጽ ለመናገር በምድር ላይ የነበረውን ጠቅላላውን አገልግሎቱን ከእነርሱ ጋር አስተሳስሮ ነበር:: ዓለም ስለ እርሱ ደንታ ላይ ኖረው ይችላል:: ይሁን እንጂ፣ ስልቱን ግን ከንቱ ሊያደርግበት አልተቻለውም:: የመንግሥቱን እውነተኛ ምሥጢር በነገራቸው ጊዜ ብዙዎች ተከታዮቹ ግራ በመጋባት ተሸንፈው ጥለው ወደ ኋላ ሲያፈገፍጉ እንኳን ያን ያህል አልተጨነቀም ነበር



(ዮሐ. 6:66):: የሚቀርቡት ደቀ መዛሙርቱ ግን ዓላማውን ስተው ሲያገኛቸው ግን ትዕግሥት አልነበረውም:: እውነቱን በሚገባ ሲረዱና በእውነቱም ይቀደሱ ዘንድ ይገባቸው ነበር (ዮሐ. 17:17)፣ ይህ ካልሆነ ግን ሁሉም ነገር ይጠፋል:: ስለዚህ «ለዓለም» ሳይሆን እግዚአብሔር «ከዓለም» ለሰጠው ለእነዚህ ለጥቂቶቹ ጸለየላቸው (ዮሐ. 17:6፣9):: ዓለም ከቃላቸው የተነሣ በእርሱ ያምን ዘንድ (ዮሐ. 17:20) ማንኛውም ነገር በእነርሱ ላይ ያረፈ ነበር::

## ብዙሃኑን ችላ አላለም

ይሁን እንጂ፣ እስከ አሁን የተነጋገርነውን መሠረት በማድረግ ኢየሱስ ሐዋርያቱን እንጂ ሌላውን ሕዝብ ችላ ብሎ ነበር ብንል እንስታለን:: ሁኔታው እንደዚያ አልነበረም:: ኢየሱስ ሰዎችን በወንጌል ለመድረስ ከማንኛውም ሰው የሚጠበቀውን ያህል የተቻለውን አድርጓል:: አገልግሎቱን ሲጀምር መጀመሪያ ያደረገው ነገር በዘመኑ ታላቅ መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ከነበረው ከመጥምቁ ዮሐንስ አገልግሎት ጋር መስማማቱን በመግለጽ በመጥምቁ እጅ መጠመቅ ነበር (ማር. 1:9-11፤ ማቴ. 3:13-17፤ ሉቃ. 3:21-22)፣ እንዲያውም በኋላ በንግግሩ ጣልቃ የዚህን ታላቅ ነቢይ አገልግሎት ሲያመሰግን እናያለን (ማቴ. 11:7-15፤ ሉቃ. 7:24-28):: በድንቅና በተአምራት የተሞላውን አገልግሎቱን አይተው ይከተሉት ለነበሩት ሁሉ ኢየሱስ ዘወትር ቃሉን ይሰብክላቸው፣ ያስተምራቸውና ተርበው ሳለም ይመግባቸው ነበር:: ድውዮቻቸውን ፈውሷል፣ አጋንንትን አስወጥቷል፣ ልጆቻቸውንም ባርኳል:: እንዲያውም አንዳንድ ጊዜ ለመብል እንኳ ጊዜ እስኪያጥረው ድረስ (ማር. 6:31) ለችግሮቻቸው መፍትሔን ሲሰጥ ነበር:: በተቻለው መንገድ ሁሉ ለሰው ልጆች ምን ያህል ግድ እንደሚለው አሳይቷል:: ሲያድናቸው ወድዶ ከሰማያት የመጣላቸው ሕዝቦች ናቸው፣ ይወዳቸዋል፣ ስለ

እነርሱ አንብቷል፣ በመጨረሻም ከኃጢአታቸው ሊያድናቸው ሞቶላቸዋል:: ጌታ ኢየሱስ ሕዝቡን በወንጌል ለመድረስ ችላ እንዳለ የሚያስብ አይኖርም::

## ብዙሃኑን ሕዝብ ቀሰቀሰ

እንዲያውም ጌታ ኢየሱስ በሕዝቡ ልቦና ያሳደረው መገረም በአገልግሎቱ ላይ ብርቱ አሉታዊ ተጽዕኖ አሳድሮ ነበር:: ለእነርሱ ያለውን ፍቅሩንና ኃይሉን በሚገባ ያሳያቸው ነበርና እንዲያውም አንድ ጊዜ በግድ ወስደው ንጉሣቸው አድርገው ሊሾሙት ፈልገው ነበር (ዮሐ. 6:15):: ከመጥምቁ ዮሐንስ ተከታዮች ዘንድ በአንድ ወቅት እንዲህ የሚል ዘገባ ነበር:- «ሁሉም ወደ እርሱ ይመጣሉ» (ዮሐ. 3:26):: ፈሪሳውያን እንኳ ሳይቀሩ ዓለም ሁሉ እንደ ተከተለው አምነው ይነጋገሩ ነበር (ዮሐ. 12:19):: ለመቀበል አስቸጋሪ ሆኖ ቢተናነቃቸውም እንኳ፣ የሕግ አዋቂዎችም በዚህ እውነት ተስማምተው ነበር (ዮሐ. 11:47-48):: ይሁን እንጂ፣ በየትኛውም አንጻር ብንመለከተው፣ የትም ስፍራ ላይ ኢየሱስ በብዛት ሆኖ የሚከተለውን ሕዝብ እንዳጣ የሚተርክ ክፍል አናገኝም:: በእርግጥ አንዳንዶች በታማኝነታቸው ጸንተው አልቆዩም:: ይህም እስከ መጨረሻው የቀጠለ ሁኔታ ነበር:: እንዲያውም ይሄው በሕዝቡ ዘንድ የነበረው የወዳጅነት ስሜት ነበር ጌታ ኢየሱስን ሊይዙት የሚፈልጉት ተቃዋሚዎች እንኳ ሕዝቡ በሌለበት ሰዓት እንዲይዙት የገፋፋቸው (ማር. 12:12፤ ማቴ. 21:26፤ ሉቃ. 20:19)::

ጌታ ኢየሱስ በሕዝቡ ዘንድ የነበረውን ተቀባይነት አደፋፍሮ ቢሆን ኖሮ የዓለምን መንግሥታት ሥልጣን ሁሉ በቁጥጥሩ ሥር ባደረገ ነበር:: ይህንን እውን ለማድረግ መውሰድ የነበረባቸው እርምጃ ቢኖር በመለኮታዊው ኃይሉ ተጠቅሞ ለሕዝቡ ለምድራዊ



ጥያቄአቸውና ለአድናቆት ፍላጐታቸው ምላሽን መስጠት ብቻ ነበር:: ድንጋይን ወደ ዳቦ እንዲለውጥና የእግዚአብሔር መላእክት ስለሚታደጉት ከቤተ መቅደስ ጫፍ ራሱን እንዲጥል በጠየቀው ወቅት በዚያ ምድረ በዳ ሰይጣን ለኢየሱስ ያቀረበለት ፈተና ይሄ ነበር (ማቴ. 4:1-7፤ ሉቃ. 4:1-4፤ 9:13):: እንደዚህ ያሉትን አስደናቂ ነገሮች ቢያደርግ ሕዝቡን በእርግጥ በመገረም ይሞላ ነበር:: ወድቆ ቢሰግድለት የዓለምን መንግሥታት ሁሉ እንደሚሰጠው ሰይጣን ቃል ሲገባ (ማቴ. 4:8-10)፣ ለኢየሱስ የሚሰጠው ምንም ነገር አልነበረም:: ታላቁ የሰዎች አሳሳች ለአፍታ ከዘላለማዊው መንግሥቱ ፊቱን ለመመለስ ፈቃዱ ቢሆን ከኢየሱስ ዓለምን ሁሉ በሥልጣኑ ሥር ሊያደርግ እንደሚቻለው ያውቅ ስለነበር ነበር::

ጌታ ኢየሱስ ግን ድራማ እንደሚያሳይ ተዋናይ መሆን አልፈለገም:: በፊንታው ግን እንዲያውም በተደጋጋሚ በመለኮታዊው ኃይሉ በሠራው ሥራ (ለምሳሌ፣ ዮሐ. 2:23-3:3፤ 6:26-27) የተነሣሣውን የሕዝቦች አድናቆት ገለል ሲያደርግ እናያለን:: አብዛኛውን ጊዜም ፈውስን ከእጁ የተቀበሉትን ሰዎች ስለ እርሱ ምንም እንዳይናገሩ ያስጠነቅቃቸው ነበር:: ይህንንም ያደረገው ስሜታቸው በቀላሉ የሚነሣሣው ሕዝብ ሁካታ እንዳይፈጥሩ ለመከላከል ነው:: በዚያ በለውጥ ተራራ ላይ ይዞአቸው ለወጣው ደቀ መዛሙርቱም እስከ ትንሣኤው ወቅት (ማር. 9:9፤ ማቴ. 17:9) ያዩትን ለማንም እንዳይናገሩ አዝዟቸው ነበር:: በሌሎች ወቅቶች ሕዝቡ አድናቆቱን እየገለጸለት ሳለ ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ወደ ሌላ ስፍራ ፈቀቅ በማለት አገልግሎቱን ይቀጥል ነበር::

ይህንን በማድረጉ ደግሞ የአገልግሎቱ ስልት ያልገባቸው ተከታዮቹን ያበሳጫቸው ነበር:: በእርሱ ያላመኑት ወንድሞቹና

እነቶቹ እንኳ ሳይቀሩ እንዲህ ያለውን አካሄዱን ትቶ በይፋ እራሱን እንዲገልጽ ይገፋፉት ነበር:: እርሱ ግን ምክራቸውን አልተቀበለም (ዮሐ. 7:2-9)::

## ጥቂቶቹ ጉዳዩን የተረዱ ይመስላሉ

ከዚህ የአሠራር መርሕ አንጻር በክርስቶስ አገልግሎት ጊዜ ጥርት ባለ መንገድ የተለወጡ ጥቂት ሰዎች መኖራቸው የሚደነቅ አይደለም:: በእርግጥ መለኮታዊው አገልግሎቱን ከመቀበል አንጻር ብዙዎች በክርስቶስ አምነው ነበር:: ነገር ግን የወንጌልን ምንነት በሚገባ የተረዱት ጥቂት ነበሩ:: በምድር ላይ በነበረው አገልግሎቱ መጨረሻ ላይ ሙሉ በሙሉ የተከተሉት ከትንሣኤው በኋላ ከተገለጠላቸው ከአምስት መቶ ወገኖች ቁጥራቸው ትንሽ እልፍ ቢል ነው (1ኛ ቆሮ. 15:6)፣ የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት ለመቀበል በኢየሩሳሌም የተሰበሰቡት አንድ መቶ ሃያ ብቻ ነበሩ (የሐዋ. 1:15):: ይፋዊ አገልግሎቱ ለሦስት ዓመታት ብቻ የዘለቀ ከመሆኑ አንጻር ሲታይ ይህ ቁጥር ትንሽ ባይሆንም፣ የወንጌል ስርጭት ውጤታማነት የሚመዘነው በተለወጡ ሰዎች ቁጥር ብዛት ከሆነ ግን፣ እንግዲያው ኢየሱስ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ በጀማ የወንጌል አገልግሎት ውጤታማ ተብለው ሊጠቀሱ ከሚችሉት አንዱ ተደርጐ እንደማይቆጠር አያጠራጥርም::

## የክርስቶስ ስልት

ለምን? ጌታ ኢየሱስ ሆን ብሎ በጥቂቶች ላይ የተለየ ትኩረት ያደርግ የነበረው ለምን ይሆን? ዓለምን ሁሉ ሊያድን አልነበረም እንዴ መጣጡ? እርሱ ቢፈልግ መጥምቁ ዮሐንስ በሕዝብ ሁሉ ጆሮ ሲያንቃጭል የነበረውን የጋለ የምስራች ቃል ተከትሎ ሺዎችን ማስከተል ይችል ነበር:: ታዲያ ዓለምን ሁሉ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት እንዲጎርፍ ማድረግ የሚችሉ ብዙ ሠራዊቶችን



በመመልመል ለምን አጋጣሚውን አልተጠቀመበትም:: በእርግጥም ብዙዎችን በአንድ ጊዜ ለመመልመል እጅግ የሚያማልል ፕሮግራም ተግባራዊ ማድረግ በቻለ ነበር:: እንዲያውም የዓለምን ሁሉ ሥልጣን በእጁ ያደረገውና ዓለምን ሊያድን ራሱን ለሞት አሳልፎ እስኪሰጥ በምድር የኖረው እርሱ የልፋቱ ፍሬ ጥቂትና ተራ የሆኑ ደቀ መዛሙርት ብቻ መሆናቸው አያበሳጭም?

እንዲህ ላለው ጥያቄ መልስ የሚሆነው አሳብ ጌታ ኢየሱስ ለወንጌል ስርጭት በነበረው እውነተኛ ዓላማ ላይ ያተኩራል:: ጌታ ኢየሱስ ጥረቱ የሚከተለውን ሕዝብ ማስደመም ሳይሆን፣ የእግዚአብሔርን መንግሥት መምጣት ማወጅ ነበር:: ይህ ማለት ሕዝቡን ሊመሩ የሚችሉ ሰዎች ያስፈልጉት ነበር ማለት ነው:: ብዙዎች እንዲከተሉት ቅስቀሳ አድርጐ የኋላ ኋላ በቀጣይነት መንገዱን የሚያሳዩ በበላይነት የሚቆጣጠሩ ባይኖሩ ለዘለቄታ አሳቡ ምን ትርፍ ያስገኛል? ተገቢው ጥንቃቄ ካልተደረገለት ሕዝቡ በቀላሉ ወደ ቀደሙት ጣዖታት እንደሚመለስ በተደጋጋሚ የታየ ሐቅ ነው:: እረኛ እንደሌላቸው በጎች ተበትነው ሲቅበዘበዙ የሚገኙ ሕዝቦች ናቸው (ማር. 6:34፤ ማቴ. 9:36፤ 14:14):: ስለ ወደፊቱ መልካም ኑሮአቸው ተስፋ የሚሰጣቸው ጠላትም ይሁን ወዳጅ ማንም ቢሆን ሊከተሉት ፈቃደኞች ነበሩ:: የወቅቱ አሳዛኝ ገጠመኝ ይሄ ነበር:: የሕዝቡ መልካም አስተሳሰብ በጊዜው ይቆጣጠሩአቸው በነበሩት በሃይማኖት መሪዎቻቸው ይነሣሡ ነበር:: ሆኖም አመለካከቱ ወዲያው ይታጠፋል:: በመንፈሳዊው አንጻር የታወሩት የእስራኤል መሪዎች (ዮሐ. 8:44፤ 9:39-41፤ 12:40፤ ከማቴ. 23:1-39 ጋር ያነጻጽሩ) ከሕዝቡ አንጻር በቁጥር ቂቶች ቢሆኑም፣ በሕዝቡ ጉዳይ ላይ ሙሉ በሙሉ ፈላጭ ቆራጭ ሆነው ነበር:: ስለሆነም በክርስቶስ የተለወጡትን ሰዎች ተስፋ ለመቁረጥ የተጋለጡ ይሆናሉ:: የኋለኛውም ሁኔታቸው ከፊተኛው የባሰ

ይሆናል። ስለሆነም ዓለም ዘላቂነት ባለው ሁኔታ እርዳታ ከማግኘቱ በፊት በእግዚአብሔር ነገር ሕዝቡን የሚመሩ ሰዎችን ማዘጋጀት ይገባ ነበር።

ጌታ ኢየሱስ እውነታዎችን እንዳሉ ነበር የሚቀበላቸው። የሰውን ብልሹ ባህሪ ከንቱነትና በሰው ላይ የሚነግሠውን የዚህን ዓለም የክፉ መናፍስት አሠራር በሚገባ ያውቅ ነበር። ይህንንም መሠረት በማድረግ ለዚህ መፍትሔ የሚሆን የወንጌል ስርጭት ስልት ቀየሰ። ግራ የተጋቡትና የተደናገጡት ሕዝቦች ሊከተሉት ዝግጁ ነበሩ። ይሁን እንጂ፣ ኢየሱስ ለእያንዳንዳቸው በግል የሚያስፈልጋቸውን እንክብካቤ ሊሰጣቸው አይችልም ነበር። የእርሱ ተስፋ በእርሱ ሕይወት ተነቃቅተው እርሱን ብለው የሚያገለግሉ መሪዎችን ማፍራት ብቻ ነበር። ስለሆነም የዚህ አመራር ጀማሪ በሚሆኑት ላይ ትኩረቱን አደረገ። ሕዝቡን ለመርዳት የተቻለውን ሁሉ ቢያደርግም፣ በመጨረሻ ሁሉ ደኅንነትን ያገኙ ዘንድ ለተመረጡት ለጥቂቶቹ ግን በቅድሚያ ራሱን ሊሰጣቸው ይገባ ነበር። የቀየሰውን ስልት ብልህ የሚያሰኘው ይኸው ነበር።

## መርሑ ዛሬ ተግባር ላይ ሲውል

መርሑ ከፍ ብሎ እንደተገለጸው ቢሆንም፣ በአስገራሚ ሁኔታ እምብዛም ተግባራዊ ግንዛቤ አላገኘም። ዛሬ በቤተ ክርስቲያን የተከናወኑ መልካም ነገሮችን ጠብቃ ማቆየት እንደምትችል በመገመት በአብዛኛው በቤተ ክርስቲያን የሚካሄደው የወንጌል ስርጭት ጥረት ብዙኃኑን መነሻ ያደረገ ነው። የዚህም አሠራር ውጤቱ ደግሞ በእኛ በኩል የዳኑና ለጥምቀት የታጩ ብዙ ሰዎችን በቤተ ክርስቲያን በማስመዝገብ የምናደርገው አስደናቂ ትኩረት ነው። ጥረት ማድረግ ቀርቶ ሥራው በዚያው መልኩ እንዲቀጥል እነዚህን ሰዎች በእግዚአብሔር ፍቅርና ኃይል ላይ ለመመሥረት



የሚደረገው ጥረት ወይንም የሚሰጠው ትኩረት ምንም ቁጥር ውስጥ የማይገባ ነው።

በእውነት ለመናገር፣ በዚህ ጉዳይ ላይ የጌታችን የኢየሱስ ስልት አንድ ነገር አመልካች ከሆነ፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ተቀዳሚ ተግባር በመጀመሪያ ውጤታም፣ ቀጣይና ወደ ብዙኃኑ የሚደርስ የወንጌልን ስርጭት አገልግሎት መሠረት መጣል እንደ ሆነ ያስተምረናል። ይህ ደግሞ ቤተ ክርስቲያን ለዓለም ያላትን አደራ ሳትረሳ ጊዜንና ችሎታን በይበልጥ በጥቂት ሰዎች ላይ ማተኮርን ይጠይቃል። ይህም ማለት የወንጌል አገልግሎትን ሥራ እንዲፈጽሙ ከመጋቢውና ከቤተ ክርስቲያን ሠራተኞች ጋር (ኤፌ. 4:12) የሠለጠኑ ደቀ መዛሙርት ማነሣሣት ማለት ነው። በብዙኃኑ አማካይነት ድል አይገኝም። ራሳቸውን የሰጡ ሰዎች የኋላ ኋላ ዓለምን ለእግዚአብሔር ያናውጣሉ።

ይህንን ክርስቲያናዊው አገልጋይ በሥራ ላይ ማዋል ሲጀምር፣ ከቤተ ክርስቲያን አባላት መካከል ለጥቂቶች አድልዎ የተደረገላቸው መስሎአቸው ይህንን ስልት የሚቃወሙ ጥቂቶች አይጠፉም። ግን ይህ እንዳለ ሆኖ፣ ጌታ በሕይወቱ ትኩረት የሰጠበት መንገድና ዘለቄታ ያላቸውን መሪዎችን ማሠልጠን ካስፈለገ፣ አሁንም አስፈላጊው ስልት ይሄ ነው። ለመላይቱ ቤተ ክርስቲያን ካለን እውነተኛ ፍቅር የተነሣና ለሰዎች ፍላጎት ተገቢው ትኩረት እየተሰጠ መሆኑ ከታየ ለተልዕኮው መሳካት ሲባል ቢያንስ ቢያንስ የሚነሣው ተቃውሞ በዕርቅ የሚፈታ ይሆናል። ሆኖም፣ የመጨረሻው ግብ ለሠራተኛው ግልጽ ሊሆን ይገባል። ከሁሉም ጋር ያለውን ግንኙነት በተመለከተ ምንም ዓይነት ራስ ወዳድ የሆነ አድልዎ በመካከላቸው መፈጠሩን የሚያመለክት ምንም ፍንጭ ሊኖር አይችልም። በጥቂቶች የሚሠራው ማንኛውም ሥራ ለብዙኃኑ ደኅንነት ሲባል ነው።

## በተግባር የታዩ አሠራሮች

ይህ ጥቂቶችን የመምረጥና በእነርሱ ላይ የማተኮር ስልት በመላው ተፈጥሮ በጥልቀት ተቀርጾ ያለ በመሆኑ፣ ቤተ ክርስቲያን አመነችም አላመነችም ማንም ተግባራዊ ካደረገው ውጤት የሚገኝበት ስልት ነው:: በንግድ፣ በኢንዱስትሪ፣ በመንግሥት አስተዳደር ወይም በወታደራዊ ትምህርት የተሰጡ ውጤታማ የአመራር ሥልጠናዎችን እንመልከት::

በዓለም አቀፋዊ ደረጃ ምን ጊዜም የሚያዋጣቸውን የሚፈልጉት የቀደሙት የኮሚኒስት መሪዎች ያለበቂ ምክንያት አይደለም በአብዛኛው የክርስቶስን ስልት የራሳቸው ስልት አድርገው የወሰዱት:: ይህን ስልት ወደ ራሳቸው ላዘመመ ግብ በመጠቀም ያህል ከሆኑ ቀናኢ ሰዎች በመነሣት እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የዓለምን ሕዝብ አጋማሽ እስኪማርክ ወደ ትልቅ የተከታዮች ሠራዊት አድጓል:: ይህ ደግሞ የሚከተሉት መሪ ከተሰጣቸው ብዙሃኑ በቀላሉ ሊሸነፉ እንደሚችሉ ኢየሱስ በዘመኑ በግልጽ ያሳየው የአዲሱ ዘመን ምሳሌ ሆነዋል::

## የተግባር ጊዜ

ይህ ጊዜ ቤተ ክርስቲያን ሁኔታዎችን በእርግጠኝነት ፊት ለፊት ልትጋፈጥ የሚገባት ጊዜ ነው:: የሚያባክኑን ቀኖቻችን እየሮጡ ናቸው:: በአንጻሩ የወንጌል ስርጭት ፕሮግራም በሁሉም አቅጣጫ በተለይም በበለጸጉት የምዕራብ አገሮች እየተዋጠና እየሰጠመ ነው:: በብዙ ቦታ ደካማዋ ቤተ ክርስቲያን እየበዛ ካለው የሕዝብ ብዛት ጋር አብራ ልትጓዝ አልቻለችም:: የዚህም ዓለም የሰይጣን ኃይላት ውጊያቸውን በጭካኔ አጠናክረው ቀጥለዋል:: ስለዚህ ጉዳይ ማሰብ ማቆም ደግሞ መቀለድ ይሆናል:: እስከ ዛሬ



ሆኖ ባልታወቀ መልኩ በቤተ ክርስቲያን የሆነ የወንጌል ስርጭትን ማከናወን የሚያስችሉ ፈጣን የግንኙነት ሁኔታዎች በተመቻቹበት በዚህ ዘመን ዓለምን ለእግዚአብሔር ለመማረክ ፈረስ የሌለው ጋሪ በነበረበት ዘመን ይከወን ከነበረው ያነሰ ውጤት በማሳየት ላይ እንገኛለን::

ይህንን አሳዛኝ ጉዳይ ዛሬ ገምግሞ በአንድ ሌሊት ለመለወጥ ሙከራ በማድረግ መጨነቅ አይገባንም:: ዋናው ችግራችንም ይሄው ሊሆን ይችላል:: የነገሩን አቅጣጫ ለመለወጥ ካለን ሽክም የተነሣ ከአንድ አጣዳፊ ፕሮግራም ወደ ሌላው አጣዳፊ ፕሮግራም በመ-ሽጋገር ለብዙሃኑ ደኅንነት በሚያስገኘው በእግዚአብሔር ቃል ለመድረስ እየጣርን ነው:: ተስፋ በቆረጥንበት ሁኔታ ውስጥ ሆነን ማስተዋል ያቃተን እውነተኛው ችግር ከብዙሀኑ ጋር የተያያዘ ማለትም ከሚያምኑት እምነት፣ ከሚሰጣቸው አመራር ወይም አስፈላጊውን ምግብ ከመመገብ አለመመገባቸው የተነሣ እንዳልሆነ ነው:: በጣም አስፈላጊ እንደ ሆኑ የሚቆጠሩት እነዚህ ነገሮች ለሌሎች መጠቀሚያ እየሆኑ ነው:: የሕዝቡን መጠቀሚያ መሆኑን ለማስቀረት ከመጣራችን በፊት ሕዝቡ እየተከተሏቸው ወዳሉት ሰዎች ልንደርስ ይገባናል::

ይህም ደግሞ በተለይ በከፍተኛ ኃላፊነትና መሪነት ላይ ያሉትን ወደዚህ አሳብ መማረክና ለማሠልጠን ቅድሚያ ይጠይቃል:: ሥራችንን ከላይ ባሉት ሰዎች መጀመር ካልቻልን፣ እኛ ካለንበት ስፍራ እንጀምርና ከታች ያሉት የበላይ እንዲሆኑ እናሠልጥን:: አንድ ሰው የእግዚአብሔርን መንግሥት ለማገልገል የግድ በዓለም የከበረ ሰው ሊሆን እንደማይገባውም በድጋሚ እናስታውስ:: ተገቢው ሥልጠና እስከ ተሰጠው ለመከተል በፈቃዱ የወሰነ ማንኛውም ሰው በዓለም ላይ አስደናቂ የሆነ ተጽዕኖ ሊያመጣ ይችላል:: ሆኖም እንደ ኢየሱስ ሥራን የምንጀምረው እዚህ ላይ ነው:: ሂደቱ

አዝጋሚ፣ አሰልቺ፣ የሚያሳምምና እንዲሁም በመጀመሪያ በሰዎች ያልተስተዋለ ሊሆን ይችላል፣ ነገር ግን መጨረሻውን እስከምናይ በሕይወት ባንኖርም ውጤቱ ግን የከበረ ይሆናል:: ነገሮችን በዚህ መልኩ መመልከቱ ደግሞ በአገልግሎት ውስጥ ትልቅ ውሳኔ ነው:: ይኸውም የአገልግሎታችን ቁም ነገር የት ላይ እንዲሆን ነው የምንፈልገው? የብዙዎችን እውቅና በምናገኝበት በጊዜያዊ ጭብጨባ ላይ ነው ወይስ እኛ ብናልፍም አገልግሎቱን በሚቀጥሉት ጥቂት የተመረጡ ሰዎች ላይ የሕይወታችንን ነጸብራቅ ማሳረፍ ነው:: ይህ በእርግጥ ለየትኛው ትውልድ ነው እየኖርን ያለነው የሚለውን ጥያቄ ያስነሣል::

ቢሆንም፣ መቀጠል አለብን:: የእርሱ ምርጦች አገልግሎቱን ተቀብለው እንዲቀጥሉ እንዴት እንዳሠለጠናቸው ማስተዋል አስፈላጊ ነው:: ጠቅላላ ሥርዓቱ የስልቱ አካል ነው፣ በመሆኑም ውጤታማነቱን ሳናፈርስ አንዱን ገጽታ ከሌላው መነጠል አንችልም::



እነሆም፣ እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ

ማቴዎስ 28:20

# 2
# መተባበር

## ከእነርሱ ጋር ኖረ

የራሱ የሆኑትን ከጠራ በኋላ፣ ኢየሱስ ከእነርሱ ጋር መሆንን ልማዱ አድርጐት ነበር:: ይህም ደግሞ የእርሱን የሥልጠና ፕሮግራም መሠረት ደቀ መዛሙርቱ እንዲከተሉት ማድረግ ነበር::

እንዲሁ ነገሩን ስናስበው፣ በአስገራሚ ሁኔታ ቀላሉ መንገድ ይሄው ነው:: ኢየሱስ መደበኛ ትምህርት ቤት፣ ማሠልጠኛ ማዕከል፣ የተነደፈ ሥርዓተ ትምህርት፣ ወቅታዊ የሆኑ የትምህርት ክፍሎችና ተማሪዎች አልነበሩትም:: ዛሬ እጅግ አስፈላጊ ናቸው ከሚባሉት በከፍተኛ ደረጃ ከተደራጁት ከእነዚህ ስልቶች የትኞቹም በእርሱ አገልግሎት ውስጥ ስፍራ አልነበራቸውም:: አስደናቂ ቢመስልም፣ ጌታ የመረጣቸውን ሰዎች ለማሠልጠን ያደረገው ነገር ቢኖር ሰዎችን ወደ ራሱ ማቅረብ ነበር:: በመሆኑም እርሱ ራሱ ትምህርት ቤትና የትምህርት ሥርዓት ነበረ::

ይህ በተፈጥሮው መደበኛ ያልሆነው የኢየሱስ የማስተማር ዘዴ መደበኛ ከሆነውና ከትምህርት ቤት አሠራር ጋር ከተዛመደው ከጸሐፍት ሥርዓት ጋር በአስገራሚ ሁኔታ የተቃረነ ነበር:: እነዚህ የሃይማኖት  አስተማሪዎች ተከታዮቻቸው ከሌሎች የሚለያቸውን አምልኮና ሃይማኖታዊ ሥነ ምግባር ጠበቅ ባለ መልኩ እንዲያከብሩ አበክረው ይሻሉ:: ጌታ ኢየሱስ ግን ደቀ መዛሙርቱን የጠየቀው እንዲከተሉት ብቻ ነው:: ጌታ ኢየሱስ እውቀትን ለተከታዮቹ ያስጨበጠው ሕግን እና ቀኖናን በማካፈል ሳይሆን፣ በሕያውነት

አብሮ በመኖር ነበረ:: የጌታ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርት መለያቸው ውጫዊ በሆነና ለታይታ በሚያሳዩት መንፈሳዊ ሥርዓቶች ሳይሆን፣ ከእርሱ ጋር በመኖርና በእርሱ አስተምህሮ ላይ በሚያሳዩት ተሳትፎ ነበር (ዮሐ. 18:19)::

## ማወቅ አብሮ መኖር ነው

ደቀ መዛሙርት «የእግዚአብሔርን መንግሥት ምሥጢር» (ሉቃ. 8:10) ሊያውቁ የቻሉት ከጌታ ጋር ከነበራቸው ኅብረት የተነሣ ነበር:: ከሚደረግ ገለጻ በፊት እውቀት ይገኝ የነበረው አብሮ በመኖርና በመተባበር ነበር:: ይህ ጉዳይ ደግሞ በሚገባ የተገለጸው ከቡድኑ ውስጥ አንዱ «መንገድህን እንዴት ልናውቅ እንችላለን» በማለት ስለ ሥላሴ ያለበትን ግራ መጋባት አስመልክቶ ባቀረበለት ጥያቄ ነው:: ጌታም መለሰ፣ «እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ አለ» (ዮሐ. 14:5-6)፣ ማለትም ደቀ መዛሙርት ዓይናቸውን ቢገልጡና ቢያስተውሉ ግልጽ በሆነው በመካከላቸው በሥጋ በተገለጠው መንፈሳዊ እውነት በኩል ቀደም ሲል ለተነሣው ጥያቄ መልሱ ተሰጥቶ ነበር::

የክርስቶስ ስልት የተገለጠው ገና ከጅምሩ ሊመራቸው ፈልጎ ለሰዎች ግብዣ ባቀረበበት ወቅት ነበር:: ዮሐንስና እንድርያስ ኢየሱስ የሚኖርበትን ቦታ «እንዲመጡና እንዲያዩ» ተጋበዙ (ዮሐ. 1:39):: ከዚህ ያለፈ ሌላ ተጨማሪ ነገር አልተነገረም:: ደግሞስ ሌላ ምን ሊባል ይችላል? ከመኖሪያ ቦታው በመምጣትና ለብቻቸው በግል በመነጋገር ከእርሱ ጋር የቅርብ ግንኙነት ሊመሠርቱና ባሕሪውንና ሥራውን ሊያዩ ይችላሉ:: ፊልጶስም የተጠራው ተመሳሳይነት ባለው «ተከተለኝ» (ዮሐ. 1:43) በሚለው አጠራር ነው:: ፊልጶስም በዚህ ቀላል አቀራረብ ተስቦ እርሱም በበኩሉ ናትናኤልን «ናና እይ» (ዮሐ. 1:46) በማለት ጠርቶታል:: እንድ



ሕያው የሆነ መልእክት ከመቶ መግለጫዎች እኩል ነው:: ከዚህም በኋላ ያዕቆብ፣ ዮሐንስ፣ ጴጥሮስና እንድርያስ መረባቸውን እየጠገኑ በነበሩበት ወቅት ኢየሱስ ያንኑ የጥሪ ቃል በመጠቀም «ከኋላዬ ኑ» በማለት ነበር የጠራቸው፤ ሆኖም ይህንን ባደረገበት ጊዜ ለምን እንደሚጠራቸው ምክንያቱን በመግለጽ «ሰዎችን አጥማጆች እንድትሆኑ አደርጋችኋለሁ» (ማር. 1:17ን፤ ከማቴ. 4:19፣ ሉቃ 5:10 ጋር ያነጻጽሩ) ብሎ ነበር:: እንደዚሁም ማቴዎስም ቢሆን ከቀረጥ መደቡ ላይ «ተከተለኝ» በሚል ተመሳሳይ የጥሪ ቃል ነበር የተጠራው (ማር. 2:14፤ ማቴ. 9:9፤ ሉቃ 5:27)::

## መርሑ በትኩረት ሲታይ

እጅግ በጣም ታላቅ የሆነውን ስልቱን እንመልከት:: ለዚህ የመነሻ ጥሪ ለሆነው ምላሽ በመስጠት አማኞች መረዳታቸው በሚያድግበትና እምነታቸው መሠረት በሚይዝበት በጌታ ትምህርት ቤት ተመዘገቡ:: በእርግጥ እነዚህ የተመረጡ ሰዎች ያልተረዷቸው አያሌ ነገሮች ነበሩ - እነዚህም ችግሮች ከጌታ ጋር በተጓዙ መጠን እየተገነዘቧቸው የነበሩ ጉዳዮች ነበሩ:: ሆኖም ጌታን አጥብቀው በተከተሉ ጊዜ የሚወገዱ ችግሮች ነበሩ:: በእርሱ ሕልውና ውስጥ ሆነው ማወቅ ያለባቸውን ሁሉ ሊማሩ ይችላሉ::

ገና ከጅምሩ በተግባር ላይ የዋለው ይህ መርሕ ወደ ኋላ ላይ «ከእርሱ ጋር ይኖሩ ዘንድ» (ማር. 3:14ን ከሉቃስ 6:13 ጋር ያነጻጽሩ) ከብዙኃኑ ሕዝብ መካከል ጌታ አሥራ ሁለቱን በመረጠበት ወቅት ለየት ያለ ትኩረት ተሰጥቶታል:: ጌታም እነዚህን በጠራቸው ጊዜ የሚልካቸው «ወንጌልን እንዲሰብኩ፣ አጋንንትን ለማውጣት ሥልጣን እንዲሆንላቸው» የሚለውን በጥሪው ላይ ጨምሮአል:: ነገር ግን ቀዳሚው የትኛው እንደ ሆነ መገንዘብ ያዳግተናል:: ስለሆነም ከመስበካቸውና አጋንንትን

ከማስወጣታቸው በፊት ከእርሱ ጋር መኖር እንዳለባቸው ጌታ ኢየሱስ ግልጽ አድርጎታል:: እውነት ለመናገር ከጌታ ጋር የማይቋረጥ ኅብረት ሹመት ወንጌልን ለመስበክ የተሰጣቸው ሥልጣን አንድ ክፍል ነበር:: ለሌላው አገልግሎት የሚያዘጋጃቸው ስለነበረ፣ ይህ ደግሞ በወቅቱ ይበልጥ በጣም አስፈላጊ ነበር::

## ሥልጠናው ሊያበቃ ሲቃረብ የነበረው መቀራረብ

ይህንን ተልዕኮውን ለመፈጸም ኢየሱስ የነበረውን ፍጹም መስጠት በወንጌላት ላይ የሰፈሩት ተከታታይ አሳቦች በግልጽ ያሳያሉ:: ይሆናል ተብሎ ከሚጠበቀው በተቃራኒ ክርስቶስ የአገልግሎት ዘመኑ ሲጨምርና ወደ ሁለተኛው ብሎም ወደ ሦስተኛው ዓመት ሲሻገር ከፊት ይልቅ አብልጦ ጊዜውን ለመረጣቸው ለደቀ መዛሙርቱ ይሰጥ ነበር እንጂ አልቀነሰም::

የሕዝብ እይታን ለማስወገድ በመፈለግ ብዙውን ጊዜ ደቀ መዛሙርቱን ለብቻቸው እርሱ ከማይታወቅበት ተራራማ ወደ ሆኑት የአገሪቱ ስፍራዎች ለእረፍት ይወስዳቸው ነበር:: ከደቀ መዛሙርቱ ጋር በአንድነት በሰሜን ምዕራብ ወደ ነበሩት ወደ ጢሮስና ወደ ሲዶና ተጉዘዋል (ማር. 7:24፣ ማቴ. 15:21)፤ ከዛም ወደ «አሥር ከተሞች» ድንበርና (ማር. 7:31፤ ማቴ. 15:29)፣ በደቡብ ምሥራቅ ገሊላ ወደሚገኘው ድልማንያ ተሻግረዋል (ማር. 8:10፤ ማቴ. 15:39)፤ በሰሜን ምሥራቅም ወደ ፊልጶስ ቂሣርያ መንደሮች ሄደዋል (ማር. 8:27፤ ማቴ. 16:13):: እነዚህ ጉዞዎች የተካሄዱት በከፊል በፈሪሳውያን ተቃውሞና በንጉሥ ሄሮድስ ጥላቻ ምክንያት ቢሆንም፣ ዋናው ምክንያት ግን ኢየሱስ ብቻውን ከደቀ መዛሙርቱ ጋር መሆን መፈለጉ ነበር:: በኋላም ኢየሱስ ለብዙ ወራት ከዮርዳኖስ በስተ ምሥራቅ በሚገኘው በፐሪያ በርካታ



ወራትን አሳልፏል (ሉቃ. 13:22-19:28፤ ዮሐ. 10:40-11:54፤ ማቴ. 19:1-20:34፣ ማር. 10:1-52):: በእነዚህ ስፍራዎች ተቃውሞ እያየለ በመጣ ጊዜ፣ «ከዚያ ወዲያም ኢየሱስ በአይሁድ መካከል ተገልጦ አልተመላለሰም፣ ነገር ግን ከዚያ በምድረ በዳ አጠገብ ወዳለች ምድር ኤፍሬም ወደምትባል ከተማ ሄደ፣ በዚያም ከደቀ መዛሙርት ጋር ተቀመጠ» (ዮሐ. 11:54):: ወደ ኢየሩሳሌም ለመመለስ ጊዜው በደረሰ ጊዜ በብዛት ከሚከተሉት መካከል አሥራ ሁለቱን ለብቻ ነጥሎ በመውሰድ በቀስታ ጉዞውን ወደ ከተማ አቀና (ማቴ. 20:17ን፣ ማር. 10:32)::

ከዚህ አኳያ ጌታ ኢየሱስ የሕማማት ሳምንት እንኳን ደቀ መዛሙርቱ ከእርሱ እንዲርቁ አለ መፈለጉ የሚደንቅ አይደለም:: ብቻውን በጌቴሴማኒ በሚጸልይበት ጊዜ እንኳን ከደቀ መዛሙርቱ የነበረው ርቀት የድንጋይ ውርወራ ያህል ብቻ ነበር (ሉቃ. 22:41):: ይህ ደግሞ ጊዜው በተቃረበ ጊዜ ሰዎች ከቤተሰባቸው ሊለዩ የሚያደርጉት ድርጊት አይደለምን? ይህን መሳይ በአካለ ሥጋ የሚደረግ ግንኙነት እንደማይዘልቅ ግንዛቤው እየጨመረ ሲሄድ፣ እያንዳንዷ ደቂቃ የምታጓጓ እየሆነች ትሄዳለች:: በዚህ ወቅት የምንለዋወጣቸው ቃላት ምን ጊዜም ቢሆን ውድ ናቸው:: በእርግጥም ጊዜው እስከሚገባደድ ድረስ የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት ጥልቅ የሆነውን ከእርሱ ጋር የመኖር ትርጉም መረዳት አልጀመሩም ነበር (ዮሐ. 16:4):: ወንጌላትን የጻፉ ሰዎች አመዛኙን ትኩረታቸውን በዚህ የመጨረሻ ቀን ላይ ለምን እንዳደረጉ ያለ ጥርጥር ይሄ ሁኔታ ይገልጻል:: ስለሆነም ስለ ኢየሱስ ከተጻፉት ታሪኮች ግማሹ የተፈጸመው በመጨረሻዎቹ የሕይወቱ ወራት ሲሆን፣ ከእነዚህም አብዛኛው የተፈጸመው መጨረሻው ሳምንት ላይ ነበር::

ክርስቶስ በምድራዊ ሕይወቱ ይከተል የነበረው ጉዳና በከፍተኛ ሁኔታ የተገለጸው ከትንሣኤው በኋላ ባሉት ቀናት ነበር። በጣም የሚያስደስተው ነገር ከትንሣኤ በኋላ ከአሥሩም የክርስቶስ ድኅረ-ትንሣኤ መገለጦች የተከናወኑት ለተከታዮቹ በተለይም ለተመረጡት ሐዋርያት ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያሳየን፣ አማኝ ካልነበሩት ሰዎች አንድም ሰው የከበረውን ጌታ አላየም። ይህም እንግዳ ነገር አይደለም። አስደናቂ በሆነው መገለጥ ብዙኃኑን ሕዝብ ማስደነቅ አስፈላጊ አልነበረም። ቢገለጽላቸውስ ምን ያደርጉ ነበር? ከክርስቶስ መስቀል በኋላ ከጭንቀት የተነሣ ሸሽተው ደቀ መዛሙርት በእምነታቸው እንዲነቃቁና ለዓለም እንዲያደርሱ ለተሰጣቸው ኃላፊነት ብቁ እንዲሆኑ ማድረግ ይገባል። መላው የእርሱ አገልግሎት በሙሉ የተጣለው በእነርሱ ላይ ነበር።

በእርግጥም እንደዚያ ነበር። ክርስቶስ በእነዚህ ጥቂት ሰዎች ላይ ያዋለው ጊዜ ከሌሎች ጋር ሲነጻጸር በጣም ብዙ መሆኑ ሆን ብሎ የተጠቀመበት ስልቱ እንደ ነበረ ያመለክታል። በእርግጥ በዓለም ከነበረው ሌላው ሕዝብ ሁሉ ይልቅ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር የበለጠ ጊዜ አሳልፏል። ከነበረውም አጠቃላይ ንቁ የአገልግሎት ዘመን በአብዛኛው አብሮአቸው በልቷል፣ አብሮአቸው ተኝቶአል፣ አብሮ ተነጋግሯል። ጭር ባሉ መንገዶች አብረው ተጉዘዋል። በሕዝብ የተጨናነቁ ከተሞችን አብረው ጎብኝተዋል። በገሊላ ባሕር ላይ አብረው ጀልባ ቀዝፈዋል፤ አብረው ዓሣም አጥምደዋል፤ አብረው በጋራ በበረሃና በተራራማ ስፍራዎች ጸልየዋል። እንዲሁም በቤተ መቅደስና በምኩራብ አብረው አምልከዋል።

## አሁንም ብዙኃኑን እያገለገለ ነው

ክርስቶስ ሌሎችን ሰዎች በሚያገለግልበት ሰዓት ደቀ መዛሙርቱ ከእርሱ ጋር እንደ ነበሩ ማንም ሰው ሊረሳው



አይገባም። ሲያጨናንቁት ለነበሩት ሕዘቦች ንግግር ሲያደርግላቸውም ሆነ፣ ሊያጠምዱት ከሚሹ ጸሐፍት ፈሪሳውያን ጋር ሲነጋገር ወይም በመንገድ ላይ ለብቻው ተቀምጦ የሚለምነውን እንደ ለማኝ ሲያነጋግር ለመመልከትና ለመስማት ደቀ መዛሙርት ከእርሱ ጋር በቅርብ ነበሩ። በዚህ ሁኔታ ጌታ ኢየሱስ ያሳለፈው ጊዜ እጥፍ ብድራት ነበረው። አገልግሎቱን ለሚሹ ይሰጥ የነበረውን መደበኛ አገልግሎት ሳይተው ደቀ መዛሙርቱን ከራሱ ጋር በማድረግ ቋሚ አገልግሎት ይሰጣቸው ነበር። ለእነርሱ በግል ይሰጣቸው ከነበረው መግለጫና ምክር በተጨማሪ ደቀ መዛሙርቱ ለሌሎች ሰዎች በሚናገረውና በሚያደርገው ሁሉ ተጠቃሚ ነበሩ።

## ጊዜ መውሰድ ይጠይቃል

በእርግጥ ይህን መሳዩ ቅርብ የሆነና ጠበቅ ያለ ኅብረት ኢየሱስ የራሱ የሆኑትን ለመጥራት ጨርሶ ጊዜ እንዳይኖረው አድርጉት ነበር ማለት ነው። የወላጅ አባታቸውን ትኩረት ለመሳብ የሚሹ ልጆች እንደሚያደርጉት ሁሉ፣ ደቀ መዛሙርቱም ዘወትር በጌታ እግር ሥር ነበሩ። የጥሞና ጊዜ ለማድረግ ለብቻው ገለል የሚልበት ወቅት እንኳ በደቀ መዛሙርቱ ፍላጎት ሊቋረጥ የሚችል ነበር (ማር. 6:46-48ን ከሉቃ. 11:1 ጋር ያነጻጽሩ)። ሆኖም፣ በዚህ ጉዳይ ኢየሱስ ሌላ መንገድ አልነበረውም። ከእነርሱ ጋር መሆን ምርጫው ነበር። ምክንያቱም እነርሱ መንፈሳዊ ልጆቹ ነበሩ (ማር. 10:24፤ ዮሐ. 13:33፤ 21:5)። አንድ አባት ደግሞ ቤተሰቦቹን ሊንከባከብ የሚችለው አብሮአቸው በመኖር ነው።

## የክትትል መሠረት

እንደ ክትትል መርሕ ግልጽ የሆነ ሆኖም የተናቀና ተግባር

ላይ ያልዋለ ሌላ መርሕ የለም። ከአገልግሎቱ ባሕርይ የተነሣ ወደ ራሱ ትኩረት አይስብም፣ ሰዎች ደግሞ ተራ የሆነውን ችላ ብለው ያልፉታል። ኢየሱስ ግን ደቀ መዛሙርቱ ይህን የመሰለ መርሕ እንዲስቱ አይሻም። ከመሄዱ በፊት በነበሩት የመጨረሻ ቀናት ጌታ ደቀ መዛሙርቱ እርሱ ላደረገው ነገር ሁሉ ጥርት ያለ መረዳት እንዲኖራቸው ያደርግ ነበር። ለምሳሌ፣ ለሦስት ዓመታት ሲከተሉተ የነበሩትን መለስ ብሎ፣ «እናንተም ደግሞ ከመጀመሪያ ኖራችኋልና ትመሰክራላችሁ» (ዮሐ. 15:27) አላቸው። ብዙ አጀብ ሳያስከትልና በዓለም ትኩረት ሳይሰጠው፣ እርሱ ከሄደ በኋላ ምስክሮች ሊሆኑ የሚችሉ ሰዎችን ያሠለጥን እንደ ነበረ ኢየሱስ ተናገረ። ይህንንም ያከናወነበት የሥልጠና ዘዴ አብሮ መኖር ነበር። በእርግጥም፣ በአንድ ሌላ ወቅት እንዳለው፣ በፈተናዎቹ ከእርሱ ጋር ጸንተው ስለ ቆሙ ነበር በዘላለማዊ መንግሥቱ መሪዎች እንዲሆኑ የተሾሙት። በዚህም መንግሥት በእርሱ ማዕድ የሚበሉና የሚጠጡ በዙፋኑም ላይ ተቀምጠው በአሥራ ሁለቱ የእስራኤል ነገዶች ላይ የሚፈርዱ ይሆናሉ (ሉቃ. 22:28-30)።

ይህ በግል የመከታተል መርሕ የተነደፈው ለሐዋርያት ቡድን ብቻ ነው ብሎ መገመት ስሕተት ነው። ኢየሱስ በእነዚህ በተመረጡት ጥቂት ሰዎች ላይ አተኩሮአል፣ ቢሆንም ለሚከተሉት ለሌሎችም ሁሉ እንደሚገደው ገልጿል። ለምሳሌ፣ በኢያሪኮ መንገድ ላይ ሕይወቱ ከተቀየረ በኋላ ከዘኪዎስ ጋር አብሮ ወደ ቤቱ ሄዷል (ሉቃ. 19:7)፣ ከተማውን ከመልቀቁ በፊት ለጥቂት ጊዜያት ከእርሱ ጋር ቆይቶ ነበር። በሰማርያም በውኃ ጉድጓድ አጠገብ ያገኛት ሴት ሕይወት ከተለወጠ በኋላ ከዚህች ከሴትዮዋ ምስክርነት የተነሣ በእርሱ ያመኑትን የአካባቢውን ኅብረተሰብ ለማስተማር በሲካር ለተጨማሪ ሁለት ቀናት ተቀመጠ። ከዚህም የተነሣ



ከሕዝቡ ጋር በፈጠረው ኅብረት ብዙዎች በእርሱ አመኑ፣ ያመኑትም ሴቲቱ ስለ መሰከረች ብቻ ሳይሆን ሰዎቹ ራሳቸው ከጌታ ስለ ሰሙ ነበር (ዮሐ. 4:39-42)። ብዙውን ጊዜ ከጌታ ዘንድ አንድ ነገር የተደረገለት ሰው ጌታን ከሚከተሉት ጋር ተቀላቅሎ እንዲከተል ይፈቀድለት ነበር- ለምሳሌ፣ በርጤሜዎስ (ማር. 10:52፤ ማቴ. 20:34፣ ሉቃ 18:43)። ከዚህም የተነሣ ጌታ በይሁዳ አውራጃ ወደ ኋላ ላይ በነበረው አገልግሎቱ ይከተሉት እንደ ነበሩት ሰባዎቹ ብዙዎች ከሐዋርያት ቡድን ጋር ራሳቸውን ቀላቅለው ነበር (ሉቃ 10:1 ፣17)። እነዚህ ሁሉ በግላቸው ከጌታ ትኩረትን አግኝተዋል፣ ሆኖም ግን ለአሥራ ሁለቱ ከተሰጠው ትኩረት ጋር ግን አይወዳደርም።

እንደ ማርያምና ማርታ (ሉቃ. 10:38-42) መግደላዊት ማርያም፣ ዮሐና፣ ሶስና እና ባላቸው ነገር ያገለግሉት የነበሩትን «ብዙ ሌሎች ሴቶች» (ሉቃ. 8:1-3) ታማኝ የሴቶች ቡድን መጥቀስ ተገቢ ነው። ከእነዚህ ሴቶች መካከል የተወሰኑት እስከ መጨረሻ ከጌታ ጋር ነበሩ። ጌታም ሴቶቹ ያደርጉለት የነበሩትን የቸርነት ልግስና አልተቃወመም። እንዲያውም ብዙውን ጊዜ በእምነታቸው ሊረዳቸው የሚችልበትን አጋጣሚ ሁሉ ተጠቅሟል። ጌታ ኢየሱስ ሴቶቹ ያደረጉለትን ድጋፍ ተቀብሏል፤ ነገር ግን እነዚህን ሴቶች ከተመረጡት ደቀ መዛሙርት ቡድን ጋር ለመቀላቀል አልሞከረም።

ጌታ ኢየሱስ ለእነዚህ ሁሉ ሴቶችና ወንዶች ግላዊና ቋሚ ትኩረት ለመስጠት ጊዜ አልነበረውም። ነገር ግን ሊያደርግ የሚገባውን ሁሉ አድርጓል። ይህ ደግሞ በደቀ መዛሙርቱ ሕይወት ውስጥ ለአዲስ አማኞች በግል ሊያደርጉት የሚገባቸውን አጣዳፊ እንክብካቤ አስፈላጊነት በማሳየት በኩል ተጽዕኖ አድርጓል። እነርሱም ጌታ ግን በዋናነት እንደ እርሱ ዓይነት ለሌሎች ትኩረት

የሚሰጡ መሪዎችን ለማሠልጠን ራሱን ሰጥቶ ነበር።

## ቤተ ክርስቲያን የማያቋርጥ የኅብረት ስፍራ

ይህ ለሁሉ አማኝ ግለሰባዊ እንክብካቤ ከመስጠት ጋር የተያያዘ ችግር ሊቃለል የሚችለው ሰዎች ስለ ቤተ ክርስቲያን ማንነትና ተልዕኮ እንደሚገባ ሲረዱ ብቻ ነው። አንድን ግለሰብ ሌሎች ወደ አሉበት ኅብረት በማምጣት በክርስቶስ ዙሪያ የተሰባሰበችው ቤተ ክርስቲያን መርሖውን ተግባራዊ እያደረገች መሆኗን እዚህ ላይ ማስተዋል መልካም ነው። ይህም የአሠራር ልምድ በአብዛኛው ጌታ ራሱ ከአሥራ ሁለቱ ጋር ሲያደርግ ከነበረው ጋር ተመሳሳይ ነው። ይህም ማለት፣ በአንድነት የሚሰባሰበው የአማኞች ኅብረት የክርስቶስ አካል ይሆናል። እያንዳንዱም ሌላውን በግልም በኅብረትም ያገለግለዋል።

እያንዳንዱ የእምነት ኅበረተሰብ አባል በዚህ አገልግሎት የሚያሟላው ድርሻ ይኖረዋል። የቤተ ክርስቲያን አባላት ይህን ሊያደርጉ የሚችሉት ከሠለጠኑና መንሣሣታቸው ከፍ እንዲል ከተደረገ ብቻ ነው። ጌታ በአካል ከእነርሱ ጋር በነበረ ጊዜ፣ መሪያቸው እርሱ ነበረ፣ እርሱ ከሄደ በኋላ ግን፣ በቤተ ክርስቲያን ያሉ ይህንን የመሪነት ስፍራ ሊረከቡ ይገባል። ይህም ማለት ጌታ ኢየሱስ ከእነርሱ ጋር ቋሚ የሆነ የራሱን ግላዊ ኅብረት ከተመረጡት ከጥቂቶች ጋር በማድረግ ተግባራዊ እንዲያደርጉት ሊያሠለጥናቸው ያስፈልገው ነበር ማለት ነው።

## ችግራችን

ይህንን ትምህርት መቼ ይሆን ቤተ ክርስቲያን የምትማረው? ለብዙሃኑ መስበክ በጣም አስፈላጊ ቢሆንም፣ ለወንጌል ስርጭት መሪዎችን ለማዘጋጀት ግን ብቁ አይደለም። ማንኛውም አልፎ



አልፎ የሚደረጉ የጸሎት ስብሰባዎችና ለክርስቲያን አገልጋዮች የሚሰጡ የሥልጠና ፕሮግራሞች ይህንን ሥራ ሊያከናውኑ አይችሉም። ሴቶችንና ወንዶችን በመንፈሳዊ ሕይወት ማነጽ ቀላል አይደለም። ልክ አባት ለልጆቹ ትኩረት እንደሚሰጥ ሁሉ፣ ይህም ሥራ የማያቋርጥ ግለሰባዊ ትኩረት ይሻል። ማንኛውም ድርጅት ወይም የትምህርት ክፍል ሊያደርገው የማይችለው ሥራ ነው። ልጆች በውክልና አያድጉም። የጌታችን የኢየሱስ ምሳሌም የሚያስተምረን ይህን መሳዩ ሥራ ሰዎች ሊመሩአቸው ከሚፈልጉአቸው ሰዎች ጋር አብሮ በመኖር ብቻ የሚደረግ መሆኑን ነው።

በዚህ ጉዳይ ላይ ቤተ ክርስቲያን ወድቃለች፣ አወዳደቋም አሳዛኝ ነው። ዛሬ ቤተ ክርስቲያን ስለ ወንጌል ስርጭትና ክርስቲያኖችን ስለ መንከባከብ ብዙ ውይይቶች ይደረጋሉ። ነገር ግን የግል ፍላጎትን መሥዋዕት ማድረግን በሚጠይቀው በግል ከሌሎች ጋር ኅብረት ከማድረግ አንጻር የተሰጠው ትኩረት ሲታሰብ በጣም ጥቂት ነው። እውነት ነው፣ ብዙ አብያተ ክርስቲያናት በተለያዩ በሳምንት ለአንድ ሰዓት ለአንድ ወር ያህል በሚቀርብ የእምነት ማጽኛ ትምህርት አሰጣጥ መንገዶች አዳዲስ አባላት ሊጨመሩ ይገባል ይላሉ። ከዚህ ውጪ በሌላ ጊዜ አዲሱ አማኝ በእሑድ አምልኮና በሰንበት ትምህርት ከመሳተፍ በስተቀር ወሳኝ የሆኑ ክርስቲያናዊ ትምህርቶችን የማግኘት ምንም ዓይነት ዕድል የለውም። አዲሶቹ ክርስቲያኖች፣ በእርግጥም የዳኑ ከሆኑ፣ በቤተ ክርስቲያን በኩል የተፈጠረባቸውን ክፍተት እርግጠኛ በሆነ መንገድ የሚሸፍኑላቸው ቤተሰቦች ወይም ጓደኞች የሚሆኑ ሰዎች ከሌሏቸው በስተቀር፣ በሕይወታቸው ለሚገጥሟቸው ከቁጥር በላይ የሆኑ ችግሮች ሁሉ መፍትሔ መፈለግ በእነርሱ ላይ ይወድቃል።

ከእነዚህ አንደኛውም ቢሆን ለአዲሱ አማኝ በእምነቱና በሕይወቱ ላይ ጥፋትን የሚያስከትል ይሆንበታል።

በዚህ የተዘበራረቀ የአማኞች ክትትል እምነቱን ከተቀበሉትና ቤተ ክርስቲያንን ከተቀላቀሉት ሰዎች ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ቀስ በቀስ ከክርስትና ሕይወት ቢወድቁና የክርስትና ልምምድ ግለት ቢጠፋባቸው የሚያስደንቅ አይሆንም። በቂ እውቀትና ጸጋ አግኝተው በእግዚአብሔር መንግሥት አገልጋይ እስከ መሆን የሚያድጉት ከእነዚህ በጣም ጥቂቶች ብቻ ናቸው። አዲሱን አማኝ ወደ ሙሉ ደቀ መዝሙርነት ለማሳደግ አብያተ ክርስቲያናት ያላቸው አገልግሎት የእሑድ አምልኮ ፕሮግራምና የአባልነት ሥልጠና ብቻ ከሆነ፣ የውሸት ዋስትና በመስጠት ዓላማቸው እንዳይሳካ እያደረጉ ናቸው። አዲሱ አማኝ ይህን የስንፍና ምሳሌ ከተከተለ፣ የኋላ ኋላ ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናል። ከሰዎች ጋር መሆንን የሚተካው ምንም ሌላ ነገር የለም። ጠንካራ ክርስቲያን መሪዎችን ለማፍራት ከታምራት በስተቀር ከዚህ ያነሰ ነገር ውጤት ያመጣል ማለት ዘበት ነው። የእግዚአብሔር ልጅ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ከጥቂት ደቀ መዛሙርቱ ጋር በተከታታይ ለሦስት ዓመታት መኖር በጣም አስፈላጊ እንደ ሆነ አምኖበት እያደረገው ሳለ፣ ከመካከላቸው አንድ ሰው በሕይወቱ ከጠፋ፣ እንግዲያው ቤተ ክርስቲያን ወረፋ ይዘው ለሚጠብቁ ብዙ ሰዎች በዓመት ካሉት ጥቂት ቀናትን ብቻ እየተጠቀመች በመሥራት እንዴት ትወጣዋለች?

## ዛሬ ተግባራዊ የሆነ መርሖ

ቤተ ክርስቲያን ማንኛውንም ዓይነት የክትትል ስልት ብትለማመድም፣ የኢየሱስ ክርስቶስ መመሪያ እዚህ ላይ በግልጽ እንደሚያስተምረን፣ ቤተ ክርስቲያን እንክብካቤ እንድታደርግላቸው



አደራ ላለባት ለእያንዳንዱ በግል የወላጅ /አሳዳጊ አያያዝን መሠረት ያደረገ አሠራር ሊኖራት ይገባል። ከዚህ የተለየ ሥራን መሥራት አዲሱን ክርስቲያን ለሰይጣን አሳልፎ እንደ መስጠት ይሆናል።

አዲሱ ክርስቲያን ራሱን ችሎ ሌላውን መርዳት እስኪችል ድረስ የሚከታተለው ክርስቲያን ጊደኛ እንዲኖረው ቤተ ክርስቲያን አንድ ስልት ሊኖራት ይገባል። አዲሱን ክርስቲያን የሚያማክረው ሰው በተቻለ መጠን አብሮት በመኖር መጽሐፍ ቅዱስን አብሮት የሚያጠና፣ አብሮት የሚጸልይ፣ አብረውም በሚቆዩበት ጊዜ ሁሉ በሕይወቱ ለሚፈጠረው ጥያቄ መልስ በመመለስ እውነትን የሚገልጽና አብሮት ሌሎችን ለመርዳት ፍላጐት ያለው ሊሆን ይገባል። ቤተ ክርስቲያን ይህን መሳይ አገልግሎት ለመፈጸም ራሳቸውን የሰጡ አማካሪዎች ከሌላት አንዳንዶችን ልታሠለጥን ይገባታል። ይህም ዓይነት ሥልጠና ሊሰጥ የሚችልበት ብቸኛው መንገድ የሚከተሉት አንድ መሪ በመስጠት ነው።

ይህ ደግሞ እንዴት ተግባር ላይ ይውላል የሚለውን ጥያቄ ይመልሳል፤ ነገር ግን አሁን ልንረዳው የሚገባን ይህ ስልት ዓላማውን ሊፈጽም የሚችለው ሠልጣኞች የተማሩትን በተግባር ለማዋል ሲለማመዱ ብቻ ነው። ስለሆነም፣ በጌታ ስልት ሌላ መሠረታዊ መርሖም ግንዛቤ ሊያገኝ ይገባል።

*ቀንበሬን በላያችሁ ተሸከሙ*

*ማቴ. 11: 29*

3

# ለአገልግሎት መቀደስ

## መታዘዝን ይጠብቅባቸው ነበር

ጌታ ኢየሱስ አብረውት የነበሩት ሰዎች እንዲታዘዙት ይጠብቅ ነበር:: ከእነርሱ የሚፈልገው ብልጣብልጥነት ሳይሆን፣ ታማኝ ሆኖ መገኘት ነበር:: ይህ ደግሞ በሌሎች ዘንድ የሚታወቁበት የመለያ ምልክታቸው እየሆነ መጣ:: «ደቀ መዛሙርት» የሚለው መጠሪያቸው የመምህሩ የኢየሱስ «ተማሪዎች» መሆናቸውን የሚያመለክት ነበር:: ምንም እንኳን ታዛዥ የሆኑ ተከታዮች በወቅቱ የመሪያቸውን ባህርይ መውረሳቸው የማይቀር ቢሆንም፣ «ክርስቲያን» የሚለውን መጠሪያ ያገኙት (ሐዋ. 11:26) በጣም ዘግየት ባለ ወቅት ነበር::

ይህ መመሪያ እንዲህ ቀለል ባለ መልኩ መቅረቡ አስገራሚ ነው ባይባልም አስደናቂ ሊባል የሚችል ነው:: ከደቀ መዛሙርቱ ማናቸውም በመጀመሪያ የእምነት አቋማቸውን እንዲገልጹ ወይም አንዳች የተቀረጸ ሃይማኖታዊ አስተምህሮ እንዲቀበሉ አልተጠየቁም:: ይሁን እንጂ፣ ኢየሱስ መሲሕ መሆኑን ያለአንዳች ማመንታት ተቀብለዋል (ዮሐ. 1:41፣ 45፣ 49፤ ሉቃ. 5:8):: በወቅቱ ከእነርሱ ይፈለግ የነበረው ጌታ ኢየሱስን መከተል ብቻ ነበር:: በእርግጥ፣ በጥሪያቸው መነሻ ላይ የነበረውን ስንመለከት በክርስቶስ ማንነት ማመንንና ለሕያው ቃሉ መታዘዝን የሚጠይቅ ጥሪ ነበር:: ይህንን በመጀመሪያው ጥሪ ሳይረዱት ቢቀሩ፣ ከጌታ



ጋር መጓዝ ሲቀጥሉ ይገለጽ ነበር:: ማንም ሰው የማያምንበትን ወይም የማይተማመንበትን ሰው ተከትሎ ጉዞ አይጀምርም:: መሪው የሚለውን ለመታዘዝ ፈቃደኛ ሳይሆንም የእምነትን እርምጃ ለመውሰድ በታማኝነት እግሩን አያነሣም::

## የመስቀሉ ጎዳና

ያን ያህል ብዙ ርቀት አልተከተሉትም ነበርና ወደ መጀመሪያው ሰሞን ጌታ ኢየሱስን መከተል ቀላል ይመስል ነበር:: ሆኖም፣ ብዙም ሳይቆይ የክርስቶስ ደቀ መዝሙር መሆን ማለት መሲሐዊውን ቃል ኪዳን በደስታ ከመቀበል ባሻገር ለሉዐላዊነቱ ራስን በማስገዛት ሁለንተናን ለጌታ መስጠት ማለት መሆኑ ግልጽ እየሆነ መጣ:: ማመቻመች ስፍራ አልነበረውም:: ጌታ ኢየሱስ እንዲህ ሲል ተናግሯል፣ «ለሁለት ጌቶች መገዛት የሚቻለው ባርያ ማንም የለም፤ ወይም አንዱን ይጠላልና ሁለተኛውንም ይወዳል፣ ወይም ወደ አንዱ ይጠጋል ሁለተኛውንም ይንቃል:: ለእግዚአብሔርና ለገንዘብ መገዛት አትችሉም» (ሉቃ. 16:13):: ከኃጢአት ፈጽሞ መለየት ይገባል:: አሮጌው አስተሳሰብ፣ አሮጌው ልማድና ከዓለም የሚገኘው ደስታ በአዲሱ የእግዚአብሔር መንግሥት ሥነ ምግባራት ሊተኩ ይገባቸዋል (ማቴ. 5:1-7፣ 29፤ ሉቃ. 6:20-49):: ፍቅርን ፍጹም ማድረግ አሁን ብቸኛው የባህርይ መመዘኛ ይሆናል (ማቴ. 5:48):: ይህ ፍቅር ደግሞ ሊያድናቸው ወድዶ ለሞተላቸው ሰዎች (ማቴ. 25:31-36)፣ ራስን በመስጠት በሚገለጠው ለክርስቶስ የመታዘዝ እርምጃ (ዮሐ. 6:25-29) ይተገበራል:: ስለ ሌሎች ብሎ ራስን በመካድ እርምጃ ውስጥ መስቀል አለበት (ማር. 8:34-38፤ 10:32-45፤ ማቴ. 16:24-26፤ 20:17-28፤ ሉቃ. 9:23-25፤ ዮሐ. 12:25-26፤ 13:1-20)::

ይህ ጠንከር ያለ ትምህርት ነበር። ብዙ ሰዎች አይቀበሉትም። ሆዳቸውን በምግብና በዓሣ ሲሞላ ሰዎች የእርሱ ተከታይ ሊሆኑ ይሻሉ፣ ነገር ግን ጌታ ኢየሱስ በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ስለሚፈለገው እውነተኛ መንፈሳዊ ማንነትና ይህንንም ለማግኘት ሊከፍሉት ስለሚገባቸው ዋጋ ሲናገር (ዮሐ. 6:25-29)፣ ከደቀ መዛሙርቱ «ብዙዎች ወደ ኋላ ተመለሱ፣ ወደ ፊትም ከእርሱ ጋር አልሄዱም» (ዮሐ. 6:66)። የእነርሱን የራሳቸውን አነጋገር በመጠቀም እንዲህ ብለው ነበር፣ «ይህ የሚያስጨንቅ ንግግር ነው፤ ማን ሊሰማው ይችላል?» (ዮሐ. 6:60)። የሚገርመው ነገር ደግሞ ጌታ ኢየሱስ ከተከታዮቹ መካከል እንዳይጎድሉና አብረውትም እንዲቆዩ ለማድረግ የማግባባት ጥረት አላደረገም። ለመንግሥቱ የሚሆኑትን መሪዎችን ነበርና የሚያሠለጥነው። ለአገልግሎቱ ምቹ ዕቃዎች መሆን ካለባቸው፣ እነዚህ ሰዎች ዋጋ ሊከፍሉ ይገባቸዋል።

## ብድራትን መተመን

እስከ መጨረሻው ሲዘልቁ ያልቻሉቱ በየጊዜው በየመንገዱ ዳር ተንጠባጥበው ቀርተዋል። በራስ ወዳድነታቸው ምክንያት ራሳቸውን ከተመረጡት መካከል አግልለዋል። እንደ ዲያብሎስ የተቆጠረው ይሁዳ (ዮሐ. 6:70)፣ እስከ መጨረሻው ድረስ ተጉዞ ነበር፣ በፍጻሜው ላይ ግን የገዛ ስግብግብነቱ አጋለጠው (ማር. 14:10፣ 11፣43፣44፤ ማቴ. 26:14-16፣ 47-50፤ ሉቃ. 22:3-6፣47-49፤ ዮሐ. 18:2-9)። ከዓለም ጋር ያለውን ትስስር ሳይፈታ፣ ማንም ጌታ ኢየሱስን እንደ ዋዛ ሊከተል አይችልም። ይከተሉ እንደነበረ ሲያስመስሉ የቆዩት እንኳ የኋላ ኋላ ያተረፉት ነገር ቢኖር የልብ ኃዘንና ጸጸት ነበር (ማቴ. 27:3-10፤ የሐዋ. 1:18-19)።



ምናልባትም ለዚህ ሳይሆን አይቀርም ጌታ ኢየሱስ፣ መምህር ሆይ፣ ወደምትሄድበት ሁሉ እከተልሀለሁ ላለው ለዚያ ጸሐፊ ጠንከር አድርጎ የተናገረው። በፈቃዱ ለማገልገል ወደ የመጣ ለመሰለው ለዚህ ሰው አገልግሎት ቀላል እንዳልሆነ ጌታ ኢየሱስ በግልጽነት ነገረው። «ለቀበሮዎች ጉድጓድ ለሰማይም ወፎች መሳፈሪያ አላቸው፣ ለሰው ልጅ ግን ራሱን የሚያስጠጋበት የለውም» (ማቴ. 8:19-20፤ ሉቃ. 9:57-58)። ሌላው ደቀ መዝሙር ደግሞ ከነበረበት የመታዘዝ ግዴታ ለጊዜው ፈቃድ እንዲሰጠውና ሄዶ አባቱን እንዲቀብር በጠየቀው ጊዜ፣ ጌታ ኢየሱስ ግን ምንም ዓይነት እረፍት ምንም ዓይነት መጓተት እንዲፈጠር አልፈቀደም። ከዚህም የተነሣ «ተከተለኝ»፣ «ሙታናቸውንም እንዲቀብሩ ሙታንን ተዋቸው» (ማቴ. 8:21-22፤ ሉቃ. 9:59-60) አለው። በራሱ መንገድ ጌታ ኢየሱስን እንደሚከተል የሚያስብ አንድ ሌላ ሰውም ነበረ። ይኼኛውም ሰው ምናልባት ቤተሰቦቹን ሄዶ ሲሰናበት ታላቅ የደስታ ጊዜ የሚያሳልፍ መስሎት ይሆናል። ጌታ ኢየሱስ ግን ያለምንም ማቅማማት፣ «ማንም ሰው እርፍ በእጁ ይዞ ወደ ኋላ የሚመለከት ለእግዚአብሔር መንግሥት የተገባ አይደለም» (ሉቃስ 9:62) አለው። ለደቀ መዝሙርነት የራሳቸውን ትርጉም ሰጥተው እርሱን የመከተል ዕቅድ ለነበራቸው ጌታ ኢየሱስ ከእነርሱ ጋር ወለም ዘለም የማለት ፍላጎት አልነበረውም።

ደቀ መዝሙሩ ሊሆኑ የሚወድ ቢኖር ደግሞ ብድራቱን እንዲያሰላ ይገባው ነበር። «ከእናንተ ግንብ ሊሠራ የሚወድ ለመደምደሚያ የሚበቃ ያለው እንደሆነ አስቀድሞ ተቀምጦ ኪሳራውን የማይቆጥር ማን ነው?» (ሉቃ 14:28)። አስቀድሞ ይህንን አለማድረግ ግን የኋላ ኋላ ዓለም እንዲሳለቅብን የመጋበዝ ያህል ነው። ጦርነትን ለማሸነፍ ምን ያህል ዝግጅት እንደሚጠይቅ

ሳያስላ ለጦርነት የሚወጣም ንጉሥ ከዚሁ ሁኔታ ጋር ይመስላል:: ይህንን ክፍል ግልጽ በሆነ አነጋገር ሲጠቀልለው ጌታ ኢየሱስ እንዲህ አለ፣ «እንግዲህ እንደዚሁ ማንም ከእናንተ ያለውን ሁሉ የማይተው ደቀ መዝሙሬ ሊሆን አይችልም» (ሉቃ. 14:33፤ ማር. 10:21፤ ማቴ. 19:21፤ ሉቃ. 18:22)::

## ጥቂቶች ዋጋ ይከፍላሉ

እርግጥ ነው ጥቅም ፈላጊዎች ከእርሱ እናገኛለን ብለው የጠበቁትን ስላልሰጣቸው በቅፍርናሆም ጥለውት ወደ ኋላ ሲመለሱ፣ ከእርሱ ጋር የቀሩት እፍኝ እንኳን የማይሞሉ ጥቂት ተከታዮች ብቻ ነበሩ:: ወደ አሥራ ሁለቱም ዘወር ብሎ፣ «እናንተ ደግሞ ልትሄዱ ትወዳላችሁን?» (ዮሐ. 6:67) አላቸው:: ይህ ጥያቄ በጣም ወሳኝ የሆነ ጥያቄ ነበር:: እነዚህ የቀሩት ጥቂቶቹ መከተላቸውን ቢያቆሙስ፣ አገልግሎቱ ምን ይሆን ነበር? ነገር ግን ስምዖን ጴጥሮስ፣ «ጌታ ሆይ፣ ወደ ማን እንሄዳለን? አንተ የዘላለም ሕይወት ቃል አለህ፤ እኛስ አንተ ክርስቶስ የሕያው የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆንህ አምነናል አውቀናልም» (ዮሐ. 6:68-69) ብሎ መለሰለት፣ እናም እነዚህ የሐዋርያው ቃሎች የጌታን አቋም የሚያጸኑ ሆኑ:: ስለሆነም ከፊት ይልቅ በበለጠ ግልጽነት ለቀሩት ደቀ መዛሙርቱ ስለ ሥቃዩና ስለ ሞቱ በዝርዝር ይነግራቸው ጀመር::

## መታዘዝ መማር ነው

ይህም ሲባል ደቀ መዛሙርት ጌታ የሚለውን ሁሉ በፍጥነት ይረዱ ነበር ማለት አይደለም:: እንዲያውም ከዚያ ፍጹም በተለየ መልኩ ነበር የሆነው:: ከሰው ደካማነትና ጥልቅ የሆኑትን የጌታን ካህናዊ አገልግሎት በሰው ድካም ውስጥ ባሉት ውሱንነቶች



የመረዳት ችሎታቸውን ጋርዶት ነበር:: ደቀ መዛሙርቱ በፊልጶስ ቂሳርያ ከሰጡት የማንነቱ ማረጋገጫ በኋላ በኢየሩሳሌም በሃይማኖት መሪዎች ለሞት አልፎ እንደሚሰጥ ጌታ ኢየሱስ ሲነግራቸው፣ ጴጥሮስ ጌታን «አይሁንብህ ጌታ ሆይ፤ ይህ ከቶ አይደርስብህም» (ማቴ. 16:22፤ ማር. 8:32) ብሎት ነበር:: ይህንን በሰማ ጊዜ ጌታ ኢየሱስ ለታላቁ ዓሣ አጥማጅ በዚያ ወቅት ሰይጣን እንዳሳተው መንገር ነበረበት:: «የሰውን እንጂ የእግዚአብሔርን አታስብም» (ማቴ. 16:23፤ ማር. 8:33) ነበር ያለው:: በዚህ ብቻ አላበቃም፣ ጌታ ኢየሱስ ደግሞ ደጋግሞ ስለ ሞቱና ሞቱ ለቀደ መዛሙርቱ ስለሚኖረው አንድምታ መንገር እንዳለበት ቢገነዘብም፣ በጠላቶቹ እጅ አልፎ እስከ ተሰጠባት እስከዚያች ቀን ግን ብዙም የተረዱት ነገር አልነበረም::

የመስቀሉን ትርጉም በሚገባ አልተረዱም ነበርና በመጀመሪያ ሰሞን በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ስለሚኖራቸው ስፍራ እንኳ ያስቡ ነበር:: ስለ ሌሎች ሰዎች ጥቅም ብለው ዝቅ ብሎ የማገልገልን ትምህርት መቀበል በጣም አስቸጋሪ ሆኖባቸውም ነበር (ሉቃ. 22:24-30፤ ዮሐ. 13:1-20):: በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ማን ታላቅ እንደሚሆን በመካከላቸው ይከራከሩ ነበር (ማር. 9:33-37፤ ማቴ. 18፤1-5፤ ሉቃ. 9:46-48):: ያዕቆብና ዮሐንስ ከሁሉ ከፍ ያለውን ስፍራ ለማግኘት ይሹ ነበር (ማር. 10:41፤ ማቴ. 20:24):: የቅንዓት መንፈስ የታየባቸው አሥሩ ደግሞ ያዕቆብና ዮሐንስ ባቀረቡት አሳብ ይቆጡ ነበር (ማር. 10:13):: ከእነርሱ ጋር ያልተስማሙትን የሌሎቹን አቋም ሲገመግሙ አግባብነት የሌለው ግልፍተኝነት አሳይተዋል (ሉቃ. 9:51-54):: ኢየሱስ ልጆቻቸውን እንዲባርክላቸው በፈለጉት ወላጆችም ላይ «ተቆጥተው ነበር» (ማር. 10:13):: ክርስቶስን የመከተል ተግባራዊ አንድምታ ሙሉ በሙሉ

ገና ተግባራዊ እንዳልሆነ በግልጽ ይታይ ነበር።

ጌታ ኢየሱስ ግን ይህ ሁሉ ጉድለት እያለባቸው ሲከተሉት ፍቃደኞች ስለነበሩ የነበረባቸውን ሥጋዊ ድካም ሁሉ በትዕግሥት ይችለው ነበር። መጀመሪያ ከተጠሩ በኋላ ወደ ቀድሞው የዓሣ ማጥመድ ሥራቸው የተመለሱባት አጠር ያለች ክፍተት ነበረች (ማር. 1:16፤ ማቴ. 4:18፤ ሉቃ. 5:2-5፣ ከዮሐ. 1:35-42 ጋር ያነጻጽሩ)። ነገር ግን በእነርሱ ዕይታ ከተጠሩ በኋላ ወደ ቀድሞው ሥራቸው መመለሳቸው ለመታዘዝ ካለመፈለግ እንደ መነጨ አድርገው አልወሰዱትም ነበር። እነርሱን መሪዎች በማድረግ በኩል ጌታ በሕይወታቸው ላይ ስለነበረው ዓላማ የሚያውቁት ነገር አልነበረም ወይም ገና አልተነገራቸውም። የሆነ ሆኖ፣ ወደሚሠሩበት ስፍራ መጥቶ ሰዎችን አጥማጆች ይሆኑ ዘንድ እንዲከተሉት ጥሪ ካደረገላቸው ከዚያች ቀን አንሥቶ «ሁሉን ትተው ተከተሉት» (ሉቃስ 5:11፣ ከማቴ. 4:22፣ ማር. 1:20 ጋር ያነጻጽሩ)። ገና ብዙ ሊማሩት የሚገባቸው ነገር ቢኖርም፣ ለክርስቶስ የነበራቸው መሰጠት ግን ጽኑ ነበር (ማር. 10:28፤ ማቴ. 19:27፤ ሉቃ. 18:28)። ስለሆነም በመንፈሳዊው ነገር ካለመብሰላቸው የተነሣ የሚመጡትን እነዚያን ሁሉ ድካሞቻቸውን ለመቻል ጌታ ኢየሱስ ፈቃደኛ ሆነ። በጸጋና በእውቀት ባደጉ ቁጥር እነዚህን ድካሞቻቸውን እንደሚያስወግዱ ያውቅ ነበር። የተረዱትን እውነት ለመለማመድ በጣሩ መጠን ተጨማሪ ትምህርቶችን (መገለጦችን) ለመረዳት የሚኖራቸው ችሎታም በዚያው ልክ ያድጋል።

ለክርስቶስ ታዛዥ መሆን አብረውት የነበሩት እጅግ ብዙ እውነት ሊማሩ የቻሉበት መንገድ ነበር። እውነት እንደ ሆነ የማያውቁትን ነገር ደቀ መዛሙርቱ እንዲከተሉ አልጠየቃቸውም። እውነት



የሆነውን ነገር ሳይማር ደግሞ ማንም ሊከተለው አይችልም (ዮሐ. 7:17)። ስለሆነም፣ ጌታ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ለአስተምህሮዎቹ ሕይወታቸውን አሳልፈው እንዲሰጡ ግድ አላላቸውም። እርሱ ራሱ አስተምህሮ ስለሆነው ጌታ ራሳቸውን አሳልፈው እንዲሰጡ ይሻ ነበር፣ አብረው በተጊዙ መጠን ብቻ ነበር ቃሉን ጠብቀው እውነት የሆነውን ወደ ማወቅ የሚደርሱት (ዮሐ. 8: 31-32)።

## የፍቅር ማረጋገጫ

ፍጹም የሆነ ታዛዥነት የፍቅር መግለጫው እንደ ሆነ አይተናል። ይህ ትምህርት ጠንከር ያለ ግንዛቤ ያገኘው ደግሞ በሞቱ ዋዜማ ላይ ነበር። በቤቱ ላይኛው ክፍል ዙሪያውን ከብበው የፋሲካን ማዕድ አብረውት ከበሉ በኋላ አንድ በነበረው ቤት አብረውት ሳሉ ጌታ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ አለ፣ «ብትወዱኝ ትእዛዜን ጠብቁ.... ትእዛዜ በእርሱ ዘንድ ያለችው፣ የሚጠብቃትም የሚወደኝ እርሱ ነው፤ የሚወደኝንም አባቴ ይወደዋል፣ እኔም እወደዋለሁ፣ ራሴንም እገልጥለታለሁ። . . . የሚወደኝ ቢኖር ቃሌን ይጠብቃል፤ አባቴም ይወደዋል፣ ወደ እርሱም እንመጣለን፣ በእርሱም ዘንድ መኖሪያ እናደርጋለን። የማይወደኝ ቃሌን አይጠብቅም፤ የምትሰሙትም ቃል የላከኝ የአብ ነው እንጂ የእኔ አይደለም . . . እኔ የአባቴን ትእዛዝ እንደ ጠበቅሁ በፍቅሩም እንደምኖር፣ ትእዛዜን ብትጠብቁ በፍቅሬ ትኖራላችሁ። . . . እኔ እንደ ወደድኋችሁ እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ ትእዛዜ ይህች ናት . . . እኔ ያዘዝኋችሁን ሁሉ ብታደርጉ እናንተ ወዳጆቼ ናችሁ (ዮሐ. 14:15፣21፣23፣24፤ 15:10፣12)።

## ጌታ ኢየሱስ ተገበረው

ለእግዚአብሔር ፈቃድ ፈጽሞ መታዘዝ ጌታ ራሱ ሕይወቱን

ያስገዛበት መርሕ ነበር። በሰብዓዊነቱ ለአባቱ ፈቃድ ሁል ጊዜ እሺ ይል ነበርና እግዚአብሔርም ሙሉ በሙሉ ዘላለማዊ ዕቅዱን በእርሱ ሕይወት እንዲፈጽም አስችሎት ነበር። በተደጋጋሚም ይህንኑ ነገር ተናግሮታል፦ «የእኔስ መብል የላከኝን ፈቃድ አደርግ ዘንድ ሥራውንም እፈጽም ዘንድ ነው።» (ዮሐ. 4:34)፤ «የላከኝን ፈቃድ እንጂ ፈቃዴን አልሻምና» (ዮሐ. 5:30፤ 6:38)፤ «እኔ የአባቴን ትእዛዝ እንደ ጠበቅሁ በፍቅሩም እንደምኖር» (ዮሐ. 15:10፤ 17:4)። ይህ ሁሉ በጌቴሴማኒ እንዲህ ሲል «የእኔ ፈቃድ አይሁን የአንተ እንጂ» (ሉቃ. 22:42፤ ማር. 14:36፤ ማቴ. 26:39፣ 42፣44) በቃተተው መቃተት ይጠቃለላል።

በመስቀል ላይ የፈጸመው ሥራ ጌታ ኢየሱስ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸም ያደረገው የመጨረሻውና እንደ ጉልላት የሚታይ የመሰጠቱ መግለጫ ነበር። ይህም በመስቀል ያከናወነው ሥራው ታዛዥነት ሊመቻመች የማይችልና ምን ጊዜም እስከ ሞትም የሚያደርስ መሰጠት መሆኑን ያሳየ ነበር።

በምድራዊው አስተሳሰብ የተያዙት እነዚያ የሃይማኖት መሪዎች ሳያውቁት በማሾፍ መልክ እንዲህ ሲሉ እውነቱን ተናግረዋል፣ «ሌሎችን አዳነ፤ ራሱን ሊያድን አይችልም» (ማር. 15:31፤ ማቴ. 27:42፤ ሉቃ. 23:35)። እውነታቸውን ነው፣ ራሱን ሊያድን አልቻለም፤ ምክንያቱም የመጣው ነፍሱን ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጂ እንዲያገለግሉት አልመጣም (ማር. 10:45፤ ማቴ. 20:28)። እርሱ የመጣው «የጠፋውን ሊፈልግና ሊያድን ነው» (ሉቃ. 19:10)። ለሕዝቦች ሁሉ ኃጢአት ራሱን መሥዋዕት አድርጎ ለእግዚአብሔር ሊያቀርብ ነው የመጣው። አመጣጡ ለመሞት ነው። የማይታጠፈው የእግዚአብሔር ሕግ ሊታረቅ የሚችልበት ከዚህ የተለየ ሌላ ምንም መንገድ አልነበረም።



ክርስቶስ የመስቀል ላይ ሞቱን ከመጀመሪያውም የተቀበለው ጉዳይ ነበርና (ራእይ 13:8፤ የሐዋ. 2:32)፣ ለክርስቶስ መስቀሉ በምድር በሚመላለስበት ጊዜ በእያንዳንዱ እርምጃው እግዚአብሔር ለሕይወቱ ያለውን ዘለዓለማዊ ዕቅድ እንዲቀበል ያደርገው ነበር። ስለሆነም ጌታ ኢየሱስ ስለ መታዘዝ ሲናገር፣ ደቀ መዛሙርቱ መታዘዝ ራሱ በሰው አምሳል ተገልጦ የማየት ያህል ይቆጥሩት ነበር። ኢየሱስም ሲናገር እንዲህ ብሏል፦ «እኔ ለእናንተ እንዳደረግሁ እናንተ ደግሞ ታደርጉ ዘንድ ምሳሌ ሰጥቻችኋለሁ። እውነት እውነት እላችኋለሁ፣ ባርያ ከጌታው አይበልጥም፣ መልእክተኛም ከላኪው አይበልጥም። ይህን ብታውቁ፣ ብታደርጉትም ብፁዓን ናችሁ» (ዮሐ. 13:15-16)። ይህንን ትምህርት ማንም ሊስተው አይገባም። ጌታ ኢየሱስ የአባቱን ፈቃድ በማድረጉ በረከትን እንደ ተቀበለ ሁሉ፣ የእርሱ ተከታዮችም በረከታቸውን የእርሱን ፈቃድ በማድረግ ያገኛሉ። የአገልጋይ ዋነኛ ሥራም ይሄ ነው። ይህ በክርስቶስ ሕይወት እውን ሆኖ ነበር። እናም ደቀ መዛሙርቱም በምንም መልኩ ከዚህ ያነሰ እንዲያደርጉ አይጠብቅም (ሉቃ. 17:6-10፤ 8:21፤ ማር. 3:35፤ ማቴ. 12:50)።

## ትኩረት የሚሻ መርሕ

በስልት ረገድ የደቀ መዛሙርቱን ሕይወት ለመቅረጽ ጌታ ኢየሱስ የተጠቀመበት መንገድ ቃሉን ማስተማርን ብቻ ነበር። የባህሪም ሆነ የዓላማ ለውጥ በደቀ መዛሙርቱ ሕይወት ለማምጣት ከቃሉ ውጭ ሌላ መንገድ አልነበረም። ልጆቹ እርሱን እንዲመስሉ የሚሻ ከሆነ አባት እንዲታዘዙት ልጆቹን ሊያስተምራቸው ግድ ነው።

ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያንን ወደ ድል የሚመሩ ሰዎችን በማ-ሠልጠን ላይ እንደ ነበረ መዘንጋት የለበትም። መሪውን መከተል

እስካልተማረ ድረስ ደግሞ ማንም መሪ ሊሆን አይችልም፡፡ ስለሆነም የወደፊት መሪዎቹንና አዛዦቹን ከሕዝብ ሁሉ ለይቶ አሠለጠናቸው፡፡ በሥልጣን ላይ ላሉት ሊሰጡት ስለሚገባቸው አክብሮትና ሊቀስሟቸው የሚገባቸውንም ሥነ ምግባራት እግረ መንገዱን በውስጣቸው አሰረፀ፡፡ በክርስቶስ ትእዛዝ ውስጥ እንቢተኝነት ስፍራ አልነበረውም፡፡ የመጨረሻው በግማሽ ልብ የሚሠራን የወንጌል ሥራን ውጤት አልባ ለማድረግ የሰይጣን ኃይላት ምን ያህል የተጠናከሩና የታጠቁ እንደ ሆኑ የኢየሱስን ያህል የሚያውቅ አልነበረም፡፡ የማሸነፊያውንም ስልት በማወቅ በኩል ብቸኛ በሆነው በእርሱ ላይ ካልተደገፉ በዚህ ዓለም ከሚገኙት አጋንንታዊ ኃይሎች በልጠው ሊገኙ አይችሉም፡፡ ይህ ደግሞ ፈጽሞ ለጌታ ፈቃድ መታዘዝንና የራስን ፈቃድ እርግፍ አድርጎ መተውን የሚያመለክት ነው፡፡

## መርሑ ዛሬ እንዴት ይተገበራል?

በዚህ ዘመን ይህንን ትምህርት በድጋሚ ልንማር ይገባል፡፡ የክርስቶስን ትእዛዝ በማመቻመች ልንቀበል አንችልም፡፡ የሕይወት ወይም የሞት ጥያቄ በሰፈነበት የውጊያ ሜዳ ላይ ነው ያለነው፡፡ ኃላፊነታችንን ልንወጣ በሚገባን በእያንዳንዷ ቀን ግድ የለሾች ሆንን ማለት በክርስቶስ ሥራ ላይ አንድ ቀን አባከንን ማለት ነው፡፡ በጣም ቀላል የሆነውን የደቀ መዝሙርነትን እውነት የተማርን ቢሆን እንኳ፣ የጌታ አገልጋዮች ልንሆንና ለቃሎቹ ልንታዘዝ እንደሚገባ ልናውቅ ግድ ነው፡፡ የተናገረውን እንዴት ሊናገረው እንደ ቻለ መመርመር እኛን አይመለከተንም፡፡ የእኛ ድርሻ ትእዛዛቱን መተግበር ብቻ ነው፡፡ የመረዳት ደረጃችን ምንም ያልበሰለ ቢሆንም እንኳ፣ ማድረግ እንዳለብን ሳወቅነው ነገር ሁሉ እንዲህ ያለ ታዛዥነት ከሌለን፣ በእርሱ አገልግሎትም ሆነ ተልዕኮ



የማደጋችንና ካለንበት ደረጃ ከፍ ብለን የመገኘታችን ነገር አጠራጣሪ ነው፡፡ በጸጋና በእውቀት የሚኖረንን እድገት የሚገታ ብቻም ሳይሆን፣ ስለ ወንጌል በሚደረገው ውጊያ በዚህ ዓለም ጦር ሜዳ ላይ እንኳ ሊኖረን የሚችለውን ጠቃሚ ሚናም የሚያጠፋ በመሆኑ፣ ቸልተኝነት በእግዚአብሔር መንግሥት ቦታ የለውም፡፡

ማንኛውም ሰው ለምንድን ነው ዛሬ ያሉ ክርስቲያኖች ባሉበት የሚረግጡትና ዕድገት የማያሳዩት? ምስክርነታቸውስ ለምንድን ነው የሚፈለገውን ያህል ውጤታማ መሆን ያቃተው? ብሎ ሊጠይቅ ይገባል፡፡ ይህንኑ ጥያቄ ሰፋ ባለ መልኩ ለማስቀመጥ፣ ዛሬ ቤተ ክርስቲያን ለምንድን ነው በወንጌል ስርጭት ረገድ በተስፋ መቁረጥ ውስጥ ያለችው? በሙሉ ጊዜ አገልጋዮችም ዘንድ ሆነ በምእመናኑ ዘንድ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ቸል ማለት ስለ ሰፈነ አይደለምን? ወይም ለብ ባለ ሕይወት እያመቻመችን መኖር ስለ ተመቸን አይደለም? እስከ መስቀል ሞት የሚያደርሰው ታዛዥነት የት አለ? ጌታ ኢየሱስ ራስን ስለ መካድ ያስተማረው ትምህርት «ደስ እንዳለህ አድርግ» በሚለው ቀለል ባለ የቀልጣፎች የተከበረ ፍልስፍና የተተካ ይመስላል፡፡

በጣም የሚያሳዝነው ነገር ደግሞ ምን እየሆነ እንዳለ በገባቸው ዘንድ እንኳ ይህን ሁኔታ ለማስተካከል የተደረገው ነገር በጣም ጥቂት መሆኑ ነው፡፡ ሌላው ይቅርና ጊዜው የተስፋ መቁረጥ ሳይሆን፣ ጊዜው የሥራ ጊዜ ነው፡፡ የቤተ ክርስቲያን አባላት በእውነተኛ ክርስቲያናዊ ደቀ መዝሙርነት መለኪያ እየታየ ተግባራዊ የሚደረግበት ዘመን ቢኖር አሁን ነው፡፡ ይህ እርምጃ ብቻ ግን በቂ አይደለም፡፡ ተከታዮች መሪ ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ይህ ማለት ደግሞ በአባላት ዙሪያ ሥራ ከመሠራቱ በፊት በቤተ ክርስቲያን መሪዎች ዘንድ ሊሠራ የሚገባው አንዳንድ ሥራ አለ፡፡

እንግዲህ ይህ ሥራ ታላቅ ሥራ ሆኖ ከታየን፣ ኢየሱስ ጥቂቶችን በመምረጥ የመታዘዝን ምሥጢር በውስጣቸው ማስረፅ እንደ ጀመረ እኛም ይህንኑ መሳይ ሥራ ልንጀምር ይገባል::

እንግዲህ ይህንን መርሕ በተግባር ማዋል የቻልን እንደ ሆነ ነው፣ በመምህሩ ድል የማድረግ ስልት መሠረት ወደ ቀጣዩ ደረጃ ሙሉ በሙሉ ልንሸጋገር የምንችለው::



*መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ*
*ዮሐንስ 20:22*

# 4

# ክህሎትን ማካፈል

## ራሱን አሳልፎ ሰጠ

ኢየሱስ ተከታዮቹ እንዲታዘዙት ይፈልግ ነበር:: ደቀ መዛሙርቱ ይህንን እውነት ሲገነዘቡ፣ ጥልቅ የሆነ የመንፈስ ቅዱስ ልምምድ እንደሚኖራቸውም ያውቅ ነበር:: በመሆኑም የእርሱን መንፈስ ሲቀበሉ እግዚአብሔር ለጠፋው ዓለም ያለውን ፍቅር ያውቃሉ:: ከዚህም የተነሣ እርሱ ለሚጠይቀው ነገር ያለ ምንም ማንጉራጉር ምላሽ ይሰጡ ነበር:: ደቀ መዛሙርት ሕግን እየጠበቁ እንዳልሆነ፣ ነገር ግን ለወደዳቸውና ራሱን ስለ እነርሱ አሳልፎ ለመስጠት ፈቃደኛ ለሆነው ጌታ ተገቢውን ምላሽ እየሰጡ እንደ ሆነ ገብቷቸው ነበር::

የጌታ ሕይወት የመስጠት ሕይወት ነበረ (ዮሐ. 15:15፤ 17:4፣8፣14):: አባቱ የሰጠውን ሁሉ ይሰጥ ነበር:: በመከራ ጊዜ ጽናት የሆነውን ሰላሙን (ዮሐ. 16:33፤ ማቴ. 11:28)፣ በኃዘንና በሥቃይ ተከቦ ሲያምጥ ሳለ በውስጡ የነበረውን ደስታውን ሰጣቸው (ዮሐ. 15:11፤ 17:13):: የሲኦል ኃይላት ሊቋቋሙት የማይችሉትን የመንግሥቱን ቁልፍ (ማቴ. 16:19፤ ከሉቃ. 12:32 ጋር አነጻጽሩ) ሰጣቸው:: እርሱ ከአብ ጋር አንድ እንደ ሆነ እነርሱም አንድ ይሆኑ ዘንድ ዓለም ከመፈጠሩ በፊት የነበረውን የገዛ ክብሩን ጨምሮ በእርግጥ ሰጣቸው (ዮሐ. 17:22፣24):: እንዳችም ሳያስቀር ያለውን ሁሉ ሰጣቸው፣ ነፍሱን እንኳ

አልከለከላቸውም።

እንግዲህ ፍቅር እንዲህ ነው - ምን ጊዜም ራሱን ለሌላው መስጠት። ያለውን በውስጡ የሚያስቀር ከሆነ ግን፣ ፍቅር ሊባል አይችልም። በዚህ ረገድ ኢየሱስ ተከታዮቹ «እግዚአብሔር ዓለሙን እንዲሁ ወዶአል» (ዮሐ. 3:16) ማለት ምን ማለት እንደ ሆነ በሚገባ እንዲረዱ አድርጓል። «አንድያ ልጁን» ጨምሮ እግዚአብሔር ለወደዳቸው ያለውን ሁሉ ሰጠ ማለት ነው። ልጁ ደግሞ፣ ይህ ፍቅር በሕይወቱ ተገልጾ እንዲታይ፣ የመኖር መብቱን መጠበቅ ሳይፈልግ ሕይወቱን ለዓለም አሳልፎ ሰጠ። ልጁ ራሱን በዓለም ፊንታ በዳረገበት አንጻር ሲታይ ብቻ ነው አንድ ሰው የመስቀሉን ሥራ ምሥጢር ሊረዳ የሚችለው። ስለሆነም ፍጹም የማይለካው የእግዚአብሔር ፍቅር ፈጽሞ በማይለካ መንገድ ራሱን ሊገልጥ ስለ ተገባ፣ በዚህ ግንዛቤ ውስጥ የክርስቶስ መስቀል ሊቀር የማይችል ጉዳይ ነው። ሰው በኃጢአቱ ምክንያቱ ሞት እንደ ተገባው ሁሉ፣ እግዚአብሔርም ከፍቅሩ የተነሣ ልጁ በእኛ ፈንታ ይሞት ዘንድ ሊልክ ተገባው። «ነፍሱን ስለ ወዳጆቹ ከመስጠት ይልቅ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር ለማንም የለውም» (ዮሐ. 15:13)።

## የወንጌል ስርጭት አስገዳጅነት

ለዚህም ነበር በእግዚአብሔር ፍቅር የተቀጣጠለች ነፍሱ የሚሰማትን መንገድ ለተከታዮቹ ለማካፈል ያገኘውን አጋጣሚ ሁሉ ይጠቀም የነበረው። ይናገርና ያደርግ የነበረው ነገር ሁሉ የነበረው በውስጡ ይቀጣጠል በነበረው ፍቅር አነሣሽነት የተፈጸመ ነበር። በአጠቃላይ ሕይወቱ እግዚአብሔር ለራሱ የሚሆን ሕዝብን ለማዳን የነበረውን ዘለዓለማዊ ዕቅድ በጊዜው ገልጦ ያሳየ ሕይወት ነበር። ደቀ መዛሙርቱም፣ በመርሕ ደረጃ ሳይሆን በተግባር፣ ሊማሩት የሚገባቸው ነገር ይሄው ነበር።



መርሑም በተለያየ መልኩ በፊታቸው ሲተገበር ዕለት ዕለት ይመለከቱ ነበር። አብዛኛውን ጊዜ ተግባራዊ ምሳሌዎቹ ለመቀበል በጣም አስቸጋሪና ከባድ ቢሆኑም፣ ዓላማቸውን ግን በሚገባ ይረዱ ነበር። ለምሳሌ፣ እግራቸውን በማጠብ ያሳያቸው ምሳሌ (ዮሐ. 13:1-20) ለመቀበል አስቸጋሪ ሆኖባቸው ነበር። መምህራቸው ከዓለም የሚገኘውን ብዙ ምቾትና ደስታ ጥሎ በመካከላቸው እንዴት አገልጋይ እንደ ሆነ ለመረዳት ችለዋል። እነርሱ የሚጓጉላቸውን ሥጋዊ እርካታን፣ ታዋቂነትን፣ ክብርንና ዝናን ከቁም ነገር ሳይቆጥር ችላ እንዳለና፤ በምትኩ ለእነርሱ ሲል እነርሱ የሚሸሹአቸውን ድህነትን፣ መናቅን ብሎም ሞትን በፈቃዱ እንደ ተቀበለ ተመልክተዋል። ድውዮችን ሲያገለግል፣ ያዘኑትን ሲያጽናና፣ ለድሆች ወንጌልን ሲሰብክ ሲመለከቱት ለእግዚአብሔር ክብር ይሁን እንጂ ትንሽ የሚለው አገልግሎት ወይም ትልቅ የሚለው መሥዋዕትነት እንደሌለው በግልጽ ይታይ ነበር። ምናልባትም ሁልጊዜ ላይረዱት ቢችሉም፣ በእርግጥ እንዲህ ነው ብለው ለመግለጽ ቢቸገሩም፣ ነገር ግን በፍጹም በተሳሳተ መልኩ ተረድተውት አያውቁም።

## የኢየሱስ ቅድስና

ሌሎችን በፍቅር በማገልገል ለእግዚአብሔር ያለውን መስጠት ያለማቋረጥ በየጊዜው በማደሱ ኢየሱስ ቅድስናውን አጽንቶ ነበር። በሊቀ ካህናዊ ጸሎቱ «ወደ ዓለም እንደ ላክኸኝ እንዲሁ እኔ ወደ ዓለም ላክኋቸው፤ እነርሱም ደግሞ በእውነት የተቀደሱ እንዲሆኑ እኔ ራሴን ስለ እነርሱ እቀድሳለሁ» (ዮሐ. 17:18-19) ብሎ በጸለየ ጊዜ ይህን በግልጽ አስቀምጦታል። እዚህ ላይ ሊስተዋል የሚገባው ነገር "እቀድሳለሁ" በሚለው ቃል የተገለጠው አሳብ ወደ ጌታ ኢየሱስ ስናመጣው መንጻት የሚለውን የሚገልጽ አይሆንም፣

ምክንያቱም እርሱ ምን ጊዜም ንጹሕ ነው፡፡ በተጨማሪም ሊጠቀምበት የሚችለው ከኃይል ሁሉ በላይ የሆነ ኃይል በእጁ ነውና ለአገልግሎቱ ኃይል መቀበል አስፈላጊ አልነበረም፡፡ ነገር ግን ከጠቅላላ ዐውዱ እንደምንረዳው፣ የእርሱ መቀደስ «ወደ ዓለም የመጣበትን» ሥራውን ለመፈጸም ባለው መሰጠትና ለዚህ የወንጌል ስርጭት ዓላማ ያለማቋረጥ «ስለ እነርሱ ሲል» ሕይወቱን በመስጠቱ ላይ የሚያተኩር ነው፡፡

ስለሆነም የኢየሱስ መቀደስ ጠቀሜታው ለእርሱ ሳይሆን፣ ደቀ መዛሙርቱ «በእውነት ይቀደሱ» ዘንድ ነው፡፡ ይህም፣ ራሱን ለእግዚአብሔር በመስጠት፣ አብረውት ያሉት ወደ ዓለም የመጣበትን ሥራውን ለመፈጸም የሚያስፈልገውን ተመሳሳይ የሆነ መስጠት ይረዱ ዘንድ ኢየሱስ ራሰን ሰጠ ማለት ነው፡፡ ጠቅላላው የወንጌል ስርጭት ዕቅዱ በዚህ መሰጠትና በምላሹም በአካባቢያቸው ለነበረው ዓለም በፍቅር ደቀ መዛሙርቱ ራሳቸውን በሰጡበት ታማኝነት ላይ ያተኮረ ነው፡፡

## የአገልግሎቱ መታወቂያ ማዕረጐች

በስሙ የሚያደርጉትን አገልግሎታቸውን የሚመዝኑበት መለኪያው እንግዲህ ይህ ነበር፡፡ በነፃ እንደ ተቀበሉ ሁሉ በነፃ ሊሰጡ ይገባቸዋል (ማቴ. 10:8)፡፡ እርሱ እንደ ወደዳቸው፣ እርስ በርሳቸው ሊዋደዱ ይገባቸዋል (ዮሐ. 13:34-35)፡፡ በዚህም ደቀ መዛሙርቱ መሆናቸው ይታወቃል (ዮሐ. 15:9-10)፡፡ ትእዛዛቱ ሁሉ ደግሞ በዚህ ይጠቃለላሉ (ዮሐ. 15:12፣17ን ከማቴ. 22:37-40፤ ማር. 12:30-31፤ ሉቃ. 10:27 ጋር አነጻጽሩ)፡፡ የፍቅር ሁሉ መለኪያ የቀራንዮ ፍቅር ነበር፡፡ ደቀ መዛሙርት ለሦስት ዓመታት እንደ አዩት፣ አብ ለወደዳቸውና የእነርሱም ጌታ ደግሞ



ለሞተላቸው ለእነዚያ ራሳቸውን ሳይሰስቱ መስጠት ነበረባቸው (ዮሐ. 17:23)፡፡

ዓለም ወንጌል እውነት መሆኑን የምታውቅበት መንገድ እንዲህ ባለ መልኩ በእነርሱ በሚገለጠው ፍቅር አማካይነት ነበር፡፡ እንዲህ ባለ መልኩ ካልሆነ እንዴት ባለ መንገድ ብዙኃኑን ማሳመን ይቻላል? የሰውን ፈቃድ ማሸነፊያው መንገድ ፍቅር ብቻ ነው፡፡ ይህንንም ፍቅር ማሳየት የሚቻለው ደግሞ ክርስቶስ በልብ ውስጥ ሲገኝ ብቻ ነው፡፡ ለዚህም ነው ኢየሱስ እንዲህ ሲል የጸለየው፣ «ጻድቅ አባት ሆይ፣ ዓለም አላወቀህም፣ እኔ ግን አወቅሁህ፤ እነዚህም አንተ እንደ ላክኸኝ አወቁ፤ እኔንም የወደድህባት ፍቅር በእነርሱ እንድትሆን እኔም በእነርሱ ስምህን አስታወቅኋቸው አስታውቃቸውማለሁ» (ዮሐ. 17:25፣26)፡፡

## የመንፈስ ቅዱስ ሥራ

ከክርስቶስ ጋር እንደነበረው ያለ እንዲህ መሳዩ ልምምድ በሰው ጉብዝናና ብቃት ሊደረግ ይችላል ብሎ ማንም ሊያስብ አይገባም፡፡ ሕይወቱ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ብቻ ወደ ሌሎች ሊተላለፍ እንደሚቻል ኢየሱስ በሚገባ ግልጽ አድርጎ ተናግሯል፡፡ «ሕይወትን የሚሰጥ መንፈስ ነው፤ ሥጋ ምንም አይጠቅምም» (ዮሐ. 6:63)፡፡ ለዚህ ነው እንግዲህ በክርስቶስ መኖር ለመጀመር እንኳ ቀዳሚው ነገር ዳግም መወለድ የሆነው (ዮሐ. 3:3-9)፡፡ የተበላሸው የሰው ተፈጥሮ ወደ ተፈጠረለት መለኮታዊ መልኩ የመለወጥ እውነተኛ ዓላማ ከመድረሱ በፊት መጀመሪያ በእግዚአብሔር መንፈስ አማካኝነት ዳግም ሊፈጠር ይገባዋል፡፡ እንደዚሁም፣ የተለወጠውን የደቀ መዝሙሩን ሕይወት በእውቀትና በጸጋ የሚደግፈውና የሚንከባከበው ይሄው መንፈስ ነው (ዮሐ. 4:14፤ 7:38-39)፡፡ በዚሁ መንፈስ አማካኝነት በቃሉ በኩል ሰው ንጹሕ ይሆናል፣

ለእግዚአብሔርም የተቀደሰ አገልግሎት ይሰያል (ዮሐ. 15:3፤ 17:17ን ከኤፌ. 5:26 ጋር ያነጻጽሩ):: ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ፣ ሕያው የሆነውን ክርስቶስን በማንኛውም መንገድ በግል መሰማመድ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው::

የመቤዠት ተልዕኮ የሆነውን የወንጌልን አገልግሎት ማከናወን የሚያስችለውም የእግዚአብሔር መንፈስ ብቻ ነው:: ከራሱ ሥራ ጋር በማዛመድ ኢየሱስ መጀመሪያ ላይ «ከእግዚአብሔር መንፈስ» ጋር በመተባበር የሠራውን ሥራ እንደ ሠራ በመናገር ይህን እውነት አስምሮበታል:: ከዚህም የተነሣ በውስጡ በነበረው ጸጋ ለድሆች ወንጌልን ሰብኳል፣ ልባቸው የተሰበረባቸውን ጠግኗል፣ ለታሰሩት መፈታትን አውጇል፣ የእውራንን ዓይን አብርቷል፣ አጋንንትን አውጥቷል፣ ለተጠቁትም ነጻነትን ሰጥቷል (ሉቃ. 4:18፤ ማቴ. 12:28):: ኢየሱስ በአካል የተገለጠ አምላክ ሲሆን፣ መንፈስ ቅዱስ ግን በተግባር የተገለጠው አምላክ ነበር:: መንፈስ ቅዱስ ዘላለማዊ የሆነውን የደኅንነትን ዕቅድ በሰው በኩል የሚያስፈጽም የእግዚአብሔር ወኪል ነው:: ለዚህም ነው ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ መንፈስ ቅዱስ ለአገልግሎታቸው መንገድን እንደሚያዘጋጅ የነገራቸው:: የሚናገሩትን እርሱ ይሰጣቸዋል (ማር. 10:19-20፤ ማቴ. 13:11፤ ሉቃ. 12:12):: ዓለምንም «ስለ ኃጢአት፣ ስለ ጽድቅ፣ ስለ ፍርድ» ይወቅሳል (ዮሐ. 16:8):: ሰዎች ጌታን ያውቁ ዘንድ እውነትን ያበራላቸዋል (ማቴ. 22:43፤ ማር. 12:36፤ ዮሐ. 16:14):: በእርሱ ኃይልም ደቀ መዛሙርት ጌታቸው የሠራውን ሥራ ለመሥራት የሚያስፈልገውን አቅምና ችሎታ እንደሚያገኙ የሚያረጋግጥ ቃል ተቀብለዋል (ዮሐ. 14:12):: እንግዲህ በዚህ መሠረት፣ ወንጌልን በሰው እንደሚከናወን የምንረዳው ጉዳይ ሳይሆን፣ ነገር ግን ከመጀመሪያ የነበረና



የእግዚአብሔር ዓላማ እስኪፈጸም ድረስም የሚቀጥል መለኮታዊ ዕቅዱ መሆኑን እንረዳለን:: በአጠቃላይ ሥራው የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነበር:: ከደቀ መዛሙርቱ የሚጠበቀው መንፈስ ቅዱስ በሕይወታቸው ሙሉ በሙሉ ኃላፊነቱን እንዲወስድ መፍቀድ ብቻ ነበር::

## ሌላው አጽናኝ

የሆነ ሆኖ፣ ከራሳቸው እርካታ አንጻር፣ ደቀ መዛሙርት መንፈስ ቅዱስ ከጌታቸው ማንነት ጋር ያለውን ኅብረት ግልጽ በሆነና በሚገባቸው መልኩ በይበልጥ ለመረዳት ፈልገው ነበር:: ኢየሱስም ይህንን ፍላጎታቸውን በማየት፣ በሥጋው የሚመላለስበት ወራት ወደ ማብቂያው ሲቃረብ፣ ስለ መንፈስ ቅዱስ የበለጠ ትኩረት ሰጥቶ አስተማራቸው:: እስከዚያን ጊዜ ድረስ ሁልጊዜ አብሮአቸው ነበር:: እርሱ አጽናኛቸው፣ መምህራቸውና መሪያቸው ነበር:: ከእርሱ ጋር ከነበራቸው ኅብረት የተነሣ ደቀ መዛሙርት ጥንካሬንና ብርታትን አውቀዋል:: ከእርሱ ጋር ሳሉ ሁሉ ነገር ማድረግ እንደሚቻል ይሰማቸው ነበር:: እነርሱ ያስጨነቃቸው ጌታ ኢየሱስ ወደ መንግሥተ ሰማይ ተመልሶ የመሄዱ ጉዳይ ነው:: ስለሆነም እርሱ ከሄደ በኋላ እንዴት እንደሚዘልቁ ኢየሱስ መንገር ነበረበት::

እንግዲህ በዚህን ጊዜ ነበር ኢየሱስ ስለ መንፈስ ቅዱስ «ሌላ አጽናኝነት»፣ ጠበቃነትና ሁልጊዜም በአጠገባቸው እየተገኘ የሚደግፋቸውና ኢየሱስ በሥጋ ተገልጦ በገሃድ በሚታየው ልምምድ የሞላውን ክፍተት በማይታየው የእውነታ ዓለም ልክ እንደ እርሱ ሆኖ እንደሚገኝ የነገራቸው (ዮሐ. 14:16):: እርሱ ለሦስት ዓመታት እንዳገለገላቸው ሁሉ፣ አሁን ደግሞ መንፈስ ቅዱስ ወደ እውነት ሁሉ ይመራቸዋል (ዮሐ. 16:13)፣ ሊመጣ

ያለውንም ያሳያቸዋል (ዮሐ. 16:13)፤ ሊያውቁት የሚገባቸውን ያስተምራቸዋል (ዮሐ. 14:26)፤ እንዲጸልዩም ይረዳቸዋል (ዮሐ.14:12፣13፤ 16:23፣24)፤ በእጭሩ፣ የክርስቶስ የሆነውን እየወሰደ ለተከታዮቹ እውን በማድረግ ልጁን ያከብረዋል (ዮሐ. 16:14-15):: ኢየሱስን አያውቀውምና ዓለም ይህንን እውነት አይቀበልም:: ደቀ መዛሙርቱ ግን አብሮአቸው ነበረና ያውቁታል፣ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነትም ለዘለዓለምም ከእነርሱ ጋር አብሮአቸው በመሆን ይቀጥላል (ዮሐ. 14:17)::

እዚህ ላይ ኢየሱስ ይናገር የነበረው ጽንሰ አሳብ፣ ወይም ስለ ሃይማኖት መግለጫ፣ ወይም እንደ ሁኔታው ሊለወጥ ስለሚችል ዝግጅት አልነበረም:: ደቀ መዛሙርት በሚገጥማቸው ጉዳት ሊደገፉበት ስለሚችሉት እውነተኛ ስለሆነ ምትክ ቃል ኪዳን እየገባላቸው ነበር:: «ሌላው አጽናኝ» እንደ ኢየሱስ ሁሉ የመምህሩን በመካከላቸው መገኘት እውን ያደርግላቸዋል:: በእርግጥ፣ ደቀ መዛሙርት ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በሚኖራቸው ጥልቅ የሆነ ኅብረት የሚያገኙት መታደል ኢየሱስ በገሊላ ጎዳናዎች አብሮአቸው ሲመላለስ በነበረበት ጊዜ ከሚያውቁትም የበለጠ ነው:: በዚህ ላይ፣ ኢየሱስ በሥጋ ሳለ በአንድ አካልና በአንድ ቦታ የተወሰነ ነበር:: መንፈስ ቅዱስ ሲመጣ ግን ይህ ገደብ ተነሣ:: አሁን ሁል ጊዜ ከእነርሱ ጋር አብሮአቸው መሆን ይችላል:: እንዲያውም እንዳይተዋቸውና እንዳይጥላቸው የሚያስችል አቋም አግኝቷል (ማቴ. 28:20፤ ዮሐ. 14:16):: ሥራውን ጨርሶ ወደ አባቱ ስለሚመለስና በእርሱ ቦታ እንዲተካም የተባረከውን አጽናኝ ስለሚልክ (ዮሐ. 16:17)፤ ከዚህ አንጻር ስንመለከተው፣ ይህ ለኢየሱስ የተሻለ ነበር::



## የአሸናፊነት ምሥጢር

እንግዲህ ይህ ቃል ኪዳን እውነት ሆኖ እስኪገለጥላቸው ድረስ ደቀ መዛሙርቱ እንዲጠብቁ ኢየሱስ ለምን እንደ ፈለገ ለመረዳት ቀላል ነው (ሉቃ. 24:49፤ የሐዋ. 1:4፣5፣8፤ 2:33):: አለበለዚያማ ጌታቸው የሰጣቸውን ተልዕኮ በደስታና በውስጣዊ ሰላም እንዴት አድርገው ነበር መፈጸም የሚችሉት? ሕይወታቸው በእርሱ መገኘ ት ይሞላ ዘንድ ከክርስቶስ ጋር ያላቸው ልምምድ እጅግ በእውነት እውን መሆን ያስፈልገው ነበር:: ወንጌል ስርጭት እስተሳሰባቸውን የሚመራና ፍላጎታቸውን የሚያጠራ አንገብጋቢ የውስጣቸው ጉዳይ ሊሆን ይገባል:: በመንፈስ ቅዱስ በግል ከመጠመቅ ያነሰ ምንም ነገር በቂ አይደለም:: ከሰዎች በላይ ለሆነው የተጠሩለት ሥራ ከተፈጥሮ በላይ የሆነ እርዳታን፣ ማለትም ከላይ የሚሰጥ ኃይልን፣ የሚሻ ነበር:: ስለዚህ ደቀ መዛሙርት በውስጣቸው የተቀመጠውን ትእቢትና ጥላቻ በመናዘዝና ፍጹም በሆነ መማረክ ራሳቸውን ፈጽመው ለክርስቶስ በማስገዛት፣ በእምነት ወደሚሆን አዲስና ልዩ ልምምድ ወደ ሆነው የመንፈስ ቅዱስ ሙላት መምጣት ነበረባቸው::

እነዚህ ሰዎች እንደ ማንኛውም የሰው ዘር የሚደርስበትን ዕጣ የሚካፈሉ መሆናቸው ምንም የፈጠረው እክል አልነበረም:: እንዲያውም ይህ መሆኑ ሁሉን ቻይ የሆነው የእግዚአብሔርን መንፈስ ሁለንተናቸውን ከእግሩ በታች ባስገዙት በደቀ መዛሙርቱ ዓላማውን መፈጸም እንደሚችል ያስታውሰናል:: ለነገሩማ፣ ኃይሉ ያለው በክርስቶስ መንፈስ ውስጥ ነው:: ልዩነት የሚያመጣው የእኛ ማንነት ሳይሆን፣ የእርሱ ማንነት መሆኑ ላይ ነው::

## ከማያምኑት የተሰወረ እውነት

ይሁን እንጂ፣ እንዲህ ወደአለው የልምምድ ክብር የደረሱት እነዚያ ጌታ ኢየሱስን እስከ መጨረሻው የተከተሉት እንደ ሆኑ መጥቀሱ መልካም ነው፡፡ በርቀት የተከተሉት ሕዝብም ሆኑ፣ እንደ ፈሪሳውያን በቃሉ ብርሃን ለመመላለስ አሻፈረኝ ያሉት፣ ይህ የተባረከው አጽናኝ ስለ ሠራው ሥራ የመስማት ዕድል እንኳ አላገኙም ነበር፡፡ ቀደም ሲል እንደ ተጠቀሰው፣ ኢየሱስ እንቁዎቹን በማይፈልጓቸው ፊት አይጥልም፡፡

ይህ በሕይወት ዘመኑ ሁሉ ያስተማረውን የሚገልጽ ባሕርይ ነበር፡፡ ለመረጣቸው ጥቂት ደቀ መዛሙርቱ፣ በተለይም ለአሥራ ሁለቱ፣ ኢየሱስ ዋነኛ ግንዛቤን የሚያሰፉ ነገሮቹን ሰውሮ ያቆይ ነበር (ሉቃ. 10:22፤ ማቴ. 11:27፤ 16:17)፡፡ በእርግጥም፣ ዓይኖቻቸውና ጆሮዎቻቸው የተባረኩ ነበሩ፡፡ እነርሱ ያዩትን ለማየት፣ እነርሱ የሰሙትንም ለመስማት ብዙ ነቢያትና ነገሥታት ናፍቀው ነበረ፣ ነገር ግን የናፈቁትን ሊያገኙ አልቻሉም (ማቴ. 13:16፣ 17፤ ሉቃ. 10:23-24፤ ማቴ. 13:10-11፤ ማር. 4:10-11፤ ሉቃ. 8:9-10)፡፡ ሥራውን በሚገባ እንዲሠሩ ያዘጋጃቸው ዘንድ ኢየሱስ ያለውን ሁሉ በእነዚህ በጥቂቶቹ ላይ ማዋሉ ግራ የሚያጋባ መመሪያ (ፖሊሲ) ሊመስል ይችላል፡፡

በዛሬው ዘመን ያለው የመርሕ ጉዳይ

ሁሉ ነገር በጌታ ማንነት ላይ ያነጣጠረ ነበር፡፡ እነርሱን የሚያሠለጥንበት መሠረታዊው መንገድ ሕይወቱ ነበር፡፡ ተከታዮቹም ይህንኑ ሊያደርጉ ይገባል፡፡ ዛሬ እኛ የእርሱን ሥራ ልንሠራና ትምህርቱን የምንተገብር ከሆነ፣ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት የእርሱ ሕይወት በእኛ ውስጥ ሊኖር ይገባል፡፡ ይህ



የሌለበት ማንኛውም ዓይነት የወንጌል ሥራ ሕይወት - አልባና ትርጉም - የለሽ ነው፡፡ በእኛ ያለው የክርስቶስ መንፈስ ልጁን ሲያከብር ብቻ ነው ሰዎች ወደ አብ የሚሳቡትና የሚደርሱት፡፡

እርግጥ ነው፣ እኛ የሌለንን ለሌሎች ልንሰጥ አንችልም፡፡ በክርስቶስ ያለንን ሕይወት ለሌሎች ማካፈል መቻላችን ያ ሕይወት በእኛ ዘንድ ለመኖሩ ማረጋገጫ ነው፡፡ ስለሆነም እኛ ለራሳችን ይዘን ልናስቀረውም አንችልም፡፡ የእግዚአብሔር መንፈስ ሁልጊዜ ክርስቶስን እንድናስተዋውቅ ይገፋፋናል፡፡ እዚህ ላይ ታዲያ ትልቅ የሕይወት እንቆቅልሽ አለ- ለክርስቶስ ለመኖር ለራሳችን ልንሞት ይገባል፡፡ በዚያም ራሳችንን በካድንበት ሕይወት በማገልገልና በመስጠት ለጌታችን ራሳችንን አሳልፈን ልንሰጥ ይገባል፡፡ የኢየሱስ የወንጌል ስርጭት ዘዴ ይህ ነበረ፡፡ ይህም ዘዴ በመጀመሪያ በጥቂት ተከታዮቹ ብቻ የተስተዋለ ሲሆን፣ በኋላ ግን በእነርሱ አማካይነት ዓለምን የሚማርክ የእግዚአብሔር ኃይል ሆኖ ተገኘ፡፡

ነገር ግን እዚህ ላይ ልንቆም አንችልም፡፡ ማንም ሕይወቱን የሚመራበት ግልጽ የሆነ መመሪያ በእኛም ውስጥ ሊያይ ያስፈልጋል፡፡ ስለዚህ፣ ጌታ ኢየሱስ በደቀ መዛሙርቱ ሕይወት ከተጠቀመው ዘዴ ልንረዳው የሚገባን አንድ ግልጽ የሆነ ሌላ ገጽታ አለ፡፡

ምሳሌ ሰጥቻችኋለሁ
ዮሐ. 13:15

# 5

# በተግባር ማሳየት

## እንዴት መኖር እንደሚገባቸው አሳያቸው

እርሱ ከሰውና ከእግዚአብሔር ጋር የኖረውን አኗኗር በሚገባ ደቀ መዛሙርቱ በመማራቸው ላይ ኢየሱስ ያተኩር ነበር:: ሰዎችን ወደ እርሱ መንፈሳዊ ኅብረት ማድረስ ብቻ በቂ እንዳልሆነ ገብቶታል:: በወንጌል ስርጭት ጊዜም ቀጣይነት ባለው ሁኔታ የሚተላለፍ ከሆነ፣ የእርሱን ልምምድ ደቀ መዛሙርት እንዴት አድርገው ከራሳቸው ጋር ሊያዋህዱና ለሌሎች ሊያካፍሉ እንደሚችሉ ማወቅ ይገባቸዋል:: በእርግጥ፣ በመርሕ ደረጃ፣ ሕይወት ከተግባር ይቀድማል፣ ፍጹም ተግባራዊ ከሆነው አንጻር ግን፣ የምንሠራው ሥራ ሕይወታችንን ይወስናል:: ለማደግ ልንተነፍስ፣ ልንመገብ፣ ልንንቀሳቀስና እንደ ማንኛውም ጊዜ እንደ ለመድነው ሥራችንን ልንሠራ ይገባል:: እነዚህን የአካላችንን ተግባራት ችላ ካልናቸው፣ ሕይወት ይቆማል:: ለዚህ ነው እንግዲህ የእርሱን መንፈሳዊ ተጽዕኖ በደቀ መዛሙርቱ ውስጥ ለማሥረጽ ሆነ ብሎ ያደረገው ጥረት የኢየሱስ ዋነኛ ዘዴ ንዑስ አካል ተደርጎ ሊታይ የሚገባው:: አስፈላጊ የሆነው ምን እንደ ሆነ እርሱ ያውቅ ነበር::

### የጸሎት ልምምድ

የኢየሱስን የጸሎት ሕይወት እንደ ምሳሌ መውሰድ እንችላለን:: ኢየሱስ አብዛኛውን ጊዜ ከአብ ጋር ሲነጋገር ደቀ መዛሙርት



እንዲያዩት የሚያደርገው በአጋጣሚ እንዳልሆነ በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል:: ጸሎት ለሕይወቱ የሰጠውን ጥንካሬ ማየት ችለው ነበር:: እንደዚሁም ስለ ምን እንደ ሆነ ብዙም ባይረዱትም፣ ከሕይወቱ ምሥጢራት አንዱ ክፍል ይህ እንደ ሆነ ሳይረዱ አልቀሩም:: አስተውሉ! ጌታ ጸሎት ላስተምራችሁ ብሎ አላስገደዳቸውም:: በስተመጨረሻ ደቀ መዛሙርት ራሳቸው ረሀባቸው ጸንቶ የምታደርገውን አስተምረን እስከሚሉት ድረስ ዝም ብሎ ይጸልይ ነበር::

የማስተማሩን ዕድል ሲያገኝ፣ ልባቸው ሊቀበለው የተዘጋጀውን ትምህርት መስጠቱን ቀጠለ:: የጸሎትን መሠረታዊ መርሖች ገለጸላቸው፣ ከመጨረሱ በፊትም ምን ማለቱ እንደ ሆነ በይበልጥ እንዲገባቸው ምሳሌያዊ ጸሎት እየጸለየ አሳያቸው (ሉቃስ 11:1-4፤ ማቴ. 6:9-13):: የተናገራቸውን እንዲደግሙ በማድረግ ይጸልዩ ዘንድ ማለማመድ ከደቀ መዛሙርት አቅም በታች የሆነ ልምምድ ነው ብለን ልናስብ እንችላለን:: ኢየሱስ ግን እንዲህ ያለውን አስፈላጊ ነገር እንዲሁ ሊሆን እንደሚችል ጉዳይ አድርጐ አልነበረም የሚያየው:: በእርግጥ፣ እንዲህ ያለው ቀላል የማስተማር ዘዴ ብዙውን ጊዜ ሰዎች እንደዚያ ያለውን ሥርዓት ባለው መልኩ እንዲጀምሩ ለማድረግ የሚጠቅም ነው:: የሚፈጀውን ጊዜ ያህል ይፍጅ እንጂ፣ ኢየሱስ ግን ይህንን ትምህርት ከእርሱ ወደ እነርሱ ለማሻገር ወስኖ ነበር::

ከዚህ በኋላ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር በተነጋገረ ቁጥር የጸሎትን አስፈላጊነት ደግሞ ደጋግሞ ይነግራቸው ጀመር:: ጥልቅ የሆነውን የመንፈስ ቅዱስን እውነት ለመረዳት በቻሉ መጠን የጸሎትን ትርጉምና አተገባበሩን ይበልጥ እያጎላ ነገራቸው:: ይህ ደግሞ እነርሱም በተራቸው ወደ ሌሎች ሊያስተላልፉት የሚገባቸው

የሥልጠናቸው አይቀሬ ክፍል ነበር:: አንድ ነገር እርግጥ ነው:: የጸሎትን ትርጉም በሚገባ ካልተረዱና እንዴት በታማኝነትና በድንቅ ሊጠቀሙበት እንደሚገባ ካላወቁ፣ ከሕይወታቸው ብዙም ትርፍ አይገኝም::

## መጽሐፍ ቅዱስን መጠቀም

ለደቀ መዛሙርቱ በግልጽ ከቀረበላቸው የኢየሱስ የሕይወት አንጻሮች ውስጥ ሌላው ነገር የመጽሐፍ ቅዱስ አስፈላጊነትና ጠቀሜታ ነበር:: ለግል የጥሞና ጊዜውም ሆነ ሌሎችን ወደ ሕይወት መንገድ ለማስገባት መጽሐፍ ቅዱስን በሚገባ ሲጠቀምበት ነበር:: አብዛኛውን ጊዜ ከመጽሐፍ ቅዱስ የተወሰደን የአንድን ክፍል ትርጉም ለተከታዮቹ ለማሳየት እጅግ በጣም ይደክም ነበር:: ከእነርሱ ጋር በነበረው በማንኛውም ንግግሩ መጽሐፍ ቅዱስን መጠቀም አቋርጦ አያውቅም:: ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ባደረገው ውይይት በአራቱ ወንጌላት ቢያንስ ስልሳ ስድስት የብሉይ ኪዳን ጥቅሶችን የተጠቀመ ሲሆን፣ ይህም ከሌሎች ሰዎች ጋር በተነጋገረበት ወቅት የጠቀሳቸውን ከዘጠና የሚበልጡ ብሉይ ኪዳንነክ አባባሎችን ሳይጨምር ነው::

ይህ ሁሉ ደግሞ ደቀ መዛሙርቱ እንዴት መጽሐፍ ቅዱስን ሊያውቁ ብሎም በሕይወታቸው ሊጠቀሙበት እንደሚያስፈልግ የሚያመላክት ነበር:: መጽሐፍ ቅዱስን ጠቅሶ ሰዎችን የመውቀሱና የመምከሩ ተግባር በተደጋጋሚ በፊታቸው ይከናወን ስለነበረ፣ መሠረታዊ የሆኑ የመጽሐፍ ቅዱስ አፈታት ሕግጋትና አተገባበራቸውን መቅሰም ችለው ነበር:: ከዚህም በላይ፣ ኢየሱስ ሳይጨነቅ የብሉይ ኪዳንን ክፍሎች የማስታወስ ችሎታው ደቀ መዛሙርቱን ሳያስደንቃቸው አልቀረም:: ስለሆነም የመጽሐፍ ቅዱስን ቃሎች በልቦናቸው ማኖርንና እነርሱንም ለንግግሮቻቸው



የሥልጣን ምንጭ እንዲሆኑ መፍቀዱ አስፈላጊ እንደ ሆነ ተረድተዋል::

በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተጻፉት ቃሎችና ክርስቶስ የተናገራቸው ቃሎች በሁሉ ነገር ይደጋገፉ ነበር እንጂ፣ የማይቃረኑ መሆናቸውን በሚገባ በግልጽ ማሳየት ተችሏል:: ስለሆነም ኢየሱስ ያስተማራቸው ነገሮች በደቀ መዛሙርት ዘንድ ትልቅ ቦታ ነበራቸው:: ጌታ ከተናገራቸው ቃሎች ጋር ተደምሮ፣ ቅዱሱ መጽሐፍ በክርስቶስ ላይ ላላቸው እምነት ዋነኛ መሠረት ሆኖላቸው ነበር:: በተጨማሪም፣ እርሱ በሥጋ ከእነርሱ ከተለየ በኋላ በመንፈስ ከእርሱ ጋር ኅብረት ማድረግ የሚቀጥሉ ከሆነ፣ በቃሎቹ ጸንተው መቀጠል ያስፈልጋቸዋል (ዮሐ. 15:7)::

## ከምንም በላይ ነፍሳትን መማረክ

ኢየሱስ እንዲህ ባለ መንገድ ራሱን በመግለጽ የግል ሕይወቱን ሥርዓት ለደቀ መዛሙርቱ አወረሳቸው:: በተጨማሪም ከዋነኛው ዓላማው አንጻር ምናልባትም ከሁሉ በላይ አስፈላጊ የሆነውን ነፍሳትን እንዴት መማረክ እንደሚችሉ አብረው በነበሩበት ጊዜ ሁሉ ያስተምራቸው ነበር::

ወደ ተግባር ስንመጣ ኢየሱስ የተናገረውም ሆነ ያደረገው መንፈሳዊ እውነትን በማብራራት አሊያም ደግሞ እንዴት አድርገው ከሰዎች ጋር መግባባት እንዳለባቸው በመግለጽ ረገድ ከወንጌል አገልግሎታቸው ጋር ግንኙነት ያለው ነበር:: በዙሪያው ያሉትን ክስተቶች ይጠቀም ነበር እንጂ ለማስተማር ሁኔታዎችን ማመቻቸት አላስፈለገውም፣ ይህም ትምህርቱ እውነትን የተመረኮዘ እንዲሆን አድርጎት ነበር:: በእርግጥ፣ ደቀ መዛሙርት በተመሳሳይ መልኩ ሰዎችን ለእግዚአብሔር ለመማረክ እንዲችሉ እያሠለጠናቸው እንደ ሆነ እንኳ ሳይገባቸው ነበር አብዛኛውን ጊዜ

ሁሉን ነገር የሚቀበሉት።

## በቀላሉ ማስተማር

ይህንን ነጥብ፣ ቀደም ሲል ብዙ ጊዜ ደጋግመን ያነሣነው በመሆኑ፣ ከዚህ የበለጠ አበክረን መነጋገር አንችልም። ኢየሱስ እንከን የማይወጣለት መምህር በመሆኑ የማስተማር ዘዴው ትምህርቱን እንዲያድበሰብስበት አልፈቀደም። እውነቱ በአቀራረቡ ሳይሆን በራሱ ትኩረትን እንዲስብ ነበር ያደረገው። በዚህ ረገድ የተጠቀመው ዘዴ የማስተማር ዘዴ እንደ ነበረው እንኳ እንዳይገለጥ የሚያደርግ ነበር። የእርሱ ዘዴ እርሱ ራሱ ኢየሱስ ነበር።

ምናልባትም ሙያዊ ክህሎት አስፈላጊ በሆነበትና ዘዴዎችን በመጠቀም ሰውን ለመሳብ በሚጣርበት በዚህ ዘመን እንዲህ ያለውን ዘዴ ማሰቡ አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል። ዛሬ ዛሬ እንዲያውም በአንዳንድ ቦታዎች፣ በሚገባ የተዘጋጁ መርጃ መጻሕፍትን ወይም በብዙ ቀለማት የደመቁና የሥራችንን ሂደት የሚያመለክቱ ሰፋፊ ማስታወሻ መጻፊያ ወረቀቶች በሌሉበት መሥራት የማንችልበት ሁኔታ ላይ የደረስን ይመስላል። ቢያንስ ቢያንስ ነፍሳትን ስለ መማረክ የሚገልጹ ትምህርታዊ ጉባኤዎች ይደረጋሉ ብለን እንጠብቃን። ይሁን እንጂ፣ ነገሩ ግራ የሚያጋባ ቢሆንም፣ ደቀ መዛሙርቱ ግን እኛ ዛሬ ለዚህ ሥራ በጣም አስፈላጊ ናቸው ከምንላቸው ነገሮች አንዱም እንኳ ተደርጐላቸው አያውቅም።

ደቀ መዛሙርት የሚያስፈልጋቸው ነገር ቢኖር እንዲማሩ የሚፈለግባቸውን ነገር አብሮአቸው በመሆን የሚያለማምዳቸው መምህር ነበር። ወንጌል ስርጭት በመንፈስ ብሎም በተግባር በመካከላቸው ነበር። እርሱን እያዩ፣ ሁሉ ነገር ምን እንደ ሆነ ተማሩ። በሁሉ የኅብረተሰብ ክፍል ውስጥ የተፈጠረውን ፍላጎትና እነርሱንም በወንጌል ለመድረስ ተገቢ የሆነውን መንገድ



እንዲያስተውሉ ረዳቸው። እንዴት ባለ መንገድ ሰዎችን ወደ ራሱ እንደሚስብ፣ እንዴት አድርጎም መተማመን እንደሚያሳድርባቸውና እምነታቸውን እንደሚያነሣሣ፣ እንዴት አድርጎ የደኅንነትን መንገድ እንደሚያመለክታቸውና እንዴት ወደ ውሳኔም እንደሚጠራቸው ተመለከቱ። በሁሉም ዓይነት ሁኔታዎች በሁሉም ዓይነት ሰዎች ዘንድ፣ ማለትም በኃብታሙና በደኃው፣ በጤነኛውና በበሽተኛው፣ በወዳጆቹና በጠላቶቹ ሁሉ መካከል ወደ ደኅንነት መንገድ ሰዎችን የሚማርከው ጌታ ሥራውን ሲሠራ ተመለከቱት። የሥራ ድርሻው በሠራተኞች መሰብሰቢያ ክፍል ባለው ጥቁር ሰሌዳ ላይ ወይም «ራሳችሁ ሞክሩት» በሚለው የመመሪያ መጽሐፍ ላይ ተጽፎ አልተቀመጠም። ዘዴው እጅግ እውነተኛና በቀላሉ ሊተገበር የሚችል ዘዴ ነበር።

## ሁል ጊዜ በትምህርት ገበታ ላይ

ግለሰቦችንም ሆነ ሕዝቡን በሚቀርብበት ወቅት ይህንኑ አሠራር ይጠቀም ነበር። ደቀ መዛሙርት የሚያደርገውን ለማየትም ሆነ የሚናገረውን ለመስማት ሁል ጊዜ አብረውት ነበሩ። ከአሠራሩ አንድ ያልገባቸው ነገር ካለ ከእነርሱ የሚጠብቀው ግልጽ እንዲያደርግላቸው መምህሩን መጠየቅ ብቻ ነበር። ለምሳሌ፣ ኢየሱስ ስለ ዘሪው ታሪክ «ለእጅግ ብዙ ሰዎች» (ማር. 4:1ን ከማቴ. 13: 1-9፤ ሉቃ. 8:4-8 ጋር አነጻጽሩ) ከተናገረ በኋላ፣ ስለ ምሳሌው ጠየቁት (ሉቃ. 8:9ን ከማር. 4:10፤ ማቴ. 13:10 ጋር አነጻጽሩ)። ኢየሱስም በተናገረው ምሳሌ ላይ ምሳሌዎቹ የሚወክሉትንና ትርጓሜአቸውን አንድ በአንድ ያብራራላቸው ነበር። በእርግጥ፣ ከተጻፈው ጽሑፍ መረዳት የምንችለው፣ ለሕዝቡ የመጀመሪያውን ትምህርት ለመስጠት ከወሰደበት ጊዜ ይልቅ ምሳሌውን ያብራራበት ጊዜ በሦስት እጥፍ ይበልጣል (ማቴ. 13:10-

23፤ ማር. 4:10-25፤ ሉቃ. 8:9-18)::

ደቀ መዛሙርት ግራ መጋባታቸውን አምነው ላለመቀበል በሚጥሩ ጊዜ ደግሞ፣ ኢየሱስ ያለማንም ጥያቄ በእራሱ ተነሣሽነት ነገሮችን ያብራራላቸው ነበር:: የባለጠጋው ጎበዝ ታሪክ ለዚህ ጥሩ ማስረጃ ሆኖ ሊቀርብ ይችላል:: ኢየሱስ ከወትሮው ይልቅ ኮስተር ብሎ ካነጋገረውና ይህም ባለጠጋ ጎበዝ ከእግዚአብሔር መንግሥት ይልቅ ኃብቱን ይወድ ስለ ነበር እያዘነ ከሄደ በኋላ፣ ወደ ደቀ መዛሙርቱ ዘወር ብሎ:- «ለባለጠጋ ወደ መንግሥተ ሰማያት መግባት ጭንቅ ነው» (ማቴ. 19:23፤ ማር. 10:23፤ ሉቃ. 18:24) አላቸው:: «ደቀ መዛሙርቱም እነዚህን ቃሎች አደነቁ» (ማር. 10:24):: ይህም ኢየሱስ ለምን ይህንን ጥሩ የሥነ ምግባር ሰው በዚህ መልኩ እንዳስተናገደው ወደሚያብራራበት ረጅም ውይይት ይዘአቸው ገባ:: በዚያውም አጋጣሚውን በመጠቀም ይህ መርሕ በእነርሱም እምነት ላይ ያለውን ተግባራዊ ሊሆን የሚችልበትን መንገድ አሳያቸው (ማር. 10:24-31፤ ማቴ. 19:24-20:16፤ ሉቃ. 18:25-30)::

## ሊተኮርበት የሚገባ መርሕ

እዚህ ላይ ኢየሱስ የተጠቀመው ዘዴ ከተከታታይ ስብከት በላይ የሆነ በዓላማ የተዘጋጀ ትምህርትም ነበረ:: ትምህርቱ ተጽዕኖ ያሳድር የነበረበትም ምሥጢሩ ይሄው ነበር:: በመጀመሪያ በገዛ ሕይወቱ ያላሳየውን ነገር ማንንም ይህን አድርግ ወይም እንዲህ ሁን ብሎ አያውቅም:: በራሱ ሕይወት በመተግበር ነገሩ በቀላሉ መፈጸም መቻሉን ማስረገጥ ብቻም ሳይሆን፣ በተልዕኮው ውስጥ ያለውን ተገቢ ቦታ ያረጋግጣል:: ሁልጊዜ ያለማቋረጥ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ስለ ነበር ይህንን ማድረግ ችሏል:: የሥልጠና ክፍለ ጊዜያቱ ተሰተንጉለው አያውቁም:: እያንዳንዱ ያደረገውም



ሆነ የተናገረው ነገር በግል ሕይወቱ ሲተገበር የታየ ተጨባጭ ትምህርት ነበር:: ደቀ መዛሙርቱ ይህን ሁሉ እያስተዋሉ አብረውት ስለ ነበሩ፣ በእያንዳንዷ ቀንና በእያንዳንዷ ቅጽበት በተግባር የሚታይን ትምህርት ይማሩ ነበር::

ከዚህ በተሻለ መልኩ እንዴት መማር ይቻል ነበር? ከልባችን የሆነን ነገር ለሰዎች መንገር ጥሩ ነው፤ በተግባር ማሳየቱ ደግሞ ከሁሉም የተሻለ ነው:: ሰዎች ከማብራሪያ ይልቅ ሲተገበር ማየትን ይፈልጋሉ::

## መርሑ ዛሬ እንዴት ይተገበራል?

ወደ ማጠቃለያው ስንመጣ፣ ሰዎችን ማሠልጠን የምንፈልግ እኛ ክርስቶስን እንደምንከተል (1ኛ ቆሮ. 11:1)፣ ሰዎች እኛን እንዲከተሉ ለማድረግ መዘጋጀት ይኖርብናል:: እኛ ምሳሌዎች ነን (ፊልጵ. 3:17፤ 1ኛ ተሰ. 2:7-8፤ 2ኛ ጢሞ. 1:13):: በእኛ ውስጥ ያዩትንና ከእኛም የሰሙትን ያንኑ ያደርጋሉ (ፊልጵ. 4:9) እንዲህ ያለው አመራር ሁልጊዜ አብረውን በሚሆኑት ላይ የአኗኗር ዘይቤአችንን ቀስ በቀስ ለማስረጽ ያስችላል::

ይህንን እውነት ወደ ሕይወታችን ልናስገባው ይገባል:: ለምናሠለጥናቸው ሰዎች መንገዱን ለማሳየት የተቀበልነውን የግል ኃላፊነት ያለ አንዳች ማፈግፈግና ያለ አንዳች ቸልተኝነት ልንወጣው ይገባል:: ይህም መገለጥ የሕይወትን ጥልቅ የሆኑ እውነቶች ግልጽ በሆነ መልኩ በተግባር ማሳየትን የሚያካትት ሊሆን ይገባል:: ይህ እንግዲህ የጌታ ዘዴ ነው፣ እናም የእርሱን ሥራ ለመሥራት ይችሉ ዘንድ ሌሎችን ለማሠልጠን ከዚህ ሌላ ብቁ የሆነ ዘዴ የለም::

በእርግጥ፣ ይህ እኛን የሚያጋልጠን ይሆናል:: እኛ እንደ

ጌታችን ፍጹማን አይደለንም:: እናም እነዚያ ሕይወታችንን የምናካፍላቸው ሰዎች ያሉብንን ብዙ እንከኖች ይመለከታሉ:: በዚህ ጊዜ ግን መንገዳችን ልክ እንዳልሆነ ስንረዳ ኃጢአታችንን ለመናዘዝ ያለንን ዝግጁነት እንዲመለከቱ ልናደርግ ይገባል:: ያስቀመየምናቸውንም ይቅርታ ስንጠይቅ እንዲሰሙን እናድርግ:: የእኛ ድካም ክርስቶስን ለመከተል ባላቸው ቅን ልቦና ላይ አብርቶ በደቀ መዝሙርነታቸው ላይ ችግር ሊፈጥር አይገባም::

እንደሚታወቀው፣ እውቀት ብቻውን በቂ አይደለም:: በተግባር የሚገለጽበት ጊዜ ደግሞ ይመጣል:: በዚህ ዕድል ለመጠቀም የሚኖረንን አጋጣሚ ቸል ማለት ግን በመማር ሒደት የተገኘውን ነገር ሁሉ ዋጋ ያሳጣዋል:: ከተግባር ጋር ያልተገናዘበ እውቀት ለምናገኘው ቀጣይ እውነት እንደ መሰናከያ ድንጋይ ሊሆን ይችላል:: ይህንንም ነገር ከጌታ የበለጠ የተረዳው ሰው አልነበረም:: አንድ ሥራ ይሠሩ ዘንድ ሰዎችን ያሠለጥን ነበር:: ከዚያ ለመጀመር የሚያስችላቸውን ያህል እውቀት እንዳገኙ ሲረዳ፣ ይህንን እውቀት መተግበር መቻል አለመቻላቸውን ማየት ነበረበት:: የዚህ መርሕ መተግበር በጣም ጕልቶ የተነገረ በመሆኑ በሠለጠኑና በመንፈሳዊ ነገራቸው ንቁ በሆኑ ሰዎች ለመውረስ የተጠቀመበት ሌላው የስልቱ አካል ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል::



*ሰዎችን አጥማጆች እንድትሆኑ አደርጋችኋለሁ*

*ማቴዎስ 4:19*

6

# ውክልና

## የሚሠሩትን ሰጣቸው

የኢየሱስ አገልግሎት ሁልጊዜ ደቀ መዛሙርቱ የእርሱን ቦታ ተክተውና ነፃ አውጪ የሆነውን ወንጌል ይዘው ወደ ዓለም ለሚወጡበት ለዚያ ጊዜ በማዘጋጀት ላይ ያተኮረ ነበር:: ይህ ዕቅድ እየተከተሉት በሄዱ ቁጥር ይበልጥ ግልጽ እየሆነ ይመጣ ነበር::

ኢየሱስ ይህንን ለደቀ መዛሙርቱ የገለጸበት ትዕግሥቱ እነርሱ ይማሩ ዘንድ በውስጡ የነበረውን መሻት ያመለክታል:: ተግባራዊ አድርገውት ለማየት በሚፈልገው በማንኛውም ነገር ላይ አይቸኩልም ነበር:: ለደቀ መዛሙርቱ ባቀረበው በመጀመሪያ የተከተሉኝ ጥሪው ላይ ወንጌልን ለዓለም ለማሰራጨት ስለ መውጣት አላነሣም:: ሆኖም የመጀመሪያ ዕቅዱ ግን ወንጌልን ለማሰራጨት እንዲወጡ ማድረግ ነበር:: የሚሠሩትን ሥራና እንዴት እንደሚሠሩት ከመንገሩ በፊት የተጠቀመው ስልት ከእግዚአብሔር ጋር ተጨባጭ ወደ ሆነ ልምምድ ውስጥ እንዲገቡ ማድረግ ነበር::

በሌላ መልኩ ደግሞ፣ እነርሱ በራሳቸው ተነሣሽነት ስለ እምነታቸው ለሌሎች መመስከር መቻላቸውን አልነቀፈባቸውም:: እንዲያውም፣ ሌሎች እነርሱ ያገኙትን እንዲያውቁ ማድረጋቸው ያስደሰተው ይመስላል:: እንድርያስ ጴጥሮስን፣ ፊልጶስም ናትናኤልን ይዘው መጡ፣ ማቴዎስም በቤቱ በነበረው ግብዣ

ጓደኞቹን ጋበዛቸው:: ኢየሱስም እነዚህን አዳዲስ እንግዶች በደስታ ነበረ የተቀበላቸው:: ከዚህ በተጨማሪም፣ በብዙ የተለያዩ አጋጣሚዎች ኢየሱስ፣ በአገልግሎቱ የተጠቀሙ ሰዎች የሆነላቸውን ለሌሎች እንዲናገሩ ያሳሰባቸው እንደ ነበር ልናስተውል ይገባል:: ይሁን እንጂ፣ ቀደም ካሉት ክስተቶች በማንኛውም የሕይወታቸው ዋነኛ ዓላማ መመስከር መሆን እንዳለበት በግልጽ የተሰጣቸው ትእዛዝ አልነበረም::

ኢየሱስ በተለያየ መንገድ በሥራው እንዲያግዙት ደቀ መዛሙርቱን ያሰማራቸው ነበር:: ያግዙት ከነበሩትም ሁኔታዎች ለምሳሌ፣ የሚበሉትን ምግብ ፈልገው የማምጣትና እየተከተሉት ሳሉ ቡድኑ የሚያርፍበትን ስፍራ ማዘጋጀትን የመሳሰሉት ተግባሮች ነበሩ:: በእርሱ መልእክት ልባቸው የተነካ አንዳንድ ሰዎችንም እንዲያጠምቁ ያደርጋቸው ነበር (ዮሐ. 4:2):: ከዚህ ውጪ ግን፣ ወንጌላትን ስንመለከት የሚያስገርመው ደቀ መዛሙርቱ ከዓመት ወይንም ከዚያም በላይ ኢየሱስ የሚሠራውን ከማየት ያለፈ ሌላ ሥራ እንዳልነበራቸው ነው:: በሚሠራው ሥራ ርእዩን በፊታቸው ያስቀምጥ ነበር፣ እናም አራቱን ዓሣ አጥማጆች በድጋሚ ሲጠራቸው እርሱን በመከተል ሰዎችን አጥማጆች እንደሚሆኑ አስታውሶአቸው ነበር (ማር. 1:17፤ ማቴ. 4:19፤ ሉቃ. 5:10):: እነርሱ ግን ለነገሩ ትኩረት የሰጡት አይመስሉም ነበር:: ለነገሩ ለአገልግሎት ከተሾሙ ከጥቂት ወራት በኋላ (ማር. 3:14-19፤ ሉቃ. 6:13-16) በራሳቸው ተነሣሽነት አንዳችም የወንጌል ስርጭት እንዳከናወኑ የሚያሳይ ምንም መረጃ አልነበረም:: ይህ ነገር እኛን ለሚከተሉን አዲስ አማኞች ሊኖረን የሚገባውን ትዕግሥት የሚያሳየን ነው::

ነገር ግን ኢየሱስ ሦስተኛውን አጠቃላይ የገሊላ ጉብኝት



በሚጀምርበት ጊዜ (ማር. 6:6፤ ማቴ. 9:35)፣ ያለምንም ጥርጥር ደቀ መዛሙርቱ ቀጥተኛ በሆነ መልኩ ይበልጥ በሥራው ሊካፈሉ እንደሚችሉ አሰበ:: ቢያንስ ለመጀመር የሚያስችላቸውን ያህል ሲያዩ ቆይተዋል:: አሁን ደግሞ መምህራቸው ሲያደርግ ያዩትን በተግባር ሊያውሉት ፈለጉ:: ስለዚህ (አሥራ ሁለቱንም ወደ እርሱ ጠራ... ይልካቸው ጀመር» (ማር. 6:7፤ ማቴ. 10:5፤ ሉቃ. 9:1-2):: እናት ንስር ጫጩቷን ከጎጆዋ ገፍታ በማስወጣት መብረር እንደምታስተምራት፣ ኢየሱስም ደቀ መዛሙርቱ ክንፋቸውን እንዲያፍታቱ ወደ ዓለም ገፍቶ አስወጣቸው::

## *መመሪያዎችን መስጠት*

ይሁን እንጂ፣ እንዲሄዱ ከማሰማራቱ በፊት ኢየሱስ ለአገልግሎታቸው የሚሆኑ አንዳንድ መመሪያዎችን ሰጣቸው:: በዚህ ጊዜ ያላቸው ነገር ለዚህ ጥናት በጣም አስፈላጊ ነገር ነው፣ ምክንያቱም እስከዚያን ጊዜ ሲያስተምራቸው የነበሩትን ነገሮች ሁሉ እዚህ ላይ በአስተዋጽኦ ደረጃ ግልጽና አጭር በሆነ መልኩ አቅርቦላቸዋል::

በመጀመሪያ ለሕይወታቸው ያለውን ዓለማ በድጋሚ አስረግጦ ነገራቸው:: እንዲሄዱ «የእግዚአብሔርን መንግሥት ወንጌል እንዲሰብኩና ድውዮችንም እንዲፈውሱ» ይጠበቅባቸው ነበር (ሉቃ. 9:1-2ን ከማቴ. 10:1፤ ማር. 6:7 ጋር አነጻጽር):: በዚህ ተልዕኮ ውስጥ ምንም አዲስ ነገር ባይኖርም፣ የተሰጣቸውን ኃላፊነት ከፊት ይልቅ ይበልጥ ግልጽ ለማድረግ ግን ጠቅሟል:: ይሁን እንጂ «መንግሥተ ሰማያት ቀርባለች» (ማቴ. 10:7) ከሚለው አወጃ አንጻር አዳዲሶቹ መመሪያዎች ሥራቸው ምን ያህል አንገብጋቢ እንደ ሆነ ያስገነዘበ ነበር:: በተጨማሪም ድውዮችን እንዲፈውሱ ብቻ ሳይሆን፣ ለምጻሞችን አንጹ፣ አጋንንትን አውጡ፣ ሙታንን

አስነሡ (ማቴ. 10:8) የሚሉ ትእዛዛትንም የሚያክልና የተሰጣቸው ሥልጣን እስከ ምን ድረስ እንደ ሆነ በሚገባ የሚያስረዳ ነበር::

ነገር ግን ኢየሱስ እዚህ ላይ አላበቃም:: በመቀጠልም መጀመሪያ ወደ ማን መሄድ እንዳለባቸው ነገራቸው:: «በአሕዛብ መንገድ አትሂዱ፣ ወደ ሳምራውያን ከተማም አትግቡ ይልቅስ የእስራኤል ቤት ወደሚሆኑ ወደ ጠፉት በጎች ሂዱ እንጂ» (ማቴ. 10:5-6):: እዚህ ላይ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ የት ቢሄዱ መልእክታቸውን የሚሰሙ ብዙ ሰዎችን በይበልጥ እንደሚያገኙ የነገራቸው ይመስላል:: የእርሱ አገልግሎት ራሱ በዚሁ መልኩ ነበር:: በእርግጥ ጊዜው እየገፋ ሲሄድ ከዚህ ወጣ ብሎም ይሠራ ነበር:: በባህልም ሆነ በሃይማኖታዊ አቋም ረገድ ይበልጥ የሚመስሉአቸው ወገኖቻቸው ስለሆኑ በእነርሱ አገልግሎት መጀመራቸው የሚጠበቅ ነው:: የሚገርመው ነገር ደግሞ፣ ከጥቂት ወራት በኋላ ሰባዎቹን ሲልካቸው ይህ የቦታ ልዩነት ትእዛዝ በድጋሚ አልተሰጣቸውም:: ምናልባትም ከዚህ ተፈጥሮአዊ ከሆነው ትስስር ባሻገር የክርስቶስ ሊሆኑ የሚገባቸውን ለመጥራት ጊዜው መድረሱን የሚያመላክት ነበር::

የሚያስፈልጋቸውን አቅርቦት በማግኘት በኩልም፣ እግዚአብሔር የሚያስፈልጋቸውን እንደሚሰጣቸው ማመን ነበረባቸው:: እነርሱ ከጌታቸው በነፃ እንደ ተቀበሉ በማስታወስ አገልግሎታቸውን በነፃ እንዲያበረክቱ ተነግሮአቸው ነበር (ማቴ. 10:8):: በዚህ ምክንያት፣ ኢየሱስ አስፈላጊ ያልሆኑ ነገሮችን እና ትርፍ የሆኑ ንብረቶችን በመያዝ በራሳቸው ላይ ሸክም እንዳይጨምሩ አዘዛቸው (ማቴ. 10:9-10፤ ማር. 6:8-9፤ ሉቃ. 9:3):: እነርሱ ለእግዚአብሔር ታማኝ በሆኑ መጠን፣ እግዚአብሔር ደግሞ የሚያስፈልጋቸውን ነገር ሊያደርግላቸው ይተጋል:-



«ለሠራተኛ ምግቡ ይገባዋልና» (ማቴ. 10:10)::

## የጌታን ስልት መከተል

እንዲያውም ኢየሱስ በደቀ መዛሙርቱ የነበረው ዕቅድ በጣም ግልጽ ስለነበረ በደረሱበት በማንኛውም ከተማ ሊቀበላቸው ፈቃደኛ ወደሆነው ሰው ቤት እንዲገቡና፣ በአካባቢው ያላቸውን አገልግሎት እስከ ቀጠሉበት ወቅት በዚያ ቤት እንዲቀመጡ ትእዛዝ ሰጥቶአቸው ነበር:: «በምትገቡባትም በማንኛይቱም ከተማ ወይም መንደር በዚያ የሚገባው ማን እንደ ሆነ በጥንቃቄ መርምሩ እስክትወጡም ድረስ በዚያ ተቀመጡ» (ማቴ. 10:11ን ከማር. 6:10፣ ሉቃ. 9:4 ጋር አነጻጽሩ):: ስለዚህ ደቀ መዛሙርት ትኩረታቸውን ሁሉ ከምንም በላይ እነርሱ ሥራቸውን ጨርሰው ከተመለሱ በኋላ የእነርሱን ሥራ ተከታትሎ ማስፈጸም መቻላቸው እጅግ አስተማማኝ በሆኑ ሰዎች ላይ እንዲያደርጉ ተነግሮአቸዋል:: ይህ ነገር ከምንም በላይ ቅድሚያ ሊሰጠው ይገባ ነበር:: በእርግጥ፣ የሚቀበላቸውና ወደ ቤቱ የሚያስገባቸው አንድም ሰው ባያገኙ፣ በላያቸው ምስክር ይሆንባቸው ዘንድ የጫማቸውን አቧራ እንኳ ሳይቀር አራግፈው ከዚያ እንዲወጡ በግልጽ ታዝዘዋል:: «በፍርድ ቀን ከዚያች ከተማ ይልቅ ለሰዶምና ለገሞራ አገር ይቀልላቸዋል» (ማቴ. 10:14-15፤ ሉቃ. 9:5ን ከማር. 6:11 ጋር አነጻጽር):: ይህም በደረሱበትና ሥራቸውን በሠሩበት አዲስ ስፍራ እነርሱ የሠሩትን ሥራ በቀጣይነት ይዞ መጓዝ የሚያስችል ሁኔታን ማመቻቸትና አገልግሎቱንም ቁልፍ ከሆነ መሪ ጋር ማያያዝ ቀለል አድርገን ልናየው አይገባም:: ጌታ ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ያደረገው ይህንኑ ነበር:: እነርሱም ይህንኑ እንዲያደርጉ ይጠበቅባቸዋል:: በጠቅላላው የወንጌል ስርጭት ዕቅዱ ይህንን መሠረት ያደረገ ነው:: ደቀ መዛሙርት ይህንን መርሕ እንዳይተገብሩ አሻፈረን ያሉባቸው

በታዎች ደግሞ በእርግጥም በራሳቸው ላይ ድቅድቅ ጨለማ እንዲመጣ ፈርደዋል::

## ችግር እንደሚመጣ መጠበቅ

አንዳንድ ሰዎች የደቀ መዛሙርትን አገልግሎት አለመቀበላቸው ሊጠብቁት ስለሚገባ ምላሽ ኢየሱስ የሰጣቸውን ማስጠንቀቂያ የሚያጠናክር ነበር:: «ነገር ግን ወደ ሸንጎ አሳልፈው ይሰጡአችኋል፣ በምኩራቦቻቸውም ይገርፉአችኋልና ከሰዎች ተጠበቁ፣ ለእነርሱና ለአሕዛብም ምስክር እንዲሆን፣ ስለ እኔ ወደ ገዥዎች ወደ ነገሥታትም ትወሰዳላችሁ» (ማቴ. 10:17-18):: ይህ ደግሞ ሊሆን ግድ ነው፣ ምክንያቱም ደቀ መዝሙር ከመምህሩ፣ ባሪያም ከጌታው አይበልጥም (ማቴ. 10:24):: ገርዎች ኢየሱስን ብዔል ዜቡል ብለውታል፣ ቤተሰቦቹማ ከዚህ ያነሰ ስድብ ሊጠብቁ አይገባም (ማቴ. 10:25):: የእርሱ አካሄድ ዓለም ጥበብ ብሎ ከተቀበለው ሥርዓት እጅግ የተቃረነ መሆኑን በድጋሚ መናገር ነው:: ስለዚህ በሰው ሁሉ ዘንድ የተጠሉ ይሆኑ ዘንድ ግድ ነው (ማቴ. 10:22-23):: የሆነ ሆኖ ኢየሱስ ደግሞ «አትፍሩ» ብሎአቸዋል:: እግዚአብሔር ፈጽሞ አይተዋቸውም፣ ምስክርነታቸውም ሕይወታቸውን አደጋ ላይ የሚጥል ቢሆን እንኳን፣ መንፈስ ቅዱስ በዚያች ቅጽበት በመድረስ ድንገተኛውን ሁኔታ እንዲቋቋሙ ይረዳቸዋል (ማቴ. 10:20-21):: ምንም ዓይነት መከራ ቢደርስባቸው፣ ኢየሱስ ስለ እርሱ በሰው ፊት ለመሰከረ በላይ በሰማይ በአባቱ ፊት እንደሚመሰክርለት ደግሞ እንኳን ቃል ገብቶላቸዋል (ማቴ. 10:32)::

ኢየሱስ ተከታዮቹ የጠላትን ኃይልም ሆነ በአንዳንድ ራስ ወዳድ ሰዎች ነፃ በሚያወጣው ወንጌሉ ላይ የሚደረገውን ተቃውሞ ዝቅተኛ የሆነ ግምት እንዳይሰጡ ያደረገበትን እውነተኛ መንገድ



አንድ ሰው ሲያስተውል መገረሙ አይቀርም:: ደቀ መዛሙርት ችግር እንዲገጥማቸው የሚፈልጉ አልነበሩም:: እንዲያውም "እንደ እባብ ልባሞች እንደ ርግብም የዋሆች ሁኑ" (ማቴ. 10:16) በማለት የሰጣቸው ምክር ጠንቃቆችና ዘዴኞች መሆን እንደሚያስፈልጋቸው የሚያስገነዝብ ነበር:: ሆኖም ምንም ያህል ተጠንቅቀው በታማኝነት ወንጌልን ቢሰብኩም፣ ዓለም በደስታ እንደማይቀበላቸው ግን የታወቀ ነገር ነበር:: የተላኩት «እንደ በጎች በተኩላዎች መካከል» ነበር (ማቴ. 10:16)::

## የሚለያይ ወንጌል

ኢየሱስ የወንጌል ግብዣ የማያሻማና የማያመቻምች ባሕሪ እንዳለው ለደቀ መዛሙርቱ መንገሩ ሊስተዋል የሚገባው ነው:: ከኃጢአት ጋር ምንም ዓይነት ማመቻመች ሊኖር አይችልም:: ስለሆነም ኃጢአትን እያደረገ ከእግዚአብሔር ጋር በድርድር ተስማምቶ መኖር የሚቻል የሚመስለው ሁሉ በዚህ ስብከታቸው መረበሹ የማይቀር ነው:: ደቀ መዛሙርት የጊዜውን ነባራዊ ሁኔታ ፍጹም ሰላማዊ በሆነ መልኩ ለማቆየት የሚጥሩ የመንግሥት መልእክተኞች አልነበሩም:: ይልቁንም፣ ኢየሱስ፣ «በምድር ላይ ሰላምን ለማምጣት የመጣሁ አይምሰላችሁ ሰይፍን እንጂ ሰላምን ለማምጣት አልመጣሁም:: ሰውን ከአባቱ፣ ሴት ልጅንም ከእናትዋ፣ ምራትንም ከአማትዋ እለያይ ዘንድ መጥቻለሁና፤ ለሰውም ቤተ ሰዎቹ ጠላቶች ይሆኑበታል:: ከእኔ ይልቅ አባቱን ወይንም እናቱን የሚወድ ለእኔ ሊሆን አይገባውም» ከእኔ ይልቅ ወንድ ልጁን ወይም ሴት ልጁን የሚወድ ለእኔ ሊሆን አይገባውም፤ መስቀሉንም የማይዝ በኋላዬም የማይከተለኝ ለእኔ ሊሆን አይገባውም" (ማቴ. 10:34-38) ነበር ያለው:: ደቀ መዛሙርት ይህን ከማለቱ በፊት ስለ ሥራቸው ቅለት እያሰቡ ከነበረ፣ በእርግጠኝነት ከዚህ በኋላ

እንደዚያ ያለውን አስተሳሰባቸውን ያስወግዱታል። ለውጥን በውስጡ የያዘውን ወንጌልን ይዘው ወደፊት ይገሰግሱ ነበር። ለሚታዘዙትም ሰዎች በእነርሱና በማኅበረሰባቸው ውስጥ ታላቅ የሆነን ለውጥ ያመጣል።

## ከጌታ ጋር አንድ መሆን

በእነዚህ ሁሉ መመሪያዎች ውስጥ ኢየሱስ ሊያስቀምጥ የፈለገው ነገር የደቀ መዛሙርቱ ተልዕኮ በመርህ ደረጃም ሆነ በስልት ረገድ ከእርሱ ተልእኮ እንደማይለይ ነው። የእርሱንም ሥራ ለመሥራት እንዲችሉ የገዛ ኃይሉንና ሥልጣኑን ለእነርሱ በመስጠት ነበር የጀመረው (ማር. 6:7፤ ማቴ. 10:1፣ ሉቃ. 9:1)። በመጨረሻም እነርሱ ይሠሩት የነበሩት እርሱ ራሱ ቢሠራ ኖሮ ይሆን የነበረውን ያህል እንደ ሆነ አስረግጦ ነገራቸው፦ እናንተን የሚቀበል እኔን ይቀበላል እናንተንም የሚቀበል የላከኝን ይቀበላል (ማቴ. 10:40፣ ዮሐ. 13:20)። ይህንን ማንነት እስቲ አስቡት! ደቀ መዛሙርት በእያንዳንዷ ጉዞአቸው የክርስቶስ ትክክለኛ ወኪሎች ነበሩ። ይህ ትስስር እጅግ ግልጽ ከመሆኑ የተነሣ «ከታናናሾቹ ለአንዱ ቀዝቃዛ ጽዋ ውኃ በደቀ መዝሙር ስም የሚያጠጣ ...ዋጋው አይጠፋበትም» (ማቴ. 10:42)።

## ሁለት በሁለት

ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ የሰጣቸው መመሪያዎች እነዚህ ነበሩ። ወደ ሥራ ከመውጣታቸው በፊት ግን ሁለት ሁለት ሆነው እንዲያያዙ አደረጋቸው። ደቀ መዛሙርት በመንገዳቸው ላይ ጓደኛ ይኖራቸው ዘንድ የነበራቸውን ፍላጐት ይህ ዕቅድ ያለ ጥርጥር አሟልቷል። አብረው በመሆናቸው እርስ በርስ ሊረዳዱ ብሎም ብዙ ጊዜ ሊፈጠር እንደሚችለው ሁሉ አስቸጋሪ ነገር በመካከላቸው ሊፈጠር እርስ በርስ ሊረዳዱና ሊጽናኑ ይችላሉ። ይህ ደግሞ



ኢየሱስ ለኅብረት የሚሰጠውን ዓይነተኛ ትኩረት የሚያሳይ ነው።

«ወጥተውም ወንጌልን እየሰበኩና በየስፍራው ሁሉ እየፈወሱ በየመንደሩ ያልፉ ነበር» (ሉቃ. 9:6ን ከማር. 6:12 ጋር አነጻጽር)። ትንሹ የደቀ መዛሙርት ቡድን እንግዲህ በስተመጨረሻ በንቃት የሚከናወነውን የክርስቶስን አገልግሎት ራሳቸውን ችለው ማካሄድ ጀመሩ።

ይህ መሆኑ ግን ኢየሱስ የገዛ ሥራውን ችላ እንዲል ሰበብ አልሆነውም። እርሱ ሊያደርግ የማይፈልገውን ነገር ማንንም አድርግ ብሎ አያውቅም። ስለሆነም ደቀ መዛሙርት ለሥራ ሲወጡ፣ ጌታም እንዲሁ በየከተሞቻቸው ሊያስተምርና ሊሰብክ በዚያ አለፈ (ማቴ. 11:1)።

## የሰባዎቹ ተልዕኮ

ይህ ከሆነ ከጥቂት ወራት በኋላ «ሌሎቹን ሰባዓ» ለጌታቸው እንዲመሰክሩ ሁለት ሁለት እያደረገ ላካቸው (ሉቃ. 10:1)። እነዚህ ሌላዎቹ ደቀ መዛሙርት እነማን እንደ ሆኑ በእርግጠኝነት የታወቀ ነገር ባይኖርም፣ አሥራ ሁለቱ በዚህ ተካትተው እንደ ነበሩ የሚያመለክቱ ነገሮች ነበሩ። የቁጥራቸው መጨመር በራሱ በተወሰነ ደረጃ ለክርስቶስ መመስከር የአሥራ ሁለቱ አገልግሎት እየሰፋ እንደ መጣ ያሳያል።

ለዚህ ለትልቁ ቡድን የተሰጠው መመሪያ ከዚህ ቀደም ለአሥራ ሁለቱ ከተሰጣቸው ጋር ተመሳሳይ ነበር (ሉቃ. 10:2-16)። በዚህ በአዲሱ ተልዕኮ ላይ የተጨመረ ነገር ቢኖር «እርሱ ሊሄድበት ወዳለው ከተማና ስፍራ ሁሉ» (ሉቃ. 10:1) እንደሚሄዱ የሰጣቸው ማሳሰቢያ ነበር። በመሆኑም እዚህ ላይ ደቀ መዛሙርት ለጌታቸው ሁኔታዎችን በማመቻቸት እንደ መንገድ ጠራጊ ሆነው ያገለግሉት ነበር። የዚህን ዝርዝር አተገባበር ወደ ውስጣቸው

ያሰረጸው ከጥቂት ሳምንታት በፊት ወደ ሰማርያ ባደረጉት ጉዞ ላይ ነበር (ሉቃ. 9:52)። ስለዚህ ነገሩ ቀደም ሲል ያላወቁት ጉዳይ ባለ መሆኑ እንግዳ አልሆነባቸውም። የመምህራቸው የወንጌል ስርጭት ስልቶች እንደ ሆኑ የተማሯቸውን ሁሉ በተግባር ማዋል እንዳለባቸው በድጋሚ የሚያሳይ ነበር።

## ከትንሣኤ በኋላ የተሰጡ ትእዛዛት

ኢየሱስ የወንጌልን ሥራ በኃላፊነት እንዲሠሩ የመስጠቱ መርሕ ከስቅለቱና ከትንሣኤው በኋላ ልክ ወደ መንግሥተ ሰማይ ከመመለሱ በፊት በተጠናቀቀ ሁኔታ በተጨባጭ ተገልጾ ነበር። ደቀ መዛሙርቱን ባገኘባቸው ቢያንስ አራት የተለያዩ አጋጣሚዎች እንዲሄዱና ሥራውን እንዲሠሩ ነግሯቸው ነበር። ቶማስ ባልነበረበት በዚያ በመጀመሪያው የፋሲካ ምሽት በላይኛው ክፍል ተሰብስበው ሳለ ለመጀመሪያ ጊዜ ለደቀ መዛሙርት ተነግሯቸው ነበር። ለተደናገጡት ደቀ መዛሙርት በሚስማር የተወጉትን እጆቹንና እግሮቹን ካሳያቸውና (ሉቃ. 24:38-40)፣ አብሯቸውም ማዕድ ከቆረሰ በኋላ (ሉቃ. 24:41-43)፣ እንዲህ አላቸው፣ «ሰላም ለእናንተ ይሁን አብ እንደ ላከኝ እኔ ደግሞ እልካችኋለሁ» (ዮሐ. 20:21)፣ ይህንንም በተናገረበት ወቅት ሥራውን ለመሥራት የሚያስችላቸው የመንፈስ ቅዱስ ሥልጣንና ቃል ኪዳን እንደ ተሰጣቸው በድጋሚ አረጋገጠላቸው።

ከጥቂት ጊዜ በኋላም በጥብርያዶስ ባሕር ዳርቻ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ቁርስ እየበሉ በነበሩበት ጊዜ፣ ለጴጥሮስ ሦስት ጊዜ በጎቹን እንዲመግብ አደራ አለው (ዮሐ. 21:15-17)። ይህ ማስጠንቀቂያ ለትልቁ ዓሣ አጥማጅ ለመምህሩ ያለውን ፍቅር የሚገልጥበት ማስረጃው ሆኖ ነበር የተወሰደው።



በገሊላ ተራራ ላይ ደግሞ ለአሥራ ሁለቱ ብቻ ሳይሆን በዚያን ወቅት ከአምስት መቶ ለሚበዙት ለጠቅላላው የቤተ ክርስቲያን አባላት (1ኛ ቆሮ. 15:6) ታላቁን ተልዕኮውን ሰጠ (ማቴ. 28:16)። ዓለምን ለመድረስ የሚያስችለውን ስልት በይፋ እያወጀ ነበር «ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ። እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፣ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጉአቸው፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ?» (ማቴ. 28:18-20ን ከማር. 16:15-18 ጋር አነጻጽር)።

በመጨረሻም፣ ወደ አባቱ ከማረጉ በፊት፣ እርሱ ከእነርሱ ጋር ሳለ ሊፈጸም ስላለው ነገር በመግለጽ ለመጨረሻ ጊዜ በድጋሚ ሁሉን ነገር ለደቀ መዛሙርቱ ነገራቸው (ሉቃ. 24:44-45)። ሥቃዩና ሞቱ፣ በሦስተኛውም ቀን ሞትን ድል አድርጎ መነሣቱ ሁሉ በታቀደው መሠረት ነበር የሆነው (ሉቃ. 24:46)። ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ የነገራቸው ሌላው ነገር «በስሙም ንስሐና የኃጢአት ስርየት ከኢየሩሳሌም ጀምሮ ለአሕዛብ ሁሉ» (ሉቃ. 24:47) እንደሚሰበክ ነበር። ይህም መለኮታዊ ዓላማ ይፈጸም ዘንድ ደቀ መዛሙርቱ ከመምህራቸው የማይተናነስ ድርሻ ነበራቸው። እነርሱ መልካሙን ዜና የሚያውጁ ሥጋ ለባሽ መሣሪያዎቹ ሲሆኑ፣ መንፈስ ቅዱስ ደግሞ ተልዕኮአቸውን የሚያግዝ የእግዚአብሔር ኃይል ሆኖ ያገለግላቸዋል። «ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፣ በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳር ድረስም ምስክሮቼ ትሆናላችሁ» (የሐዋ. 1:8ን ከሉቃ. 24:48-49 ጋር አነጻጽር)።

## መርሑ ግልጽ ነው

በግልጽ ማየት እንደሚቻለው ኢየሱስ የወንጌል ስርጭት አገልግሎትን ከሰው አድናቆትን ለማትረፍ ወይም ለሰው እንዲመች አድርጐ አልተወውም:: ለደቀ መዛሙርቱ በደቀ መዝሙርነት ጅማሬያቸው ላይ በብዙ ግፊት የተቀበሉት በኋላ ግን ቀስ በቀስ በተከተሉት ቁጥር ለአእምሮአቸው የበራላቸው፣ በመጨረሻም ያለምንም ማቅማማት በግልጽ የተቀመጠ ቁርጥ ትእዛዝ ነው:: ኢየሱስ ያን ያህል ርቀት አብሮት የተጓዘ ማንም ከዚህ ማጠቃለያ ውጪ አይሆንም:: ያኔ እንዲያ ነበር፤ ዛሬም ያው ነው::

ክርስቲያን ደቀ መዛሙርት ወንዶችና ሴቶች ዛሬም ጌታ ሕይወቱን ለሰጠበትና ለተላከበት ተመሳሳይ የወንጌል ሥራ ተልከዋል:: ወንጌል ስርጭት በሕይወታችን እንደ አንድ አማራጭ ተቀጥላ የምንወስደው ነገር አይደለም:: እንድንሆንና እንድናደርግ ለተጠራንበት ነገር ሁሉ እንደ ልባችን ትርታ ነው:: በክርስቶስ ስም ለሚደረግ ለማንኛውም ዓይነት ሥራ ትርጉም የሚሰጥ የቤተ ክርስቲያን ተልዕኮም ነው:: በዚህ ዓላማ ላይ ተነጣጥሮ የተደረገና የተባለ ማንኛውም ዓይነት አገልግሎት የእግዚአብሔርን ነፃ የማውጣት ዓላማ በክብር ይፈጽማል:: በትምህርት ማዕከሎች፣ በማኅበራዊ እንቅስቃሴዎች፣ ሆስፒታሎች በክርስቶስ ስም የሚደረጉ ማንኛውም ዓይነት የቤተ ክርስቲያን ስብሰባዎች ከሆነ ትክክል የሚሆነውና ትርጉም የሚሰጡት ይህን ተልእኮ ለመፈጸም በቂ መሠረት አላቸው::

## መርሑ ዛሬ ሲተገበር

ነገር ግን ይህንን በአሳብ ደረጃ ብቻ መያዙ በቂ አይደለም:: አዳኙን ጌታ በመከተል ላይ ያሉት ተጨባጭ በሆነ መልኩ ሊገልጡት



ይገባል:: ይህ መደረጉን እርግጠኛ የምንሆንበት የተሻለው መንገድ ደግሞ ሥራውን በተግባር እንዲገልጽ መመሪያ መስጠትና ተግባራዊ እንደሚሆንም መጠበቅ ነው:: ይህ ዓይነቱ አሠራር ሰዎች ሥራውን እንዲጀምሩ ያደርጋቸዋል፣ እናም የሚሠሩትን ሥራ እንዴት እንደሚሠሩት በአስተማሪያቸው ሕይወት አይተው ከሆነ ሥራው የማይጠናቀቅበት ምንም ምክንያት አይኖርም:: ቤተ ክርስቲያን ይህንን ትምህርት ዋና ቁም ነገሯ አድርጋ ወስዳ ኮስተር ብላ የወንጌልን ሥራም በተግባር ስታውል፣ ተቀምጠው ተመልካች የነበሩት ሁሉ ተነሥተው ለእግዚአብሔር ሥራ መሮጥ ይጀምራሉ::

ይሁን እንጂ፣ አንድ ሰው ወይም አንዲት ሴት ሥራውን ጀመረ ወይም ጀመረች ማለት ይቀጥላል ወይም ትቀጥላለች ማለት ላይሆን ይችላል:: ሰው የነበረበትን ፍዘት አሸንፎ ከወጣ በኋላ ወደፊት መገስገሱና በትክክለኛው ጎዳና ላይ መጓዝ መቀጠሉ አስፈላጊ ነገር ነው:: ኢየሱስ ለተከታዮቹ በተለይም ወደ መጀመሪያው አካባቢ የሰጠው መመሪያ ከሥልጠናው ትምህርት ቤት ማንም እንዳይወጣ የሚያዝ ነበር:: ለምረቃ ዝግጁ ከመሆናቸው በፊት ሊማሩት የሚገባቸው ብዙ ነገር ነበር:: ያም ጊዜ እስኪመጣ ድረስ ከእርሱ የግል መመሪያ ላይ ፈቀቅ እንዲሉ አይፈልግም ነበር:: በዚህ ረገድ የነበረው ትኩረት ግልጽ ነበር:: በተግባር ለማዋል የተጠቀመበት ዘዴ እጅግ ጉልቶ የወጣ በመሆኑ የፍጻሜውን ድል ማምጣት በሚያስችለው ስልት ውስጥ ሌላ ቀጣይ ደረጃ ተደርጎ ተወስዷል::

*ገና አልተመለከታችሁምን? አላስተዋላችሁምን?*
*ማርቆስ 8:17*

# 7

# ቁጥጥር

## ሥራቸውን ይከታተል ነበር

ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ ተዘዋውረው ካገለገሉ በኋላ ከእርሱ ጋር ተገናኝተው ስለ ሥራቸው ሪፖርት እንዲያቀርቡና እርሱ ያደርግ እንደ ነበር በማድረጋቸው የእርሱ በሆነው አገልግሎት ያገኙትን በረከት እንዲያካፍሉት ያደርግ ነበር:: ከዚህ የተነሣም፣ ትምህርቱ መመሪያና የሥራ ኃላፊነትን መስጠት የሚፈራረቁበት ነበር ማለት ይቻላል:: አብሯቸው በሚሆንበት ጊዜ ሁሉ ቀደም ሲል ተፈጥረው የነበሩ ሁኔታዎች ለምን እንደ ተፈጠሩ ይገባቸው ዘንድ ይረዳቸዋል ወይም በቀጣይ ለሚሆኑ አዳዲስ ክስተቶች ያዘጋጃቸዋል:: ጥያቄው፣ ማብራሪያው፣ ማስጠንቀቂያው እና ተግሣጹ ሁሉ የእርሱን ዓለምን በወንጌል የመድረስ ሥራ ማስፈጸም ይችሉ ዘንድ ማወቅ የሚገባቸውን ሁሉ እንዲያውቁ በሚል ነበር የሚያደርገው::

ስለሆነም፣ አሥራ ሁለቱን ወደ ዓለም ከላካቸው በኋላ ብዙም ሳይቆይ «ወደ ኢየሱስ ተሰብስበው ያደረጉትን... ሁሉ ነገሩት» (ማር. 6:30፤ ሉቃ. 9:10):: ከመጽሐፍ ቅዱስ እንደምንረዳው ይህ መሰባሰብ ቀደም ብሎ የታሰበበት ነበር:: ስለሆነም በመጀመሪያ ብቻቸውን የወጡበት የመስክ ሥራቸው ከመምህሩ ጋር ገና በሥልጠና ላይ ሳሉ ጊዜ የሆነ ነበር::

ይህን የወንጌል ስርጭት ጉዞአቸውን ተከትሎ የተደረገው በየቡድኑ መመደብ፣ ለነፍሳቸው ብሎም ለሥጋቸው እረፍትን እንዲወስዱ ዕድልን የሰጠ አጋጣሚ ነበር:: ለምን ያህል በመስክ ሥራ ላይ እንደ ነበሩ መጽሐፍ ቅዱስ አይነግረንም:: ምናልባት ጥቂት ቀናት፣ ወይም አንድ ሳምንት ሊሆን ይችላል:: እዚህ ላይ የጊዜው ርዝመት አስፈላጊ አይደለም:: ከመጽሐፍ ቅዱስ እንደምንረዳው፣ ዋናውና አስፈላጊው ነገር ደቀ መዛሙርት ለሥራ ከተላኩ በኋላ የገጠማቸውን ለመላው የቡድኑ አባላት እንዲያካፍሉ መጠበቁ ነበር::

በተመሳሳይ መልኩ፣ ሰባዎቹ ከተላኩ በኋላ ኢየሱስ ወደ ራሱ ጠርቶ የሥራቸውን ሪፖርት እንዲያቀርቡ ያደርግ ነበር:: «ሰብዓውም በደስታ ተመልሰው:- ጌታ ሆይ፣ አጋንንት ስንኳ በስምህ ተገዝተውልናል አሉት» (ሉቃ. 10:17):: በመጀመሪያውና በአሥራ ሁለቱ ተልዕኮ ጊዜ፣ በአገልግሎታቸው ጊዜ የሆነ ምንም አስደናቂ ስኬት አልተጠቀሰም:: በዚህኛው ጊዜ ግን የሚያነቃቃና የድል ዘገባ ነበራቸው:: ምናልባትም ለውጡን ያመጣው ደቀ መዛሙርት ያገኙት ተጨማሪ የሆነ ልምድ ሊሆን ይችላል::

ከዚህ የበለጠ ኢየሱስን ደስ የሚያሰኘው ነገር አልነበረም:: የኋላ ኋላ በእነርሱ ሥራ እርግጥ የሆነውን ድል በዓይነ ሕሊናው ሲያይ:- «ሰይጣንን እንደ መብረቅ ከሰማይ ሲወድቅ አየሁ» (ሉቃ. 10:18) አለ:: በዚያም ሰዓት ኢየሱስ «በመንፈስ ቅዱስ ሐሴት አደረገ»፣ ድምጹንም ከፍ አድርጎ ስለሆነው ሁሉ እግዚአብሔርን አመሰገነ (ሉቃስ 10:21-22):: ኢየሱስ ለረጅም ወራት ሲለፋ የነበረው ለዚህ ነበር:: አሁን ደግሞ ልፋቱ ፍሬ ሲሰጥ ማየት ጀምሯል:: ነገር ግን ሰው ከሕይወት ተሞክሮው እውነትን እንዲማር ያለውን መሻት ለማሳየት፣ ደቀ መዛሙርቱ ከሠሩት ሥራ የተነሣ እንዳይታበዩ ይህንን አጋጣሚ ተጠቅሞ ሲያስተምራቸው እናያለን:: እንዲህም አላቸው፣ «ነገር ግን

መናፍስት ስለ ተገዙላችሁ በዚህ ደስ አይበላችሁ፣ ስማችሁ ግን በሰማያት ስለ ተጻፈ ደስ ይበላችሁ» (ሉቃ. 10:20)።

## ቀጣይነት ያለው ክትትልና አተገባበሩ

የደቀ መዛሙርቱን ጉብኝት አስከትሎ በእነዚህ የምዘና ወቅቶች በግልጽ የታየው ኢየሱስ በጠቅላላው የአገልግሎት ዘመኑ የተጠቀመበትን አንድ ሌላ ስልት ያሳየናል። ደቀ መዛሙርቱ የገጠሟቸውን ክስተቶች በሚገመግምበት ጊዜ በሕይወታቸው ሊተገበር የሚገባውን ነገር ያወጣል።

ይበልጥ ግልጽ እንዲሆን፣ የዲዳ መንፈስ ያደረበትን ያንን ብላቴና ለመፈወስ ደቀ መዛሙርቱ ሳደረጉት ፍሬቢስ ጥረት ኢየሱስ እንዴት ምላሽ እንደ ሰጠ አንድ ማስረጃ እንውሰድ። ሁኔታው የተፈጸመው በመገለጥ ተራራ ላይ ኢየሱስ ከጴጥሮስ፣ ከያዕቆብና ከዮሐንስ ጋር በነበረበት ጊዜ ነበር። የተቀሩት ደቀ መዛሙርት እርሱ በሌለበት አባቱ አምጥቶ በእጃቸው ያኖረውን በአጋንንት የተያዘ ብላቴና ለመፈወስ ጥረት አድርገው ነበር። ያጋጠማቸው ጉዳይ ከእነርሱ የእምነት ደረጃ በላይ ነበር። ኢየሱስ ነገሮች በምን ሁኔታ ላይ እንደ ነበሩ ለማየት ሲመለስ፣ የበሽተኛው ብላቴና አባት በምስኪኖቹ ደቀ መዛሙርት ፊት ልጁን ሲያንቀጠቅጠው በማየቱ በኀዘን ተኩራምቶ አገኘው። በእርግጥ፣ ኢየሱስ ብላቴናውን ፈወሰው፣ ነገር ግን ይህ ክስተት በተስፋ መቁረጥ ውስጥ ለገቡት ደቀ መዛሙርት በጣም የሚያስፈልጋቸውን ትምህርት ሳይሰጣቸው እንዲያልፍ አልወደደም። ለደቀ መዛሙርቱ ይህ አጋጣሚ በብዙ ጾምና ጸሎት በመሆን የእግዚአብሔርን ታማኝነት እንዴት መጠበቅ እንደሚገባቸው የሚማሩበት ነበር (ማር. 9:17-29፤ ማቴ. 17:14-20፤ ሉቃስ 9:37-43)።



በሌላ ጊዜ ደግሞ፣ ሁሉን ማድረግ ስላስቻለው በእርሱ ስላለው ኃይል ግንዛቤ እንዲኖራቸው ያንን ሁሉ ሕዝብ ለመመገብ የእነርሱን ድርሻ እንዲወጡ በጠራቸው ጊዜ የተጠቀመበትን መንገድ አስቡ። ይህንን ሲያደርግ በዚያውም መንፈሳዊ መረዳትን አስመልክቶ እግረ መንገዱን ወሳኝ የሆነ ትምህርት አስተምሯቸው ነበር (ማር. 6:30-44፤ 7:31-8:9፤ 13-21፤ ማቴ. 14:13-21፤ 15:29-38፤ ሉቃ. 9:10-17፤ ዮሐ. 6:1-13)። ይህ የሆነው ኢየሱስ በዘመኑ የነበሩት የሃይማኖት መሪዎች በነበራቸው ጠንካራ ምልክት ፈላጊ የሆነ ልብ የተነሣ ካወገዛቸው በኋላ (ማር. 8:10-12፤ ማቴ. 15:39-16:4) የገሊላን ባሕር በታንኳ እያቋረጡ ሳሉ ነበር። በባሕሩ በዚያኛው ዳርቻ በሆነው ነገር ልቡ ያለ ጥርጥር ያዘነበት ኢየሱስ፣ ወደ ደቀ መዛሙርቱ ዘወር ብሎ፡- «ተጠንቀቁ፣ ከፈሪሳውያንና ከሄሮድስ እርሾ ተጠበቁ አላቸው»። መንፈሳዊ ነገር የማይገባቸው ደቀ መዛሙርቱ ግን፣ እርቦአቸው ስለ ነበርና በእጃቸውም የነበረው አንድ እንጀራ ብቻ በመሆኑ፣ ከማያምኑ ሰዎች እንጀራ መሸመት እንደሌለብን ሲያስጠነቅቀን ነው ብለው አሰቡ። ከዚህም የተነሣ ምግባቸውን ከየት ማግኘት እንዳለባቸውም አሳብ ሆነባቸው። ኢየሱስም የሚያምን ልብ እንዳይኖራቸው እንዲጠነቀቁ የተናገረውን መንፈሳዊ መልእክት እንዳልተረዱት ገባውና እንዲህ አላቸው፡- «እናንተ እምነት የጐደላችሁ፣ እንጀራ ስለ ሌላችሁ ስለ ምን ትነጋገራላችሁ? ገና አልተመለከታችሁምን? አላስተዋላችሁምን? ልባችሁስ ደንዝዟልን? ዓይን ሳላችሁ አታዩምን? ጆሮስ ሳላችሁ አትሰሙምን? ትዝስ አይላችሁምን? አምስቱን እንጀራ ለአራት ሺህ በቈረስሁ ጊዜ፣ ቍርስራሹ የሞላው ስንት ቅርጫት አነሣችሁ? አላቸው። ደቀ መዛሙርቱም መልሰው "አሥራ ሁለት" አሉት» (ማቴ. 16:8፣ ማር. 8:17-19)።

ይህ ጊዜ ያለምንም ጥርጥር ደቀ መዛሙርት ሕዝቡን ራት

እንዲበሉ ባስቀመጧቸውና ኢየሱስም በእንጀራው ላይ የሠራውን ተአምር በተመለከቱ ወቅት የነበረውን ሁኔታ የሚያስታውስ ነበር፡፡ ከዚህ በተጨማሪም፣ ሰው ሁሉ የሚበቃውን እስኪያገኝ ድረስ እንዲያከፋፍሉ ኃላፊነትን እንዴት እንደ ሰጣቸውና የተረፈውንም እንዲሰበስቡ እንዴት እንዳዘዛቸው ትዝ ብሎአቸዋል፡፡ አዎ፣ ሰው ሁሉ በልቶ ካበቃ በኋላ አሥራ ሁለቱ እያንዳንዳቸው በያዙት ቅርጫት ሙሉ የሚሆንን ምግብ ሰብስበው ነበርና በሚገባ ያስታውሳሉ፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ፣ አራት ሺውን ከመገቡ በኋላ የተረፈውን ሰባት ቅርጫት ትራፊም አስታውሰዋል፡፡ ስለሆነም ቀደም ሲል ያዩት የኢየሱስ ተአምራዊ ኃይሉ ቢያስፈልግ የእነርሱን አንዲት እንጀራ ባርኮ አሥራ ሁለቱን መመገብ እንደሚችል ምስክር ነበር፡፡ «እነርሱም ከፈሪሳውያንና ከሰዱቃውያን ትምህርት እንጂ ከእንጀራ እርሾ እንዲጠበቁ እንዳላላቸው ያን ጊዜ አስተዋሉ» (ማቴ. 16:12)፡፡

## ስለ ትዕግሥት የተሰጡ ትምህርቶች

ከደቀ መዛሙርት የመስክ ሥራ በኋላ ጌታ ከሰጣቸው የማስተካከያ ትምህርቶች አንዱ የሆነው የሐዋርያት ኅብረት አባል ባልሆኑትና በአገልግሎት ይሳተፉ በነበሩት ሌሎች ሰዎች ላይ በነበራቸው አመለካከት ላይ ያተኮረ ነበር፡፡ በጉዞአቸው ወቅት በኢየሱስ ስም አንዳንድ ሰዎች አጋንንትን ሲያወጡ ያጋጠማቸው ይመስላል፡፡ ነገር ግን እነዚህ ሰዎች የእነርሱ የእምነት ቡድን አባል ስላልነበሩና ስለማይከተሉአቸው አጥብቀው ተቃወሙአቸው (ማር. 9:38፤ ሉቃ. 9:49)፡፡ ያለምንም ጥርጥር የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ልክ የሠሩ መስሎአቸው ነበር፡፡ ሆኖም፣ ወደ መምህሩ መጥተው ስለሆነው ሁሉ ዘገባ ባቀረቡበት ጊዜ ግን በስሙ የሚካሄድን ማንኛውም ቅን ሥራ ማጣጣል የሚኖረውን ጉዳት ሰፋ ባለ መልኩ



ማስጠንቀቂያ መስጠት አስፈላጊ እንደ ሆነ ተገነዘበ (ማር. 9:39-50፤ ማቴ. 18:6-14)፡፡ ስለሆነም ኢየሱስ "የማይቃወማችሁ ከእናንተ ጋር ነውና አትከልክሉት" (ሉቃ 9:50) አላቸው፡፡ በማስከተልም አባባሉ ጠቅለል ባለ መልኩ ልበ ንጹሕ የሆኑ ሰዎችን በተለይም ሕጻናትን እንዲመለከት በማሰብ፣ "በእኔም ከሚያምኑት ከእነዚህ ከታናናሾቹ አንዱን የሚያሰናክል ሁሉ ትልቅ የወፍጮ ድንጋይ በአንገቱ ታስሮ ወደ ባሕር ቢጣል ይሻለው ነበር" አላቸው (ማር. 9:42)፡፡ «እንደዚሁ «ከእነዚህ ከታናናሾቹ አንዱ እንዲጠፋ በሰማያት ያለው አባታችሁ ፈቃድ አይደለም" አላቸው (ማቴ. 18:14)፡፡

ወደ ሰማርያ በመሄድ ተልዕኳቸውን እያከናወኑ ሳሉ በሚሠሩት ሥራ ተቃውሞ ገጠማቸው፡፡ ከዚህም የተነሣ በስሜታዊነት ገንፍለው፣ ከሰማያት እሳትን ለማውረድና ሕዝቡን በዚያች ቅጽበት ለማጥፋት ፈልገው ነበር (ሉቃ. 9:51-54)፡፡ በአቅራቢያቸው ቆሞ የነበረው ኢየሱስ ግን፣ «ዘወር ብሎ ገሠጻቸውና፡- "ምን ዓይነት መንፈስ እንደ ሆናችሁ አታውቁም፤ የሰው ልጅ የሰውን ነፍስ ሊያድን እንጂ ሊያጠፋ አልመጣም" (ሉቃ. 9:55-56) አላቸው፡፡ እንዲህ ያለውን ችግር እንዴት ሊፈቱት እንደሚገባ ሊያሳያቸውም ስለ ፈለገ፣ «ወደ ሌላ መንደርም ሄዱ» (ሉቃ. 9:56)፡፡

## የተገለጠው መርሕ

ደቀ መዛሙርቱ የተለያዩ ብዙ አስቸጋሪ ሁኔታዎች በሚገጥማቸው ጊዜያት የሚወስዱትን እርምጃና የሚሰጡትን ምላሽ ኢየሱስ እንዴት ባለ መንገድ ይቆጣጠር እንደ ነበረ ለማሳየት ከዚህም በላይ ብዙ ገለጻዎችንና ማብራሪያዎችን መጠቀም ይቻላል፡፡ በምድር ላይ የነበረው አገልግሎቱ ወደ ማብቂያው እየቀረበ ሲመጣ፣ የበለጠ ትኩረት ሰጥቶ ያለማቋረጥ ይከታተላቸው ነበር፡፡

በስኬትም ሆነ በሽንፈት ውስጥ ሲያልፉ በቃኝ እንዲሉ አይፈቅድላቸውም:: ምንም ሠሩ ምንም ከዚያ የሚበልጥ የሚሠሩትና ከዚያ የሚበልጥ የሚማሩት ነበራቸው:: በስኬታቸው ሐሤት ያደርጋል፣ ነገር ግን ዋነኛ ግቡ ዓለምን ሁሉ መማረክ ስለ ነበረ፣ እዚያ ደረጃ እስኪደርሱ ድረስ ጥረታቸውን ከሥር ከሥሩ ይገመግም ነበር::

ይህ እንግዲህ በጥሩ ሁኔታ የተካሄደ የሥራ ላይ ሥልጠና ነበር:: ኢየሱስ ተከታዮቹ በራሳቸው አንድ ነገር አይተው አንዳች ልምምድ ወይም አጋጣሚ እንዲኖራቸው ያደርግና፣ ይህንኑ ልምምድ እንደ መነሻ ተጠቅሞ የደቀ መዝሙርነት ትምህርት ይሰጣቸው ነበር:: ባይሳካላቸውም እንኳ፣ የእግዚአብሔርን ሥራ ለመሥራት ያደርጉት የነበረው ጥረት ያለባቸውን ጉድለት እንዲያውቁትና መምህሩ ለሚሰጣቸው እርማት ይበልጥ ክፍት ሆነው እንዲቀበሉት አድርጎ ነበር:: ከዚህም በተጨማሪ፣ የነበራቸው የሕይወት ተሞክሮ ኢየሱስ በተወሰኑት መሻቶቻቸው ላይ በይበልጥ እንዲያተኩርና ነባራዊ ከሆኑ ሁኔታዎቻቸው ጋር እያይዞ እንዲያስተምራቸው አስችሎታል:: ብዙ ጊዜ ትምህርትን ይበልጥ የምናደንቀው በመርሕ ደረጃ የተማርነውን ነገር በተግባር ማዋል ዕድል ያገኘን እንደ ሆነ ነው::

በዚህ መለኮታዊ ራእይ ኢየሱስ ያደርግ የነበረው የክትትል ሥራ ዋነኛው ትኩረት ደቀ መዛሙርት እንዲደርሱበት ወደ ዐቀደላቸው ግብ እስኪደርሱ ድረስ ጉዞአቸውን እንዲቀጥሉ ማድረግ ነው:: ማድረግ ከሚችሉት በላይ ከእነርሱ አይጠብቅም፣ ከእነርሱ የሚጠብቀው የተቻላቸውን ሁሉ እንዲያደርጉ ነበር:: በእውቀትና በጸጋ ባደጉ ቁጥር ደግሞ ይህ ችሎታቸውም እንዲሻሻል ይጠብቃል:: በምሳሌ፣ በተግባር፣ ከዚያም በማያቋርጥ ክትትል የማስተማር ዕቅዱ ሁሉ በውስጣቸው ካለው ምርጥ የሆነውን



ችሎታቸውን ሁሉ ማውጣት እንዲችሉ ታስቦ የታቀደ ነበር::

## መርሑ ዛሬ ሲተገበር

ዛሬም ቢሆን ሌሎችን ለወንጌል ስርጭት ሥራ ለማሠልጠን ከሚሹ ሰዎችም ቢሆን ከዚህ የማይተናነስ ትዕግሥትና ቆራጥ የሆነ ክትትል ያሻል:: ሥራውን ለመሥራት ፈቃደኛ የሆነን አንድ ሰው እንዴት እንደሚሠራ በማሳየትና ታላቅ ውጤትን ይዞ እንደሚመለስ ታላቅ የሆነ ጉጉት እንዲኖረው በማድረግ ብቻ ሥራው በሚገባ ይሠራል ብለን ፈጽሞ ልናስብ አይገባም:: ሥራውን የሚያደናቅፉና ተስፋ አስቆራጭ እንዲሆን የሚያደርጉ ብዙ ነገሮች ሊፈጠሩ ይችላሉ:: እነዚህ ክስተቶች ብቁ በሆኑና ነገሮችን የመረዳት ችሎታ ባላቸው ሰዎች እርምጃ ካልተወሰደባቸው፣ አገልጋዩ በቀላሉ ሊደናቀፍ ብሎም ሊሸነፍ ይችላል:: በተመሳሳይ መልኩ፣ ለነፍስ ተድላን የሚሰጡ በርካታ የሆኑ የጸጋ ስጦታዎች ለመላው ዓለም ብርሀን ከሆነው ከክርስቶስ ተልዕኮ አንጻር ትርጉም ሲሰጣቸው ግልጽ ያለና ጠለቅ ያለ አቋም ሊኖራቸው ይገባል:: ስለሆነም በወንጌል ሥራ ላይ የተሰማሩቱ በራሳቸው ብቁ ሆነው መቆም የሚችሉበት ጊዜ እስኪደርስ ድረስ በግላቸው የሚከታተላቸውና የሚመራቸው ሰው ያስፈልጋቸዋል::

አንድ ነገር ደግሞ ሁልጊዜ ልናስታውስ ይገባል:: ይሄውም ግባችን ዓለምን ሁሉ መውረስ ነው:: ከዚህ ጋር የማይስተካከልና ያነሰ ነገር በወቅቱ የምንተልመውን ስልት ተቆጣጥሮ ትኩረታችንን ሊወስድ አይገባም:: ሁልጊዜ እንደሚሆነው በዚህ ዘርፍ የሚያገለግል አንድ ሰው ምንም ተጨማሪ ሥልጠናና መነቃቂያ ሳያገኝ ከአገልግሎቱ ይወገዳል:: የዚህም ውጤቱ በደስታ አዙሪት ውስጥ በአንድ ስፍራ ብቻ መሽከርከር ይሆናል:: እድገት የለም:: በሚሠራው ሰው ውስጥ ታምቆ ያለው የመሥራት ችሎታ

እንዲያድግ አልተደረገም፣ በመሆኑም ከጥቂት ጊዜ በኋላ መሪ ሊሆን የሚችለው ይህ ሰው ከክትትል እጦት የተነሣ ዋጋ ቢስ ይሆናል:: በድል ዋዜማ ስኬት ሲጠፋ፣ እንግዲህ እንዲህ ነው:: በአንድ ወቅት ጥሩ ይመስል የነበረው ቀስ በቀስ እጅግ በጣም ጥሩ ለሚሆነው የማሰናከያ ዓለት ሆኖ ይገኛል::

ያለምንም ጥርጥር በዚህ ምክንያት ለእግዚአብሔር መንግሥት ሥራ የምንጥረው ጥረታችን ሁሉ ከንቱ ሆኖብናል:: ሽንፈት የገጠመን፣ ሥራውን ለመሥራት ስለማንሞክር ሳይሆን፣ ነገር ግን ያደረግናት ትንሿ ጥረታችን ከዚያ የበለጠ ሥራ እንዳንሠራ እንደ ማሳበቢያ ስለምንጠቀምባት ነው:: በውጤቱም አፈግፍገን በመውጣታችን የዓመታት ጥረታችንንና ለዓመታት ዋጋ የከፈልንበትን እንጥለዋለን::

ለምስክርነት የወጡት ይዘውት በሚመለሱት የመጀመሪያ ፍሬያቸው አለመርካትን ከክርስቶስ የምንማረው መቼ ይሆን? ደቀ መዛሙርት ሙሉ ወደ ሆነ እድገት ሊመጡ ይገባቸዋል:: የተሟላ ድል ማግኘትን የሚተካ ምንም ነገር የለም:: የውጊያ ሜዳችን ደግሞ ዓለም ናት:: ምሽግን ይዘን እንድንቀመጥ አልተጠራንም:: የተጠራነው እንድንወጣ፣ ከፍታዎችንም እንድናፈርስ ነው:: የክርስቶስን ስልት የመጨረሻውን ደረጃ መረዳት የሚቻለው በዚህ መልኩ ሲታይ ነው::



*ልትሄዱና ፍሬን ልታፈሩ ... ሾምኋችሁ*
*ዮሐንስ 15:16*

# 8

# መባዛት

## ብዙ ፍሬ እንዲያፈሩ ይጠብቅባቸው ነበር

ከዓለም ተሰብስበው የወጡ ሰዎች ባሉበት በቤተ ክርስቲያን ውስጥና በቤተ ክርስቲያንም አማካኝነት ደቀ መዛሙርቱ እርሱን የሚመስሉትን እንዲያበዙ ኢየሱስ ይፈልግ ነበር:: ስለሆነም በመንፈስ የሆነው የእርሱ አገልግሎት በደቀ መዛሙርቱ ሕይወት ውስጥ ባካሄደው አገልግሎቱ አማካኝነት በብዙ እጥፍ ይበዛል:: በእነርሱና እነርሱን በሚመስሉ በሌሎች አመካኝነት ዳርቻዎቹን እያሰፋ ሕዝብ ሁሉ ከመምህሩ ጋር በነበሩበት ጊዜ ያገኙትን መልካም ዕድል ተመሳሳይ በሆነ መልኩ እስኪያውቅ ድረስ ማደጉን ይቀጥላል:: በዚህ ስልት ዓለምን የመድረሱ ጉዳይ የጊዜና እነርሱ ለዕቅዱ ባላቸው ታማኝነት ብቻ የሚወሰን ነው::

ኢየሱስ በደቀ መዛሙርቱ ሕይወት ውስጥ የሞትንና የሲኦልን ሥልጣናት ሁሉ መዋጋትና ማሸነፍ የሚያስችለውን የቤተ ክርስቲያንን ይዘት አስቀምጧል:: እንደ ሰናፍጭ ቅንጣት በትንሹ ትጀምራለች፣ ነገር ግን በቁመትና በጥንካሬ እየጨመረች ዛፍ እስክትሆን ድረስ ታድጋለች «ከአታክልቶች ትበልጣለች» (ማቴ. 13:32ን ከማር. 4:32፣ ሉቃ. 13:18-19 ጋር አንጻጽር):: ኢየሱስ ሰው ሁሉ እንደሚድን አይጠብቅም (ከእውነታው አንጻር የእግዚአብሔር ጸጋ ቢኖርም እንኳ የሰውን ዐመፀኛነት ያውቃል)፤ ነገር ግን ለፍጥረት ሁሉ አሳማኝ በሆነ መልኩ አንድ ቀን የደኅንነት

ወንጌል በስሙ እንደሚታወጅ ይታየው ነበር። በዚያም ምስክርነት በውጊያ ላይ ያለችው ቤተ ክርስቲያን አንድ ቀን ድል አድራጊዋ ቤተ ክርስቲያን ስትሆን ዓለም አቀፋዊ አቋም ይኖራታል።

ይህ ደግሞ በቀላሉ የሚከናወን ድል አይደለም። ብዙዎች ይሰደዳሉ፣ በውጊያው ሜዳ ላይም ወድቀው ሰማዕታት ይሆናሉ። ሊያልፉበት ያለው መከራ ምንም ያህል ታላቅ ቢሆንም ምንም ያህል በትግሉ ወቅት በአነስተኛ ግጭቶች ሽንፈት ሊያጋጥም ቢችልም በመጨረሻ ግን ታላቅ ድል እንዳለ እርግጥ ነው። በመጨረሻም የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን አሸናፊ ትሆናለች። ምንም ነገር ለዘለቄታው አይቋቋማትም። (ማቴ. 16:18)

## በምስክርነት ያለ ድል

ኢየሱስ ወደፊት በሚሆነው ላይ ያለው ይህ አስደናቂ መተማመን አሁን አብረውት ሆነው ያመልኩት በነበሩት ሰዎች ባለው እውቀት ላይ የተመሠረተ ነበር። ደቀ መዛሙርቱ ቢያንስ ከክብሩ የተወሰነ መጠን እንደ ተማሩ ያውቃል። የቡድኑ አፈ ጉባኤ የነበረው ጴጥሮስ ስለ ኢየሱስ ማንነት በሰጠው የማረጋገጫ ቃል ይህንኑ ጠቅለል አድርጎ ገልጾታል፦ «አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ» (ማቴ. 16:16ን ከማር. 8:29፤ ሉቃ. 9:20 ጋር አነጻጽር)። እዚህ ላይ የተገለጸው ፍጹም የማይናወጥ እውነት ነበር። ኢየሱስም በዚህ መሠረት ላይ ሆኖ ነበር ሊመጣ ያለው ድሉ እውን እንደሚሆን ያየውና፦ «አንተ ጴጥሮስ ነህ በዚችም ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ» (ማቴ. 16:18) ያለው። ነገሮች ወደ መሆን እንዲመጡ የሰው ተነሣሽነት ምን ያህል አስፈላጊ እንደ ሆነ በእነዚህ ቃላት ውስጥ ያለው ኃይል ያመለክታል። ክፍሉ ካለው መንፈሳዊ ይዘት የተነሣ የተፈጠረውን አስደሳች ስሜት ወደ ጐን አድርገን በአንድ ነገር ላይ ልንስማማ



ይገባናል። ቢያንስ ኢየሱስ የተናገረው በጌታው ላይ ያለውን የግል እምነት ሳረጋገጠ አንድ ሰው ነበር። እርግጥ ኢየሱስ በግልጽ እንዳስቀመጠው፣ ጌታው የልዑል እግዚአብሔር ልጅ መሆኑን የመረዳቱ ነገር ጴጥሮስ በራሱ ጥረት የደረሰበት ነገር አልነበረም (ማቴ. 16:17)። ይሁን እንጂ፣ በሕይወቱ የነበረው የዚህ መገለጥ ልምምዱ «በሥጋና በደሙ» ውስጥ ሰርጾ ነበር። ይህንንም እውነት ለሌሎች በታማኝነት በመግለጥ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ለድል ታጭታ ነበር። እንዴት ልትጠፋ ትችላለች? ሕያው በሆነው በክርስቶስ ላይ የነበረው እምነት በየጊዜው እያካበተ በመሄዱ እንደ ዓለት እየጠጠረ ሄዶ፣ ጴጥሮስ ጌታ እንደ ሆነ የመሰከረለት «የማዕዘን ራስ ሆነ፣» አማኞች ሁሉ ሕያዋን ድንጋዮች በመሆን ቤተ ክርስቲያን ለመሆን ይታነጻሉ (1ኛ ጴጥ. 2:4-8፤ ኤፌ. 2:20-22)።

የሆነ ሆኖ፣ የክርስቶስ ምስክር በመሆንና በስተመጨረሻ ባለው ታላቁ ድል መካከል ያለውን ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት ቸል ልንለው አይገባም። አንዱ ከሌላው ተነጥሎ የሚሆን አይደለም። በመንፈስ ቅዱስ ኃይል አማካኝነት እነዚህን ሁለት ታላላቅ እውነቶች በአንድነት አጣምሮ ማስኬድ መቻል በክርስቶስ የወንጌል ስርጭት ስልት ውስጥ ወሳኙ ጥበብ ነው።

## የተገለጠው መርሕ

ይህ እንግዲህ ወደ ደቀ መዛሙርቱ ይመልሰናል። ሁሉንም ለሚጠቅሰው ለእርሱ እንቅስቃሴ ዘብ የቆሙት እነርሱ ነበሩ። «ከቃላቸው የተነሣ» ሌሎች በእርሱ እንዲያምኑ ነው (ዮሐ. 17:20)' ያመኑትም በተራቸው ለሌሎች በመንገር ኢየሱስ ማን እንደ ነበረና ለምን እንደ መጣ ዓለም እስኪያውቅ ድረስ ቃሉ ከአንዱ ወደ ሌላው እንዲሸጋገር ነበር የተፈለገው (ዮሐ. 17:21፣

23):: ጠቅላላው የወንጌል ስርጭት ስልት ወደ ዓለም የመጣበት ዓላማ መፈጸሙ፣ በመስቀል ላይ መሞቱና ከመቃብር መነሣቱ የመረጣቸው ደቀ መዛሙርቱ ለዚህ ሥራ ባላቸው ታማኝነት ላይ የተመሠረተ ነበር:: እነርሱ ብዙ ፍሬን እስካፈሩና ያፈሩአቸውንም ደቀ መዛሙርቶቻቸውን ፍሬን እንዲያፈሩ እስካስተማሩዋቸው ድረስ፣ አሁን ቁጥራቸው ትንሽ መሆኑ ችግር አልነበረውም:: ለሌሎች እንዲመሰክሩ መንፈሱና እርሱ የተጠቀመበት ስልት እስከሚያስገድዳቸው ድረስ አዳኙን ጌታ ጠንቅቀው በተሰጡ ሕይወቶች አማካይነት ነው የእርሱ ቤተ ክርስቲያን ወደ ድል የምትደርሰው:: ቀላል ይምሰል እንጂ፣ ወንጌል የሚያሸንፍበት መንገድ ግን ይኸው ነበር:: ኢየሱስ ከዚህ የተለየ ሌላ ዕቅድ አልነበረውም::

## አገልግሎቱ ሲፈተን

ከባዱ ፈተና እዚህ ላይ ነበር:: እርሱ ከሄደ በኋላ ደቀ መዛሙርቱ ሥራውን መቀጠል ይችሉ ይሆን? ወይም እጅግ ቀጥተኛ በሆነ መልኩ፣ እርሱ በመሃከላቸው በሥጋ ሆኖ ይከታተላቸው በነበረ ጊዜ በጥሩ ሁኔታ ያገለግሉ እንደ ነበረ፣ እርሱ ሳይኖርስ እንደዚያው ያገለግሉ ይሆን? ይህ ምናልባት ከሚገባው በላይ እንደ መጠየቅ ሊወሰድ ይችላል:: በክርስትና እድገታቸው እዚህ ደረጃ ላይ እስከ ደረሱበት ጊዜ ድረስ፣ እንደ ሰው አስተሳሰብ ኢየሱስ በእነርሱ ሕይወት ላይ ያደረገው ጥረት ለእግዚአብሔር መንግሥት ሥራ በቂ ለመሆኑ እርግጠኛ ሊሆን አልቻለም:: ደቀ መዛሙርት መንፈሱንና ስልቱን ወደ ሌሎች ማሻገር ባይችሉ? ሥራውን ማን ይቀጥለዋል፣ ያንን ሁሉ ዓመት እነርሱን ያሠለጠነበት አገልግሎት ሁሉ መና ሆነ ማለት ነው::

ሕይወት ያለው ነገር ሁሉ ራሱን የመተካቱና የመራባቱን



አስፈላጊነትና አይቀሬነት ኢየሱስ በደቀ መዛሙርቱ ውስጥ በማይረሱት መልኩ ማስረጹ አስገራሚ አልነበረም:: ይህንንም በወይኑና በቅርንጫፎቹ ምሳሌነት ነበር ያስተማራቸው (ዮሐ. 15:1-17):: ከምሳሌዎች ሁሉ እጅግ በጣም ቀላል ሆኖም ጠለቅ ባለው በዚህ ጌታ የሰጠው ምሳሌ፣ የወይኑ ግንድም (ራሱ ክርስቶስ) ሆነ የቅርንጫፎቹ (በእርሱ የሚያምኑት) ዓላማ ፍሬን ማፍራት ሊሆን እንደሚገባ ገለጸላቸው:: ፍሬ የማያፈራውን ማንኛውንም ቅርንጫፍ ዋጋ የለውምና ገበሬው ይቆርጠዋል:: ከዚህ በተጨማሪ፣ ደግሞ ፍሬ የሚያፈሩ ቅርንጫፎች ደግሞ የበለጠ ያፈሩ ዘንድ ገበሬው ያጠራቸዋል (ዮሐ. 15:2):: ሕይወትን የሚያቆየው የወይኑ ግንድ ኃይል ሕይወት - አልባ በሆኑት ቅርንጫፎቹ እንደማይገባ ግልጽ ነው:: የሚጠበቅበት ጉዳይ ነውና፣ በወይኑ ላይ የሚኖር ማንኛውም ቅርንጫፍ ለመኖር ሲል ፍሬ እንዲያፈራ ይጠበቅበታል:: ኢየሱስም ይህንን ከደቀ መዛሙርቱ ሕይወት ጋር አገናዘበው:: በእርግጥ የሕይወቱ ተካፋዮች ነበሩና የእርሱን ፍሬ ያፈራሉ (ዮሐ. 15:5-8)፣ ከዚህም ባሻገር ፍሬአቸው ይኖራል (ዮሐ. 15:16):: ፍሬ-አልባነትና ክርስትና ሁለት አብረው የማይሄዱ ነገሮች ናቸው:: የዛፍ ምንነቱ በፍሬው ይታወቃል::

ይህንን መርሕ በአገልግሎት ዘመኑ ሁሉ ትኩረት ይሰጠው ነበር:: ራሱን ለዓለም መሥዋዕት አድረጎ ለማቅረቡ መቅረት የሌለበት ዋጋ ተደርጎም የሚወሰድ ነው (ዮሐ. 12:24ን ከ17:19 ጋር አነጻጽር):: በሰማይ ያለውን የአባቱን ፈቃድ የሚያደርጉ ሰዎች የሚለዩበት ተግባር እንዲሆን ተደርጓል (ማቴ. 7:16-23፣ ሉቃ. 6:43-45):: ደቀ መዛሙርቱ በመከሩ ጊዜ ለሚሠሩት ሥራ የሚቀበሉት ደመወዝ ነው የሚል ትርጉምም ተሰጥቶታል (ዮሐ. 4:36-38):: «የዚህ ዓለም አሳብና የባለጠግነት ማታለል የሌላውም

ነገረ ምኞት ገብተው ቃሉን ያንቃሉ» (ማር. 4:18-20፤ ማቴ. 13:22፣ 23፤ ሉቃ. 8:14፣ 15) የተባለባቸው እንደማያገኙት ተገልጾ የነበረ ጉዳይ ነው:: በውስጣቸው አለመኖሩ ስለ ተገለጠ ሰዱቃውያንና ፈሪሳውያን ዘንድ ደግሞ በዓይኑ ፊት እንዲቀሉ ያደረጋቸውም ይሄው ነው (ማቴ. 3:7-8፤ 12:33፣ 34፤ ሉቃ. 13:6-9):: በተለያየ መንገድና በሁሉ ዓይነት ሰዎች ዘንድ፣ የሕይወታቸው ፍሬ እንዲመዝን ኢየሱስ ጥሪውን አቅርቧል:: ምን እንደ ነበሩ የተገለጹበት መንገዱ ይህ ነበር:: በእርግጥ፣ ፍሬያማነት ሰፋ ባለው ዓምዱ መጀመሪያ በራሳችን ከዚያም በሌሎች ሕይወት የክርስቶስን ሕይወት በሰው ማንነት ውስጥ ማፍራት መቻል ከሚለው ትርጉሙ ከወሰድነው፣ መምህሩ ያደረጋቸውም ሆኑ የተናገራቸው ነገሮች ሁሉ ተጠቅልለው ወደ እዚህ መርሕ ያመለክታሉ::

## ታላቁ ተልዕኮ

ክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያን በሰጠው ታላቁ ተልዕኮ ውስጥ “እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ... ደቀ መዛሙርት አድርጉአቸው” (ማቴ. 28:29) በሚለው ትእዛዝ ይሄው አሳብ ጠቅለል ብሎ ተገልጿል:: ይህ ቃል እንደሚያመለክተው ደቀ መዛሙርት ወደ ዓለም ወጥተው እነርሱ ራሳቸው እንደ ሆኑት ሁሉ የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት እንዲሆኑ ሌሎችን ማርከው እንዲያመጡ ነበር የታዘዙት:: ይህንን ክፍል በተለይ በግሪክ ትርጉም ያጠናነው እንደ ሆነ፣ ለዚህ ተልዕኮ ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጥ ጠበቅ ያለ ነገር እናገኛለን:: ሂዱ፣ አጥምቁ፣ አስተምሩ የሚሉት ቃላት እንደ ግሥ አጋዥ ሲሆኑ «ደቀ መዛሙርት አድርጉአቸው» በሚለው ዋና እና የበላይ በሆነው የማሰሪያ አንቀጽ ይጠቃለላሉ:: እንግዲህ ታላቁ ተልዕኮ ስንል እስከ ዓለም ዳርቻ ድረስ ወንጌልን እየሰበኩ መሄድ



(ማር. 16:15)፣ ወይም የተለወጡትን ብዙ ሰዎች በሥላሴ ስም ማጥመቅ፣ አለዚያም የክርስቶስን ትእዛዛት ለእነዚሁ ሰዎች ማስተማር ብቻ አይደለም፣ ነገር ግን እንደ እነርሱ ያሉ ለክርስቶስ ተልዕኮ ግድ የሚላቸውንና ተከታይ ብቻ ሳይሆኑ፣ ሌሎችም የእርሱን መንገድ ይከተሉ ዘንድ የሚያደፋፍሩ ሰዎችን በማፍራት ደቀ መዛሙርት ማድረግ ነው:: ደቀ መዛሙርትን ማፍራት ሲችሉ ብቻ ነበር ሌሎች የዚህ ተልዕኮ ተግባራት ግባቸውን የሚመቱት::

## መከሩን ለሚሰበስቡት ጸልዩ

ትኩረቱ በአመራር ላይ ነበር:: ልቡ የተወናበደው ሕዝብ ለመከሩ እንደ ደረሰ ኢየሱስ ራሱ በአገልግሎቱ አይቶ ነበር:: ነገር ግን እነዚህን ሰዎች መንፈሳዊ መሪዎች ካልመሯቸው፣ እንዴት አድርገው ሊማረኩ ይችላሉ? ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ፣ “እንግዲህ የመከሩን ጌታ ወደ መከሩ ሠራተኞችን እንዲልክ ለምኑት” በማለት ሲያሳስባቸው እናያለን (ማቴ. 9:37-38ን ከሉቃ. 10:2 ጋር አነጻጽር):: በእነዚህ ቃላት ውስጥ ጥድፊያን የሚያመለክት አሳብ እንዳለ መመልከት ይቻላል:: ይህም ጥድፊያ ዓለም ካላት ጥልቅ መሻት የተነሣ ለሰዎች ማለትም ለነፍሳቸው ግድ የሚላቸውና ከእነርሱ ጋር የሚያገለግሉ ሠራተኞች ለማግኘት ከመናፈቅ የወጣ መሻት ነው:: ለዓለም መጸለይ ምንም ጥቅም የለውም:: ምን በጐ ነገር ያከናውናል? እግዚአብሔር እንደ ሆነ አስቀድሞ ወዷቸዋል፣ ሊያድናቸውም ልጁን ሰጥቷል:: አዎ፣ በደፈናው ለዓለም መጸለይ ጥቅም የለውም:: ዓለም ጠፍቷል፣ በኃጢአትም ታውሯል:: ያለው ብቸኛ ተስፋ የደኅንነትን ወንጌል ይዘውለት የሚሄዱና ለአዳኙ ጌታም ከማረኩት በኋላ ባለበት የሚተዉት ሳይሆኑ፣ በታማኝነት፣ በትዕግሥትና በታላቅ ጥንቃቄ በአካባቢያቸው ያሉ ሰዎች ቤዛ በሆነላቸው ፍቅር መዓዛቸው እንዲለወጥ የሚያደርጉ

ክርስቲያኖች እስኪሆኑ ድረስ የሚለፉ ሠራተኞችን ማግኘት ነው።

## መርሑ በሕይወታችን ሲተገበር

እንግዲህ እዚህ ላይ በመጨረሻ የዓለም አዳኝ ለሆነው ለእርሱ ታላቅ ዓላማ ሕይወታችንና ምስክርነታችን ምን ያህል አስተዋጽኦ እንዳደረገ ልንመዝን ይገባል። ክርስቶስን ብለው እኛን የተከተሉን ሰዎች ዛሬ ሌሎችን ወደ ክርስቶስ እየመሩና እኛ እንደሆንነው ሁሉ ሌሎች ደቀ መዛሙርት እንዲሆኑ እያስተማሯቸው ነውን? አንድ ነገር ልናስተውል ይገባል። ሊጠፉ ያሉትን ከጥፋት ማስጣል፣ የግድ መደረግ ያለበት ቢሆንም፣ ብቻውን ግን በቂ አይደለም። የመጀመሪያው ቡቃያ እንዲጸና በክርስቶስ የተወለዱትን አዳዲስ ሕጻናት በእምነት ማሳደጉ፣ አስፈላጊ ቢሆንም፣ አጥጋቢ ግን አይደለም። እርግጥ ሥራው እንደሚፈልግብን ነፍሳትን ማርከው እንዲያመጡ መላኩ፣ የሚመሰገን ተግባር ቢሆንም፣ በቂ አይደለም። ሥራችን እስከ መጨረሻው ቀጣይነት እንዲያገኝና እንዲጸና ከተፈለገ ዋናው ነገር በእኛ አማካይነት የተለወጡት ሰዎች ብዙ ተከታዮች ማፍራታቸው ሳይሆን፣ በእነርሱ አማካይነት የተለወጡትን ሰዎች መሪዎች ማድረግ የቻሉ እንደ ሆነ ነው። እርግጥ ነው፣ ትውልዳችንን ለክርስቶስ መማረክ፣ ይህንንም አሁኑኑ ማድረግ፣ መሻታችን ነው። ሆኖም፣ ይህ ብቻውን በቂ አይደለም። ወንጌልን ከሰበከውና ቤዛችን በሆነው (በክርስቶስ) ነፃ የወጡት ሰዎች ሕይወት ውስጥ ቀጣይነቱ ካልተረጋገጠ በቀር ሥራችን በፍጹም አልተጠናቀቀም።

ማንኛውም ዓይነት የወንጌል ስርጭት ሥራ የሚመዘነው አሁን እየሆነ በሚታየው፣ ወይም በየኮንፍራንሱ በሚሰማው ሪፖርት ሳይሆን፣ ሥራው በቀጣዩ ትውልድ ውስጥ ምን ያህል በውጤታማነት እየተካሄደ ነው ከሚለው ጥያቄ አንጻር ነው።



በተመሳሳይ መልኩ፣ ቤተ ክርስቲያን ስኬቷን የምትመዝንበት መለኪያዋ በአባላት ስም ዝርዝር ማስፈሪያው መዝገብ ላይ ምን ያህል አዳዲስ ሰዎች ተጨምረዋል፣ ወይም በጀቱ በምን ያህል አድጓል? በሚለው ሳይሆን፣ ምን ያህል ክርስቲያኖች ነፍሳትን በመማረክና እነርሱም ብዙዎች ሌሎችን እንዲማርኩ በማሠልጠን ተግባር ላይ በንቃት ይሳተፋሉ? በሚለው ሊሆን ይገባል። ዋናውና ተፈላጊው ነገር ምስክርነታችን የሚሰፋበት ድንበር ልክ ነው። ስለዚህ እሴቶች የሚመዘኑበት ዘላለማዊው መለኪያ ብቻ ይሆናል ማለት ነው።

ከዚህ አኳያ ተነሥተን ሕይወታችንንና አገልግሎታችንን በድጋሚ የምናይበት ጊዜው አይደለምን? ደውሰን ትሮትማን የተባለው ሰው እንዳለው፣ "ሰዎቻችን የት አሉ?» ለእግዚአብሔርስ ምን እየሠሩ ነው? ላደረግነው ልፋታችን ሁሉ ብድራት የሚሆን አንድ እውነተኛ ደቀ መዝሙር ብቻ ያፈራን ቢሆን ይህ ለነገዋ ቤተ ክርስቲያን ምን ማለት እንደ ሆነ እስቲ አስቡት። ይህ የእኛን ተግባር እጥፍ አያደርገውምን? የመጀመሪያው የተሳካለት እየሆነ ሳለ አንድ ሌላ እኛን የሚመስል ሰው ደግሞ ጨመርን እንበል፣ ይህ ሕይወታችንን በአራት እጥፍ አያበዛውምን? ቢያንስ ቢያንስ በጽንሰ አሳብ ደረጃ፣ እንዲህ ባለው የማባዛት ስሌት እንኳ የእኛ አገልግሎት ብቻ ብዙዎችን በወንጌል ለመድረስ ጊዜው ሩቅ አይሆንም። ይህ የሚሆነው ግን ደቀ መዝሙር አድርገነዋል ያልነው ሰው የመምህሩን አካሄድ በእውነት የተከተለ እንደ ሆነ ብቻ ነው።

## በቤተ ክርስቲያን ሲተገበር

በእነዚያ በመጀመሪያዎቹ ሐዋርያት ይህ ተግባራዊ በመደረጉ ልናመሰግን ይገባል። ወንጌልን በሕዝቡ መሀል አሰራጪ፣

በዚያውም ባመኑት መካከል ደግሞ ኅብረት እንዲመሠረት ያደርጉ ነበር። ጌታ በየቀኑ የዳኑትን ለቤተ ክርስቲያን ይጨምር እንደ ነበር፣ ደቀ መዛሙርትም እንደ መምህራቸው አገልግሎታቸውን እስከ ምድር ዳር ማድረስ የሚችሉትን ሰዎች እያሳደጉ ነበር። የሐዋርያት ሥራ እንደ እውነቱ ቀደም ሲል በክርስቶስ ሕይወት ተገልጦ የነበረው የወንጌል ስርጭትን መርሕ እያደገች ባለችው ቤተ ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ ተግባራዊ እየሆነ መምጣቱን የሚገልጽ ነበር።

የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን ዓለምን ለመድረስ የሚያስችለው የመምህሩ ዕቅድ በሚገባ እንደሚሠራ አረጋግጣለች ማለት ይቻላል። ምስክርነታቸው ያሳድር ከነበረው ታላቅ ተጽዕኖ የተነሣ ክፍለ ዘመኑ ከመጠናቀቁ በፊት በጊዜው የነበረው ጣዖት አምላኪ ኅብረተሰብ ከመሠረቱ ተናግቶ ነበር። ዋና ዋና በነበሩት የሕዝብ ማዕከሉችም በየጊዜው እድገት የሚያሳዩ አብያተ ክርስቲያናት ተተክለዋል። የወንጌል ስርጭት መጀመሪያ በተነሣበት በዚያ ፍጥነት ቀጥሎ ቢሆን ኖሮ፣ በጥቂት ምእተ ዓመታት ውስጥ የዓለም ሕዝብ ሁሉ የጌታን የምሕረት እጅ ባወቀ ነበር።

## አቋራጭ መንገዶች አልዘለቁም

ነገር ግን አሁን ጊዜው ተቀይሮአል፣ እናም ቀስ በቀስ ቀላል የነበረው የክርስቶስ የወንጌል ስርጭት ስልት አዲስ መልክ መያዝ ግድ ሆኖበታል። በእርግጥ፣ ሁኔታዎች ሲለወጡ እንደየሁኔታዎቹ መርሖዎችን ማስተካከል ሁልጊዜ አስፈላጊ ነው። ነገር ግን በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ «ለወንጌል ሰባኪው» የተለየ ገጽታ ለመስጠት በመሻት መርሖዎቹ ራሳቸው ተዘበራርቀዋል። ትልቅ ዋጋ ያላቸው መሪን የማሳደግና የመብዛት መርሖዎች ቀላል በሆነው በጀማ ምልመላ ስልት የተዋጡ ይመስላል። በሰው ዘንድ



ተቀባይነት በማግኘት ላይ ያተኮረው የቅርቡን ብቻ የሚያስበው ዓላማ ዓለምን መድረስ የረጅም ርቀት ግቡ ካደረገው መርሕ ይልቅ ዛሬ ቅድሚያ ስለተሰጠው በቤተ ክርስቲያን፣ በግለሰብም ሆነ በኅብረት እየተንጸባረቀ ያለው የወንጌል ስርጭት ስልት ይህንኑ መልክ ተከትሎ እንደሚጓዝ ይታያል። በታላላቅ መንፈሳዊ መነቃቃቶች አንዳንድ ጊዜ እንደሚሆነው፣ የክርስቶስ ስልት መርሕ ቅድሚያ ያገኛል፣ ነገር ግን የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ሳስተዋለው እንዲህ ያሉት ጊዜያት ዕድሜያቸው አጭር ከመሆኑም በላይ በአብዛኞቹ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ዘንድ ብዙም ትኩረት አልተሰጣቸውም። የኢየሱስ ዕቅድ ቸል ተብሎ ሳይሆን፣ ከነአካቴው እርግፍ ተደርጎ ተትቷል። ቀድሞ የነበረው ለመዘከር ያህል ይታወስ ይሆናል እንጂ፣ አሁን ላለው ሥራ እንደ ተግባር መመሪያ ትኩረት የተሰጠው ጉዳይ አይደለም።

## ዛሬ እየሆነ ያለው

ዛሬ ያለብን የአሠራር ችግር ይህ ነው። በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በተሞሉ ሰዎች ብቻ የሚሠራውን ሥራ በበጎ ተነሣሽነት በሚካሄዱ ሥነ ሥርዓቶች፣ በፕሮግራሞች፣ በድርጅቶች፣ በተልዕኮዎችና በሰው ቅልጥፍና በሚፈጸሙ ዘመቻዎች በቀራጥነት ውጤት ለማምጣት ይሞከራል። ይህ ሲባል ግን እነዚህን የተቀደሱ ጥረቶች ለመንቀፍ አይደለም፣ ምክንያቱም ያለ እነዚህ ተግባራት ዛሬ ቤተ ክርስቲያን አሁን እየሠራች ያለችውን ያህል እንኳን መሥራት አትችልም ነበር። ይሁን እንጂ፣ እነዚህ ዕቅዶች የጌታን አገልግሎት ተልዕኮ በሙላት ካላካተቱ ባሏቸው መመሪያዎችና መዋቅሮች ሁሉ ውስጥ ቤተ ክርስቲያን መሥራት እንደሚገባት ልትሠራ አትችልም።

የወንጌል ስርጭት በሰዎች አማካኝነት እንጂ በሆኑ ክንውኖች

አማካኝነት እንደማይሠራ የምንረዳው መቼ ይሆን? ወንጌል የእግዚአብሔር ፍቅር መግለጫ ነው፣ እግዚአብሔር ደግሞ እኔነት ያለው ነው። ሕልውናው በማንነቱ የሚገለጽ በመሆኑ፣ መጀመሪያ በክርስቶስ በሙላት የተገለጸ ሲሆን፣ አሁን ደግሞ በመንፈስ ቅዱስ በኩል ሕይወታቸውን ለእርሱ በሰጡ ሕያዋን ውስጥ ይገለጣል። ኮሚቴዎች ይህን ነገር ለማስተባበርና ለመምራት ያገለግላሉ፣ በዚህም ረገድ በእርግጥ አስፈላጊዎች ናቸው፣ ሥራው ግን የሚሠራው በክርስቶስ እንዲያምኑ ሌሎችን ሰዎች በሚደርሱ ሰዎች ነው።

ለዚህም ነው ከኢ. ኤም. ቦንድስ ጋር አብረን «ሰዎች የእግዚአብሔር ስልቶች ናቸው» ልንል የሚገባን። እንደዚህ ያሉ መንፈስ ቅዱስ ከሕይወታቸው ጋር የተዋኸደና ለዕቅዱ ራሳቸውን የሰጡ ሰዎች እስከሌሉን ድረስ፣ የትኛውንም ዓይነት ዘዴ ብንቀይስ ዋጋ ቢስ ነው።

የሚያስፈልገን አዲስ የወንጌል ስርጭት ይህ ነው። የሚያስፈልገን የተሻለ ዘዴ ሳይሆን ከግል ልምምዳቸው የተነሣ ቤዛ የሆናቸውን ጌታ የሚያውቁ የተሻሉ ወንዶችና ሴቶች፣ ለዓለም ያለው ፍቅሩ የሚሰማቸው የእርሱን ራእይ የሚያዩ ወንዶችና ሴቶች፣ እርሱ ሁሉን ይሆን ዘንድ ኢምንት ለመሆን ፈቃዳቸውን የሰጡ ወንዶችና ሴቶች፣ ክርስቶስ እንደ መልካም ፈቃዱ በእነርሱ ውስጥና በእነርሱ አማካኝነት ሕይወቱን እንዲያበዛ ብቻ የሚፈልጉ ወንዶችና ሴቶችን የያዘ ዘዴ ነው። ዓላማው በምድር ላይ ተቀባይነትን እንዲያገኝ ጌታ የተጠቀመበት የመጨረሻው ስልት ይህ ነው። በዚህ መልኩ የእርሱን ስልት ተከትለን የምንጓዝ ከሆነ፣ ዓለምን በወንጌል የመድረሱን ሩጫ የሲኦል ደጆች ፈጽመው ሊቋቋሙት አይችሉም።

አልፋና ዖሜጋ እኔ ነኝ
ዮሐንስ ራእይ 1:8

# ዝክረ ታሪክ

# መምህሩና የአንተ ዕቅድ

## ሕይወት ዕቅድ አለው

ለሕይወትህ ያለህ ዕቅድ ምንድን ነው? ማንም ሰው የራሱ በሆነ አንድ ዕቅድ ሊኖር ይገባል:: ዕቅድ ማለት የሕይወታችንን ዓላማ ከግብ ለመድረስ የሚያስችል የተቀናጀ መርሕ ነው:: ከእያንዳንዱ እንቅስቃሴአችን በስተጀርባ ዕቅድ እንዳለ ላናውቅ ወይም ዕቅድ እንዳለን እንኳ ትዝ ላይለን ይችላል:: የምናደርጋቸው ነገሮች በራሳቸው በጉዳዮቻችን ማዕከላዊ ስፍራ ላይ አንድ ዓይነት ሥርዓት እንዳለ መግለጣቸው አይቀሬ ነው::

ሙሉ በሙሉ ራሳችንን በጉዳዩ ውስጥ አስገብተን ግባችን ምን እንደ ሆነና ያንንም ለመጨበጥ እንዴት መጓዝ እንዳለብን ማየት ስንሞክር የምናገኘው ነገር አጥጋቢ ላይሆን ይችላል:: ነገር ግን በታማኝነት የምንወስደው ግለ ሂስ (ግላዊ ምዘና) ሁላችንን ለጥሪያችን ግድ እንዲለን ማድረግ መቻል ይኖርበታል:: ቢያንስ ቢያንስ የክርስቶስ አሠራር መንገድ እያንዳንዱ የምንሠራው ሥራ ልንመዝንበት የሚገባ መመሪያ ነው ብለው ለሚያምኑ ይህ እውነት ሊሆን ይገባል::

ትልቅ ቦታ የሰጠናቸውን ራሳችን ያቀናበርናቸውን ዕቅዶች ልንለውጣቸው ምናልባትም ከነ አካቴው ልንተዋቸው ያስፈልግ ይሆናል:: ከዚህ እኩል አስቸጋሪ የሚሆነው ምእመናኑ ጌታ ለዚህ አገልግሎት ካለው እይታ ጋር ራሳቸውን ማስተካከል መቻላቸው ነው:: በየትኛውም አማራጭ ሁኔታ ቢሆን ለስኬት ያለንን

አጠቃላይ አስተሳሰብ ግን በድጋሚ ልናጤነው ያስፈልጋል:: የሆነ ሆኖ፣ እዚህ ላይ የቀረቡት መርሖዎች ተገቢዎች ናቸው ካልን እንደ ተግባራዊ መመሪያ ተደርገው ሊወሰዱ ይገባቸዋል:: በሕይወታችን እውነተኛ የሆነ ትርጉም የሚኖራቸው በዕለት ተዕለት የሥራ ሕይወታችን ውስጥ ተግባራዊ ስናደርጋቸው ብቻ ነው:: ትክክለኛ መንገዶች ናቸው ካልን ደግሞ አግባብነት አላቸው ማለታችን ነው::

## ስልቶች ይለያያሉ

እንግዲህ እያንዳንዳችን በመረጥናቸው የወንጌል ስርጭት ስልቶች ውስጥ የክርስቶስን ስልት ጥበብ የምናካትትበትን አንድ ዓይነት ዘዴ ልንቀይስ ይገባል:: ሁሉ ሰው አንድ ዓይነት ሥርዓት ወይም ቅንጅት እንዲከተል አይገደድም፣ ወይም ሁሉ አንድ ዓይነት ይዘት እንዲይዝ ልንፈልግ አይገባንም:: ልዩነት በተፈጥሮ አወቃቀር ሥርዓት ውስጥ ተካትቶ የሚገኝ ነው:: እግዚአብሔር ሊጠቀምበት የወደደው ማንኛውም ዓይነት ስልት ጥሩ ስልት ነው ማለት ነው:: ይህ ማለት ግን የበለጠ ለማሻሻል እኛ የምንጨምረው ነገር አይኖርም ማለት አይደለም:: ጌታ ልንከተለው የሚገባንን ንድፈ-አሳብ ሰጥቶናል፣ በዙሪያችን ካለው ሁኔታና ከባህል ጋር አጣምረን ዝርዝር ሁኔታውን ግን እኛ እንድናሟላ ይጠበቅብናል:: ይህ ደግሞ ያለንን እምቅ ችሎታ እስከ መጨረሻዋ እንድንጠቀም የሚጠይቅ ነገር ነው:: ሁኔታዎች መልካቸውን በቀየሩ ቁጥር አዳዲስና ግልጽ የሆኑ አቀራረቦችን ልንሞክር ያስፈልጋል:: የተሞከረ ሁሉ ግን ይሠራል ማለት አይደለም:: ሥራውን ሊሠራ እየፈለገ ለመውደቅ ግን ፈቃደኛ ያልሆነ ሰው መቼም ቢሆን ሥራውን አይጀምርም፣ ደግሞ ደጋግሞ መሞከር የሚፈራም ሰው የሚያሳየው እድገት እምብዛም ነው::



## ቅድሚያ ለሰዎች

ስልታችን ምንም ዓይነት አካሄድ ይከተል፣ የክርስቶስ ሕይወት ግን ሰዎችን የሚደርሱ ሌሎች ሰዎችን መምረጡና ማሠልጠኑ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ ተግባር እንደ ሆነ ያስተምረናል:: ሕያው የሆኑ ምስክሮችን እስካላገኙ ድረስ በውጭ ያሉት ወንጌልን ሊያውቁ አይችሉም:: ለእነርሱ መግለጫ መስጠት ብቻ በቂ አይደለም:: ግራ በመጋባት ውስጥ ያሉት የዚህች ዓለም ሰዎች ሊያምኑት ስላለው ነገር ተጨባጭ የሆነ መረጃ ሊያቀርብላቸው የሚችል ሰው ይሻሉ:: በመካከላቸውም ቆሞ «ተከተሉኝ፣ መንገዱን እኔ አውቀዋለሁ» የሚል መካሪ ሊያገኙ ይገባቸዋል:: ዕቅዶቻችን ሁሉ ሊያተኩሩ የሚገባው እንግዲህ እዚህ ላይ ነው:: ከዚህ ውጪ ትኩረቶቻችን ሁሉ ምንም ያህል መንፈሳዊ ቢሆኑም እንኳ፣ የምናደርጋቸው ነገሮች ሁሉ ዘለቄታዊ ጥቅም የሚታየው ይህንን ተልዕኮ ምን ያህል በሚገባ ያስፈጽማሉ ከሚለው መመዘኛ አንጻር ይሆናል::

ይሁን እንጂ፣ ኢየሱስ የሚፈልገው ዓይነት ኃይል በድንገት እንደማይከሰት ልናስተውል ይገባል:: በጥንቃቄ ማቀድና የተጠናከረ ጥረት ማድረግ ይጠይቃል:: ሰዎችን የምናሠለጥን ከሆነ፣ እነርሱን ለማዘጋጀት መሥራት ይኖርብናል:: ሄደን ልንፈልጋቸው፣ ማርከን ልናመጣቸው፣ ከሁሉ በላይ ደግሞ፣ ልንጸልይላቸው ይገባል:: አንዳንዶች በቤተ ክርስቲያን በሥልጣን ላይ ያሉ፣ ሌሎች ደግሞ ወደ ክርስቶስ ለመምጣት የግብዣውን ጥሪ በመጠባበቅ ላይ የሚገኙ ሊሆኑ ይችላሉ:: የትም ሆኑ የት፣ ለጌታችን ውጤታማ ምስክሮች እንዲሆኑ ወደ እነርሱ በመሄድ ልናሠለጥናቸው ይገባል::

## ጥቂቶችን መያዝ

ለመጀመር ብዙ ሕዝብ መጠበቅ የለብንም፣ እንዲያውም ብዙ

ሕዝብ ልንፈልግም አይገባንም:: ምንጊዜም ጥሩ ሥራ የሚሠራው በጥቂቶች ነው:: ፕሮግራም እንዳይስተጓጎል ያህል ከመላው ምእመን ጋር ዕድሜ ልካችንን ከመቆየት፣ ሌሎችን ለክርስቶስ መማረክ ምን ማለት እንደ ሆነ ከምናስተምራቸው አንድ ወይም ሁለት ሰዎች ጋር ለአንድ ዓመት ወይም ከዚያ በላይ መቆየቱ የተሻለ ነው:: ጅማሬው ትንሽና ተስፋ አስቆራጭ መሆኑ ችግር የለውም:: ቁም ነገሩ በሕይወታችን ቅድሚያ የሰጠናቸው እነዚህ ሰዎች የተቀበሉትን ለሌሎች ማካፈል መማራቸው ላይ ነው::

ይህ ማለት ግን ደቀ መዛሙርትን በማፍራቱ ሥራ ላይ የምንሳተፈው እኛ ብቻ ነን ማለት አይደለም:: ሌሎች ሰዎችም ለምሳሌ እናቶች፣ አባቶች፣ ሚስቶች፣ ባሎች፣ ልጆች፣ የቤት ክርስቲያን ሠራተኞች፣ መምህራን፣ ጓደኞችና የመሳሰሉት የሚሰጡት አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ ምስክርነት በሕይወታቸው ላይ የሚያሳድረው የራሱ የሆነ አስተዋጽኦ አለው:: ለአንድ የተወሰነ ጊዜ፣ በክርስቲያናዊ እድገታቸው ላይ ወሳኝ ተጽዕኖ የምናሳድረው እኛ ብቻ ልንሆን እንችላለን::

ጠለቅ ብለን ካየነው፣ በእርግጥ፣ መሪዎቹ እኛ ሳንሆን ክርስቶስ ነው:: ይህ ደግሞ በጣም ግልጽ ሊሆንልን ይገባል:: ደቀ መዛሙርትን በማፍራቱ ሥራ ላይ አንዱ የበላይ ሊቅ በመሆን የፈላጭ ቆራጭነት ሥልጣንን ለመያዝ ቦታ የለውም:: ስለሆነም ትኩረታችን ሁሉ በኢየሱስ ላይ ይሁን:: በመንፈሱና በቃሉ አማካኝነት ይመራናል:: ለእርሱ በመገዛት፣ ደቀ መዝሙርና ደቀ መዝሙር አድራጊው በኢየሱስ እግሮች ሥር ሆነው ይማራሉ::

## አብሮ መቆየት

ይህንን ለማድረግ ብቸኛው ተጨባጭ ዘዴ አብሮነት ነው:: እየተከተሉን ያሉት ሰዎች ሊሆኑ ያሉትን በእኛ ውስጥ ማየት



ካለባቸው፣ አብረናቸው ልንሆን ግድ ነው:: የዕቅዱ ፍሬ ነገር ያለው እንግዲህ እዚህ ላይ ነው- ራእያችንን እንዲካፈሉንና ከዕለት ተዕለት ልምምዳችን ጋር ራእያችን ምን ያህል የተሳሠረ እንደ ሆነ እንዲያዩ ማድረግ መቻላችን ነው:: ከዚህም የተነሣ የወንጌል ስርጭት በሁሉ ነገር ውስጥ ተግባራዊ ሲደረግ የሚችልና በሌሎች ሁኔታዎችም ላይ የሚንጸባረቅ ጉዳይ እየሆነላቸው ይመጣል:: ወንጌል የሥነ መለኮት አስተምህሮ ሳይሆን፣ እንደ አንድ የሕይወት ዘይቤ ይሆንላቸዋል:: በተጨማሪም፣ ከእኛ ጋር በቆዩ መጠን፣ በሥራው ውስጥ ተሳታፊ የመሆናቸው ጉዳይ አይቀሬ ይሆናል::

## ጊዜ ስጧቸው

በእርግጥ፣ እንደ ማንኛውም ዋጋ ያለው ነገር ሁሉ፣ እንዲህ ያለው ዕቅድም ጊዜን የሚጠይቅ ይሆናል:: ነገር ግን ትንሽ ብናስብበት፣ ለማንኛውም ማድረግ የሚገቡንን ብዙ ነገሮችን ከእነርሱ ጋር አብረን ማድረግ የምንችልበትን ዘዴ መቀየስ እንችላለን:: ለምሳሌ፣ አብረናቸው ጉብኝት ማካሄድ፣ ወደ ኮንፍራንሶች መሄድ፣ መዝናናትና እንዲያውም አብረን የጽሞና ጊዜን ልንወስድ እንችላለን:: ይሁን እንጂ፣ አብረን የምንሆንባቸው ጊዜያት እንደ ትልቅ ሸክም ሊሆኑ አይገባም:: ንቁዎች ከሆንን፣ ለሌሎች አገልግሎት በምንሰጥባቸው ወቅቶች፣ ደቀ መዝሙሮቻችን ከእኛ ጋር ሲሆኑ፣ አንዳንድ ጊዜም፣ ሰፋ ባሉ የወንጌል ስርጭት አገልግሎታችን ሲረዱን ይችላሉ::

## በቡድን መሰባሰብ

ሆኖም፣ ይህ የወንጌል ስርጭት ዘዴ ዘለቄታዊ አቋም እንዲኖረው፣ ቡድኑ፣ በሙላትም ሆነ በከፊል፣ ከእኛ ጋር የሚሰባሰብበትን የተለዩ ወቅቶች ማመቻቸት ሳያስፈልግ አይቀርም:: በእነዚህ ምንም መደበኛ ባልሆኑ የስብሰባዎቻችን ወቅቶች መጽሐፍ

ቅዱስ ልናጠና፣ ልንጸልይና በአጠቃላይ ጥልቅ የሆኑ የውስጥ ጥያቄዎቻችንን እርስ በርስ ልናካፍል እንችላለን:: ምን እየተደረገ እንዳለ ማወጅ ወይም መጀመሪያ ላይ ዕቅዳችን ምን እንደ ሆነ ለቡድኑ መንገሩ አስፈላጊ አይደለም:: ስብሰባዎቹ ኅብረት ለማድረግ ከመነጨ የጋራ ፍላጎት ብቻ በመነሣት እንዲያድጉ አድርጉ:: ከዚያም በቤተ ክርስቲያን የአሠራር ዘይቤ መሠረት ቡድኑ የራሱ የሆነ ሥርዓቶችን ሊያበጅ ይችላል::

ይህ የቡድን አሳብ ዛሬ በብዙ ቦታዎች ቀድሞ የነበረውን ትኩረት እያገኘ ነው:: ከዚህም የተነሣ በወንጌል ስርጭት ረገድ መነቃቃት እንደሚመጣ ከሚያሳዩ ምልክቶች አንዱና ተስፋ ሰጪ የሆነው ምልክት ሊሆን ይችላል:: በማንኛውም የሕይወት ጎዳናና በማንኛውም ዓይነት ቤተ ክርስቲያናዊ ግንኙነቶች ውስጥ አነስ አነስ ያሉ መንፈሳዊ ድርጅቶች በየቦታው ብቅ ብቅ እያሉ እንደ ሆነ እናያለን:: አንዳንዶቹ ገና የሚጓዙበትን ትክክለኛ አቅጣጫ ለማግኘ ት ሲታገሉ፣ አንዳንዶቹ ደግሞ ከመሥመር ወጣ ያሉ ሲሆን፣ በአጠቃላይ ግን እነዚህ እንቅስቃሴዎች ተጨባጭ ለሆነ ክርስቲያናዊ ልምምድ በሰው ልብ ውስጥ ያለውን ታላቅ መሻት የሚያሳዩ ናቸው:: ውጫዊ ከሆነ ሥርዓት ወይም ውሱን ሕግጋት ነፃ ስለሆኑ፣ በእነዚህ ትንንሽ ማኅበሮች መካከል ሰፊ የትኩረትና የይዘት ልዩነት አለ:: ነገር ግን ሥርዓትን የጠበቀና የተሳሰረ ኅብረትን ማካሄድ በአብዛኞቹ ዘንድ ያለ የጋራ መርሕ ነው:: ይህ መርሕ ማዕከላዊ መሆኑ የስልቱን እድገት እንዲፋጠን ያደርገዋል:: ስለሆነም ሁላችንም በአገልግሎታችን ውስጥ ብንጠቀምበት የበለጠ ውጤታማ እንሆናለን::

ዛሬ በዓለም እውቅ የሆኑት የወንጌል ሰው፣ ዶ/ር ቢሊ ግርሃም፣ ቤተ ክርስቲያን በአግባቡ ልትጠቀምበት ከቻለች በዚህ ዕቅድ ውስጥ ታላቅና የታመቀ ኃይል እንዳለ መገንዘባቸው ትልቅ



ትኩረት ሊነፈገው አይገባም:: «በአንድ ዋና ከተማ ውስጥ የአንድ ትልቅ ቤተ ክርስቲያን መጋቢ ቢሆኑ የተግባር መመሪያዎ ምን ይሆን ነበር?» ተብለው ለቀረበላቸው ጥያቄ ዶ/ር ግርሃም ሲመልሱ:- «በመጀመሪያ በሳምንት ለጥቂት ሰዓታት በመገናኘት ዋጋ የሚከፍሉ ስምንት፣ አሥር ወይም አሥራ ሁለት ሰዎችን ያቀፈ ትንሽ ቡድን ከእኔ ጋር እንዲሠራ የማሰባሰብ ይመስለኛል! በጊዜና በጥረት ረገድ ለእነዚያ ሰዎች ዋጋ ሳያስከፍላቸው አይቀርም:: የሆነ ሆኖ፣ የቀሰምሁትን ሁሉ ለተወሰኑ ዓመታት አካፍላቸዋለሁ:: ከዚያ ከምእመኑ መሀል ሌሎች እያንዳንዳቸው ስምንት፣ አሥር፣ ወይንም አሥራ ሁለት ሰዎችን ይዘው የሚያስተምሩ አሥራ ሁለት አገልጋዮች ይኖሩኛል ማለት ነው:: ይህንን የሚያደርጉ አንድ ወይም ሁለት አብያተ ክርስቲያናትን አውቃለሁ:: ይህም እርምጃ አብያተ ክርስቲያናትን ታላቅ ወደ ሆነ የለውጥ ጎዳና እያመጣቸው ነው:: ክርስቶስ ሥርዓቱን ያስቀ-መጠልን ይመስለኛል:: ሰፋ ያለውን ምድራዊ ዘመኑን ያሳለፈው ከአሥራ ሁለቱ ሰዎች ጋር ነበር:: ከብዙ ሕዝብ ጋር በመሆን ጊዜውን አላባከነም:: እንዲያውም፣ ብዙ ሕዝብን ባስከተለባቸው ጊዜያት ብዙ ውጤት የታየ አይመስለኝም:: አሁንም እኔ እንደሚመስለኝ ታላላቆቹ ውጤቶች የተመዘገቡት ከሰዎች ጋር በግል በነበረው የውይይት ጊዜና ከአሥራ ሁለቱ ጋር ባሳለፋቸው ጊዜያት ነው::» እንግዲህ እዚህ ላይ እንደምናየው ቢሊ ግርሃም የክርስቶስን ስልት በሚገባ እያስተጋቡ ነው::

## ውጤት ጠብቁባቸው

ሰዎችን ቤተ ክርስቲያን ከመግለጫዎቹ አንዷ በሆነችበት አንድ ዓይነት የቡድን ኅብረት ውስጥ እንዲሳተፉ ማደረጉ ብቻ በቂ አይደለም:: የተማሯቸውን ነገሮች የሚገልጡበት አንድ ዓይነት ዘዴ

ሊቀየስላቸው ይገባል:: ወጥተው እንዲመሰክሩ ሁኔታዎች ካልተመቻቹ፣ ቡድኑ በራሱ ውስጥ ባለው ኅብረት በመርካት እርስ በርሱ የሚሞጋገስበት ስብስብ ሆኖ ይቀራል:: ዓላማችንን ግልጽ ልናደርግ ይገባል:: ከዓለም ተለይተን የምንወጣባቸው ጊዜያት ጦርነቱ የሚቆምባቸው ጊዜያት ሳይሆኑ፣ ከፊት ይልቅ አብልጠን ማጥቃት እንድንችል ኀይልን የምንታጠቅባቸው ስልታዊ እንቅስቃሴዎች ናቸው::

የምናሠለጥናቸው ሰዎች በውስጣቸው ያለውን የመጨረሻ ችሎታ የሚጠይቅ አንድ የሚሠሩት ሥራ ሰጥተናቸው እንደ ሆነ የማረጋገጡ ተግባር የእኛ ድርሻ ነው:: ማንኛውም ሰው የመሥራት ችሎታ አለው:: መጀመሪያ የምንሰጣቸው ሥራ የተለመደውን ዓይነት አካሄድ የተከተለና ቀለል ያለ እንደ ደብዳቤ መላክ፣ አንዳንድ የስብሰባ ስፍራዎችን ማዘጋጀት፣ ወይም አንዳንዴ ወደ ቤታቸው ወስደው እንዲያስተናግዱን ማድረግ ሊሆን ይችላል:: የበለጠ መሥራት እየቻሉ በሄዱ ቁጥር እነዚህ ኃላፊነቶችም እየጨመሩ ይሄዳሉ:: የማስተማር ስጦታ ያላቸው በሰንበት ትምህርት ቤት ውስጥ ሊሰማሩ ይችላሉ:: ብዙም ሳይቆይ በአስተማማኝ ሁኔታ ችሎታቸውን በሚመጥን የመጋቢነት አገልግሎት ላይ ልንሾማቸው እንችላለን:: ብዙዎቹ ለታመሙት ስልክ ሊደውሉላቸው ወይም በተኙበት ሆስፒታል ሄደው ሊጎበኟቸው ይችላሉ:: ሌሎች ደግሞ እኛ በተጋበዝንበት የስብከት አገልግሎት እኛን ተከትለው ሊሄዱ ወይም በቅርብ ያለን የመድረክ አገልግሎት ሊሸፍኑ ይችላሉ:: ማንኛውም ሰው በግል የወንጌል ስርጭት እንጻር የራሱ የሆነ የሥራ ድርሻ እንዲሰጠው ይሻል::

ምናልባትም አዳዲስ ነፍሳትን ከመከታተል ባሻገር በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ሌላ ጠቃሚ የሆነ አስተዋጽኦ እያደርጉ ይሆናል:: እነርሱ ሲማሩበት በነበረውና እነርሱ በተጓዙበት



በተመሳሳይ ጎዳና በክርስቶስ ሕጻናት የሆኑትን ሰዎች በመምራት በዚህ የአገልግሎት ዘርፍ ምትክ የማይገኝለት ሚና ይጫወታሉ:: በመሆኑም ለዚህ ሥራ ያሠለጠንናቸው ሰዎች ቤተ ክርስቲያን የምታካሂደውን ማንኛውንም ዓይነት የወንጌል ሥራ አጽንተው መቀጠል የሚያስችሉ ቁልፍ ሰዎች ይሆናሉ:: ስለሆነም የእነርሱ አስተዋጽኦ ወደ ፊትም ያለውን እድገት መጠበቅ ብቻም ሳይሆን የስርጭቱንም ቀጣይነት ያስተማምናሉ::

## እንዲገፉበት እርዱአቸው

እንግዲህ በእነዚህ ሰዎች የግል የሕይወት ዕድገትም ሆነ ከሌሎች ጋር ባላቸው ሥራ አጠቃላይ ሂደቱ ብዙ ክትትልን የሚጠይቅ ይሆናል:: ከእነርሱ ጋር መገናኘትንና ነገሮች በምን ሁኔታ ላይ እንዳሉ ከእነርሱ መስማትን ልማድ ልናደርገው ያስፈልጋል:: ይህ ማለት ደግሞ ያሉበትን ሁኔታ መጠየቅና ከእኛው ጋር ሌላ ሥራ እየሠሩ ሳሉ ማማከር ማለት ነው:: ችግር ያስከተለው ክስተት ትዝታው ሳይደበዝዝና ገናም ከአእምሮአቸው ሳይጠፋ ከገጠመኞቻችው ላጋጠሟቸው ጥያቄዎች ወዲያው ምላሽ ሊሰጣቸው ያስፈልጋል:: የተሳሳቱ አመለካከቶቻቸውም ሆነ አካሄዳቸው በጊዜ ሊታዩና በሚገባ ሊታረሙ ያስፈልጋል:: ከዚሁ ጋር ተመሳሳይ በሆነ መልኩ፣ አስከፊ የግል ልማዶቻቸው፣ መሠረተ ቢስ የሆኑ አስተሳሰቦቻቸውና ማንኛውም ዓይነት ከሰውና ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን የክህነት አገልግሎት የሚያደናቅፍ ነገር ሁሉ በጊዜ ሊታረም ይገባዋል::

ዋናው ነገር በጸጋና በእውቀት ማደጋቸውን እንዲቀጥሉ መርዳቱ ላይ ነው:: ከሰብዓዊ የማስታወስ ችሎታችን አንጻር በሥልጠናቸው ወቅት ሊሸፍኑት ይገባቸዋል ለምንላቸው ትምህርቶች ዕቅድ ብናወጣና የቀረ ነገር እንደሌለ እርግጠኛ

ስመሆንም በየጊዜው የሚያሳዩትን መሻሻል መዝግበን ብንይዝ የተሻለ ነው። በተለይ እያንዳንዳቸው በተለያየ የዕድገት ደረጃ ላይ ካሉ ከብዙ ሰዎች ጋር በአንድ ጊዜ በምንሠራበት ጊዜ ይህ በጣም ያስፈልገናል። በአብዛኛው እድገታቸው በጣም አዝጋሚና በብዙ መሰናክሎች የተከበበ የመሆን ዕድሉ ከፍ ያለ ስለሆነ ትዕግሥትን ልንለማመድ ያስፈልጋል። ነገር ግን እውነትን ለማወቅ በታማኝነት እስከ ተጉና፣ ለዚህ እውነት ለመታዘዝ ፈቃደኞች እስከ ሆኑ ድረስ፣ አንድ ቀን በክርስቶስ ወደ ሆነ ብስለት ማደጋቸው አይቀርም።

## ቀንበራቸውን እንዲሸከሙ እርዱአቸው

ምናልባትም ከመላው የሥልጠና ሂደት ከባድ የሆነው ክፍል አስቀድመን ችግሮቻቸውን የማወቃችንና ሊገጥማቸው ወይም ሊጋፈጡት ላለው ነገር የማዘጋጀታችን ጉዳይ ነው። ይህ እጅግ በጣም አስቸጋሪና ትዕግሥት አስጨራሽ ነው። ይህ ማለት ለአፍታ እንኳ ከአእምሮአችን ልናወጣቸው አንችልም ማለት ነው። ደቀ መዛሙርቶቻችንን በግል የጽሞና ጊዜያችንም ሆነ በጥናታችን ጊዜ በጸሎታችንና በህልማችን ሁሉ መካተታቸው አይቀሬ ነው። ግን ልጆቹን የሚወድ ወላጅ ከዚህ በተለየ መልኩ እንዲሆን ይፈልጋል እንዴ? ገና በራሳቸው መሸከም የሚችሉበት ጊዜ እስኪመጣ ድረስ ያልበሰሉባቸው ወቅቶች የሚያስከትሉብንን ቀንበር እኛ ልንሸከም ይገባል። በተለይም በመጀመሪያዎቹ የዕድገት ወራቶቻቸው የሚገጥማቸውን ማንኛውንም ነገር በራሳቸው መወጣት ይችላሉ ብሎ ማሰብ ውድቀትን መጋበዝ ነው። በጣም አስተዋዮች መሆን አለብን። አሳዳጊያቸውና መካሪያቸው እንደ መሆናችን መጠን፣ መንፈሳዊ ልጆቻችንን ለጌታ እንዴት መኖር እንዳለባቸው የማስተማር ኃላፊነት አለብን።



## እንዲቀጥሉ አድርጓቸው

የምናደርገው ማንኛውም ነገር እነዚህን የተመረጡ ወንዶችና ሴቶች እንደ ዝንባሌያቸው የየራሳቸውን የአገልግሎት መስክ ወደሚረከቡበት ወቅት የሚመራ መሆን አለበት። ይህም ቀን እየደረሰ በሄደ ቁጥር እያንዳንዳቸው በእነርሱ ምስክርነት ለክርስቶስ በማረኳቸው ወይም እንዲከታተሉአቸው ከተሰጧቸው ሰዎች ጋር በሥልጠናው ፕሮግራም ደህና እርምጃ ማሳየት ይኖርባቸዋል። ቀስ በቀስ እኛ የተጠቀምንበትን ስልት ሳይታወቃቸው በተግባር አውለውት ይገኛሉ። ይሁን እንጂ፣ ተድበስብሶ የቀረ ነገር እንዳይኖር የነበረንን ኃላፊነት ከማውረዳችን በፊት ከመጀመሪያ የነበረንን ዕቅድ በሚገባ ልናሳውቃቸው ያስፈልጋል። ሕይወታቸውን ይመዝኑበት ዘንድ ብሎም በቀጣይ ሊረዷቸው በሚፈልጓቸው ሰዎች ውስጥ ማስረጽ ይችሉ ዘንድ ሁሉ ነገር ግልጽ ሆኖ በአእምሮአቸው ሊቀመጥ ያስፈልጋል።

## ከሁሉ በላይ መንፈሳዊ ልምምድ

በእርግጥ በጣም ወሳኙ ነገር፣ የራሳቸው መንፈሳዊ ልምምድ ነው። ከእኛ ውጪ ከመሆናቸው በፊት ዓለምን የማሸነፍ ኃይል ባለው እምነት በሚገባ ሊታነጹ ያስፈልጋል። በሲኦል ያሉትን የመናፍስት ኃይላት ሁሉ በማስተባበር፣ ሰይጣን በሚያገኘው የማታለያ ዘዴ ሁሉ ተጠቅሞ ሊያሸንፋቸው ይጥራል። ለተልዕኮ የሚወጡበት ይህ ዓለም በእርሱ እኩይ ቁጥጥር ሥር ነው። ተጀምሮ እስኪያበቃ በውጊያ ሜዳ ላይ ናቸው። ጠላት መቼም ቢሆን እጁን ስለማይሰጥ፣ እያንዳንዱን የመሻሻል እርምጃ በድል አድራጊነት ልንወርወስ ይገባናል። ይህንን ፈተና ተቋቁሞ ለመጽናት በክርስቶስ መንፈስ ከመሞላት ያነሰ ምንም ነገር በቂ አይደለም።

ወደ እርሱ ተጠግተው እየኖሩ በእርሱ ቅድስናና ኃይል ወደ ፊት መጓዝ ካልቻሉ፣ እነርሱን ለማጥፋት በሚረባረቡ ኃይላት በቀላሉ ይጠቃሉ፣ የእኛም ልፋት መና ሆኖ ይቀራል።

የሠራነው ሁሉ በእነዚህ ሠራተኞች ታማኝነት ላይ የተመሠረተ ነው። ምን ያህል ሰዎችን ለክርስቶስ ምርኮ አድርገው አመጡ የሚለው እንጂ፣ ለዚህ ዓላማ ምን ያህል ሰዎች መዘገብን የሚለው ምንም ዋጋ የለውም። ለዚህ ነው ተጀምሮ እስኪያበቃ ትኩረታችን የሕይወት ጥራት ላይ መሆን ያለበት። ተገቢውን ጥራት የያዘ አመራር ካገኘን፣ ሌላው ነገር ሁሉ ይህንን ተከትሎ ይመጣል። ይህን መሳዩን አመራር ካላገኘን፣ ሌላው ሊከተለው የሚበቃ ምንም የረባ ነገር አይኖርም።

## የድል ዋጋ ከፍተኛ ነው

እውነት ለመናገር፣ እንዲህ ከፍተኛ ደረጃ ያለውን ነገር መጠበቅ ከፍተኛ ዋጋን ይጠይቃል። ምናልባትም አብረውን ለአገልግሎት የሚወጡ ሰዎች ከመጠን ያለፈ ነው ብለው ስለሚያስቡ መንገድ ላይ በፍርሀት ወድቀው ይቀራሉ። እኛም አሁን ይህንኑ ብንጋፈጠው ክርስቲያናዊ አገልግሎት ብዙ የሚጠይቀው ነገር አለ። ሰዎችም ለእግዚአብሔር ጠቃሚ ሆነው መገኘት ከፈለጉ፣ አስቀድመው መንግሥቱን ሊሹ ይገባል። አዎ፣ የሚያበሳጩ ነገሮች ይኖራሉ። ይህንን በድል ተወጥተው፣ በእርሻው ማሳ ላይ የእኛን ሕይወት ለሌሎች ለማሳየት የሚወጡ ሰዎች፣ ዓመታት ባለፉ ቁጥር ደስታችንን የሚያልቁ የሐሴት ምንጮቻችን ይሆናሉ።

እየኖርን ያለነው በዋናነት ለዛሬ አይደለም። የምንረካው በቀጣዩ ትውልድ ውስጥ ስለ ክርስቶስ የሰጠነው ምስክርነታችን በእነርሱ አማካኝነት ፈጽሞ በማይቋረጥ ሁኔታ ይህኛው



ለሚቀጥለው እያቀበለ እስከ ምድር ዳር ድረስ እስከ ዘመኑ ማብቂያ ፍሬን እያፈራ መገስገስ ላይ መሆኑን በማወቃችን ነው።

## ይሄ የአንተ ራእይ ነውን?

ዛሬ ዓለም የሚከተለውን ሰው በታላቅ ጉጉት በመፈለግ ላይ ነው። መቼም አንድን ሰው መከተላቸው አይቀሬ ነው፣ ግን ያ የሚከተሉት ሰው የክርስቶስን መንገድ የሚያውቅ ሰው ነው? ወይስ ያ ሰው የእነርሱ ቢጤ የሆነና ወደ ድቅድቅ ጨለማ የሚመራቸው ነው?

የሕይወት ዕቅዳችን ወሳኙ ጥያቄ ይህ ነው። ዛሬ የምናደርገው የማንኛውም ነገር አግባብነት እንደ ሠራነው መጠን ብያኔ ያገኛል፣ ይህንንም ተከትሎ፣ የሕዝቦች ሁሉ ዕጣ ፈንታ ሥራችን በሚኖረው ዋጋ በሚዛን ላይ ይቀመጣል።

# የወንጌል ስርጭት ቁልፍ ዕቅድ

## የጥናት መመሪያ

### በሮይ ጂ. ፊሽ

## መግቢያ

በዚህ ዘመን ወንጌልን ለሌሎች የሚያሰራጩ ወንጌላዊ ክርስቲያኖች ከሚያጋጥሟቸው አሳሳቢ ችግሮች አንዱ ከወንጌል ስርጭት አጠቃላይ ስልት ጋር የተያያዘ ነው። የዚህ የጥናት መመሪያ መሠረታዊ ዓላማ በአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ የምናገኘውንና በሮበርት ኢ. ኮልመን በተጻፈው የወንጌል ስርጭት ቁልፍ ዕቅድ መጽሐፍ ውስጥ የተብራራውን የኢየሱስን የወንጌል ስርጭት ስልት በሚገባ ሰዎች ይረዱት ዘንድ ለማገዝ ነው። የጥናት መመሪያው ማዕከላዊ ግቦች የሚከተሉት ናቸው፡-

1. የኢየሱስን ስልት ለማግኘት ጥረት በማድረግ ወንጌላትን በጥልቀት መመርመር።
2. እርሱ ያስቀመጣቸውን መርሖዎች ትርጓሜያቸውንና ጠቀሜታቸውን በድጋሚ ማየት ወይም መመልከት።
3. ለስልቱ ከፍተኛ መሰጠት እንዲኖር ወደሚያስችለው መንገድ ማመልከት።
4. የእርሱን ስልት በሕይወታችን ተግባራዊ ወደምናደርግበት መንገድ ማመላከት ነው።

ይህንን የጥናት መመሪያ እንደሚገባ እንዴት መጠቀም ይቻላል የሚለውን ጥያቄ በተመለከተ፣ እነዚህን ሁለት አሳቦች መመልከቱ



ጠቃሚ ሳይሆን አይቀርም። አንደኛ ይህ የጥናት መመሪያ ሲዘጋጅ በእጃችሁ እርሳስ ይዛችሁ በላዩ ላይ እየጻፋችሁ ማጥናት እንድትችሉ በማሰብ የተዘጋጀ ነው። ሁለተኛ ለማመሳከሪያ እንዲሆናችሁ አዲስ ኪዳን በአጠገባችሁ ይሁን።

መመሪያው በውስጡ 13 ትምህርቶችን ይዟል። እያንዳንዱ ትምህርት በይዘቱ ተመሳሳይነት አለው። በመጀመሪያ፣ የምዕራፉ ወይም ሊጠና ያለው የመጽሐፉ የተለየ ክፍል አጠቃላይ አሳብ ይኖራል። ይህ ክፍል የምዕራፉን ማዕከላዊ አሳብ ወይም በዋነኝነት ሊያሳውቅ የፈለገውን ነገር ያስቀምጥና ወደ ምዕራፉ መሠረታዊ የትምህርት ግብ ትኩረትን ይስባል። ከዚያም በመቀጠል «የመማር ሂደት» በሚለው ርእስ ሥር የምዕራፉን ዋነኛ አሳብ ለመፈለግ እንዲያስችል ታስበው የተዘጋጁ ጥያቄዎችን የያዘውን ክፍል እናገኛለን። በአንድ ጊዜ መሠራት ያለበት አንድ ምዕራፍ ብቻ ነው። ከተቻለ አንድ ጊዜ ቁጭ ብሎ አንድን ትምህርት ለመጨረስ በቂ ጊዜ መመደብ ያስፈልጋል። የጥያቄዎቹ መልሶች በሚያስፈልጉን ጊዜ ከመጽሐፉ መመሪያ መጨረሻ ገጽ ማግኘት ይቻላል።

ከዚህ ክፍል ቀጥሎ የምናገኘው ለቡድን ውይይትና ለቡድን ተግባራት የሚሆኑ አሳቦችን የያዘውን ክፍል ነው። ይህንን ክፍል በቡድን በሚያጠኑበት ጊዜ ቡድኑ በአንድነት ከመሰባሰቡ በፊት «የመማር ሂደት» በሚለው ርእስ ሥር በቀረቡት ጥያቄዎች እያንዳንዱ የቡድኑ አባል መልስ ቢሰጥባቸው ጠቃሚ ይሆናል።

የዚህ ጥናት ዋነኛ ዓላማ የክርስቶስን ዕቅድ በአንባቢው ሕይወት ውስጥ ተግባራዊ እንዲሆን ማድረግ ነው። ስለሆነም ማንኛውም ሰው በግሉ ተግባራዊ ያደርገው ዘንድ ለማበረታታት እያንዳንዱ ትምህርት አንዳንድ የስኬት የመድረሻ ግቦችንና ሂደቶችን

ያመለክተናል። በእያንዳንዱ ምዕራፍ ማጠቃለያ ላይ ከምዕራፉ ጋር አግባብ ያላቸው ለተጨማሪ ጥናት የሚጠቅሙ አሳቦችን የያዘ አጠር ያለ ክፍል አለ። ይህ የጥናት መመሪያ ለሕይወታችሁ ታላቅ በረከት እንዲሆንና የመምህሩን ዕቅድ በግል ሕይወታችሁ በመረዳትና ተግባራዊ ለማድረግ እንዲያስችላችሁ ከጸሎት ጋር ቀርበላችኋል።

ሮይ ጄ. ፊሽ



# ትምህርት 1
## መምህሩና ዕቅድ

በዛሬይቱ ቤተ ክርስቲያን የጌታችንን ታላቁን ተልዕኮ ለመታዘዝ የመፈለግ ተሐድሶ ያለ ይመስላል። ይህንን ፍላጎት ተከትሎም ለአዳዲስና ቀልጣፋ ለሆኑ የወንጌል ስርጭት ስልቶች ከፍተኛ ትኩረት እየተሰጠ ይገኛል። ይሁን እንጂ፣ እየተነቃቃ ከሚታየው ፍላጎትና ቀልጣፋ ከሆኑት ስልቶች ጎን ለጎን ይበልጡኑ ወሳኝ የሆነና ፈጣን ምላሽን የሚፈልግ ነገር ተከሰተ። ይሄውም ወሳኝ ጉዳይ ከስልት ጋር በተለይም መሠረታዊ ከሆነው ከራሱ ከኢየሱስ የወንጌል ስርጭት ስልት ጋር የተያያዘ ነገር ነው።

ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ በተመላለሰ ጊዜ በሚገባ የታሰበበት የወንጌል ስርጭት ስልት እንደ ነበረው ትንሽ ጥያቄ እንኳ የሚያስነሣ ሐቅ ነው። «የጠፉትን ሊፈልግና ሊያድን» (ሉቃስ 19:10) እንደ መጣ በሚገባ ጠንቅቆ ያውቅ ነበር። ሕይወቱንም ይመራ የነበረው በዚህ መርሕ ነበር። ኢየሱስ የተናገረው ወይም ያደርግ የነበረው ነገር ሁሉ ለእርሱ ከመለኮታዊው የወንጌል ስርጭት ስልቱ አንዱ ክፍል ነበረ። የዛሬይቱ ቤተ ክርስቲያን ሳታስተውለው ልታልፍ የማይገባት ነገር ቢኖር ኢየሱስ ዕቅዱን እየተገበረ ሳለ፣ ቤተ ክርስቲያን በዘመናት ሁሉ የምትገለገልበትን የወንጌል ስርጭት ስልትም በዚያው እያመለከታት ነበር።

ስለሆነም፣ አዲስ ስልትን መፈለስፍ የቤተ ክርስቲያን ተግባር አይደለም። የእኛ ተግባር የእርሱን ስልት በሚገባ በመረዳት በተግባር ላይ ማዋል ነው። የቀድሞውን አሠራር የሙጥኝ ማለታቸውና የዘመኑንም የሃይማኖት ባህል ተቀብለው በመንዛቸው

ብዙ አብያተ ክርስቲያናትን የኢየሱስን ስልት ከመረዳት እንደ አገዳቸው የሚያሳዩ በርካታ መረጃዎች አሉ:: ስልቱን እንደሚገባ ከተገነዘብነው፣ እጅግ ልዩ ከመሆኑ የተነሣ የሚያስከትለው ግንዛቤ ሥር ነቀል ከመባል ያላነሰ ሆኖ እናገኘዋለን:: ነገር ግን ወንጌልን ለማሰራጨት በምናደርገው ጥረታችን የእርሱን ልዩ በረከት እንቀበል ዘንድ በተቻለን መጠን የመምህሩ ስልት ተግባራዊ ሊሆን የሚችል መሆኑን በአሳባችን መቀበል አለብን:: አላስፈላጊ የሆኑ ሃይማኖታዊ ተግባራትን መተውና እንደ ቅዱስ የቆጠርናቸውን አንዳንድ ድርጅታዊ አሠራሮችን መለወጥ ቢጠይቅ እንኳ፣ ያንን ለማድረግ ዋጋ ልንከፍልና ስልቱን ተግባራዊ ልናደርግ ይገባል::

## የመማር ሂደት

1. «የወንጌል ስርጭት ቁልፍ ዕቅድ»ን ማውጫ ለአንድ ደቂቃ ገደማ ተመልከቱ:: ከዚህ በታች የየምዕራፎቹ አርእስት ቅደም ተከተላቸውን ባልጠበቀ መልኩ ተቀምጠዋል:: ትክክለኛውን ቅደም ተከተል ካጠናችሁ በኋላ፣ ትክክለኛውን ቅደም ተከተል ማስቀመጥ ትችሉ እንደ ሆነ እራሳችሁን ፈትኑ:: የማውጫውን ዝርዝር በድጋሚ ተመልከቱና ከእናንተ ቅደም ተከተል ጋር ስታስተያዩት እንደሚከተለው መሆኑን አረጋግጡ::

   አመራርና ቁጥጥር __________

   ውክልና__________

   ምርጫ __________

   መተባበር __________

   ለአገልግሎት መቀደስ __________

   መባዛት __________

   ክህሉትን ማካፈል__________



   በተግባር ማሳየት __________

2. ጸሐፊው በገጽ 1 ላይ ስለ «ቤተ ክርስቲያን የወንጌል ስርጭት እንቅስቃሴ» ይናገራል:: የእናንተን የወንጌል ስርጭት ትርጓሜ ከዚህ በታች ጻፉ::

3. ዶክተር ኮልመን «ስልት» የሚለውን ቃል ሲጠቀሙ ከዚህ በታች ከተጠቀሱት ሦስት ቃላት እርሳቸው ማለት ከፈለጉት አሳብ ጋር በይበልጥ ተስማሚ የሆነው የትኛው ቃል ነው?

   ዓላማዎች ______

   ዘዴዎች ______

   መርሖዎች ______

4. የወንጌል ስርጭትን በተመለከተ ከታተሙት መጻሕፍት ሁሉ የሚልቀው መጽሐፍ ______ ነው::

5. የሚከተሉትን «የእውነት/ሐሰት ጥያቄዎች» እውነት ከሆነ «እ»፣ ሐሰት ከሆነ ደግሞ «ሐ» በማለት ከጥያቄዎቹ ፊት ለፊት ባለው ባዶ ቦታ ላይ በመሙላት መልሱን ጻፉ::

   ሀ. ኢየሱስ በአገር ውስጥና ከአገር ውጭ በሚደረገው የተልዕኮ አገልግሎት መካከል ግልጽ የሆነ ልዩነት አስቀምጧል:: __________

   ለ. ኢየሱስ ሰዎችን ለማሠልጠን የተጠቀመባቸው ስምንቱ መርሖዎች ያለመዛነፍ የታቀደላቸውን ቅደም ተከተል ጠብቀው የቀረቡ ነበሩ:: ______

   ሐ. በወንጌል ስርጭት ውስጥ ዘዴና ስልት በመሠረቱ ትርጓሜአቸው አንድ ነው:: ______

# የቡድን ውይይትና ተግባራት

ይህ የቡድን ውይይት የሚያተኩረው እርስ በርሳቸው ተያያዥነት ባላቸው 4 ጥያቄዎች ላይ ነው:: በምትወያዩባቸውም ጊዜ እዚህ ላይ የቀረበውን ቅደም ተከተላቸውን በመጠበቅ ሊሆን ይገባል::

1. ኢየሱስ ከተናገረው ነገር በመነሣት የቤተ ክርስቲያን ተቀዳሚ ዓላማ ምን እንደ ሆነ ተወያዩ:: በማቴዎስ 28:19፣ በዮሐንስ 20:21 እና በሐዋ. ሥራ 1:8 የሚገኙትን ታላላቅ ተልዕኮዎች ተመልከቱ::
2. የቤተ ክርስቲያናችሁን ወይም የክርስቲያናዊ ቡድናችሁን ሁኔታ በሚገባ ተመልከቱና የቤተ ክርስቲያናችሁን ወይንም የክርስቲያናዊ ቡድናችሁን ዓላማዎች ከኢየሱስ ዓላማ ጋር አነጻጽሩ::
3. ከዚህም በኋላ እንዲህ ብላችሁ ራሳችሁን ጠይቁ:- የቤተ ክርስቲያናችን ወይም የቡድናችን መዋቅርና እንቅስቃሴ እውነት የኢየሱስን መሠረታዊ ዓላማ ለማስፈጸም የተዘጋጀ ነው?
4. ቤተ ክርስቲያናችሁ ወይንም ቡድናችሁ ከጌታችን ዓላማ ጋር ከሞላ ጎደል በተገቢ ሁኔታ መቀራረብ ይችል ዘንድ መደረግ ያለባቸው ለውጦች ምንድን ናቸው?

## የመድረሻ ግቦች

በዚህ ጥናት መግቢያ ላይ፣ በወንጌል ስርጭት ረገድ ቀድሞ የነበራችሁን ስኬት ፈትሹ:-

1. ሌሎች ሰዎችን ለእርሱ ለመማረክ በማሰብ ስለ ክርስቶስ እናገራለሁ

   ሁልጊዜ------

   አንዳንድ ጊዜ --------

   አልፎ አልፎ----------

   ተናግሬ አላውቅም-----

2. አማኞች በክርስትና ሕይወታቸው ወደ በለጠ ብስለት እንዲያድጉ ለማገዝ እሞክራለሁ

   ሁልጊዜ -------

   አንዳንድ ጊዜ -------

   አልፎ አልፎ-----

   አግዤ አላውቅም ------

3. ራሳችሁን ጠይቁ:- በግል ሕይወቴ የራሴ የሆነ የወንጌል ስርጭት ስልት አለኝ? ከሌለኝስ፣ የእርሱ ስልት አካል ለመሆን ፈቃደኛ ነኝ?



# ትምህርት 2

## ምርጫ

አንድ ሰው የመምህሩን ስልት በሚያስብበት ጊዜ፣ በቀላልነቱ ከመገረም በቀር ምንም ሊያደርግ አይችልም:: «በጥቂቶች ላይ ያተኩረ» የሚለው ሐረግ ጥሩ አድርጎ ይገልጸዋል:: በጣት የሚቆጠሩ ሰዎችን እንዲከተሉት እንደ ዋዛ በጠራበት በመጀመሪያ ወቅት ግራ የሚያጋባ አልነበረም:: በዚህ ትንሽ ቡድን ውጫዊ ብቃት ላይ ማንም የተደነቀ አይመስልም:: እውነቱን ለመናገር፣

ተራ ሰዎች ቢሆኑም እንኳ፣ መማር የሚችሉ ነበሩ:: በዚህ ታናሽ ቡድን ላይ ነበር ኢየሱስ የምድር ላይ አገልግሎቱን ያተኰረው::

ጥቂቶችን በማገልገል ዓላማ ኢየሱስ አያሌውን ሕዝብ ጨርሶ ቸል ብሏቸው ነበር ተብሎ በፍጹም ሊታሰብ አይገባም:: ለሰፊው ሕዝብ የነበረው ራእይ ምንጊዜም ከፊቱ ነበር:: ወንጌላትም ሕዝቡን ሲያገለግል እንደ ነበር የሚያመለክቱ ታሪኮችን አዘውትረው ዘግበዋል:: ነገር ግን ኢየሱስ ሕዝቡ ለዘለቄታ የሚሆን እርዳታ ከማግኘቱ በፊት እርሱ ለብቻው ሊደረግላቸው ከሚችለው በላይ የሆነ እንክብካቤ እንደሚያስፈልጋቸው ጠንቅቆ ተረድቶ ነበር:: የእርሱም እውነተኛ የአገልግሎት ተስፋ የተመሠረተው በኋላ ሕዝቡን ሁሉ በእግዚአብሔር ነገር ሊመራ የሚችልን ታናሽ ቡድን በማሠልጠን ላይ ነበር::

ይህ የኢየሱስ አካሄድ የአንድ መንፈሳዊ መሪ የመጀመሪያ ኃላፊነት የወንጌል አገልግሎት የሚታነጽበትን መሠረት መጣል ላይ መሆን እንደሚገባው ሊያስተምረን ይገባል:: እንዲህ ያለውን መሠረት መጣል በጥቂቶቹ ጊዜና ችሎታ ላይ ማተኰርን ይጠይቃል:: የዚህ መሳዩ ዕቅድ ውጤት ዝግ ብሎ የሚመጣና ምናልባት በብዙዎች ትኩረት የማይሰጠው ቢሆንም፣ በስተ መጨረሻ በዚህ ስልት አማካኝነት የሚሠራው መልካም ሥራና በወንጌል የሚደረሱ ሰዎች ብዛት ግን በጣም ታላቅ ነው::

## የመማር ሂደት

1. ከዚህ በታች ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከተሰጡት ሦስት ምርጫዎች ትክክለኛውን መልስ በመምረጥ ዙሪያውን ክበቡት::



ሀ. አብዛኞቹ ደቀ መዛሙርት የመጡት ከገሊላ ነው:: ከይሁዳ ሳይመጣ እንዳልቀረ የሚገመተው ደቀ መዝሙር ——— ነው::

ቶማስ፣ ይሁዳ፣ ጴጥሮስ

ለ. ለሞት አልፎ በተሰጠበት ጊዜ የኢየሱስ ታማኝ ተከታዮች የነበሩት —— ይደርሱ ነበር::

100፣ 500፣ 10,000

ሐ. ከተመረጡት የሐዋርያት ቡድን ውስጥ በተለይ ሦስቱ ከመምህሩ ጋር ይበልጥ የተለየ ኅብረት ነበራቸው:: ከእነዚህ ከሦስቱ አንዱ —— ነበር::

እንድርያስ ማቴዎስ ዮሐንስ

2. ከዚህ በታች በተሰጡት ባዶ ቦታዎች ትክክለኛውን ቃል ሙሉ:: መልሶቹን ለማግኘት ምንባቡን ተመልከቱ::

ሀ. የኢየሱስ ዋነኛ ትኩረት ሕዝቡን በወንጌል በሚደርስበት - ——— ላይ ሳይሆን፣ ሕዝቡ በሚከተሉት ——— ላይ ነበር::

ለ. የመጀመሪያው የኢየሱስ ዕቅድ ——— ሲሆን፣ ከዚያ በኋላ ወደ አባቱ ተመልሷል::

ሐ. በኢየሱስ የተመረጡት ሰዎች በጸሐፊው ሲገለጹ ——— ፣ ———፣ ——— ሲሆኑ፣ በአካባቢያቸው ያለው ——— ሁሉ የሚታይባቸው ሰዎች ነበሩ::

መ. አንድ ሰው ——— በዓለም ካለው ——— በስተቀር ——— መለወጥ አይችልም———፣ በመምህሩ እጅ ተይዘው መልክ እንዲይዙ ካልተደረጉ በቀር ——— ሊለወጡ አይችሉም::

3. የሚከተሉትን የእውነት ወይም ሐሰት ጥያቄዎች መልሳቸው

እውነት ከሆነ «እ» ወይም መልሳቸው ሐሰት ከሆነ «ሐ» በማለት ከጥያቄዎቹ ፊት ለፊት ባሉት ባዶ ቦታዎች ላይ ሙሉ።

————ሀ. ኢየሱስ አብዛኛውን ጊዜውን ለአሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት በመስጠት ለሕዝቡ ብዙም ግድ እንደሌለው አሳይቷል።

————ለ. ኢየሱስ አሥራ ሁለቱ እንዲከተሉት ያደረገላቸው ጥሪ በጊዜው በነበረው ሃይማኖታዊ እንቅስቃሴ ላይ ቅጽበታዊ ተጽዕኖ አሳድሮ ነበር።

————ሐ. ኢየሱስ በአገልግሎት የሚጠቀምባቸውን መሠረታዊ መርሖዎች በሚገባ የሚገልጸው «ትኩረት» የሚለው ቃል ነው።

# የቡድን ውይይት እና ተግባራት

1. ከመጽሐፍ ቅዱስ 2ኛ ጢሞ. 2:2ን ተመልከቱና ኢየሱስ ከተጠቀመበት ስልት ጋር ስላለው ተመሳሳይነት ተወያዩበት። ይህን መርሕ እንዲገልጽላችሁ ሥዕል ሣሉ።

   ጳውሎስ ጢሞቴዎስ የታመኑ ሰዎች ሌሎች

2. በገጽ 26 ላይ፣ ዶክተር ኮልመን «የወንጌል ስርጭት ውጤታማነት የሚመዘነው በተለወጡ ሰዎች ቁጥር ብዛት ከሆነ፣ እንግዲያው ኢየሱስ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ በጀማ የወንጌል አገልግሎት ውጤታማ ተብለው ሊጠቀሱ ከሚችሉት አንዱ ተደርጐ እንደማይቆጠር አያጠራጥርም» ብለዋል። ይህ እውነት ከሆነ፣ ኢየሱስን «ታላቁ ወንጌላዊ» አድርገን የምንወስደው ከምን አንጻር ነው? በዚህ ከተወያያችሁ በኋላ «ስልቱ» በሚለው ርእስ ከገጽ 26-28 የቀረበውን አንብቡ።

3. «በጥቂቶች ላይ ማተኮር» በሚለው መርሕ ላይ ሊኖሩ በሚችሉት ተቃውሞዎች ላይ ተወያዩባቸው።

4. «እስከ ዛሬ ሆኖ ባልታወቀ መልኩ በቤተ ክርስቲያን የሆነ የወንጌል ስርጭትን ማከናወን የሚያስችሉ ፈጣን የግንኙነት ሁኔታዎች በተመቻቹበት በዚህ ዘመን ዓለምን ለእግዚአብሔር ለመማረክ ፈረስ የሌለው ጋሪ በነበረበት ዘመን ይከወን ከነበረው ያነሰ ውጤት በማሳየት ላይ እንገኛለን።» በሚለው አሳብ ላይ ተወያዩበት።

## የመድረሻ ግብ

1. ከአንድ አዲስ ወይም ገና እንደሚገባ ካላደገ ክርስቲያን ጋር ኅብረት ማድረግ የምትችሉባቸውን አጋጣሚዎች በማስታወሻችሁ ላይ በዝርዝር ጻፏቸው። አንዳንዶቹ አጋጣሚዎች ቀደም ሲልም ዝግጁ ሆነው የተቀመጡ ሊሆኑ ይችላሉ። ለምሳሌ፣ በሰንበት ትምህርት ቤት ውስጥ በአንድ ክፍል የሚያስተምር አስተማሪ ወይም ዲያቆን፣ ሽማግሌም መጋቢ ከሆናችሁ ለጥቂት አባላት ኃላፊነት ሊኖርባችሁ ይችላል። ሌሎች ዕድሎችን ግን ማቀድ ይኖርባችኋል።

2. አብራችሁት ልትሠሩና ወደ ደቀ መዝሙርነት ሕይወት ልትመሩት ወደምትችሉት ቢያንስ ወደ አንድ ሰው እንዲያመለክታችሁ እግዚአብሔርን ጠይቁ።

3. በዚህ ሰው ውስጥ ልታገኙ የምትፈልጓቸውን ነገሮች አስቀድማችሁ ወስኑ።

4. በዚህ ሰው ሕይወት ውስጥ ተፈጽመው ማየት የምትፈልጓቸውን አንዳንድ ነገሮች በማስታወሻችሁ በጽሑፍ ያዙ።

# ትምህርት 3

## መተባበር

የኢየሱስ የሥልጠና መርሐ ግብር ፍሬ ነገር የሚያተኩረው በደቀ መዛሙርቱ ከእርሱ ጋር በመሆን ላይ ነው። ዓለምን ለመማረክ ሰዎችን ያሠለጠነው እነርሱን ወደ ራሱ ስቦ ለማስጠጋት ብቻ ነው። መጀመሪያ ከእርሱ ጋር አብረው በመሆን ተማሩ። እርሱ በመካከላቸው ከመገኘቱ የተነሣ ሊማሩ የሚፈልጉትን ነገር ሁሉ ሊማሩ እንደሚችሉ ኢየሱስ ያውቃል። ስለሆነም የኢየሱስ የአገልግሎት ዘመን ወደ ሁለተኛውና ሦስተኛው ዓመት እየተራዘመ ሲሄድ የሚበልጠውን ጊዜውን ለ12ቱ መስጠቱ የሚያስገርም አይደለም። እርሱ አደረጋቸው ተብለው የተዘገቡትን ነገሮች ሁሉ ያደርግ የነበረው ቢያንስ ጥቂት ደቀ መዛሙርቱ ባሉበት ነበር። ከእነርሱ ጋር በመሆን የሰዎችን ሕይወት ያንጽ ነበር።

የዛሬይቱ ቤተ ክርስቲያን ይህንን መርሕ ለመረዳት ረጅም ጊዜ ወስዶባታል። የበሰሉ ክርስቲያኖች የአማኞችን ዕድገት ለመከታተል ያደረጉት ጥረት ባልበሰሉት ክርስቲያኖች በኩል የሚፈለገውን ዓይነት የግል ትኩረት ሊያሳይ አልቻለም። ሰዎችን እንደሚገባ መንከባከብ የሚያስችል ዘዴ ካለመኖሩ የተነሣ በየጊዜው ወደ የአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናቱ ከሚቀላቀሉት 50 በመቶ የሚሆኑት የኋላ ኋላ ፍሬ አልባዎች ይሆናሉ። በመኪና የመገጣጠሚያዎች ዓይነት አሠራር ደቀ መዛሙርትን ለማፍራት ጥረት ተደርጓል፣ ውጤቱ ግን ትልቅ - ጉስቁልናን ያስከተለ ነበር። እያንዳንዱ/ዷ



አዲስ ክርስቲያን በአንድ በበሰለ አማኝ ጥላ ሥር የሚሆንበትንና/የምትሆንበትና ሌላን ሰው መምራት ወደሚችልበት/ወደምትችልበት ብስለት እስኪደርስ/እስክትደርስ እርሱ ወይም እርሷ ከእርሱ ጋር የሚቆዩበት አንድ ስልት መገኘት አለበት። እንዲህ ላለው የክትትል አገልግሎት ሰዎችን ማሠልጠን እንዲህ ያለው መርሐ ግብር ቀደም ሲል የሌላት እያንዳንዷ ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት ልትጋፈጠው የሚገባት ወቅታዊና አስገዳጅነት ያለው ጉዳይ ነው።

## የመማር ሂደቶች

1. ደቀ መዛሙርት ከኢየሱስ ጋር የነበራቸውን የአብሮነት ጊዜ ለማሳየት በሉቃስ ምዕራፍ ስምንት እና ዘጠኝ ላይ ከእርሱ ጋር በመሆን ያሳለፏቸውን ቢያንስ ከአሥር በላይ የሚሆኑ ልምምዶችን እናገኛለን። ከእነዚህም ውስጥ ቢያንስ ለ8 ጊዜ ያህል እርሱ ሲሠራ የማየት ዕድል ነበራቸው። እነዚህን 8 ጊዜያት ጥቀሱ።

________________ ________________

________________ ________________

________________ ________________

________________ ________________

2. ባዶ ቦታዎችን በትክክለኛው መልስ ሙሉአቸው።

ሀ. የኢየሱስ የሥልጠና መርሐ ግብር መሠረታዊው አሳብ ——— ነበር።

ለ. እውቀት በ——— ከመገኘቱ አስቀድሞ በ———

———ተገኝቶ ነበር::

ሐ. በአሥራ ሁለቱ ከታየው የክትትል ምሳሌ በተጨማሪ ሌሎቹ ሦስት ምሳሌዎች ———፣ —————— እና —— ——— ነበሩ::

3. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ በመምረጥ አክብቡ::

ሀ. ኢየሱስ በሁለተኛውና በሦስተኛው የአገልግሎቱ ዓመታት (የሚበልጠውን) (ያነሰውን) ጊዜውን ለአሥራ ሁለቱ ይሰጥ ነበር::

ለ. በየጊዜው ወደ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናቱ ከሚጨመሩት በግምት (1/5) (1/3) (1/2) የሚሆኑት ወደ ኋላ ይመለሳሉ::

ሐ. ኢየሱስ ከትንሣኤው በኋላ ለአሥር ጊዜ ያህል የተገለጠው (ያምኑ ዘንድ ለማያምኑት) (ለደቀ መዛሙርትና ለአይሁድ መሪዎች) (ለደቀ መዛሙርት ብቻ) ነበር::

## የቡድን ውይይትና ተግባራት

1. የቤተ ክርስቲያናችሁን ወይም የቡድናችሁን ጠቅላላ አባላት ቁጥር ያዙና ከዚህ በታች በተሰጡት አሳቦች ላይ ተወያዩ:-

ሀ. ከአባሎቻችን ምን ያህሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ወይም የሰንበት ትምህርት ይከታተላሉ?

ለ. ከመቶኛ ሲታሰብ ምን ያህሉ አባላት በአምልኮ ፕሮግራሞች ላይ በታማኝነት ይገኛሉ?

ሐ. ምን ያህሉስ በጸሎት ፕሮግራሞች ላይ ይገኛሉ?

መ. በአንድ ዓይነት የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ውስጥ ምን ያህሉ ይሳተፋሉ?

ረ. በእነዚህ ጥያቄዎች ያገኛችሁት መልስ አነስተኛ ከሆነ፣ ለምን ይህን ያህል ጥቂቶች ሆኑ? በሚለው ላይ ተወያዩ::

## የመድረሻ ግብ

1. አብሯችሁ የሚሠራውን ሰው ከመረጣችሁ በኋላ፣ የመጀመሪያውን ግንኙነት መቼ ታደርጋላችሁ?

2. ከዚህ ሰው ጋር በየስንት ጊዜ አብራችሁ ለመሆን አስባችኋል?

3. ለዚህ ሰው በምትሰጡት አገልግሎት የመጀመሪያው እርምጃችሁ ምንድን ነው?

# ትምህርት 4

## ለአገልግሎት መቀደስ

ኢየሱስ ከተከታዮቹ የሚፈልገው የመጀመሪያው ነገር ለእርሱ ለመታዘዝ ያላቸውን ፈቃደኝነት ነው:: እርግጥ አንዳንዶቹ በጣም አስተዋዮች ነበሩ:: ነገር ግን ከእነርሱ የሚፈልገው ዋነኛው ነገር አስተዋይነትን አልነበረም:: ጌታችን ከምንም በላይ አጥብቆ ይፈልግ የነበረው ለእርሱ ያላቸውን ታማኝነት ነበር:: ታማኝ ሆኖ መገኘት ከባድ እየሆነ በሄደበት ጊዜ እንኳን እርሱ ግን ታማኝነታቸውን መፈለግ አላቋረጠም:: ደቀ መዝሙሩ ለመሆን አንድ ሰው ሲያደርግ

የሚገባውን ሁኔታና የሚጠበቅበትን ነገር ማስቀመጥ የእርሱ መብት እንደ ሆነ አዘውትሮ ይናገር ነበር:: ነገር ግን ከእነርሱ የሚፈልገውን የመታዘዝ መንፈስ በእርሱ ዘንድ በማየታቸው ከእርሱ ጋር መቆየት ግድ ሆነባቸው::

በመታዘዝ ወደ ተሻለ እውቀት መድረስ እንደሚቻል ኢየሱስ ያውቅ ነበር:: ደቀ መዛሙርቱ ሊታዘዙት ፈቃደኞች ሆነው እስከ ተገኙ ድረስ ስለ እርሱ እውነቶችን የመማራቸው ወይም የማወቃቸው ጉዳይ በጊዜው እንደሚመጣ ተገንዝቧል:: በቅድሚያ ተከታይ መሆንን ያልተማረ ሰው መሪ ሊሆን አይችልም:: የባሕርይና የዓላማ እድገት የሚመጣው በመታዘዝ ውስጥ ብቻ እንደ ሆነ ያውቅ ነበር:: ለዚህም ነበር ሊታዘዙት ፈቃደኛ እስከ ሆኑ ድረስ ብዙውን ሰብዓዊ ድካሞቻቸውን በትዕግሥት ያለፈው::

በዛሬይቱ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አሳሳቢ የሆነ ለክርስቶስ ጌትነት የመገዛት አስፈላጊነት ይታያል:: አስፈላጊው ዋጋ ሁሉ ተከፍሎ መታዘዝ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል የሚለው መልእክት የቤተ ክርስቲያን የተሐድሶ መልእክት መታወቂያ ሊሆን ይገባል:: ሰባኪዎችም ሆኑ ተራው ምእመን የክርስቶስን ትእዛዛት ቸል የማለቱን ነገር ማቆም ይኖርባቸዋል:: ይህ ጉዳይ ሊፈወስ የሚገባው ነገር ነው:: ምናልባትም አብያተ ክርስቲያናት በተሰጡ ጥቂት ሰዎች የተዋጣ የወንጌል ስርጭት መጀመር ይኖርባቸው ይሆናል:: እነዚህም ጥቂት ሰዎች ትንሽ ቁጥር ያላቸውን ሰዎች ወደ ራሳቸው ሊስቡና ለዚህ ቡድን ለክርስቶስ የመታዘዝን እውነተኛ ትርጉም ሊያስርጹ ይችላሉ:: እንደዚህ ያለው እንቅስቃሴ ቢያንስ እንደ መነሻ ይሆናል::

## የመማር ሂደት



1. በሉቃስ 9:57-62 ላይ እርሱን ለመከተል ፈልገው ወደ ኢየሱስ የመጡትን ሦስት ሰዎች እናገኛለን:: ኢየሱስ ለእያንዳንዱ የሰጠውን ምላሽ በእናንተ አገላለጽና መረዳት አብራሩት:: ከዚያ በገጽ 47-50 ያለውን ተመልከቱ::

   ሀ. ____________________

   ለ. ____________________

   ሐ. ____________________

2. (ሀ) «ደቀ መዝሙር» ለሚለው ቃል የምትሰጡት የእናንተ ትርጓሜ ምንድን ነው?

   (ለ) የዶክተር ክልመንስ ትርጓሜ ምንድን ነው?

3. ለክርስቶስ ላለን እውነተኛ ፍቅር ማረጋገጫ የሚሆነው መሠረታዊው ነገር ምንድን ነው?

4. ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያኑን ወደ ድል ይመሩአት ዘንድ መሪዎችን እያሠለጠነ እንደ ነበር ማስታወስ ይገባል:: አንድ ሰው (አንዲት ሴት) ደግሞ መሪ -------- ካልተማረ/ች------- በቀር ፍጹም መሆን አይችልም/ አትችልም::

5. በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ለደቀ መዝሙርነት ወሳኝ የሆኑ ሦስት ነገሮች ተጠቅሰዋል:: ጥቅሶቹን እያያችሁ ከፊት ለፊታቸው በተሰጠው ቦታ ላይ ጻፏቸው::

   ሀ. ዮሐንስ 8:31 ____________________

   ለ. ዮሐንስ 13:35 ____________________

   ሐ. ዮሐንስ 15:8 ____________________

6. ኢየሱስ በእያንዳንዱ ክርስቲያን ሕይወት ክፍል ውስጥ ጌታ ሊሆን ይገባል። ከዚህ በታች የተዘረዘሩት በክርስቲያን ሕይወት ውስጥ ከምናገኛቸው የሕይወቱ ክፍሎች አንዳንዶቹ ናቸው። ከተሰጡት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ጋር አዛምዷቸው።

| | |
|---|---|
| ንብረት | ሀ. መዝሙረ ዳዊት 19:14 |
| ዘመን | ለ. ማቴዎስ 6:19-21 |
| ንግግር | ሐ. ቈላስይስ 3:18-21 |
| አስተሳሰብ | መ. ኤፌሶን 5:15-16 |
| የቤተሰብ ሕይወት | ሠ. ፊልጵስዩስ 4:8 |

## የቡድን ውይይትና ተግባራት

1. «ራስን መስጠት» በሚለው በቃሉ ትርጉም ላይ ተወያዩ። ከዚያ የቻላችሁትን ያህል በአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ራስን ስለ መስጠት የተጠቀሰባቸውን ክፍሎች ለማስታወስ ሞክሩ።
2. የተዋወቃችኋቸውን ክርስቲያኖች አስቡና ከእነዚያ ውስጥ ራስን ስለ መስጠት ምሳሌ የሚሆኑ ካሉ ለማግኘት ሞክሩ።
3. በመጽሐፉ ገጽ 54 ጸሐፊው ለእግዚአብሔር ፈቃድ ኢየሱስ የነበረውን መሰጠት የሚያሳዩ በርካታ ክፍሎችን ዘርዝሯል።

   ዮሐንስ 4:34፤ ዮሐንስ 5:30፤ ዮሐ. 15:10፤ ሉቃስ 22:42። እነዚህ ክፍሎች ለኢየሱስ ምን ማለት እንደ ሆኑ ተወያዩባቸው።
4. በአንድ ሰው ሕይወት ውስጥ ክርስቶስ ጌታ መሆኑ ከምስክርነት አገልግሎቱ ጋር እንዴት ይገናኛል?
5. በምታውቋቸው ክርስቲያኖች መካከል ክርስቶስን ችላ ማለት በስፋት የሚታይ ከሆነ፣ ይህንን ሁኔታ ለመቀየር ምን እርምጃ መውሰድ ይኖርባችኋል?



6. እያንዳንዱ/ዷ የቡድናችሁ አባል ስለ ግል የክርስትና ሕይወቱ/ቷ እንዲያስቡ ጠይቋቸው።

## የመድረሻ ግብ

1. እንደ ደቀ መዝሙር ኢየሱስ ከእኔ የሚጠብቀው ምንድን ነው?
2. ከዚህ በታች የተጠቀሱት ክፍሎች ኢየሱስ ለተከታዮቹ የሰጠውን ትእዛዛት ይወክላሉ። አንብቧቸውና በስተ ግርጌ በቀረቡት ባዶ መስመሮች ላይ ስለ ራሳችሁ ያደረጋችሁትን ግምገማ ግለጹ።

   ዮሐንስ 5:39 ሉቃስ 18:1 ማቴዎስ 4:19

ለዚህ ትእዛዝ ታዛዥ ነኝ:-

_______________ ሁልጊዜ

_______________ አብዛኛውን ጊዜ

_______________ አንዳንድ ጊዜ

_______________ አልፎ አልፎ

_______________ ታዛዥ አይደለሁም

3. ራሳችሁን ገምግሙ።

ስለ ክርስቶስ ለሌሎች ሰዎች የምመሰክረው አልፎ አልፎ ነው፣ ምክንያቱም

_______________ ሌላውን ሰው አስቀይማለሁ ብዬ እሰጋለሁ።

_______________ የምመሰክርለት ሰው ክርስቶስን ለመቀበል ፈቃደኛ አይሆንም ብዬ እሰጋለሁ።

_______________ የክርስትና ሕይወቴ ወጥ (የማይለዋወጥ) አይደለም።

____________የእኔ ኃላፊነት ወይም የሥራ ድርሻ ነው ብዬ በእርግጥ አላስብም።

____________እኔ ልመልሳቸው የማልችላቸው ጥያቄዎች ቢነሡ ብዬ እሰጋለሁ።

____________ሌሎች ሰዎች ክርስቶስን እንደሚፈልጉ እርግጠኛ አይደለሁም።

____________እኔ እራሴ ከክርስቶስ ጋር እውነተኛና የጠበቀ ኅብረት እንዳለኝ እርግጠኛ አይደለሁም።

4. አስፈላጊ መስሎ ከታያችሁ፣ እዚህ ላይ ቆም በሉና ከላይ የተሰጡትን ትእዛዛት በተመለከተ ራሳችሁን ለእግዚአብሔር በታማኝነት ለመስጠት የምትጸልዩበት የጸሎት ጊዜ ውሰዱ። ምናልባትም ይህ ጸሎት ስሜታችሁን ያመላክት ይሆናል፡-

እግዚአብሔር ሆይ፣ ታዛዥ መሆን ባለብኝ መጠን ለክርስቶስ ትእዛዛት ታዛዥ እንዳልነበርኩ አውቃለሁ። ቃልህን በማጥናት በጸሎት ሕይወቴና የኢየሱስን የምስራች ለሌሎች ለማካፈል እንድተጋ በሕይወቴ እንደምትሠራ በማመን በዚህ ሰዓት ራሴን እንደገና ለአንተ እሰጣለሁ። አሜን።

5. ለግል የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናታችሁና ጸሎታችሁ ወደፊት ልታመቻቹ ያቀዳችሁትን ዕቅድ ግለጹ።

______________________________

______________________________

6. ለክርስቶስ ለመታዘዝ ፍላጎት ያላቸው የማይመስሉ ክርስቲያን ጓደኞች ካሏችሁ፣ ልትረዷቸው የምትችሉባቸው አንዳንድ መንገዶች እነሆ።

ሀ. ልትጸልዩላቸው ወስኑ። «ለክርስቶስ ባላቸው መሰጠት ያድጉ ዘንድ ለሚከተሉት ክርስቲያኖች እጸልያለሁ፡-



____________

____________

____________» ብላችሁ ወስኑ።

ለ. እንደዚህ ብላችሁ በመወሰን ከእነርሱ ጋር የቅርብ ትውውቅን አዳብሩ። «ከሚከተሉት ጋር የቅርብ ትውውቅን አዳብራለሁ። ጥልቅ ወደ ሆነ ክርስቲያናዊ ሕይወት እነርሱን ለመምራት የተቻለኝን ሁሉ ለማድረግ እጥራለሁ፡-

____________

____________

____________።»

# ትምህርት 5

## ክህሎትን ማካፈል

የኢየሱስ ሕይወት የመሰጠት ሕይወት መሆኑ ደቀ መዛሙርትን በጣም ያስገርማቸው ነበር። ሙሉ በሙሉ ነፍሱን አሳልፎ በሰጠበት ወቅት ታላቅ የሆነውን የፍቅር መግለጫ ወይም ትርጓሜ አሳይቷል። የጠፋውን ዓለም የመውደዱ ነገር ሁልጊዜም ያስደንቃቸው ነበር። የወንጌል የመጨረሻ ግብ ለሆነው ለዓለም መቤዠት ሕይወቱ የተለየ እንደ ነበረ ኢየሱስ ተረድቶት ነበር። ይህንንም ለእነርሱ ሊነግራቸው ሁልጊዜ ይጥር ነበር። ደቀ መዛሙርት ራስን የመስጠትን እውነተኛ ምንነት ከኢየሱስ ድርጊቶች በሚገባ ተረድተዋል። ራስን መስጠትን የመማራቸው እውነት አሕዛብ የወንጌልን እውነት አምነው እንዲቀበሉ የሚያደርግ ጉዳይ ነበር።

ይሁን እንጂ፣ ኢየሱስ የገዛ ሕይወቱን ባያካፍላቸው ኖሮ አሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት እንዲህ ያለውን ፍቅር ፈጽሞ ሊረዱት ባልቻሉ ነበር። ይህንን ያደረገው በሕይወታቸው ይኖር ዘንድ መንፈስ ቅዱስን ወደ እነርሱ በላከበት ጊዜ ነበር። መንፈስ ቅዱስን ለተከታዮቹ በመስጠትም ለወንጌል ስርጭት አገልግሎት እያስታጠቃቸውም ነበር። የወንጌል አገልግሎት የሰው ሳይሆን የመንፈስ ቅዱስ ሥራ እንደ ሆነ በተደጋጋሚ አበክሮ ይነግራቸው ነበር። ኢየሱስ ከአሥራ ሁለቱ ጋር ያሳለፋቸው የመጨረሻዎቹ ሰዓታት መንፈስ ቅዱስ ለወንጌል ሥራ ብቁ የሆነ ድጋፍ እንደሚሆንላቸው ያረጋገጠበት ወቅቶች ነበሩ። ስለሆነም ተከታዮቹ በወንጌል አገልግሎት ውስጥ መኖር፣ ሌሎችን መውደድ፣ ብሎም ማገልገል ከመጀመራቸው በፊት ጰራቅሊጦስ (አጽናኙ መንፈስ) እጅግ በጣም አስፈላጊ ነበር።

ዛሬም ያለው እውነት ይኸው ነው። በኢየሱስ የተጀመረው ሥራ በቤተ ክርስቲያን ውስጥና በእርስዋም አማካኝነት መከናወን ካለበት፣ የኢየሱስ ሕይወት በተከታዮቹ ውስጥ በአጽናኙ መንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ሊገኝ ግድ ነው። በሚገባ ልንነቃቃ የምንችለው ፣ እርሱን ለሌሎች ለማስተዋወቅ ጉልበትን የምናገኘውና ውጤታማ ለሆነው የወንጌል ስርጭት አስፈላጊ የሆነውን እራስን አሳልፎ የመስጠትን መንፈስ መግለጥ የምንችለው ይህ በሚሆንበት ጊዜ ብቻ ነው።

## የመማር ሂደት

1. ታዛዥነት ሕግን ከመጠበቅ ያለፈ ነው። ታዛዥነት ______________ ነው።
2. ኢየሱስ ያለማቋረጥ ለእግዚአብሔር ያለውን መስጠት ማደሱ



በ______________ ተገልጾ ታይቷል።

3. ኢየሱስ እራሱን የቀደሰበት ዋነኛው /ቀዳሚው ዓላማ ______________ ነበር።
4. ኢየሱስ በ ______________ እግዚአብሔር ሲሆን፣ መንፈስ ቅዱስ ግን በ______________ እግዚአብሔር ነበር።
5. ኢየሱስን ከደቀ መዛሙርቱ ጋር የሚያነጻጽር አሳብ ከዚህ ቀጥሎ ቀርቧል። ደቀ መዛሙርት በታ የሚሰጧቸው ኢየሱስ ግን የሚቃወማቸው ነገሮች ነበሩ። በሌላ በኩል ደግሞ፣ እነርሱ ለማምለጥ የሚሞክሯቸው እርሱ ግን በፈቃደኝነት የተቀበላቸው ነገሮችም ነበሩ። ከዚህ በታች ሰባት ቃላት አሉ። በሁለቱ ረድፎች አሥራ ሁለቱ ደስ ይሰኙባቸው የነበሩትን ነገሮችና ኢየሱስ በፈቃደኛነት የተቀበላቸውን ነገሮች ዘርዝሩ።

   ሥጋዊ እርካታ — ድህነት — ውርደት— ክብር— ሞት— ታዋቂነት— ኀዘን

| ደቀ መዛሙርት | ኢየሱስ |
| --- | --- |
| ______________ | ______________ |
| ______________ | ______________ |
| ______________ | ______________ |

6. ኢየሱስ ለተከታዮቹ እንደ ሰጣቸው ጸሐፊው የጠቀሳቸውን አምስት ነገሮ ዘርዝሩ

| | |
| --- | --- |
| ______________ | ______________ |
| ______________ | ______________ |
| ______________ | ______________ |

## የቡድን ውይይትና ተግባራት

1. በዮሐንስ 17:18፣19 መሠረት፣ «ቅድስና» ማለት ምን ማለት

እንደ ሆነ ተወያዩ:: ከዚያም ከመጽሐፉ ገጽ 61 ካለው ጋር አመሳክሩ::

2. ቡድናችሁ በርካታ አባላት ካሉት፣ ለሦስት ንዑስ ቡድኖች ክፈሉት:: ለየቡድኑ የሚከተሉትን ሥራዎች አከፋፍሉ:-
   ሀ. ክርስቲያን ክርስቶስን እንዲመስል በማድረግ በኩል መንፈስ ቅዱስ የሚሠራው ሥራ ምን እንደ ሆነ የመጀመሪያው ቡድን እንዲያብራራ ጠይቁ::
   ለ. ለውጤታማ የወንጌል ስርጭት የመንፈስ ቅዱስ ሥራና አስፈላጊነት ምን እንደ ሆነ እንዲያብራራ ሁለተኛውን ቡድን ጠይቁ::
   ሐ. ሦስተኛው ቡድን ለመንፈስ ቅዱስ ሙላት መሟላት ያለበትን ሁኔታ እንዲያብራራ ጠይቁ::
3. ከዛሬው ጥናት ባገኛችሁት ግንዛቤ መሠረት መለወጥ ወይም መጠናከር የሚያስፈልገው የሕይወታችሁ አንደኛው ክፍል ምንድን ነው?

## የመድረሻ ግብ

1. ለብቻችሁ ከእግዚአብሔር ጋር የምትሆኑበትን ጊዜ ወስናችሁ የምታውቁትን ኃጢአታችሁን ወይም ድካማችሁን በዝርዝር ጻፉ:: መንፈስ ቅዱስ በሕይወታችሁ ውስጥ ስሕተት እንደ ሆነ የሚያሳያችሁን ሁሉ እስከሚሰፍር ድረስ አንድ በአንድ ጻፏቸው:: ከዚያ ከመጽሐፍ ቅዱሳችሁ 1ኛ ዮሐንስ 1:9ን አውጡ:: ኃጢአታችሁን ሁሉ ለእግዚአብሔር ተናዘዙና ቀድዳችሁ ጣሉት::

2. ሕይወታችሁን ስትመለከቱት ለክርስቶስ ያልተሰጠ አንዳች ክፍል እንዳለ ከተረዳችሁ፣ ይህንን የሕይወታችሁን ክፍል አሁኑኑ አሳልፋችሁ ስጡ /አስገዙ/::



3. ከዚያ የሚከተለውን ጸሎት ጸልዩ:-

ውድ አባት ሆይ፣
ለአንተ ያላስገዛኋቸው የሕይወቴ ክፍሎች እንደ ነበሩ አሁን እናዘዛለሁ:: በዚህም ምክንያት አንተን በድያለሁ:: ፈጽመህ ስለ ማርከኸኝም አመሰግንሃለሁ:: በአሁኑ ወቅትም ሁለንተናዬን ፈጽሜ ለአንተ አስገዛለሁ:: በእምነትም የመንፈስ ቅዱስን ሙላት እንደ ተቀበልኩ እመሰክራለሁ:: ሕይወቴን ስለ ተቆጣጠርክና በመንፈስህም ስለ ሞላኸኝ አመሰግንሃለሁ:: አሜን::

# ትምህርት 6

## በተግባር ማሳየት

ኢየሱስ የእርሱ ሕዝቦች እንዲኖሩት ያቀደውን የአኗኗር ዘይቤ እንዴት ሊኖሩት እንደሚገባ የማሳየቱ ተግባር በጥንቃቄ ከታሰበበት የኢየሱስ ስልቶች አንዱ አካል ነበር:: ስለሆነም አሥራ ሁለቱ ሊኖሩትና ለሌሎች ሊያስተምሩት የሚገባቸውን ሕይወት በእርሱ ውስጥ ተመልክተውታል:: ኢየሱስ ያደረገውና የሆነው ሁሉ ለእነርሱ ብሎም ለእኛ ምሳሌ ለመሆን ያደረገውና የሆነው ነበር:: ሆን ብሎ ከአባቱ ጋር በጸሎት ሲነጋገር እንዲያዩት ያደርግ ነበር:: ጸሎት በእርሱ ላይ ያመጣውን ነገር በመመልከታቸው ያው ጸሎት በእነርሱ ሕይወት የሚሠራውን ለማወቅ ይጓጉ ነበር:: የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን ጠንቅቆ በማወቁና በአግባቡ የመጠቀም ችሎታውም እጅግ በጣም ይገረሙ ነበር:: ይኸውም ሰዎችን ወደ ራሱ ሲማርክ የመመልከታቸው ነገር የተለየ አስፈላጊነት የሚሰጠው ጉዳይ ነው:: እንዲማሩ የሚፈልገውን ነገር በፊታቸው ሲያደርግ በማየት ተምረዋል:: ታላቁ መምህር በተለመደ ዓይነት

መንገድ እያንዳንዱን አጋጣሚና ሁኔታ ትምህርት የመቅሰሚያ ዕድል እንዲሆናቸው ስለሚያደርግ፣ ሁልጊዜ በትምህርት ላይ ነበሩ::

መንፈሳዊ መሪዎች ዛሬም የክርስቶስን ስልት ሊወርሱ ይገባል:: ይህንን ለማድረግ ደግሞ ሌሎች እንዲማሩ የምንፈልገውን ነገር በገዛ ሕይወታችን ለማሳየት ፈቃደኛ ልንሆን ይገባል:: ይህንን ለመፈጸም ልንመራቸው ከምንፈልጋቸው ሰዎች ጋር አብረን መሆን ይኖርብናል:: አብረናቸው ልንጸልይ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናታቸው ልንረዳቸውና ሌሎች ሰዎችን ለክርስቶስ ለመማረክ በምንጥርበት ጊዜም ከእኛ ጋር ይዘናቸው ልንሄድ ይገባል:: በእኛ ውስጥ እንዲያዩት ባደረግን ቁጥር ብቻ የሕይወትን መንገድ ለሌሎች ሰዎች እናካፍላለን:: ይህ እንግዲህ የመምህሩ ስልት ሲሆን፣ ሌሎችም የእርሱን ሥራ ለመሥራት በሚገባ መሠልጠናቸው ግድ ነው::

## የመማር ሂደት

1. የኢየሱስ ሕይወት እንዴት መኖር እንዳለብን የሚያሳይ ዘላቂ ምሳሌ ቢሆንም፣ ጸሐፊው ግን አሥራ ሁለቱን ለማስተማር በተለይ የፈለጋቸውን ሦስት ምሳሌነቶች ለይቶ ይጠቅሳል:: እነዚህም ምሳሌነቶች____________፣ _______________እና _________________ ነበሩ::

2. ተከታዮቹ መጻሕፍትን ማወቅ እንዳለባቸው የኢየሱስ ምሳሌ ምልክት ነው:: ከሚከተሉት ጥቅሶች አኳያ ዛሬ በምንኖረው ኑሮአችን የእግዚአብሔር ቃል እንዴት ሊያግዘን ይችላል?

   ሀ. 1ኛ ጴጥሮስ 2:2



   ለ. መዝሙር 119:105

   ሐ. ዮሐንስ 15:7

3. ከኢየሱስ የጸሎት ሕይወት ልትማሯቸው የምትችሏቸው ትምህርቶች ምንድን ናቸው?

   ሀ. ማቴዎስ 14:23

   ለ. ማርቆስ 1:35

   ሐ. ሉቃስ 6:12

## የቡድን ውይይትና ተግባራት

1. ኢየሱስ ለእግዚአብሔር ቃል ያለውን አመለካከት በ2ኛ ጢሞ. 3:16-17 ላይ ከተገለጸው ከጳውሎስ አሳብ ጋር አነጻጽሩ::

2. 1ኛ ቆሮ. 11:1፤ ፊልጵ. 3:17፤ 2ኛ ጢሞ. 1:39፤ ፊልጵ. 4:9 ምን እንደሚያመለክቱ ተወያዩ::

3. መተወን በሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ሰዎች መሃከል የሚደረግ፣ የሰውን ልጅ ትግል የሚያሳይና ያልተጠና ድራማዊ ተግባር ሲሆን፣ ቡድኑ ነገሮችን የበለጠ መተንተን እንዲችል የሚያግዝ ነው:: የትወናን ሒደት ተግባራዊ በማድረግ የሚከተለውን የሚተውኑ ሦስት የቡድን አባላት ምረጡ::

ጥያቄው:- በጌታ ማደግ የሚፈልግ አንድ አዲስ ክርስቲያን አለ እንበል:: መጸለይ አስቸጋሪ ሆኖበታል:: መጽሐፍ ቅዱስን እንዴት ማጥናት እንዳለበትም አያውቅም:: ሰውን ለክርስቶስ ለመማረክ ባደረገው የመጀመሪያ ሙከራ አሳዛኝ ውድቀት ደርሶበታል::

በእነዚህ ሦስት ጉዳዮች ሊሳካለት ያልቻለውን ይህንን ሰው በመወከል አንድ ሰው ይተውን:: ደኅንነትን ያላገኘን ሰው የሚወክል አንድን ሰው ለክርስቶስ ለመማረክ የሚያጋጥመውን ውድቀት

በተውኔት እንዲያሳይ ያስፈልጋል:: ከዚያ የበሰለ ክርስቲያንን በመወከል የሚተውነው ሦስተኛ ሰው በእነዚህ ጉዳዮች ዙሪያ የሚያስተምር ሰው ማግኘት ምን ያህል እጅግ አስፈላጊ ሊሆን እንደሚችል ያሳያል::

## የመድረሻ ግቦች

1. ከአንድ ሰው ጋር ስትሠሩ ቆይታችሁ ከሆነ፣ ይህ ሰው ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ነገሮች ይማር ዘንድ እንዴት እንደምትረዱት አንድ በአንድ በመለየት ወስኑ:-

   ሀ. እንዲጸልይ

   ለ. መጽሐፍ ቅዱስን በሚገባ እንዲያጠና

   ሐ. የምስራቹን ቃል ለሌሎች እንዲያካፍል

   መ. ፈተናዎቹን ድል እንዲያደርግ

   ሠ. ኃጢአት ባደረገ ጊዜ ንስሐ እንዲገባ

2. በየዕለቱ መጽሐፍ ቅዱስ በማጥናትና በመጸለይ ይህን ያህል ሰዓት እጠቀማለሁ:-

   ከግማሽ ሰዓት ያነሰ

   ከ 1/2 -1 ሰዓት

   1-2 ሰዓት

   2-3 ሰዓት

   ከሦስት ሰዓት በላይ

3. መጽሐፍ ቅዱስን በቃላችሁ የምታጠኑበት ስልት አላችሁ? ከሌላችሁ፣ ቢያንስ በሳምንት አንድ ጥቅስ በቃላችሁ ለማስታወስ በመሞከር ጀምሩ::



# ትምህርት 7

## ውክልና

በኢየሱስ አገልግሎት የመጀመሪያው ዓመት ደቀ መዛሙርት እርሱ ሲሠራ ከመመልከት ያለፈ እጅግም ሥራ አልነበራቸውም:: ኃላፊነት ከመጀመሪያውም የተሰጣቸው ቢሆንም፣ ከሁሉ ቀዳሚ የነበረው ተሳትፏቸው ግን ሙያ በማይጠይቁ ጥቃቅን አገልግሎቶች ላይ ነበር:: ነገር ግን ይህም ከመምህሩ ስልት አንዱ አካል ነበር:: መጀመሪያ ከእግዚአብሔር ጋር ወሳኝ ወደ ሆነ ኅብረት ውስጥ አስገባቸው:: ከዚያ ደግሞ እርሱ እንዴት እንደሚሠራ አሳያቸው:: የሥራ ድርሻቸው ምን ድረስ እንደ ሆነ የነገራቸው ከዚህ ሁሉ በኋላ ብቻ ነበር:: ነገር ግን እነርሱ እርሱን ተከትለው የሚያገለግሉበት ጊዜ ላይ በማተኮር ሁልጊዜ አብሯቸው ይሠራ ነበር::

በመጨረሻ፣ ከዓመት በላይ ለሚሆን ጊዜ ያህል ካሠለጠናቸው በኋላ ብቻቸውን የወንጌል ሥራን ለማከናወን ዝግጁ እንደ ሆኑ ተረዳ:: ነገር ግን እንዲሄዱ ሳይልካቸው በፊት ሊያደርጉት ስለሚገባቸው ነገር ሁሉ አንድ በአንድ በጥንቃቄ ነግሯቸዋል:: እነዚህ ሊያደርጓቸው ስለሚገቧቸው ነገሮች የሰጣቸው መመሪያዎች ከፍተኛ ጠቀሜታ ነበራቸው:: ምክንያቱም እነዚህ ትእዛዛት ከመጀመሪያ ጀምሮ ጥቅል በሆነ መንገድ ሲያስተምሯቸው የነበሩትን ትምህርቶች ሁሉ በግልጽ ተንትኖ ያስቀመጠባቸው ትእዛዛት ነበሩ:: እነርሱ ከሄዱ በኋላ በእነርሱ ፋንታ ተተክተው ሥራውን መቀጠል እንደሚችሉ ይበልጥ ተስፋ በሚጣልባቸው ላይ ማተኮር የተለየ ሥራቸው ሊሆን እንደሚገባ መናገሩን ማስተዋል ከፍተኛ አስፈላጊነት አለው:: ከፊት ለፊት የሚጠብቃቸው ነገር

ቀላል እንደማይሆንላቸው አስረግጦ በመንገር ሁለት፣ ሁለት እያደረገ ለአገልግሎታቸው ላካቸው::

የጌታችን እውነተኛ ተከታይ የሆነ ማንኛውም ሰው በወንጌል ሥራ ውስጥ መሳተፍ ሊፈጽመው የሚገባ ትእዛዝ ነው:: ለምናሠለጥናቸው ሰዎች የሥራ ኃላፊነት መስጠት ይኖርብናል:: ይህ ኃላፊነት መጀመሪያ ላይ በቀላሉ ተግባራዊ ሊያደርጉት የሚችሉት መሆን ይኖርበታል:: ነገር ግን ምንጊዜም አንድን ሥራ እንዲሠሩ ስናደርጋቸው ሥራው ነፃ በሚያወጣው በጌታችን አገልግሎት ውስጥ ቀጥተኛ ተሳታፊ መሆን ይችሉ ዘንድ እንዲያዘጋጃቸው መሆን ይኖርበታል::

## የመማር ሂደት

1. ዓለምን በወንጌል የመድረስን ሥራ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ከመንገሩ በፊት ስልቱ___________ እና ___________ ያጠቃልላል::
2. በግምት ______________ ለሚሆን ጊዜ ያህል ደቀ መዛሙርት ኢየሱስ ሲሠራ ከማየት ያለፈ ብዙም ሥራ አልነበራቸውም::
3. ኢየሱስ ለአሥራ ሁለቱ «በአሕዛብ መንገድ አትሂዱ:: ወደ ሳምራውያንም ከተማ አትግቡ:: ይልቅስ፣ የእስራኤል ቤት ወደሚሆኑት ወደ ጠፉት በጐች ሂዱ እንጂ::» (ማቴ. 10:5-6) ለምን እንዳላቸው የዚህ መጽሐፍ ደራሲ የሰጡት ማብራሪያ ምንድን ነው?
4. «በምትገቡባት በማናቸይቱም ከተማ ወይም መንደር በዚያ የሚገባው ማን እንደ ሆነ በጥንቃቄ መርምሩ:: እስክትወጡም ድረስ በዚያ ተቀመጡ::» የሚለውን የኢየሱስን ትእዛዝ የዚህ መጽሐፍ ደራሲ እንዴት ይተረጉሙታል?



5. አሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት በመጀመሪያው አገልግሎታቸው ያደረጓቸው የምስክርነት ጥረቶች በተወሰነ ደረጃ ውጤታማ እንደ ነበሩ የሚያመለክት ምን ነገር ነበር?
6. እነዚህን ጥቅሶች ይዛችሁ የአዲስ ኪዳን መጽሐፍን በመጠቀም የሚከተሉትን አዛምዱ:-

| | |
|---|---|
| ሉቃስ 24:44-47 | ሀ. «ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው» |
| ዮሐንስ 20:19-24 | ለ. «ቶማስ ከእነርሱ ጋር አልነበረም» |
| ማቴዎስ 28:19 | ሐ. ስለ መንፈስ ቅዱስ የተገባ ቃል ኪዳን |
| የሐዋርያት ሥራ 1:8 | መ. «በጐቼን አሰማራ» |
| ዮሐንስ 21:15-17 | ሠ. «ወደ ዓለም ሁሉ» |
| ማርቆስ 16:15 | ረ. «ንስሐና የኃጢአት ስርየት. . . ይሰበካል» |

## የቡድን ውይይትና ተግባራት

1. በዚህ አሳብ ዙሪያ ተወያዩ:-

ዛሬም ክርስቲያን ደቀ መዛሙርት ወንዶችና ሴቶች ናቸው:: ጌታ ሕይወቱን ለሰጠበትና ለተላከበት ተመሳሳይ የወንጌል ሥራ ተልከዋል:: ወንጌል ስርጭት በሕይወታችን እንደ አንድ አማራጭ ተቀጥላ ተቀጥላ የምንወስደው ነገር አይደለም:: እንድንሆንና እንድናደርግ ለተጠራንበት ነገር ሁሉ እንደ ልባችን ትርታ ነው:: በክርስቶስ ስም ለሚደረግ ለማንኛውም ዓይነት ሥራ ትርጉም የሚሰጥ የቤተ ክርስቲያን ተልዕኮም ነው:: በዚህ ዓላማ ላይ ተነጣጥሮ የተደረገና የተባለ ማንኛውም ዓይነት አገልግሎት የእግዚአብሔርን ነፃ የማውጣት ዓላማ በክብር ይፈጸማል:: በትምህርት ማዕከሎች፣ በማኅበራዊ እንቅስቃሴዎች፣ ሆስፒታሎች

በክርስቶስ ስም የሚደረጉ ማንኛቸውም ዓይነት የቤተ ክርስቲያን ስብሰባዎች ከሆነ ትክክል የሚሆኑትና ትርጉም የሚሰጡት ይህን ተልዕኮ ለመፈጸም በቂ መሠረት አላቸው::

2. በማቴ. 10:34-38 ባለው በኢየሱስ ቃል ላይ ተወያዩ::

እኔ የመጣሁት ሰላምን በምድር ላይ ለማስፈን አይምሰላችሁ፤ ሰይፍን እንጂ ሰላምን ለማውረድ አልመጣሁም:: እኔ የመጣሁት ልጅን ከአባት፣ ሴት ልጅን ከእናቷ፣ ምራትንም ከዐማቷ ለመለያየት ነው፤ የሰው ጠላቶቹ የገዛ ቤተ ሰዎቹ ይሆናሉ:: ከእኔ ይልቅ እናቱን ወይም አባቱን የሚወድ ለእኔ ሊሆን አይገባም፤ ከእኔ ይልቅ ወንድ ልጁን ወይም ሴት ልጁን የሚወድ ለእኔ ሊሆን አይገባም:: መስቀሉን ተሸክሞ የማይከተለኝ የእኔ ሊሆን አይገባውም::

አሁንም ዶክተር ኮልመን በገጽ 85 ላይ የገለጹትን አሳብ ተመልከቱ::

3. የዚህ መጽሐፍ ጸሐፊ ለማቴ. 10:5-6 የሰጡትን ትርጉም አስፈላጊነት እናንተ ምስክር እንዲሆን ከምታሠለጥኑት ሰው የመጀመሪያ ጥሪት በተያያዘ መልኩ ተወያዩበት::

4. ለአሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት ሊገጥማቸው ስለሚችለው አስቸጋሪ ሁኔታ /መከራ/ ኢየሱስ የሰጣቸውን ማስጠንቀቂያዎች ተመልከቷቸውና በ1ኛ ጴጥ. 2:21፤ በፊልጵ. 1:29፣ እና በ2ኛ ጢሞ. 3:12 መሠረት መዝኗቸው::

## የመድረሻ ግቦች

1. አብራችሁ እያገለገላችሁ ላላችሁት አዲስ ክርስቲያን እንዲሠራ የምትሰጡትን የሥራ ድርሻዎች በዝርዝር ጻፉ::
2. ከአንድ ክርስቲያን ጋር በግል ወንጌልን የመመስከር አገልግሎት እየሰጣችሁ በአንዳንድ ቀለል ባሉ ጉዳዮች ላይ እርሱ/ እርሷ ከማያምን ሰው ጋር እንዲናገሩ ዕድል ስጡ::
3. ራሳችሁን ይህንን ጥያቄ ጠይቁ፣ «ዘለፋና ትችት የሚያስከትል ቢሆን እንኳ፣ ለኢየሱስ ለመመስከር ፈቃደኛ ነኝ?»
4. ከመመስከር የሚያግድህ ነገር እንዳለ ከመሰለህ፣ ያ ነገር ከእነዚህ አንዱ ይሆን? ከመመስከር የሚያግዳችሁ ምን እንደ ሆነ ለማወቅ ለራሳችሁ ታማኝ ሆናችሁ ያገዳችሁን ነገር ፊት ለፊት ተጋፈጡ:: ዛሬ ታይቶ ነገ የማይጠፋን ዘላቂ ብርታት እንደሚሰጣችሁም እግዚአብሔርን እመኑ::

ቅድሚያ የምትሰጧቸው ሌሎች ነገሮች

ስንፍና

ፍርሃት

ለወንጌል ስርጭት ያላችሁ የተሳሳተ አመለካከት

የሥጋ ሥራ (ኃጢአት)

ከምንም በላይ፣ አስቀድማችሁ ራሳችሁን ለእግዚአብሔር ስጡ /አስገዙ/::

# ትምህርት 8

## ቁጥጥር

በአንዳንድ የወንጌል ሥራ ኃላፊነቶች ውስጥ እንዲሳተፉ ተስፋ ያደረጋቸው ቢሆንም፣ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን የትምህርት ጊዜያቸውን ጨርሰው ለመመረቅ ብቁ እንደ ሆኑ ተማሪዎች ገና አልቆጠራቸውም ነበር:: በተሳተፉባቸው የተወሰኑ የመቤዠት አገልግሎቶች እንኳ ክትትል የሚያደርግ ተቆጣጣሪ አስፈልጓቸው

ነበር:: ስለዚህም ኢየሱስ ለአገልግሎት በሄዱባቸው ስፍራዎች ሁሉ እየተከተለ የአገልግሎት ሪፖርታቸውን ሊያዳምጥና ሊያጋጥሟቸው በሚችሉ አስቸጋሪ ሁኔታዎች ወይም ባገኙዋቸው ድሎች ያለውን እውቀት ሊያካፍላቸው አብሯቸው ይሆን ነበር:: በእርግጥም ይህ የአንድ ጊዜ ክስተት አልነበረም:: ከእነርሱ ጋር የማያሰልስ ኅብረትን በማድረግ በማያቋርጥ መንገድ ኢየሱስ አሥራ ሁለቱን ይከታተላቸው ነበር:: ከእነርሱ ጋር በነበረው አገልግሎት ሁሉ የድልም ሆነ የሽንፈት የደቀ መዛሙርት ተሞክሮዎች በትምህርቱና በተግባር በሚያሳያቸው ነገሮች ውስጥ ሁሉ እንደ መርጃ መሣሪያ የሚጠቀምባቸው ነበሩ:: እርሱ የሚያደርግላቸው ክትትል እነርሱን ለአገልግሎት በማስታጠቅ ሂደት አንድ እርምጃ ወደ ፊት የሚያስኬዳቸው እንደ ሆነ ስለሚያውቅ የሚያደርጉትን ነገርም ሆነ የሚሰጡትን ምላሽ በንቃት ይከታተል ነበር:: በመጨረሻ ወደ አባቱ ሲመለስና እነርሱን ሲተው፣ ሥራቸውን የመከታተሉን ተግባር ይቀጥል ዘንድ መንፈስ ቅዱስን እንደሚልክ ቃል ገባላቸው::

ዛሬ ለወንጌል አገልግሎት ሰዎችን ለማስታጠቅ እንዴት እንደሚሠሩ በማሳየት ብቻውን የሚሠራውን ሥራ ውጤት ያስገኛል ብለን መጠበቅ አንችልም:: የአንድ ሥራ በጥሩ ሁኔታ መጠናቀቅም ቢሆን ያንን ሥራ እንዲሠራ የሠለጠነው ሰው ከሥልጠናው በኋላ ለብቻው ለመሥራት ብቁ መሆኑን ያመለክታል ብለን መቁጠር አንችልም:: ደቀ መዛሙርት ፍጹም ወደ ሆነ የብስለት ደረጃ እስከሚደርሱበት ጊዜ ድረስ በቅርበት ሆኖ የሚከታተላቸው አሁንም ቢሆን ያስፈልጋቸዋል::

## የመማር ሂደት

1. የአሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርት የዘገባ ወቅት ከሰባኪዎች



የዘገባ ወቅት ጋር አነጻጽሩ::

2. ሰባዎቹ ላቀረቡት ዘገባ ኢየሱስ የሰጠው ምላሽ ምን ነበር?

3. ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርት ድካም/ውድቀት በመነሣት ሊያውቁት የሚገባቸውን እውነት የገለጠበትን አንድ አጋጣሚ ጥቀሱ::

4. የኢየሱስን የማስተማር ስልት ለመግለጽ የዚህ መጽሐፍ ደራሲ ሦስት ቃላትን ይጠቀማል:: እነዚህም____________፣ ____________ እና ____________ናቸው::

## የቡድን ውይይትና ተግባራት

1. የዚህ መጽሐፍ ደራሲ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ «ዓለምን መማረክ» የሚለውን ቃል ሁለት ጊዜ ተጠቅመውበታል:: በእናንተ አመለካከት ይህንን ሲሉ ምን ማለታቸው ነው?

2. በዚህ አሳብ ዙሪያ ተወያዩ:-

   ለምስክርነት የወጡት ይዘውት በሚመለሱት የመጀመሪያ ፍሬያቸው አለመርካትን ከክርስቶስ የምንማረው መቼ ይሆን? ደቀ መዛሙርት ሙሉ ወደ ሆነ እድገት ሊመጡ ይገባቸዋል:: የተሟላ ድል ማግኘትን የሚተካ ምንም ነገር የለም:: የውጊያ ሜዳችን ደግሞ ዓለም ናት:: ምሽግን ይዘን እንድንቀመጥ አልተጠራንም:: የተጠራነው እንድንወጣ፣ ክፍታዎችንም እንድናፈርስ ነው:: የክርስቶስን ስልት የመጨረሻውን ደረጃ መረዳት የሚቻለው በዚህ መልኩ ሲታይ ነው::

3. አብረነው ስናገለግልና ስናሠለጥነው የቆየነው ሰው የሚያሳፍር /የማያስደስት/ ሆነ ብላችሁ አስቡ:: ይህ የሆነው በአንድ ወይም በብዙ መልኩ ሊሆን ይችላል:: የሚከተሉት ሁኔታዎች

ሲያጋጥሙት/ሟት እንዴት ልትረዱት/ዷት እንደምትችሉ ተወያዩ::

ሀ. ገና ራሱን ሊያስተዋውቅ ሲል ፊቱ ላይ በር ተዘጋበት::

ለ. የምስራቹን ወንጌል ለሌሎች ሲያካፍል ከመሃከል አንድ ሰው በቅንነት «ቆይ አንተ እውነት መሆኑን እንዴት አወቅክ?» ብሎ ጠየቀው::

ሐ. «እግዚአብሔር አለ ብዬ አላምንም» አለው::

መ. «ክርስቲያናዊ ልምምድ ሥነ ልቦናዊ ብቻ አይደለም እንዴ?»

4. ይህ ስብሰባችሁ ዘገባ (ሪፖርት) የምትቀበሉበት ጊዜ ነው እንበልና፣ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ጠይቁና ራሳችሁ ምላሽ ስጡባቸው::

ሀ. በዚህ ሳምንት ውስጥ እርዳታ የሚያስፈልገው ሰው አግኝተህ ነበር?

ለ. እና ምን አደረግህለት?

ሐ. በዚህ ሳምንት ውስጥ ያላችሁን ክርስቲያናዊ መገደድ ልትገልጹላቸው ስለምትችሏቸው ከቤተሰብ፣ ከጓደኛ፣ ወይም ከሥራ ባልደረቦቻችሁ ውስጥ ሦስት ሰዎችን አስቡ:: ከእነርሱ ጋር ጥቂት አሳቦችን ለመከፋፈል ወይም በሚገባ ያሰባችሁበትን ቸርነት (መልካም ነገር) ለማድረግ ጥቂት ደቂቃዎችን መድቡላቸው:: ይህንን በስልክ፣ በአካልም ሆነ በደብዳቤ ያደረጋችሁትን ነገር መዝግቡ:: ከዚያ በኋላ ምን እንደ ተከሰተ ጻፉ::

## የመድረሻ ግቦች



1. ጓደኛችሁ (አብራችሁት የምታገለግሉት ሰው) አንድ ክርስቲያናዊ አገልግሎት እንዲያከናውን ከላካችሁት በኋላ በሚገባ የታሰበበት ዘገባ ማቅረቢያ ወቅት ይኑራችሁ::

2. ለምስክርት የሚወጣ አንድ አዲስ ሰው ሊያጋጥሙት የሚችሉ ተስፋ አስቆራጭ እክሎችን በዝርዝር ጽፋችሁ በመያዝ የምታሠለጥኑትን/ኗትን በእነዚህ ጉዳዮች ላይ ልትረዱት/ዷት እንድትችሉ ዝግጁ ሁኑ::

# ትምህርት 9

## መባዛት

ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ የነበረው የመጨረሻ ግቡ የእርሱ ሕይወት በእነርሱ እንዲታተምና በእነርሱ አማካኝነትም የእርሱ ሕይወት በሌሎች ሕይወት ውስጥ ይበዛ ዘንድ ነው:: ይመራቸው የነበሩት ሰዎች በቁጥር ጥቂት መሆናቸው ልዩነት አላመጣም:: በበቂ ሁኔታ ከሠለጠኑ በሕይወታቸው የሚመስሏቸውን ማፍራት ይችላሉ:: ዓለም ሁሉ የእርሱን መልእክት እንደሚሰማ ኢየሱስ አርቆ እስኪመለከት ድረስ እነዚህን የመሰለ ሕይወት ያላቸው ተመሳሳይ ፍሬን የሚያፈሩ ይሆናሉ:: እነርሱ ስለ እርሱ በታማኝነት በሚሰጡት ምስክርነት ከታለመው ግብ መድረስ ይቻላል:: እነርሱ ብዙ ፍሬን ባፈሩና የሚከተሏቸውንም ፍሬን ማፍራት እንዲችሉ ባስተማሯቸው መጠን የኢየሱስ ወንጌል እያሸነፈ ይሄዳል:: ጌታችን ከአሥራ ሁለቱ ይፈልግ የነበረው ፍሬን ያፈሩ ዘንድ ሲሆን፣ የመጨረሻውና ዋነኛው ግቡ ግን መባዛት ነበር::

በዚያን ጊዜ እንደ ነበረ ሁሉ ዛሬም ቢሆን አንድ የወንጌል

ስርጭት መርሐ ግብር የሚፈተሽው መጀመሪያ ውሳኔ እንዲያደርጉ በወንጌል በሚደረሱ ሰዎች ቁጥር ብዛት አይደለም:: እውነተኛው መመዘኛ እነዚያ በወንጌል የተደረሱት ሰዎች ሌሎችን በወንጌል እየደረሱ ነው? የሚለው ነው:: እኛ ያፈራነው ፍሬ ሌላ ፍሬን እያፈራ ነው? ሰዎች እንዲለወጡ ብቻ እያደረግን ነው ወይስ በተራቸው እነርሱም ሌሎችን ለመሪነት ማድረስ የሚችሉ መሪዎችን እያነጽን ነው?

ጥንታዊቷ ቤተ ክርስቲያን ሰዎች ፍሬን የማፍራትንና የማሳደግን ስልት በማካተቷ የኢየሱስ ስልት ሊተገበር የሚችል መሆኑን አረጋግጣለች:: ነገር ግን ከዚያ በኋላ በነበሩት ክፍለ ዘመናት ይህ ስልት በጅማ በመመልመል ስልት እንደ ተተካና ፈጽሞ እንደ ተጣለ ለመመልከት በቅተናል:: በዚህ ዘመን በጣም አስፈላጊ የሆነው ሰዎች ሌሎች ሰዎችን ወደ ክርስቶስ ማምጣትና ያመጧቸውንም ሰዎች ሌሎችን ማርከው እንዲያመጡ ደቀ መዛሙርት አድርገው እንዲያንጿቸው ወደሚያስችል ዓይነት ወንጌል ስርጭት መመለስ ነው::

## የመማር ሂደት

1. የሚከተሉትን የእውነት/ ሐሰት ጥያቄዎች መልሱ::

ሀ. የወንጌል ስርጭት ዋነኛው ግብ ፍሬ ማፍራት ነው:: ________

ለ. ቤተ ክርስቲያን የምታደርገው የጅማ ምልመላ ክርስቲያናዊ እንቅስቃሴዎችን የመጐተት ውጤት አስከትሏል:: ________

ሐ. ከአራተኛው ክፍለ ዘመን ወዲህ ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስን የወንጌል ስርጭት ስልት ያን ያህል በስፋት ተግባራዊ



አላደረገችውም:: ________

መ. በማቴ. 28:19-20 ላይ ያለው ትእዛዝ ትክክለኛ አሳብ ደቀ መዛሙርትን ማፍራት ነው:: ________

2. ማቴ. 9:36-38 ላይ በጣም በርካታ ሕዝቦችን በማየት ኢየሱስ ስለ ነበረው ልምምድ ይገልጻል:: ለዚህ የሰጠውን ምላሽ አብራሩ::

3. በምን ጉዳይ ላይ እንዲጸልዩ ነበር ደቀ መዛሙርቱን ያበረታታቸው? የእግዚአብሔርን የመቤዠት ዕቅድ በሚመለከት የመጨረሻ የሕይወታችንና የምስክርነታችን መመዘኛ ምንድን ነው?

4. ስለሆነም፣ ማንኛውም የወንጌል ሥራ የሚመዘነው በ________ሳይሆን በ________ ነው::

5. በተመሳሳይ መልኩም፣ ቤተ ክርስቲያን ውጤታማነቷን የምትመዝነው በ ________ወይም በ________ ሳይሆን በ________ሊሆን ይገባል::

6. የወንጌል አገልግሎት የሚከናወነው በ ________እንጂ በ________ አይደለም::

7. የሚፈለገው አዲስ የወንጌል ስርጭት የተሻለ ስልት ሳይሆን የተሻለ ________ነው::

## የቡድን ውይይትና ተግባራት

1. ዶክተር ኮልመን ኢየሱስ አስቀድሞ «የደኅንነት ወንጌል በሰው ለፍጥረት ሁሉ በሚያሳምን መልኩ «የሚታወጅበትን» ዘመን አስቀድሞ እንዳየ ተናግረዋል:: ይህ በእኛ ትውልድ ውስጥ

የመሆኑ ዕድል ምን ያህል እንደ ሆነ ተወያዩ::

2. ዮሐ. 15:1-16ን በጥንቃቄ አጥኑት:: «ፍሬ» የሚለው ቃል በዚህ ምንባብ ውስጥ ምን ያህል ጊዜ እንደ ተጠቀሰ አስተውሉ:: ኢየሱስ «ፍሬ» ሲል ምን ማለቱ እንደ ሆነ ተወያዩ:: ከዚያ በገጽ 105 ላይ የተጻፈውን ተመልከቱ:: በቁጥር 16 ላይ ኢየሱስ ስለሚኖር ፍሬ እንደ ተናገረ አስተውሉ:: ይህ ምን ማለት ነው?

3. በዚህ መጽሐፍ በገጽ 108 ላይ ባለው አሳብ ላይ ተወያዩ:-

*ሥራችን እስከ መጨረሻው ቀጣይነት እንዲያገኝና እንዲጸና ከተፈለገ ዋናው ነገር በእኛ አማካይነት የተለወጡት ሰዎች ብዙ ተከታዮች ማፍራታቸው ሳይሆን፣ በእነርሱ አማካይነት የተለወጡትን ሰዎች መሪዎች ማድረግ የቻሉ እንደ ሆነ ነው:: እርግጥ ነው፣ ትውልዳችንን ለክርስቶስ መማረክ፣ ይህንንም አሁኑኑ ማድረግ፣ መሻታችን ነው:: ሆኖም፣ ይህ ብቻውን በቂ አይደለም:: ወንጌልን በሰበክነውና ቤዛችን በሆነው (በክርስቶስ) ነፃ የወጡት ሰዎች ሕይወት ውስጥ ቀጣይነቱ ካልተረጋገጠ በቀር ሥራችን በፍጹም አልተጠናቀቀም::*

4. የሚከተሉትን ዓይነት ሰዎች ለክርስቶስ ለመማረክ ምን እንደምታደርጉ ተወያዩ::

ሀ. አብያተ ክርስቲያናት እንዲጠፉ የሚፈልግ አንድ ሰው በጐረቤታችሁ ይኖራል:: ይህ ሰው ለክርስቲያኖች ያለውን ጥላቻ በግልጽ ያሳያል:: ለኅብረተሰቡም ጠንቅ ናቸው ብሎ ያምናል:: አንዳንዴ እንዲያውም ይህ ጥላቻው ወደ ቁጣ ይለወጣል:: ይህንን ሰው ለክርስቶስ ለመማረክና በወንጌል ለመድረስ መደረግ ያለበት ነገር ምንድን ነው? ይህ ሰው ሊድን ይችላል ብላችሁ ከልባችሁ ታምናላችሁ? የሐዋ. 8:3፤ 9:1-6ን አንብቡ::

ለ. እጅግ ሲበዛ ሃይማኖተኛ የሆነ አንድ ሰው በጐረቤታችሁ



ይኖራል:: ይህ ሰው ይጸልያል፣ ድሆችን ይመግባል፣ ቤተሰቦቹም ሃይማኖተኞች በሚሆኑበት ጐዳና ይመራቸዋል:: ይሁን እንጂ፣ በግሉ ክርስቶስን አያውቀውም:: ለዚህ ሰው ያላችሁ አመለካከት ምንድን ነው? ይህንን ሰው በወንጌል ለመድረስ ምን ታደርጋላችሁ? ክርስቲያን ሊሆን ይችላል ብላችሁ ታምናላችሁ? የሐዋ. 10ን አንብቡ::

## የመድረሻ ግቦች

1. ወንጌልን ለሌሎች መመስከር እንድትችል በማገዝ ዓላማ አንዲትን ሴት ስታሠለጥኗት ቆያችሁ:: ከእናንተ ጋር ለምስክርነት ስትወጣ በየጊዜው ትንሽ ትንሽ እንድትናገር በኋላም ሰፊውን የውይይት ጊዜ እንድትወስድና ክርስቶስን የግል አዳኛቸው አድርገው እንዲቀበሉ በድፍረት መጠየቅ ደረጃ እስክትደርስ ይበልጥ እርሷ እንድትናገር አበረታቷት:: የምታሠለጥኗት ሴት ይህን ማድረግ ከምትችልበት ደረጃ ላይ ካልደረሰች እስክትደርስ ድረስ አብራችኋት ቆዩ::

አብሬው ከማገለግለው ሰው /የማሠለጥነው ሰው/:-

ወደ ምስክርነት የሚያመራ ንግግር መጀመርና ንግግሩም ውስጥ ስለ ክርስቶስ ማንሣት_______________::

ወደ ውሳኔ እንዲደርሱ ለመጠየቅ ገና ባይደርስም፣ በልበ ሙሉነት ወንጌልን ለሌሎች ማካፈል _______________::

ወንጌልን ለሌሎች መንገርና ወደ ውሳኔም እንዲደርሱ መርዳት_______________::

2. ግባችሁ አብረዋችሁ ሲያገለግሉ የነበሩትን ግለሰቦች ሌሎችን ሰዎች ወደ ክርስቶስ ማምጣት እንዲችሉ መርዳት ብቻ

አይደለም:: ወደ ክርስቶስ ያመጧቸውን ሙሉ ወደ ሆነ እድገት/ ብስለት ማድረስ ይችሉ ዘንድም አብራችኋቸው ስትሠሩ ቆይታችኋል:: አብረዋችሁ ሲያገለግሉ የነበሩት ይህንን በሚገባ መረዳታቸውን እርግጠኛ ሁኑ::

# ትምህርት 10

## መምህሩና የአንተ ዕቅድ

**- 1ኛ ደረጃ**

አንድ ሰው በአሳቡ የቀረጸው አንድ ታሪክ አለ:: ነገሩ እንዲህ ነው:: ኢየሱስ ወደ መንግሥተ ሰማያት አርጐ ልክ እዚያ እንደ ደረሰ መልአኩ ገብርኤልን ያገኘዋል:: ገብርኤልም ጌታችን በምድር ሳለ ምን ይሠራ እንደ ነበር ለማወቅ እጅግ ጓጉቶ ኖሮ፣ ምን ሲሠራ እንደ ሰነበተ ጠየቀው:: ኢየሱስም በምድር ላይ በነበረ ጊዜ የሰውን ልጆች ከኃጢአታቸው ለማዳን የመስቀል ሞት እንደ ሞተና በእግዚአብሔርም ኃይል ከሙታን እንደ ተነሣ፣ አሁን ግን እንደ ቀድሞ በእግዚአብሔር ቀኝ ሲቀመጥ፣ ሲያድናቸው ለወረደላቸውም የሰው ልጆች ሲማልድ እንደ ተመለሰ አብራርቶ አስረዳው:: ጨምሮም፣ በማንኛውም ስፍራ ያሉ ሰዎች ሁሉ እነርሱን ለማዳን ያደረገላቸውን እንዲሰሙ እንደሚፈልግ በመግለጽ ኢየሱስ መግለጫውን ደመደመ:: ገብርኤልም፣ «ታዲያ ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ ምን ዐቅደሃል?» ሲል ጠየቀው:: ጌታችንም እንዲህ ሲል መለሰለት፣ «ወደዚህ ከመምጣቴ በፊት መልእክቴን አሥራ ሁለት ለሚሆኑ ሰዎች አስተላልፌአለሁ:: በሁሉ ስፍራ እንደሚያሰራጩትም እተማመናለሁ::» ገብርኤልም በነገሩ በመደነቅ፣ «አሥራ ሁለት ሰዎች! እነርሱ ባይሳካላቸውስ?» ብሎ



ጠየቀው:: ኢየሱስም እንዲህ ሲል እንደ መለሰለት ይነገራል፣ «እንግዲያው ሌላ ዕቅድ የለኝም::»

በአሳብ የተቀረጸ መሆኑን ከግምት ውስጥ ሳናስገባ፣ የዚህ ታሪክ ዋና ነጥብ እውነት ነው:: አዎ! ኢየሱስ የወንጌልን ሥራ አደራ የሰጠው በቁጥር ጥቂት ለሆኑ ሰዎች ነው:: ነገር ግን እነዚህ ጥቂቶቹ ውጤታማ የሆኑ ምስክሮችን ማፍራት የሚችሉ ሌሎችን እንደሚገባ በማሠልጠናቸው በአጭር ጊዜ ውስጥ በርካታ ቁጥር ያላቸው የሠለጠኑ ደቀ መዛሙርት በኢየሩሳሌም፣ በይሁዳ፣ በሰማርያ፣ በገሊላ፣ ኋላም እስከ ምድር ዳር ድረስ ስለ ኢየሱስ የሚናገረውን እውነት አሰራጩት::

ሌሎችን መማረክና ማሠልጠን የሚችሉትን ይማርኩና ያሠለጥኑ ዘንድ በሠለጠኑ ደቀ መዛሙርቱ ዙሪያ የሚያጠነጥነው ይህ የኢየሱስ ስልት ዛሬም ፈጽሞ አልተለወጠም::

## የመማር ሂደት

1. ከአንድ ሰው ጋር እያገለገላችሁ ሳላችሁ ይህንን ሰው ለደቀ መዝሙርነት ማሠልጠን የምትችሉባቸውን አጋጣሚዎች ጻፉ::
2. ከአንድ ሰው ወይም አነስተኛ ቡድን ጋር ስትሠሩ አብራችሁ በምትቆዩበት ጊዜ አንዳንድ ልትሠሯቸው የምትችሏቸው ነገሮች ምንድን ናቸው?
3. ለደቀ መዝሙርነት ለምታሠለጥኑት ሰው ልትሰጡት የምትችሏቸው የሥራ ኃላፊነቶች ምንድን ናቸው?

   ሀ. በቅድሚያ ወይም መጀመሪያ ሰሞን የምትሰጡት ኃላፊነት::

   ለ. በጌታ ያለው ሕይወት በበሰለ ጊዜ የምትሰጡት ኃላፊነት::

4. አብራችሁት ለምታገለግሉት/ለምታሳድጉት ሰው ስለ ስልታችሁ የምታስረዱት ምን ደረጃ ላይ ሲደርስ ነው?

# የቡድን ሥራና ውይይት

1. ይህንን ክፍለ ጊዜ ዘገባ የማቅረቢያ ክፍለ ጊዜ አድርጉትና፣ በዚህ ሳምንት የእኔን እርዳታ የሚፈልግ ማንን አገኘሁ? በዚህ ሳምንት አንድን ሰው ለመርዳት ምን አደረግሁ? ያገኘሁት ምላሽስ ምን ነበር? በሚሉት ጥያቄዎች ዙሪያ ተወያዩ::

2. «ዘመናችንን ሁሉ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከምእመናን ጋር ፕሮግራሞችን እያካሄድን ከመኖር፣ ለክርስቶስ የመማረክን አገልግሎት ምንነት ከሚማሩ አንድ ወይም ሁለት ሰዎች ጋር አንድ ሁለት ዓመት ማሳለፍ ይሻላል::» የቡድናችሁ አባላት በዚህ አሳብ ይስማሙ ወይም አይስማሙ እንደ ሆነ ጠይቋቸው:: የዚህ ዐረፍተ ነገር አንድምታ ምንድን ነው? «ለክርስቶስ መማረክ» የሚለው ሐረግ ምንና ምንን ያካትታል?

3. ደቀ መዝሙር መሆን ፈልገው ነገር ግን ደቀ መዝሙር ለመሆን የቀረበው መመዘኛ ከባድ እንደ ሆነ ስላሰቡ ወደ ኋላ ስለ ተመለሱ ሰዎች ዶክተር ኮልመን በገጽ 124 ላይ ይነግሩናል:: በአዲስ ኪዳን መጽሐፍ ውስጥ ይህን ስላደረጉ ሰዎች አስቡ:: የሐዋ. 1:25፤ 1ኛ ጢሞ. 4:10፤ 2ኛ ጢሞ. 1:15፣ 2ኛ ጢሞ. 1:19፣20ን ተመልከቱ:: ከምታሠለጥኗቸው ሰዎች አንዳንዶቹ ሊሠለጥኑ የማይችሉ፣ ዋጋ ለመክፈል ፈቃደኞች የማይሆኑና ወደ ኋላ የሚመለሱ ቢሆኑ ምላሻችሁ ምን ይሆናል?

4. በቡድን የጸሎት ጊዜያችሁ እያንዳንዱን የቡድናችሁን አባል በስም እየጠራችሁ በጋራ ጸልዩ::

# የግል የመድረሻ ግብ

1. ክርስቲያን መሆንን በሚመለከት ከ150 - 200 በሚደርሱ ቃላት



የግል ምስክርነታችሁን መሠረት አድርጋችሁ ጻፉ:: የምትጽፉት ምስክርነት የሚከተለውን አስተዋጽኦ ያዝ፤ መጀመሪያ ሕይወታችሁ፣ ከዚያ ክርስቶስን ከተቀበላችሁ በኋላ ሕይወታችሁ ምን እንደሚመስል ግለጹ:: ከባድ የሆኑ የሥነ መለኮት ቃላትን እንዲሁም ክርስቲያን ላልሆነው አብዛኛው ሰው ትርጉም የማይሰጡ አባባሎችን ከመጠቀም ተቆጠቡ:: ክርስቶስ ለእናንተ ምን ማለት እንደ ሆነና ዛሬ እያደረገላችሁ ባለው ነገር ላይ አተኩሩ:: ጽፋችሁ ስታበቁ በቃላችሁ አጥኑ::

2. የሰንበት አስተማሪዎች ናችሁ እንበል:: በክፍላችሁ ውስጥ ያሉት ተማሪዎች ሁሉ ክርስቲያኖች ናቸው:: በተወሰነ ደረጃም አዘውትረው ትምህርታቸውን ይከታተላሉ:: እናንተም በታማኝነት ትምህርቶችን ታዘጋጃላችሁ፣ ቀሪዎችን ትጎበኛላችሁ፣ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ለተማሪዎቻችሁ የሽርሽርና የመዝናኛ ፕሮግራሞችን ታዘጋጃላችሁ:: ይሁን እንጂ፣ ይሄ ነው የሚባል አንዳችም ለውጥ በተማሪዎቻችሁ ሕይወት አልተከሰተም:: ታዲያ የመምህሩን ስልት እንዴት ባለ መልኩ ተግባራዊ በማድረግ ለመቀጠል ዐቀዳችሁ? በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ያሉትን የየምዕራፎቹን ርእሶች በድጋሚ ተመልከቷቸውና በውስጣቸው በያዟቸው አሳቦች መሠረት ሥራችሁን ቀጥሉ::

3. በቀደሙት ዘጠኝ ምዕራፎች የተማራችኋቸው ዋና ዋና ትምህርቶች ምንድን ናቸው? እነዚህን ትምህርቶች ተግባራዊ ማድረግ የጀመራችሁት እንዴት ነው? ለወደፊት ያላችሁ ዕቅድስ ምንድን ነው?

# ትምህርት 11

## መምህሩና የአንተ ዕቅድ

2ኛ ደረጃ

በቅርቡ የመንፈሳዊ መባዛትን አስፈላጊነት በሚመለከት እኔ እስከማስታውሰው ድረስ ብርቱ የሆነ ገላጭ ሁኔታ አይቻለሁ:: በርካታ ሰዎችን በያዘ አዳራሽ ውስጥ ሁለት ሰዎች ወደ መድረኩ እንዲመጡ ተጠየቁ:: ሁለቱም ሰዎች በግል ምስክርነታቸው ሌሎች ሰዎችን ወደ ክርስቶስ የሚማርኩ መጋቢዎችን የሚወክሉ ነበሩ:: ከሁለቱ አንደኛው (ምናልባትም በጣም ደፋሩ መስካሪ) በግሉ ብዙዎችን ለክርስቶስ የሚማርከውን፣ ሆኖም በመመስከር በጣም ስለሚተጋ ሌሎች መስካሪዎች እንዲሆኑ ለማሠልጠን ጊዜ የሌለውን መጋቢ ይወክላል:: ሌላው ሰው (በግል የወንጌል አገልግሎቱ ምናልባት እጅግም ውጤታማ ያልሆነው) ግን የማረካቸውን ሰዎች ሌሎችን መማረክ እንዲችሉ ጊዜ ወስዶ ያሠለጥናቸዋል:: እንዲያውም አንድ ደረጃ ወደ ፊት በመሄድ የማረኳቸውን ሰዎች እንዴት ማሠልጠን እንደሚችሉም ያሠለጥናቸዋል::

ገላጭ ትዕይንቱ የጀመረው ሁለቱ ሰዎች ወደ ምእመናኑ (በአዳራሹ ወደ ተሰበሰበው ጉባዔ) እየገቡ ለክርስቶስ የማረኳቸውን የሚወክሉ ሰዎችን አንድ በአንድ በመያዝ ተመልሰው ወደ መድረኩ በወጡ ጊዜ ነበር:: የመጀመሪያው መጋቢ ይህንኑ ተግባር በመቀጠል ወደ ጉባዔው አሥር ምልልስ በማድረግ አንድ በአንድ ሰዎችን እያወጣ መድረኩ ላይ ወደ ክርስቶስ ያመጣቸውን የሚወክሉ ሰዎችን ደረደራቸው:: የማረካቸውን ሲያሠለጥን የቆየው ሁለተኛው መጋቢ ደግሞ ያሠለጠነውን አንድ ሰው ይዞ ወደ ጉባዔው መካከል ገባ እናም እርሱና ደቀ መዝሙሩ አንድ አንድ ሰው ይዘው ተመለሱ:: አሁን አራት ሆኑ ማለት ነው:: አራቱ እንደገና ወደ ጉባኤው መካከል ገቡ:: አራቱም እያንዳንዳቸው አንድ አንድ ሰው ይዘው ተመለሱ፤ በአንድነትም ቁጥራቸው ስምንት ሆነ:: ይህ ሰውና ያሠለጠናቸው ሰዎች ወደ ጉባዔው መሀል የገቡት አምስት ጊዜ ያህል ብቻ ነው:: ነገር ግን 10 ሰዎችን ይዞ ከቆመው ከሌላኛው መጋቢ ጋር ሲነጻጸር ከዚህ መጋቢ ጋር 32 ሰዎች አብረው ቆመው ነበር:: ይህ መጋቢና እርሱ ያሠለጠናቸው ወደ ጉባዔው አሥር ምልልስ አድርገው ቢሆን ኖሮ 1024 ሰዎች ከእርሱ ጋር ቆመው ነበር:: ይህ ልዩነት በመደመርና በማባዛት የሒሳብ ስሌት መሃከል ያለው ልዩነት ነው:: ነፍስን ከመማረክ ይልቅ ነፍስን የሚማርከውን ማሠልጠን ይበልጥ አስፈላጊ ነው:: ጌታችን ከእኛ የሚጠብቅብንን ያህል በዚህ በጠፊው ዓለም ላይ ተጽዕኖ ማድረግ ካሰብን ቤተ ክርስቲያን ወደ ማባዛት መርሕ ፊቷን መመለስ ይኖርባታል::

### የመማር ሂደት

1. ወደ ብስለት በሚያመራ መንፈሳዊ ዕድገት ውስጥ በርካታ አሳቦች ተካትተዋል:: ከእነርሱም አንዳንዶቹ ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ጥቅሶች ውስጥ ይገኛሉ:: እያንዳንዱን በማንበብ የትኛውን የዕድገት ዓይነት እንደሚያመለክት ለማወቅ ሞክሩ::

   1ኛ ዮሐንስ 5:13

   ኤፌሶን 4:14

   ኤፌሶን 4:13

ማቴዎስ 4:19

ማቴዎስ 28:19

2. የሒሳብ ትምህርትን የምትወድዱ ካላችሁ የሚከተለውን ጥያቄ ሞክሩ:: በዓለም ላይ ያለኸው ክርስቲያን አንተ ብቻ ነህ እንበል:: በሚቀጥሉት ስድስት ወራት ውስጥ እርሱ በተራው ሌሎችን እንዲማርክ ብሎም እንዲያሠለጥን አንድ ሰው ለክርስቶስ ማርከህ አሠለጠንከው:: በስድስተኛው ወር መጨረሻም መማረክም ማሠልጠንም የሚችሉ ሁለት ክርስቲያኖች ተገኙ:: በቀጣዩ ስድስት ወራት እያንዳንዳችሁ አንድ አንድ ሰው በመማረክ ብታሠለጥኑ ደግሞ አራት ትሆናላችሁ:: በሚቀጥሉት ሌሎች 6 ወራት እያንዳንዳችሁ አንድ ሰው ብትማርኩና ብታሠለጥኑ 8 ሆናችሁ ማለት ነው:: ይህንን ሒደት በመከተል በ16 ዓመታት ውስጥ ለክርስቶስ ስንት ሰዎችን መማረክ ይቻላል? ያለመሰልቸት ለመሥራት ሞክሩ::

መልሱ:-

## የቡድን ውይይትና ተግባራት

1. ባለፈው ዓመት ጌታን ተቀብለው በቤተ ክርስቲያናችሁ የተጨመሩትን ሰዎች ቁጥር አስቡ:: ከዚያም የቤተ ክርስቲያናችሁ ጠቅላላ አባላት ቁጥር ምን ያህል እንደ ሆነ ወስኑ:: ጌታን ተቀብለው ወደ ኅብረቱ የተቀላቀሉትን ሰዎች ቁጥር ለጠቅላላው የአባላት ቁጥር አካፍሉ:: በዚህ የምታገኙት ውጤት ባለፈው ዓመት አንድን ሰው ለክርስቶስ ለመማረክና በጉባኤው መካከል እምነቱን በይፋ እንዲገልጽ ለማድረግ ያስፈለገውን የሰው ብዛት ያመለክታል::



2. አሁን ደግሞ በሚቀጥለው ዓመት እያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን አባል አንድ አንድ ሰው ለክርስቶስ መማረክ ቢችል በሚቀጥለው ዓመት ስንት ሰዎች ወደ ጌታ እንደሚማረኩ አስቡ:: በዓመቱ መጨረሻ የአባላት ቁጥር በግምት ስንት ይደርሳል? እነዚህ አባላት ደግሞ በቀጣዩ ዓመት አንድ አንድ ሰው መማረክ ቢችሉ ስንት ሰዎችን ይማርካሉ?

3. ወደ ቡድን ስብሰባችሁ ስትመጡ አሮጌ ጋዜጦችን ይዛችሁ ኑ:: ከዚያ ከእግዚአብሔር የተለየ ነገር ግን ከእግዚአብሔር ጋር ተስማምቶ ልታዩት ስለምትፈልጉት አንድ ሰው ለአንዳፍታ አስቡ:: የዚያ ሰው መሠረታዊ ፍላጐቶች ናቸው ብላችሁ በምታምኑባቸው ነገሮች ላይ በማተኮር የሚያስጨንቁትን፣ አጣብቂኝ የሆኑበትን፣ የሚያሳስቡትን ነገሮች ለማሰብ ሞክሩ:: ከዚያም ራሳችሁን በእርሱ/በእርሷ ቦታ አስቀምጡ:: ጥቂት ደቂቃዎችንም በመውሰድ በጋዜጣው ላይ ያሉትን ርእስ አንቀጾች፣ ማስታወቂያዎች፣ ሥዕሎች አንድ በአንድ እየቀደዳችሁ አውጡ:: ከእግዚአብሔር ጋር የተለየውን ወዳጃችሁን የሚያስታውሳችሁን እያንዳንዱን ነገርም እንዲሁ:: በጋዜጣው ላይ የቀረውን ክፍል ጣሉት:: ከዚያ ከጋዜጣው ቀዳችሁ ያወጣችኋቸውን የጋዜጣውን ክፍሎች በመጠቀም በሁለት ደቂቃ ውስጥ ለቡድናችሁ አባላት ስለ ጓደኛችሁ ግለጹላቸው::

## የግል የመድረሻ ግብ

1. ኤፌ. 4:11፣ 12ን ከአዲሱ መደበኛ ትርጉም መጽሐፍ ቅዱስ ላይ አንብቡ:: በዚህ ክፍል ጳውሎስ ወንጌልን ማሰራጨት በክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አባል በሆነ ሰው አንዱና ዋነኛ

ው የሕይወቱ ክፍል መሆን እንዳለበት በግልጽ ይናገራል:: በወንጌል አገልግሎት ለመሳተፍ ስለ መጠራት ያላችሁን እውነተኛውን የግል መረዳት ከዚህ በታች ጻፉ:: በዚህ ጉዳይ ላይ ያላችሁን አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ስሜትና ለምን እንደዚያ እንደ ተሰማችሁ ምክንያታችሁን አብራሩ::

2. በእምነታቸው እንዲያድጉ ለመርዳት ከሌሎች ጋር አብሮ ማገልገል አስቸጋሪ የሚሆንበትን ምክንያቶች ዘርዝሩ:: እነዚህ ችግሮች እንዴት ሊፈቱ ይችላሉ?

3. ሰዎችን ወደ ጌታ ለማምጣት ሞክራችሁ ከሆነና ጌታን ለመቀበል ያቀረባችሁላቸውን ግብዣ አሻፈረኝ ብለው ከሆነ፣ ላለመቀበል እንደ ምክንያት ያቀረቧቸው ነገሮች ምንድን ናቸው? ደካማውንና ጠንካራውን ጐናችሁ በመጨመር ስለ ሰጣችሁት ምስክርነት ተንትናችሁ ጻፉ::

# ትምህርት 12

## መምህሩና የአንተ ዕቅድ

### 3ኛ ደረጃ

በቅርቡ በአሜሪካ አገር በፍጥነት በማደግ ላይ ካሉት አብያተ ክርስቲያናት አንዱን ጐብኝቼ ነበር:: በዚህ ጉባኤ ባየሁት ግልጽ የመንፈሳዊ ብስለትና የወንጌል ስርጭት ስልት ቅንጅት የተደነቅሁትን ያህል በፍጹም ተደንቄ አላውቅም:: በዚህች ቤተ ክርስቲያን ቀስ በቀስ እያደገ የመጣው የወንጌል ስርጭት መርሐ ግብር አስደናቂ ነበር:: ከጊዜ አንጻር ሲታይ ይህ ሁኔታ የጀመረው የቤተ ክርስቲያኒቱ መጋቢ ለምእመናኑ የወንጌልን ቃል መመስከር እንደሚገባቸው በሰበከበት ወቅት ነበር:: ይህ እርምጃ ግን አንድም



ምስክር የሚሆን ሰው አላፈራም:: ከዚያ የተለያዩ ትምህርቶችን ማስተማር ወይም የጥናት ወቅቶችን ማዘጋጀት ጀመረ:: ይህም እንደ ቀድሞው ውጤት አልባ በመሆኑ ምንም ምስክር አልተገኘም:: ከዚያ ግን ይህ ሰው የወንጌልን ቃል ለመመስከር ሲወጣ አንድ ሰው ይዞ መውጣት ጀመረ:: ይዞት የሄደውም ሰው መጋቢው ሰዎችን ወደ ክርስቶስ ሲያመጣ ለሳምንታት ሲመለከት ሰንብቶ፣ ብዙም ሳይቆይ አሠራሩን ስለ ተረዳው፣ በግሉ ወንጌል መመስከር ጀመረ:: ከዚያ እርሱም በሥሩ አንድ ሰው፣ መጋቢውም እንዲሁ ሌላ ሰው ይዘው ለወንጌል ይወጣሉ:: ወዲያውም ቁጥራቸው ወደ አራት ከፍ አለ:: ሰዎች ወደ ክርስቶስ በተማረኩ ቁጥር ሌሎችን መማረክ የሚያስችላቸውን ሥልጠና ይወስዱ ነበር:: አራቱ ስምንት፣ ስምንቱ አሥራ ስድስት እየሆኑ:: እምነታቸውን ለሌሎች በሚገባ ማካፈል የሚችሉ አምስት መቶ የሚደርሱ አባላት እስከሚኖራት ያቺ ቤተ ክርስቲያን አደገች:: ባለፈው ዓመት የዚህች ቤተ ክርስቲያን አባላት ወደ አንድ ሺህ የሚሆኑ ሰዎች ወደ ክርስቶስ መምራታቸው አስደናቂ አይደለም! <u>የማባዛትን ምሥጢር ተረድተዋል</u>:: እነርሱ የመምህሩን የወንጌል ስርጭት ስልት እየተከተሉ ነው::

## የመማር ሂደት

1. አዲስ ኪዳን አማኞችን መከታተል የምንችልባቸውን በርካታ መንገዶች ያመለክተናል:: ከዚህ በታች አራት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ቀርበዋል:: በጥቅሶቹ ውስጥ የተመለከቱት የተለዩ ሰዎችን የመከታተያ ስልቶች የትኞቹ እንደ ሆኑ ዘርዝሩ::

   ሀ. የሐዋ. 15:36

   ለ. ፊልጵ. 1:19

ሐ. 1ኛ ተሰ. 3:1-2»

መ. ገላ. 6:11

2. ሰዎችን በመከታተል አገልግሎት ውስጥ ከጸሎት የሚልቅ ምንም ነገር የለም:: በኤፌሶን መልእክት የተጠቀሱትን ጳውሎስ ለአማኞች ያደርጋቸውን ሁለት የጸሎት አሳቦች ይዘት ተመልከቱ:: ስለ እነርሱም ያቀረበውን የጸሎት ጥያቄ ዘርዝሩ::

ሀ. ኤፌ. 1:15-20

ለ. ኤፌ. 3:14-19

## የቡድን ውይይትና ተግባራት

1. በቤተ ክርስቲያናችን የአሠራር መዋቅር ውስጥ የመምህሩን ስልት ለመተግበር የሚረዱን ምን ዓይነት የረጅም ጊዜ ዕቅዶች አሉ? ለዚህ ዓመት እንዴት ያሉ የአጭር ጊዜ ዕቅዶች ሊኖሩን ይገባል?
2. አንድ ችግሮችን ለመፍታት ልንጠቀምበት የምንችለው ዘዴ አለ:: ይኸውም በቡድን ውስጥ ያሉ አባላት ሁሉ የመጣላቸውን ለችግሩ መላ ይሆናል ብለው ያሰቡትን አሳብ ጥይት እንደ መተኮስ በፍጥነት ይሰነዝራሉ:: ሒስ መሰንዘር የተከለከለ ነው:: የተሰጡት አሳቦች በኋላ ይገመገማሉ:: ይህንን አሳብ የማፍለቅ ዘዴ አዳዲስ ነገሮችን የሚያፈልቅና አማራጮችን የሚያቀርብ አዲስና ቀራጥ አቀራረብ የሚል ስያሜ ሰጥታችሁ ተጠቀሙበት::
3. ከዚህ በፊት በነበረው ምዕራፍ ውስጥ አንደኛው ንዑስ ርእስ «ዘዴዎች ይለያያሉ» ይላል:: በግለሰብም ሆነ በትንሽ ቡድን



ሊተገበሩ በሚችሉ የተለያዩ ዘዴዎች ላይ ተወያዩ::

4. በማገገሚያ ስፍራዎች /በሆስፒታሎች/፣ ማረሚያ ቤቶች፣ ወይም በፀባይ ማረሚያዎች ውስጥ የማያገለግል የወንጌል ስርጭት ቡድን አባል ከሆናችሁ፣ በክርስቶስ ለማደግ ውሳኔ ላይ የደረሱትን ሰዎች መርዳት የምትችሉባቸውን መንገዶች ተወያዩ::

## የግል የመድረሻ ግብ

1. ከአንድ ሰው ጋር ስትሠሩ ቆይታችሁ ከሆነ፣ የምስክርነት አገልግሎቱን ለእነማን በመመስከር መጀመር እንደሚገባው አንዳንድ ሰዎችን ጠቁሙለት:: ከእነዚህም ሰዎች መሃከል:-
2. ከዚህ በታች የተሰጡት «የጽሞና ጊዜ እንዴት ማካሄድ እንደሚችል» የሚጠቁሙ አንዳንድ አሳቦች ናቸው:: እነዚህን አሳቦች ለምታሠለጥኗቸው ሰዎች ንገሯቸው::

   ሀ. የተወሰነ ጊዜ መድቡ:: ለእናንተ በጣም አመቺ የሆነውን ጊዜ ምረጡ::

   ለ. የተወሰነ ቦታ ይኑራችሁ:: ቦታው ከተቻለ ፀጥ ያለና የሚረብሽ ሁኔታ የሌለበት ቢሆን ይመረጣል:: ከእግዚአብሔር ጋር ለብቻችሁ የምትሆኑበት ጊዜ ይሁን::

   ሐ. አንድ የተወሰነ ዕቅድ ይኑራችሁ:: በመጀመሪያ የምታቀርቧቸውን የጸሎት ጥያቄዎች ዝርዝር ጻፉ:: ከዚያም መጽሐፍ ቅዱስን ለማጥናት ጥቂት ጊዜ ውሰዱ::
3. መቼም እስከ አሁን ሰዎችን ለመማረክና ወደ ሙሉ ዕድገት እንዲደርሱ ለማገዝ በምታደርጉት ጥረታችሁ የጠላት ተግዳሮት እንደ ነበረባችሁ ምንም ጥርጥር የለውም:: አብረዋችሁ

የሚሠሩትም ይህን የመሰለ ልምምድ ያጋጥማቸዋል። ሰይጣን እናንተንም ሆነ እነርሱን እንደዚህ እያለ ይፈታተናችኋል፣ «ሰውን ወደ ክርስትና ሕይወት ለማምጣት እየሞከርኩ ነው ስትል ምን ማለትህ ነው? አንተ ይህን ለማድረግ ፈጽሞ ብቁ አይደለህም። ስለ ራስህ ደኅንነት እንኳ እርግጠኛ አይደለህም።» የእርሱን ጥቃት የእግዚአብሔርን ቃል ተጠቅማችሁ መመከት ተማሩ። ይህን መሳዩን ጥቃት በ1ኛ ዮሐንስ 5:11-13 ተቋቋሙ።

ከዚያ ቀጥሎ፣ «እሺ ክርስቲያን ልትሆን ትችላለህ፣ ክርስቲያን ከሆንክ ወዲህ የወደቅህባቸውን ሁኔታዎች መለስ ብለህ አስብ፣» እያለ ያሾከሽክባችሁ ይሆናል። ለዚህ ፈተና 1ኛ ዮሐ. 1:9ን በመጥቀስ መልስ ስጡ።

በሦስተኛ ደረጃ፣ ክርስቲያን ብትሆንም እንኳ፣ ፈተናንን ለመቋቋም እጅግ ደካማ ነህ ሊላችሁ ይችላል። በዚህን ወቅት 1ኛ ቆሮንቶስ 10:13ን አስታውሱ።

# ትምህርት 13

## መምህሩና የአንተ ዕቅድ

4ኛ ደረጃ

የዓለማችን የሕዝብ ቁጥር ለማመን በሚያዳግት ፍጥነት እያደገ ነው። ሰዓታችን አንዲት ሰከንድ በቆጠረ ቁጥር፣ የዓለም የሕዝብ ቁጥር በሁለት ሰዎች ጭማሪ ያሳያል። ይህ ማለት ደግሞ፣ በተባበሩት መንግሥታት ስሌት መሠረት፣ ዛሬ ካለው ይልቅ ነገ 200,000 የሚሆን ሕዝብ ይጨመራል። ይህ አካሄድ በዚህ መልኩ ከቀጠለ፣ በአንድ ትውልድ ብቻ የዓለም ሕዝብ ብዛት ከ7 ቢሊዮን ያልፋል።



የሕዝብ ብዛቱ እንዲህ ባለ የሮኬት ፍጥነት እየተተኮሰ ሳለ፣ ሰዎች በወንጌል የሚደረሱበት ፍጥነት ግን እንደ ፈረስ ጋሪ በዝግታ በማዝገም ላይ ይገኛል። ባለፉት አሥርት ዓመታት በዓለማችን ላይ ያሉት የወንጌላዊ ክርስቲያኖች ቁጥር በመቶኛ ሲሰላ እያሽቀለቀለ ሄዷል። አንድ የታወቀ የወንጌል ሰባኪ ሲናገሩ፣ «ዓለማችንን ለክርስቶስ እየማረክንለት ሳይሆን ለክርስቶስ መሆን የሚገባትን ዓለም እያጣን ነው» ብለው ነበር። ይህንን አካሄድ የምንገታበት አንድ ተስፋ አለን። ይኸውም ቤተ ክርስቲያን በበኩሏ ወደ መምህሩ የወንጌል ስርጭት ስልት ፊቷን መመለሷ ነው።

በዚህ እግዚአብሔር በሰጣችሁ በአንዱ ሕይወታችሁ ልታደርጉ ያሰባችሁት የሕይወት ዕቅዳችሁ ምንድን ነው? ከሰዎች ጋር መሥራትን ቀዳሚ ባደረገ አገልግሎት ላይ እያዋላችሁት ነውን? በእርሱ ወይም በእነርሱ የእናንተን ማንነት የምትተኩበት ሰው ወይም አነስተኛ ቡድን አላችሁ? ዓለምን በወንጌል ለመድረስ ከዚህ የተሻለ አቋራጭ መንገድ የለም። ለዛሬ አስገራሚ የሆነና የሚታይ ስታቲስቲካዊ ዘገባ የሚያስገኝልን ባይሆን እንኳ፣ የኢየሱስን ስልት መከተል ይገባናል። የወደፊቱን አሻግራችሁ እየተመለከታችሁና ስሙ በሁሉ ዘንድ የሚታወጅበትን ራእይ ይዛችሁ ሥራውን በእርሱ መንገድ ለመሥራት ዛሬ እንደገና ሁለንተናችሁን ለኢየሱስ ስጡ።

## የመማር ሂደት

1. አዲስ ኪዳን አዲስን ወይም ያልዳነን ክርስቲያን እንደ------ ይገልጸዋል።
2. የክትትልን አስፈላጊነት አስመልክቶ ከላይ የተጠቀሰው ቃል ምን ይጠቁማል? የሚከተሉትን ጥቅሶች በማንበብ አንድ አዲስ

ወይም ያልዳነ ክርስቲያን የሚያስፈልጉትን ነገሮች ዘርዝሩ::

ሀ. ኤፌሶን 4:14

ለ. 1ኛ ተሰሎንቄ 2:7፣11

ሐ. 1ኛ ጴጥሮስ 2:2

3. በጳውሎስ ሁለተኛ የአገልግሎት ጉዞ እርሱና በርናባስ ተሰሎንቄ በምትባል ከተማ ለአምስት ወራት ገደማ ቆይተው ነበር:: በ1ኛ ተሰሎንቄ 1 መሠረት በዚያ ያለችው ቤተ ክርስቲያን ምን ትመስል እንደ ነበር ግለጹ::

እንዲህ ያለች ቤተ ክርስቲያን በዚያ አጭር ጊዜ አገልግሎት እንዴት ልትገኝ ቻለች?

4. አማኞችን ፍጹም ወደ ሆነ መንፈሳዊ ብስለት ለማድረስ ስንሠራ ቆይተናል:: ከዚህ በታች በአንድ የበሰለ አማኝ ከሚታዩ ምልክቶች አንዳንዶቹ ቀጥለው በተዘረዘሩት ጥቅሶች ተጠቁመዋል:: እነዚህን ምልክቶች ዘርዝሩ::

ሀ. 2ኛ ቆሮንቶስ 5:7

ለ. 1ኛ ተሰሎንቄ 5:8

ሐ. 2ኛ ቆሮንቶስ 9:7

መ. 1ኛ ዮሐንስ 3:16፣17

ሠ. ኤፌሶን 6:18

ረ. ዕብራውያን 5:14

## የቡድን ውይይትና ተግባራት

1. በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ የመምህሩን ስልት መተግበር የሚችሉ ቀደም ሲል የተቋቋሙ እንዴት ያሉ አነስተኛ ቡድኖች



አሉ? በጥቁር ሰሌዳ ላይ ዘርዝሯቸው::

2. ከመጽሐፋችሁ ገጽ 114 እስከ 124 በማውጣት ሌሎችን ደቀ መዝሙር የሚያደርጉ ከሆነ ቢጠቀሙባቸው አስፈላጊ ናቸው ተብለው የሚቆጠሩትን ነጥቦች በአስተዋጽኦ መልክ ዘርዝሯቸው:: በአገኛችኋቸው ነጥቦች ዙሪያ ተወያዩ::

3. በምትመሰክሩ ጊዜ ያጋጣሟችሁን አስቸጋሪ ሁኔታዎችና እነዚህም ሁኔታዎች እንዴት ሊወገዱ እንደሚችሉ በግልጽ ተወያዩባቸው:: አንዳችሁ ለሌላችሁ በመጸለይም በጋራ የነበራችሁን ጊዜ አጠቃልሉ::

## የግል የመድረሻ ግብ

1. በቅርብ ጊዜ አንድን ሰው ወደ ክርስቶስ የማምጣት ዕድል አጋጥሟችሁ ከሆነ፣ ይህ ሰው ወደ መንፈሳዊ ብስለት እንዲደርስ በመርዳት ያወጣችሁትን ዕቅድ ዝርዝር ግለጹ::

2. በግል ሕይወታችሁ ዘላቂ የሆነ የወንጌል ስርጭት ስልት እንዲኖራችሁ ያኗችሁን ዕቅዶች በአጭሩ ግለጹ::

## የመማር ሂደት መልሶች

(በዚህ ክፍል የተጠቀሱት ገጾች «ለወንጌል ስርጭት ቁልፍ ዕቅድ» መጽሐፍ የተወሰዱ ናቸው::)

## ትምህርት 1

3. መርሖዎች
4. በወንጌላት ላይ የሰፈሩት
5. (ሀ) ሐ (ለ) ሐ (ሐ) ሐ

## ትምህርት 2

1. (ሀ) ይሁዳ (ለ) 500 (ሐ) ዮሐንስ

2. (ሀ) ገጽ 10 (ለ) ገጽ 10 (ሐ) ገጽ 11 እና 12 (መ) ገጽ 13

3. (ሀ) ሐ (ለ) ሐ (ሐ) እ

## ትምህርት 3

2. (ሀ) ገጽ 26 (ለ) ገጽ 27 (ሐ) ገጽ 33

3. (ሀ) አብዛኛውን (ለ) 1/2 (ሐ) ደቀ መዛሙርት

## ትምህርት 4

2. (ለ) ገጽ 40 3. ዮሐንስ 14:21 4. ገጽ 48 6. ለ፣ መ፣ ሀ፣ ሠ፣ ሐ፣

## ትምህርት 5

1. ገጽ 51 2. ገጽ 53 3. ገጽ 54 4. ገጽ 57 5. ገጽ 52፣53 6. ገጽ 51

## ትምህርት 6

1. ገጽ 62-67

## ትምህርት 7

1. ገጽ 71 2. ገጽ 72 3. ገጽ 74 4. ገጽ 75 5. ገጽ 79 6. ረ፣ ለ፣ ሀ፣ ሐ፣ መ፣ ሠ

## ትምህርት 8

1. ገጽ 84-85 2. ገጽ 85 3. ገጽ 86 4. ገጽ 90

## ትምህርት 9

1. (ሀ) ሐ (ለ) እ (ሐ) እ (መ) እ 3. ገጽ 98 4. ገጽ 100 5. ገጽ 100-101

## ትምህርት 10



1. ገጽ 108 2. ገጽ 109-111 3. (ሀ) ገጽ 111 (ለ) ገጽ 113 (4) ገጽ 114

## ትምህርት 11

1. ማረጋገጫ (ድፍረት)
   በትምህርት ንፋስ አለመፍገምገም
   ክርስቶስን መምሰል
   ሰዎችን መማረክ
   ሌሎችን ደቀ መዝሙር ማድረግ

2. 4,294,967,296

## ትምህርት 12

1. (ሀ) በግል ማግኘት
   (ለ) ጸሎት
   (ሐ) ሌላ ሰው መላክ (መልእክተኛ)
   (መ) ደብዳቤዎች

## ትምህርት 13

1. ሕፃናት

2. (ሀ) ከሐሰት ትምህርት መጠበቅ
   (ለ) በፍቅር መንከባከብ እና የመገደድ ስሜት
   (ሐ) ምግብ፣ የቃሉን ወተት

4. (ሀ) በእምነት መኖር
   (ለ) በነገር ሁሉ ማመስገን
   (ሐ) በልግስና መስጠት
   (መ) ለሌሎች ርኅራኄን ማሳየት
   (ሠ) ሁልጊዜ መጸለይ
   (ረ) ለይቶ ማወቅ

## የወንጌል ስርጭትንና የደቀ መዝሙርነትን መሠረታውያን በተመለከተ የተመረጡ ዋቢ መጻሕፍት

## (Selected Bibliography in Basic Evangelism and Discipleship)


Adsit, Christopher. *Personal Disciple-Making* (Here's Life, 1989).

Aldirch, Joseph. *Life-Style Evangelism* (Multnomah, 1981).

_______. *Gentle Persuasion,* (Multnomah, 1981).

Allen, Roland. *Missionary Methods: St. Paul's or Ours* (World Dominion Press, 1953).

_______. *Spontaneous Expansion of the Church and Causes Which Hinder It* (World Dominion Press, 1949).

Anderson, Leith. *A Church for the Twenty-first Century* (Bethany House, 1992).

Arn, Win and Charles. *The Master's Plan for Making Disciples* (Church Growth Press, 1982).

Augsburger, Myron S. *Invitaion to Discipleship* (Herald, 1969).

Bayly, Joseph. *The Gospel Blimp* (Zondervan, 1966).

Belben, Howard. *The Mission of Jesus* (NavPress, 1985).

Bisagno, John R. *How To Build An Evangelistic Church* (Broadman, 1972).

Boer, Harry R. *Pentecost and Missions* (Eerdmans).

Brooks, Hal. *Follow-up Evangelism* (Broadman, 1972).

Bonar, Horatius. *Words to Winners of Souls,* rev. ed. (American Tract Society, 1950).

Bounds, E.M. *Preacher and Prayer* (London: Marshall Brothers, 1912).

Brengle, S.L. *The Soul-Winner's Secret,* 6th ed. (Salvation Army, 1920).

Bright, Bill. *Witnessing Without Fear* (Here's Life, 1987).

Briscoe, Stuart. *Everyday Discipleship for Ordinary People* (Victor, 1988).

Brown, Staney C. *Evangelism in the Early Church* (Eerdmans, 1963).

Bruce, A. B. *The Training of the Twelve* (Keats, 1979 [1871]).





Chaffer, Lewis Sperry. *True Evangelism* (Marshall, Morgan & Scott, 1919).

Cho, Paul Y.*More Than Numbers* (Word, 1984).

*Choose Ye This Day: How to Effectively Proclaim the Gospel Message* (World Wide, 1989).

Coleman, Lyman. *Serendipity Bible for Groups* (Zondervan, 1988).

_______. *Encyclopedia of Serendipity* (Serendipity House, 1976).

Coleman, Robert E. *The Master Plan of Discipleship* (Revell, 1987).

_______. *Mind of the Master* (Revell, 1977).

_______. *They Meet the Master* (Christian Outreach, 1973).

_______. *The Heartbeat of Evangelism* (NavPress, 1985).

_______. *The Spark That Ignites* (World Wide, 1989).

_______. *ed. Evangelism on the Cutting Edge* (Revell, 1986).

_______. *The Great Commission Lifestyle* (Revell, 1992).

Coppedge, Allan. *The Biblical Principles of Discipleship* (Zondervan, 1989).

Cosgrove, Francis M.*Essentials of Discipleship* (NavPress, 1980).

Dawson, David. *Equipping the Saints* (Greenville, TX, 1982).

Dawson, John. *Taking Over Cities for God* (Creation House, 1989).

Drummond, Lewis. *Leading Your Church in Evangelism* (Broadman, 1975).

_______. *The Awakening That Must Come* (Broadman, 1989).

_______. *The Word of the Cross: A Contemporary Theology of Evangelism* (Broadman, 1992).

Eims, Leroy. *The Lost Art of Disciple Making* (Zondervan, 1978).

_______. *Be the Leader You Were Meant to Be* (Victor, 1975).

_______. *Disciples in Action* (Victor, 1981).

Eisenman, Tom. *Everyday Evangelism* (IV, 1988).

Engel, James F. and H. Wilbert Norton. *What's Gone Wrong with the Harvest?* (Zondervan, 1975).

*Evangelistic Preaching: A Self-Study Course in Creating and Presenting Messages that Call People to Christ* (World Wide, 1990).

Fernando, Ajith. *Leadership Lifestyle* (Tyndale, 1984).

Finney, Charles. *Lectures on Revivals of Religion,* reprint (Revell, 1958).

Fish, Roy. *Every Member Evangelism for Today* (Harper & Row, 1976 [1922]).
Ford, Leighton. *Good News is for Sharing* (David C. Cook, 1977).
_______. *The Christian Presuader* (Harper & Row, 1966).
Friedeman, Matt. *The Master Plan of Teaching* (Victor, 1990).
Fryling, Alice, ed. *Disciple Makers' Handbook* (InterVarsity, 1989).
George, Carl. *Prepare Your Church For the Future* (Revell, 1991).
Graham, Billy. *A Biblical Standard for Evangelists* (World Wide, 1984).
_______. *The Billy Graham Christian Worker's Handbook* (World Wide, 1981).
Green, Michael. *Evangelism in the Local Church* (Tyndale, 1992).
Hadidian, Allen. *Successful Discipling* (Moody, 1979).
Hanks, Billie, Jr., and William A. Shell, eds. *Discipleship: The Best Writings of the Most Experienced Disciple Makers* (Zondervan, 1981).
Hanks, Billie, Jr. *Everyday Evangelism* (Zondervan, 1984).
Harrison, E. Myers, and Walter L. Wilson. *How To Win Souls* (Van Kampen, 1952).
Hartman, Doug, and Doug Sutherland. *A Guidebook to Discipleship* (Harvest, 1976).
Heck, Joel D. T*he Art of Sharing Your Faith* (Revel, 1989).
_______. *Make Disciples: Evangelism Program of the Eighties* (Concordia, 1984).
Hendricks, Howard. *Say It With Love* (Gospel Light, 1972).
Hendrix, John, and Lloyd Hoseholder, eds. *The Equipping of Disciples* (Broadman, 1977).
Henrichsen, Walter A. *Disciples Are Made, Not Born* (Victor, 1975).
Hull, Bill. *Jesus Christ, Disciple - Maker* (NavPress, 1984).
_______. *The Disciple-Making Pastor* (Revell, 1988).
_______. *The Disciple-Making Church* (Revell, 1990).
Hunter, George. *The Contagious Congregation* (Abingdon, 1980).
Huston, Sterling W. *Crusade Evangelism and the Local Church* (World Wide, 1984).
Hyde, Douglas. *Dedication and Leadership* (University of Notre Dame Press, 1966).
Jacks, Bob and Betty. *Your Home a Lighthouse* (NavPress, 1986).



Jones, Charles E. *Life is Tremendous* (Tyndale, 1968).
Kennedy, James. *Evangelism Explosion* 3d. ed. (Tyndale, 1983).
Kincaid, Ron. *A Celebration of Disciplemaking* (Victor, 1990).
Kuhne, Gary W. *The Dynamics of Personal Follow-Up* (Eerdmans, 1976).
_______. *Dynamics of Discipleship Training* (Zondervan, 1978).
Kunz, Marilyn, and Catherine Schell. *How to Start a Neighborhood Bible Study* (Tyndale, 1970).
Latham, Henry. *Pastor Pastorum* (Deighton Bell & Co., 1910).
*Let the Earth Hear His Voice,* ed. by J. D. Douglas (World Wide, 1975). Addresses and papers given at the International Congress on World Evangelism in Lausanne, Switzerland.
*Let the Church Obey His Voice.* Four reproducible notebooks issued by the American Festival of Evangelism in Kansas City in 1981.
Lewis, Larry. *Organize to Evangelize* (Victor, 1980).
Little, Paul E. *How to Give Away Your Faith* (InterVarsity, 1966).
MacDonald, William. *True Discipleship* (Walterick, 1962).
Mainhood, Beth. *Reaching Your World* (NavPress, 1986).
Mayhall, Carole. *From the Heart of a Waman: Basic Discipleship from a Woman's Viewpoint* (NavPress, 1976).
Mayhall, Jack. *Discipleship* (Victor, 1984).
McCloskey, Mark. *Tell It Often - Tell It Well* (Here's Life, 1986).
McClung, Floyd. *Basic Discipleship* (InterVarsity, 1990).
McGavran, Donald. *Understanding Church Growth.* 3d ed., revised and edited by Peter Wagner (Eerdmans, 1990).
Miller, John C. *Evangelism and Your Church* (Presbyterian and Reformed, 1980).
Miles, Delos. *Master Principles of Evangelism* (Broadman, 1982).
Moore, Waylon. *Multiplying Disciples* (NavPress, 1981).
_______. *New Testament Follow-Up* (Eerdmans, 1972).
Morgan, G. Campbell. *The Great Physician* (Revell, 1937).
Neighbor, Ralph W. *Target Group Evangelism* (Broadman, 1975).
_______. *Where Do We Go From Here* (Torch, 1990).
Nicholas, Ron, and others. *Good Things Come in Small Groups* (InterVarsity, 1990)

Ogden, Greg. *The New Reformation* (Zondervan, 1990).
*One Race, One Gospel, One Task ed. by Carl F. H. Henry and W. Stanley Mooneyham, 2 vols.* (World Wide, 1967). Papers and addresses given at the World Congress on Evangelism in Berlin in 1966.
Olford, Stephen. *Lord, Open the Heavens* (Shaw, 1980).
_______. *The Secret of Soul-Winning* (Moody, 1963).
Ortez, Juan C. *The Disciple* (Creation House, 1970-1989)
_______. *Call to Discipleship* (Logos, 1975).
Palmer, Bernard and Marjorie Palmer. *How Churches Grow* (Bethany, 1976).
Packer. J. I. *Evangelism and the Sovereignty of God* (InterVarsity, 1961).
Peace, Richard. *Small Group Evangelism* (InterVarsity, 1985).
Pentecost, J. Dwight. *Design for Discipleship* (Zondervan, 1971).
*Perspectives on the World Christian Movement,* ed. Steven C. Hawthorne and Ralpha D. Winter (William Carey Library, 1981).
Peterson, Jim. *Evangelism as a Lifestyle* (NavPress, 1980).
Philips, Keith. *The Making of a Disciple* (Revell, 1981).
Poterski, Donald C. *Reinventing Evangelism* (InterVarsity, 1989).
Powell, Paul W. *Dynamic Dsicipleship* (Broadman Press, 1984).
Pratney, Winkie. *Youth Aflame* (Communication Foundation, 1974).
Prince, Matthew. *Winning Through Caring* (Baker, 1981).
Prior, David. *Parish Renewal at the Grassroots* (Zondervan, 1983).
Rainer, Thom S., ed. *Evangelism in the Twenty-First Century* (Harold Shaw, 1989).
Ratz, Calvin, Frank Tillapaugh, and Myron Augsbourger. *Mastering Outreach and Evangelism* (Multnomah, 1990)
Robertson, Roy. *The Timothy Principle* (NavPress, 1986).
Rudnick, Milton L. *Speaking the Gospel Through the Ages* (Concordia, 1984).
Salter, Darious. *What Really Matters in Ministry* (Baker, 1990).
Sanny, Lorne. *Marks of a Disciple* (NavPress, 1975) .
Schweer, G. William. *Personal Evangelism for Today* (Broadman, 1984).
Segovia, Fernando F. *Discipleship in the New Testament* (Fortress, 1985).
Shaver, Charles "Chic." *Conserve the Converts* (Beacon Hill, 1976).



_______. *The Bible Speaks to Me About My Witness* (Beacon Hill, 1991).
Shoemaker, Samuel A. *Revive Thy Church Beginning With Me* (Harper & Brothers, 1948).
_______. *With the Holy Spirit and With Fire* (Harper & Brothers, 1960).
Shumate, Charles R. *On the Grow* (Walner, 1984).
Smith, Bailey. *Real Evangelism* (Broadman, 1978).
Smith, Glenn C., ed. *Evangelizing Adults* (Paulist National Catholic Evangelization Association and Tyndale House, 1985).
Smith, Oswald. *The Passion for Souls* (Marshall, Morgan & Scott, 1950).
Snyder, Howard. *The Problem of Wineskins: Church Structure in a Technological Age* (InterVarsity 1975).
Spurgeon, Charles H. *The Soul Winner,* ed. David Otis Fuller (Zondervan, 1984).
Sott, John R. W. *Our Guilty Silence* (Hodder & Stoughton, 1967).
_______. *Personal Evangelism* (InterVarsity, 1970).
Street, R. Alan. *The Effective Invitation* (Revell, 1984).
Sweazy, George E. *Effective Evangelism,* rev. ed. (Harper & Brothers, 1976).
Tam, Stanley. *Every Christian A Soul Winner* (Thomas Nelson, 1975).
Taylor, Mendall. *Exploring Evangelism* (Beacon Hill, 1964).
*The Calling of An Evangelist*, ed. by J. D. Douglas (World Wide, 1987). Addresses given at the International Congress for Itinerant Evangelists in Amsterdam in 1986.
*The Work of An Evangelist,* ed. By J. D. Douglas (World Wide, 1983). Addresses given at the International Congress for Itinerant Evangelists in Amsterdam in 1983.
Thomas, Ian. *The Saving Life of Christ,* (Zondervan, 1961).
Thompson, W. Oscar, Jr. *Concentric Circles of Concern* (Broadman, 1981).
Towns, Elmer L., assisted by John Vaughan and David Siefert. *The Complete Book of Church Growth,* 2nd ed. (Tyndale, 1985).
Trotman, Dawson. *Born to Reproduce* (Back to the Bible, 1957).
Trueblood, Elton, *The Incendiary Fellowship* (Harper & Row, 1967).
_______. *The Company of the Committed* (Harper & Row, 1980).

Trumbull, Charles Gallaudet. *Taking Men Alive* (Revell, 1907).
Tuttle, Robert, Jr. *Someone Out There Needs Me* (Zondervan, 1983).
Veerman, David R. *Youth Evangelism* (Victor, 1988).
Voelkel, Jack. *Student Evangelism* (Zondervan, 1974).
Wagner, C. Peter. *Strategies for Church Growth* (Regal, 1987).
_______. *Your Church Can Grow* (Regal, 1976).
_______. *Your Church Growth, State of the Art,* ed. by Wagner, with Towns (Tyndale, 1986).
Warr, Gene. *You Can Make Disciples* (Word, 1978).
_______. *The Godly Man* (Creative Resources, 1976).
Warr, Irma. *The Godly Woman* (Creative Resources, 1976).
Warren, Richard. *Twelve Dynamic Bible Stydy Methods* (Victor, 1981).
Watson, David. *Called and Committed* (Harold Shaw, 1982).
_______. *I Believe in Evangelism* (Eerdmans, 1976).
Wilkins, Michael J. *Following the Master: Discipleship in the Steps of Jesus* (Zondervan, 1992).
Willard, Dallas. *The Spirit of the Disciplines* (Harper & Row, 1988).
Wilson, Carl. *With Christ in the School of Disciple Building* (Zondervan, 1976).
Wimber, John *Power Evangelism* (Harper & Row, 1986).
Wood, A. Skevington. *Evangelism: Its Theology and Practice* (Zondervan, 1966).